# የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ

## 2013 - 2022

ኢትዮጵያ፤ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# የአስር ዓመት
# የልማት ዕቅድ

## 2013 - 2022

ኢትዮጵያ፤ አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ማውጫ

መቅድም

መግቢያ

ክፍል አንድ፥ ያለፉት አስር ዓመታት (2003-2012) የልማት አፈጻጸም

ምዕራፍ አንድ፥ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም 2

1.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ 3

1.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ 5

1.3 የፊስካል ፖሊሲ 8

1.4 የገንዘብ ፖሊሲና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት 10

1.5 የውጭ ንግድ 12

ምዕራፍ ሁለት፥ የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም 15

2.1 የግብርና ልማት 16

2.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት 19

2.3 የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት 20

2.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት 22

2.5 የንግድ ልማት 24

2.6 የባህልና ቱሪዝም ልማት 24

ምዕራፍ ሦስት፥ የመሠረተ ልማት አፈጻጸም 26

3.1 የትራንስፖርት ልማት 27

3.2 የኢነርጂ ልማት 30

3.3 የውኃ ኃብት ልማት 31

3.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት 32

ምዕራፍ አራት፥ የማህበራዊ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም 33

4.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት 34

4.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት 34

4.1.2 የትምህርትና ሥልጠና ልማት 34

4.1.3 የጤና ልማት 36

4.2 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት 37

4.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት 39

ምዕራፍ አምስት፥ የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ 41

5.1 የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ 42

5.2 የፍትሕ ዘርፍ 42

5.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ 44

ምዕራፍ ስድስት፥ የሰላም ግንባታና የውጭ ጉዳይ አፈጻጸም 46

6.1 የሰላም ግንባታ 47

6.2 የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት 47

ምዕራፍ ሰባት፥ የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ አፈጻጸም 49

## ክፍል ሁለት፥ ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶችና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ

ምዕራፍ አንድ፥ ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች 53

1.1 ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች 54

1.2 መልካም አጋጣሚዎች 57

ምዕራፍ ሁለት፥ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች 58

2.1 የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ 59

2.2 የክፍላተ ኢኮኖሚ ዘርፎች ማሻሻያ 61

2.3 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ጉዳዮች ማሻሻያ 62

ምዕራፍ ሦስት፥ የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህርያት 65

3.1 የሀገራችን የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ 66

3.2 የአስር ዓመት ዕቅዱ አስፈላጊነት 67

3.3 የአስር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪት 68

## ክፍል ሦስት፥ የአስር ዓመት (2013-2022) የልማት ዕቅድ

ምዕራፍ አንድ፥ የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች 73

1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች 74

1.2 የልማት ዕቅዱ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች 75

1.3 የልማት ዕቅዱ የትኩረት መስኮች 86

1.4 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ስምምነቶች እና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ትስስር 96

ምዕራፍ ሁለት፥ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ 98

2.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና የድህነት ቅነሳ 99

2.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ 101

2.3 የፊሲካል ፖሊሲ 103

2.4 የገንዘብ ፖሊሲና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት 105

2.5 የልማት ፋይናንስ 106

ምዕራፍ ሦስት፥ የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 109

3.1 የግብርና ልማት 110

3.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት 117

3.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት 121

3.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት 123

3.5 የንግድ ልማት 126

3.6 የከተማ ልማት 128

3.7 የባህልና ቱሪዝም ልማት 131

ምዕራፍ አራት፥ የመሠረተ ልማት ዕቅድ 134

4.1 የትራንስፖርት ልማት 135

4.2 የውኃ ሀብት ልማት 139

4.3 የኢነርጂ ልማት 143

4.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት 144

ምዕራፍ አምስት፥ የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ 148

5.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት 149

5.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት 149

5.1.2 የትምህርትና ሥልጠና ልማት 150

5.1.3 የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት 152

5.1.4 የጤና ልማት 155

5.2 የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት 158

5.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት 161

ምዕራፍ ስድስት፥ የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ስራዓት ግንባታ ዕቅድ 164

6.1 የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ 165

6.2 የፍትሕ ዘርፍ ልማት 166

6.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ 169

ምዕራፍ ሰባት፥ የሰላም ግንባታና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዕቅድ 172

7.1 የሰላም ግንባታ ልማት 173

7.2 የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት 174

ምዕራፍ ስምንት፥ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ 178

## ክፍል አራት፥ የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ምዕራፍ አንድ፥ የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች 181

ምዕራፍ ሁለት፥ የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች 185

ምዕራፍ ሦስት፥ ክልላዊ እና አካባቢያዊ የተመጣጠነ ልማት እና ተወዳዳሪነት 188

ምዕራፍ አራት፥ የልማት ዕቅዱ ስጋቶችና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች 192

4.1 የልማት ዕቅዱ ስጋቶች 193

4.2 የልማት ዕቅዱ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች 194

ምዕራፍ አምስት፥ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት 196

5.1 የክትትል ሥርዓት 197

5.2 የግምገማ ሥርዓት 199

5.3 የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች 199

# መቅድም

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት አስመዝግባለች። ይህ ዕድገት በመንግስት ከፍተኛ ወጪ በተስፋፋ የመሠረተ ልማት አማካይነት የተመዘገበ ነው። ይህም ለዓመታት የዋጋ ግሽበት የፈጠረ ሲሆን ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል በተፈለገው መጠን በቋሚነት አልፈጠረም። ወጪው በከፍተኛ ብድር እና እርዳታ የተሸፈነ ስለነበር ከፍተኛ የብድር ጫና ፈጥሯል። የሸቀጦች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሲታይ ከተወሰኑ የግብርና ምርቶች አቅርቦት ተላቅቆ፤ በአይነትና በጥራት በተሻለ መልኩ ምርቶችን በማብዛት ቀጣይና አስተማማኝ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ማስገኘት ተስኖታል። የማህበራዊ አገልግሎቶችና የመሠረተ ልማት ዘርጋታዎችም ከፍተኛ የጥራትና ፍትሐዊነት ጉድለት አለባቸው። በተመሳሳይ በመልካም አስተዳደርና ፍትሕ እንዲሁም በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዙሪያ ከፍተኛ ጉድለት ታይቷል።

በመሆኑም እነዚህን ህጸቶች በማረም በቀጣይ አስር ዓመታት ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ጉዞ የሚያራምድ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱ የሀገራችንን ርዕይ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲን፣ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የባለፉትን አስር ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም፣ ሀገራችን የተስማማችባቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ጉዳዮችን እና ዓለም አቀፍና ከባቢያዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን እንደ ዋና መነሻ በመውሰድ እንዲዘጋጅ ከተደረገ በኋላ ከህዝቡ ጋር በተደረገ ውይይት ይበልጥ እንዲዳብር ተደርጓል። የልማት ዕቅዱ ዓላማ የታለመውን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ሀገራዊ የረጅም ጊዜ የልማት ርዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና መጫወት ነው። ይህ የልማት ዕቅድ የዝግጅት ሂደት ግልፅና አሳታፊ የነበረ ሲሆን የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ለልማት ዕቅዱ መነሻ ጥናቶች ሲካሄዱ ጀምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዕቅዱን በግልፅ እንዲወያዩበት፣ በሚገባ እንዲገነዘቡት፣ በባለቤትነት እንዲይዙት፣ ለዕቅድ ዝግጅቱ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ እና ለትግበራው ዝግጁ እንዲሆኑ መግባባት የመፍጠር ሥራዎች ተከናውነዋል።

በመጨረሻም ረቂቅ ዕቅዱ ከህዝብ ውይይቶች በተገኙ ግብዓቶች ተሻሽሎና ዳብሮ በመጀመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዝርዝር ውይይቶች ከተደረጉበት በኋላ ሥራ ላይ እንዲውል ፀድቋል። በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የኢኮኖሚውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገቱ በሂደት በግሉ ዘርፍ ወደሚመራበት በማሸጋገር የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር ለመፍጠር፣ ድህነትን በሁሉም መገለጫ በተጨማጭ ለመቀነስ፣ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል። በባለፉት ዓመታት ዕቅድ የተመዘገቡ ስኬታማ አፈጻጸሞችን እንደተጨማሪ አቅም የሚወሰዱ ሲሆን በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል ሁሉም የልማት ተሳታፊዎች በመደመር አስተሳሰብና ተግባር የተቀናጁና ተመጋጋቢ የሆኑ የልማት ሥራዎች በላቀ ቁርጠኝነትና ትጋት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንደሚከናወኑ ይጠበቃል። በምናደርገው ርብርብ የአስር ዓመቱ ዕቅድ ዓላማዎችና ግቦች እንደሚሳኩ እምነቴ የፀና ነው።

ክቡር ዐቢይ ኣህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

# መግቢያ

ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ በተደረጉት የልማት ዕቅዶች በኢትዮጵያ ተከታታይ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት፤ የማህበራዊ ልማት እና የመሠረተ ልማት መስፋፋት ተመዝግቧል። ይህም የኢኮኖሚ ዕድገት በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በአገልግሎት ዘርፎች ከተመዘገበው አንጻራዊ ዕድገት የመነጨ ነበር። ሆኖም ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት ከጥራት አኳያ በርካታ ጉድለቶች ነበሩበት። በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይሳካል ተብሎ ታቅዶ ከነበረው የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር አንጻር የአፈጻጸም ጉድለቶች ተመዝግበዋል። የሸቀጦች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሲታይ ከተወሰኑ የግብርና ምርቶች አቅርቦት ተላቅቆ፤ በአይነትና በጥራት በተሻለ መልኩ ምርቶችን በማብዛት ቀጣይና አስተማማኝ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ማስገኘት ተስኖታል።

ሀገራዊ የልማት ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነውን የፋይናንስ አቅም ከሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ ማሰባሰብ ባለመቻሉ የልማት ወጪውን በውጭ ብድርና ዕርዳታ መሸፈን ግዴታ ሆኗል። ይህም የውጭ ዕዳ ጫና ከማሳደሩም በላይ ውስን የሆነው የውጭ ምንዛሪ ገቢያችን ለውጭ ዕዳ ክፍያ እንዲውል አድርጓል። የማህበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት እና የመሠረተ ልማት ዝርጋታን ለማስፋፋት ባለፉት ዓመታት ትኩረት ተሰጥቶ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም ካለው ፍላጎት አኳያ ሲታይ አሁንም ከፍተኛ የሆነ ጉድለት ይስተዋላል። በተጨማሪም የተከናወኑት የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች እና የማህበራዊ ልማት አገልግሎቶች ከፍተኛ የሆነ የጥራትና ፍትሐዊነት ጉድለት አለባቸው። በተመሳሳይ በመልካም አስተዳደርና ፍትሕ እንዲሁም በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዙሪያ ከፍተኛ ጉድለት ታይቷል። የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛነትና የሙያ ነፃነት ያልዳበረ መሆኑ፤ ወንጀሎችን ለመከላከልና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አቅም አለመገንባቱ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶችና በዚህ ሂደት ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ በተሟላ መልኩ ማቅረብ አለመቻሉ እና የሰብዐዊ መብት አያያዝና አጠባበቅ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት አለመከበሩ፣ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን ሌብነት በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቷል።

መንግሥት ባለፉት ዓመታት በልማት ዕቅድ ትግበራ የታዩ ክፍተቶችን እንዲሁም የተመዘገቡ ጠንካራ ጎኖች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀጣይ አስር ዓመታት የኢትዮጵያን የብልጽግና ጉዞ ለማሳለጥ የሚረዳ እና የተቀመጠውን "አፍሪካዊ የብልጽግና ተምሳሌት" ሀገራዊ ርዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና የሚኖረው ሀገራዊ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ አዘጋጅቷል። ይህ የልማት ዕቅድ በዋናነት ከህዝቡ ጋር ሰፊ ምክክር ተደርጎበት የዳበረና መግባባት የተደረሰበት እንዲሁም የዜጎች ባለቤትነት የተረጋገጠበት ዕቅድ ሲሆን ሂደቱም ከታች ወደ ላይ እና ከላይ ወደ ታች በሆነ የዕቅድ አዘገጃጀት መንገድን የተከተለ እንዲሁም በዘርፎች መካከል ትስስር እንዲኖር ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። የልማት ዕቅዱ በኃይል፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በመስኖ የተፈጠሩት አቅሞች፣ ሊለማ የሚችል ከፍተኛ የሆነ የመስኖ አቅም፤ ሰብዓዊ ካፒታል፤ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂና የምርታማነት ደረጃዎች እና ያልለሙ ዘርፎች እንደ አዲስ የዕድገት ምንጭ አቅሞች ለልማት ዕቅዱ እንደመነሻ ተወስደዋል።

ይህ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ በርካታ ልዩ ባህሪያት ያሉት ሲሆን በዋናነት የልማት ዕቅድ ዝግጅቱ የዘርፎችን ትስስር ያማከለ እንዲሆን በማድረግ በዘርፎች ተሳትፎና ቅንጅት የተዘጋጀ መሆኑ፤ የዕቅዱ የአዘገጃጀት ሂደት አሳታፊና ሀገራዊ የልማት ማዕከላትን በመለየት ትኩረቶችና የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ከተመረጡ የልማት ማዕከላት ጋር የሚቀናጁበትን አግባብ ግምት ውስጥ መውሰዱ፤ የሥርዓታት ድክመትን እንደ ዋና ተግዳሮት በመውሰድ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የሚደረግበት አቅጣጫ መያዙ፤ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ መሻሻያ ተነድፎ ወደ

ተግባር መገባቱ እና ለዚህ ዕቅድ እንደመነሻ መወሰዱ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ዋና የኢኮኖሚ ዕድገት መዘውር መሆኑን በእርግጥ በመቀበል የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ትብብር የማጠናከር አቅጣጫ መያዙ ይጠቀሳሉ።

የልማት ዕቅዱ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት (pragmatic market based economic system) በመከተል የግል ዘርፉን ጉልህ ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የበለጸገች ሀገር መገንባት፤ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነት፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጐልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ (structural economic transformation) ማረጋገጥ፤ የማህበራዊ አካታችነትን የሚያረጋግጡና ሌሎች የመሠረተ ልማቶች ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤ ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ እና ሰላምና ፍትሕን የሚያረጋግጡ ጠንካራ ሥርዓታት በመገንባትና የሕግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማስከበር የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

ይህ ሰነድ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በክፍል አንድ ለዕቅዱ መነሻ የሆነው ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም በየዘርፉ ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርቧል። በክፍል ሁለት ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶችና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ የቀረበ ሲሆን በክፍል ሶሥት የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ በዝርዝር ቀርቧል። የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ሥልቶች እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በክፍል አራት በአጭሩ ቀርቧል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ክፍል አንድ

## ያለፉት አስር ዓመታት
## (2003-2012)
## የልማት አፈጻጸም





# ምዕራፍ አንድ

## የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ አፈጻጸም

# 1.1 የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

በመጀመሪያው እና በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት ተከታታይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል። ከአቅርቦት አንጻር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ2008 ቋሚ የገበያ ዋጋዎች (constant prices) በአማካይ በየዓመቱ በ9.2 በመቶ በማደግ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 828.2 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1.99 ትሪሊዮን ብር ከፍ ብሏል። ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት በተመሳሳይ ወቅት ታቅዶ ከነበረው የ11 በመቶ አማካይ ዕድገት ግብ አንጻር ሲታይ የ1.8 መቶኛ ነጥብ ጉድለት ያሳያል። የኢኮኖሚ አፈጻጸሙ ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች አንጻር ሲታይም የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ የ5.3፣ የ17.2 እና የ9.7 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግበዋል (ሠንጠረዥ 1.1)።

ሠንጠረዥ 1.1፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶኛ)

| | አማካይ | | |
|---|---|---|---|
| | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 |
| ግብርና ዘርፍ | 6.6 | 4.1 | 5.3 |
| የሰብል ምርት | 7.5 | 4.8 | 6.1 |
| የእንስሳት ምርት | 5 | 2.5 | 3.7 |
| ኢንዱስትሪ ዘርፍ | 19.1 | 15.2 | 17.2 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 15.1 | 13 | 14.1 |
| ኮንስትራክሽን | 27.7 | 17.3 | 22.5 |
| አገልግሎት ዘርፍ | 11.1 | 8.2 | 9.7 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 11.7 | 8.9 | 10.3 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 13 | 11.5 | 12.2 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 11.4 | 12.5 | 11.9 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 10.1 | 8.2 | 9.2 |

ምንጭ:- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የግብርና ዘርፍ በአማካይ የ24 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ውስጥ የዋና ዋና ሰብሎች ንዑስ ዘርፍ 72.7 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይይዛል። የኢንዱስትሪ ዘርፉም በአማካይ የ37.9 በመቶ አስተዋጽዖ ያደረገ ሲሆን ለዚህም የኮንስትራክሽን እና የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች በቅደም ተከተል የ77.1 በመቶ እና የ22.8 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ይህም ለተመዘገበው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት ዋነኛው ምንጭ የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ መሆኑን ያመላክታል። በሌላ በኩል የአገልግሎት ዘርፍ ለተመዘገበው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት 40.8 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፍ 37.8 በመቶ ድርሻ ይይዛል። በአጠቃላይ ከአቅርቦት አንጻር የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዋነኛነት በቅደም ተከተል ከኮንስትራክሽን፣ ከዋና ዋና ሰብሎች እና ከጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፎች የመነጨ መሆኑን የአፈጻጸም መረጃው ያሳያል።

ባለፉት አስር ዓመታት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው በነበረው የገበያ ዋጋ (current prices) በአማካይ በየዓመቱ የ23.9 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 395.9 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት 3.37 ትሪሊዮን ብር ደርሷል። ከዚህ ውስጥ ጠቅላላ ፍጆታ

የ79 በመቶ ድርሻ ሲይዝ የግል ፍጆታ ደግሞ ከሦስት አራተኛ በላይ አስተዋጽዖ ነበረው። በሌላ በኩል ጠቅላላ ኢንቨስትመንት፣ የወጪ እና የገቢ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) በቅደም ተከተል ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በአማካይ የ35.1 በመቶ፣ የ10.1 በመቶ እና የ25.9 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። በአጠቃላይ የተመዘገበው የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ከፍላጎት አንጻር በቅደም ተከተል ከግል ፍጆታ፣ ከጠቅላላ ኢንቨስትመንት እና ከተጣራ የወጪ ንግድ (አገልግሎትን ጨምሮ) የመነጨ መሆኑን ያሳያል።

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 31.1 በመቶ በ2009 በጀት ዓመት ወደ 38.4 በመቶ ደርሶ የነበረ ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት ግን በወቅቱ በሀገሪቱ በነበረው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ምክንያት የውጭና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች በመቀዛቀዛቸው እንዲሁም የመንግስት ካፒታል ወጪ እየቀነሰ በመምጣቱ ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ምጣኔ ወደ 34.1 በመቶ ዝቅ ብሎ ነበር። ይሁን እንጂ በ2010 የተካሄደውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ በ2011 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ መሻሻል አሳይቶ ወደ 35.2 በመቶ ከፍ ብሎ ነበር። ሆኖም በ2012 በጀት ዓመት በኮቪድ-19 (Covid-19) ወረርሽኝ ምክንያት ወደ 30.8 በመቶ ዝቅ ብሏል።

ሠንጠረዥ 1.2፡ የመጨረሻ ጠቀሜታ ወጪዎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | አማካይ | | |
|---|---|---|---|
| | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 |
| ጠቅላላ ፍጆታ | 80.7 | 77.6 | 79 |
| የመንግሥት ፍጆታ | 10.5 | 10.2 | 10.3 |
| የግል ፍጆታ | 70 | 67.5 | 68.7 |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | 35 | 35.2 | 35.1 |
| የወጪ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ | 12.5 | 7.8 | 10.1 |
| የገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ | 29.5 | 22.2 | 25.9 |
| የሀብት ክፍተት | (17.1) | (14.5) | (15.8) |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ | 19.3 | 22.4 | 21 |

ምንጭ:- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

የሀብት ክፍተት (ማለትም በወጪ ንግድና በገቢ ንግድ መካከል ያለው ልዩነት) የመስፋት አዝማሚያ ያሳየ ሲሆን ይህም በአማካይ በየዓመቱ 15.8 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ለዚህም በዋነኛነት የወጪ ንግድ አፈጻጸም እጅግ ደካማ መሆንና የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የማመንጨት አቅም ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም አብዛኛው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በገቢ ንግድ ላይ የተመሠረተ መሆን ከፍተኛውን አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከአጠቃላይ ዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 17.3 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 20.9 በመቶ አድጓል። በተመሳሳይ የነፍስ ወከፍ ገቢ (per capita GDP) በአማካይ የ10.7 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 389 የአሜሪካን ዶላር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1,080 የአሜሪካን ዶላር አድጓል።

ሀገራዊ የድህነት ምጣኔ በ2003 ከነበረበት 29.6 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 23.5 በመቶ ዝቅ ብሏል። ይህ ምጣኔ በገጠር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 30.4 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 25.6 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን በከተማ ደግሞ ከ25.7 ወደ 14.8 በመቶ ወርዷል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን በተመለከተ፣ የዜጎች የገቢ አለመመጣጠን አመልካች (Gini coefficient) በ2003 በጀት ዓመት 0.30 የነበረው በ2008 በጀት ዓመት 0.33 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፣ በዚሁ ጊዜ በገጠርና በከተማ በተከታታይ ከ0.37 ወደ 0.38 እና ከ0.27 ወደ 0.28 ከፍ ብሏል።

የሥራ አጥነት ሁኔታን በተመለከተ ሀገር አቀፍ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በሁለቱም ጾታዎች የመጨመር አዝማሚያ አሳይቷል። የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት 18 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 18.7 በመቶ ከፍ ብሏል። በ2012 በጀት ዓመት ከ15-29 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የሥራ አጥነት ምጣኔ በአማካይ 25.7 በመቶ ሲሆን ይህም ከሀገር አቀፉ የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ አንጻር ከፍተኛ ጭማሪ ያሳያል። የከተማ የሥራ አጥነት ምጣኔ በጾታ ስብጥር ሲታይ በ2003 በጀት ዓመት የወንዶች 11.4 በመቶ እና የሴቶች 25.3 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 12.2 እና 26.1 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል።

## 1.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነትን ከሚያመላክቱ ሂደቶች ውስጥ አንዱ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ነው። የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎችና ንዑስ ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎችና ንዑስ ዘርፎች በሚደረግ ሽግግር የሚገለፅ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የግብርናው ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ እየቀነሰ ቢመጣም በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የግብርና ንዑስ ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ንዑስ ዘርፎች የተደረገው ሽግግር እጅግ አዝጋሚ በመሆኑ በግብርና ዘርፍ ውስጥ የተመዘገበው መዋቅራዊ ሽግግር አጥጋቢ አልነበረም።

በተመሳሳይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ እምብዛም ለውጥ አለማሳየቱ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) እና ቱሪዝም በአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ መሆን፣ በአንጻሩ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ከፍተኛውን ድርሻ መያዙ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጡ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታሉ።

የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት የሎጂስቲክስ፣ የምርትና ምርታማነት፣ ጥራት እና የዋጋ ተወዳዳሪነት አቅም በሚፈለገው መልኩ ባለማደጉ የወጪ ንግድ ዘርፍ አፈጻጸም ደካማ እንዲሆን አድርጓል። በተጨማሪም የሸቀጦች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ መምጣት፤ የሀገሪቱ የውጭ ዕዳ የመክፈል አቅም ከወጪ ንግድ (debt service to exports) አፈጻጸም አኳያ እያሽቆለቆለ መሄድ እና የሥራ አጥነት በተለይም የወጣቶች የሥራ አጥነት መጨመር የኢኮኖሚው መዋቅራዊ ለውጥና የተወዳዳሪነት አቅም ደካማ አፈጻጸም መገለጫዎች ሆነዋል።

**የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ፦** የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ከማሳካት አንጻር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ባለፉት ዓመታት ዕድገት ያስመዘገበ ቢሆንም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ እምብዛም ለውጥ ሳያሳይ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 4.5 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት 6.9 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል (ሠንጠረዥ 1.3)። ይህም በቀጣይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ለማረጋገጥ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ከማሣደግ አንጻር የተቀናጀ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል።

ሠንጠረዥ 1.3፡ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2003 | 2007 | 2012 |
|---|---|---|---|
| **ግብርና** | 45.7 | 39.6 | 32.7 |
| የሰብል ምርት | 28 | 24.9 | 21.3 |
| የእንስሳት ምርት | 13.7 | 11.1 | 8.5 |
| **ኢንዱስትሪ** | 14.8 | 21.2 | 29 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 4.5 | 5.6 | 6.9 |
| ኮንስትራክሽን | 6.9 | 14.2 | 21.1 |
| **አገልግሎት** | 38.3 | 39.5 | 39.5 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 12.4 | 13.9 | 14.3 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 4 | 4.6 | 5.3 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 3 | 2.7 | 3.3 |

ምንጭ: - የፕላንና ልማት ኮሚሽን

**የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ ስብጥር አንጻር፦** የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ከሚያመላክቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸሞች መካከል የሸቀጦች የወጪ ንግድ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ያላቸው ድርሻ አንዱ ነው። ከዚህ አኳያ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ከጠቅላላ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ያላቸው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.7 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 13.3 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን፣ የግብርና ምርት በተመሣሣይ ጊዜ ከ72 በመቶ ወደ 77 በመቶ ከፍ ብሏል (ሠንጠረዥ 1.4)። ይህም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ አኳያ ያለው አፈጻጸም ደካማ መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም በቀጣይ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢን በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መሥራት እንደሚጠይቅ የሚያመላክት አፈጻጸም ነው።


### ሠንጠረዥ 1.4፡ የዘርፎች ወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ያለው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2003 | አማካይ | | | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 | |
| ግብርና | 72 | 71.2 | 76.4 | 73.8 | 77 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 8.7 | 10.2 | 14.1 | 12.2 | 13.3 |
| ማዕድን | 16.4 | 16.2 | 6.3 | 11.2 | 6.9 |
| ኤሌክትሪክሲቲ | 0 | 0.9 | 2.1 | 1.5 | 2.2 |
| ሌሎች | 2.8 | 1.5 | 0.9 | 1.2 | 0.5 |
| ጠቅላላ ድምር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ : - የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

**የዘርፎች የሠራተኛ ስምሪት ለውጥ፡-** መዋቅራዊ ለውጥ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ከሚኖራቸው የአስተዋጽዖ ለውጥ በተጨማሪ በየዘርፎቹ በሚሠማራው የሠራተኛ ኃይል ስብጥር ለውጥም ይንፀባረቃል። በዚህም መሠረት በግብርና ተሠማርቶ የነበረው የሰው ኃይል በሥራ ላይ ከነበረው አጠቃላይ የሰው ኃይል 72.7 በመቶ ድርሻ እንደነበረው የ2005 በጀት ዓመት የናሙና ጥናት መረጃ ያሳያል። ከአጠቃላይ በሥራ ላይ ይገኝ ከነበረው ሠራተኛ ውስጥ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርቶ የነበረው የሠራተኛ ኃይል 7.5 በመቶ እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፍ የተሠማራው የሠራተኛ ኃይል 19.8 በመቶ ነበር። የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ በ2005 በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ከተሰማራው የሰው ኃይል 60 በመቶ፣ ከአጠቃላይ የሰው ኃይል ደግሞ 4.5 በመቶ ለሚሆነው የሥራ ዕድል የፈጠረ ነበር (ሥዕል 1.1)።

### ሥዕል 1.1፡ በ2005 ሀገር አቀፍ የሠራተኛ ኃይል ስብጥር (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ

# 1.3 የፊስካል ፖሊሲ

የፊስካል ፖሊሲ ዋና ዓላማ የወጪ በጀትን በዋናነት በሀገር ውስጥ ገቢ በመሸፈንና የበጀት ጉድለት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን ማስፈን ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ገቢን በተለይም የታክስ ገቢን ማሳደግና በሀገር በቀል ፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ በመመስረት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሀገሪቱ ቅድሚያ የሰጠቻቸውን የልማት ፕሮግራሞች ፋይናንስ ለማድረግ ቁልፍ ሚና አለው።

**ጠቅካላ የመንግስት ገቢና ወጪ አፈጻጸም፦** የመንግስትን ገቢ ከማሳደግ አኳያ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በ2003 ከነበረበት ብር 69 ቢሊዮን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ ብር 354 ቢሊዮን አድጓል። ከዚህ ውስጥ የታክስ ገቢ በአማካይ በየዓመቱ የ22.3 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት ከብር 43 ቢሊዮን ወደ ብር 312 ቢሊዮን አድጓል። የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ያለው ድርሻም በተመሣሣይ ጊዜ ከ85 በመቶ ወደ 88 በመቶ ከፍ ብሏል (ሠንጠረዥ 1.5) ።

ሠንጠረዥ 1.5፡ ጠቅላላ የመንግሥት ገቢና ወጪ አፈጻፀም

| | 2003 | አማካይ (በቢሊዮን ብር) | | | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 | |
| ጠቅላላ የመንግስት ገቢ | 85.6 | 139.2 | 308.5 | 223.9 | 395 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ | 69.1 | 125.8 | 284.9 | 205.4 | 354.3 |
| የታክስ ገቢ | 59 | 110 | 243.2 | 176.6 | 311.5 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 10.1 | 15.7 | 41.8 | 28.8 | 42.8 |
| የውጭ ዕርዳታ | 16.5 | 13.5 | 23.8 | 18.6 | 40.7 |
| ጠቅላላ ወጪ | 93.8 | 156.5 | 371.6 | 264.1 | 480.1 |
| መደበኛ ወጪ | 40.5 | 68 | 207.6 | 137.8 | 276 |
| የካፒታል ወጪ | 53.3 | 88.5 | 164 | 126.3 | 204.2 |
| የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ | 62.4 | 106.6 | 227.5 | 167.1 | 289.1 |
| የመንግስት በጀት ጉድለት | (8.2) | (17.3) | (63.1) | (40.2) | (85.2) |
| ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ) | | | | | |
| ጠቅላላ የመንግስት ገቢ | 16.2 | 15.2 | 13.6 | 14.4 | 11.7 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ | 13.1 | 13.6 | 12.7 | 13.1 | 10.5 |
| የታክስ ገቢ | 11.2 | 11.8 | 10.7 | 11.3 | 9.2 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 1.9 | 1.8 | 1.9 | 1.9 | 1.3 |
| የውጭ ዕርዳታ | 3.1 | 1.7 | 1 | 1.3 | 1.2 |
| ጠቅላላ ወጪ | 17.7 | 17.02 | 16.3 | 16.7 | 14.2 |
| መደበኛ ወጪ | 7.7 | 7.3 | 9 | 8.2 | 8.2 |
| የካፒታል ወጪ | 10.1 | 9.7 | 7.3 | 8.5 | 6.1 |
| የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ | 11.8 | 11.6 | 10.1 | 10.8 | 8.6 |
| የመንግስት በጀት ጉድለት | 1.6 | 1.8 | 2.7 | 2.3 | 2.5 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር

ከላይ በሠንጠረዥ 1.5 እንደሚታየው ባለፉት አስር ዓመታት የታክስ ገቢ ከመጠን አኳያ ከፍተኛ ዕድገት ያሣየ ቢሆንም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር ሲታይ ግን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው።

በ2003 በጀት ዓመት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11.2 በመቶ የነበረ ሲሆን ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ግን የመቀነስ አዝማሚያ በማሳየት በ2012 በጀት ዓመት 9.2 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ለዚህ ደካማ አፈጻጸም ከኢኮኖሚው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የታክስ ፖሊሲ አለመቅረፅ፣ የታክስ አስተዳደሩ አሠራሮችን በተሟላ መንገድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመደገፉና ያሉትን ተቋማዊ አቅሞች አሟጦ

አለመጠቀሙ፣ አሠራሩን ለማሳለጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የታክስ ሥርዓት (electronic taxation system) በተሟላ መንገድ አለመተግበሩ፣ ቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆኑ፣ የሕግ ተገዥነትን ለማሳደግ የሚያስችል የታክስ ከፋዮች ትምህርት ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በፈቃደኝነት ታክስ አስታውቆ የመክፈል ባህል ዝቅተኛ መሆኑ፣ የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር በመንሰራፋቱ በየዓመቱ ሕገወጥ ኪሳራ በማጋጠሙ፣ ባዶ እና ተመላሽ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣ የኮንትሮባንድ መስፋፋት እና የመከላከል አቅም ደካማ መሆኑ፣ በኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀሰውን ሃብት ወደ ታክስ መረቡ ማስገባት አለመቻሉ ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው። በመሆኑም በቀጣይ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን በዘላቂነት በማጠናከር እንዲሁም አስፈላጊ ፖሊሲዎችን በመቅረፅና በማሻሻል የታክስ ገቢን በፍጥነት ለማሳደግ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች መፍጠርና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

ከወጪ አኳያ በ2003 በጀት ዓመት 94 ቢሊዮን ብር ለመደበኛ እና ካፒታል ወጪ ተደርጎ የነበር ሲሆን ይህ ወጪ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 480 ቢሊዮን ብር ከፍ ብሏል። የወጪ አመዳደቡ በካፒታል ኢንቨስትመንት እና ድህነትን ከመቀነስ አንጻር ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል። ከዚህ አኳያ ከ2003 እስከ 2008 ድረስ ባሉት በጀት ዓመታት የወጪው ድርሻ በአማካይ ለካፒታል 56 በመቶ ለመደበኛ 44 በመቶ ሆኖ የቆየ ሲሆን ከ2009 እስከ 2012 ባሉት በጀት ዓመታት ደግሞ የመደበኛ ወጪ ከካፒታል ወጪ ብልጫ አሳይቷል። በተመሳሳይ ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ 65 በመቶ የሚሆነው ድህነትን ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋጽዖ ላላቸው የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ዘርፎች እንዲውል ተደርጓል።

በሌላ በኩል የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ከ3 በመቶ እንዳይበልጥ ለማድረግ ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል። ከዚህ አኳያ የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2009 በጀት ዓመት ወደ 3.2 በመቶ ከፍ ብሎ የነበረ ቢሆንም ያለፉት አስር ዓመታት አማካይ አፈጻጸም ሲታይ ግን መልካም የሚባል ነው።

**የዕዳ ጫና ሁኔታ፦** ባለፉት አስር ዓመታት የሀገሪቱ የውጭ ብድር ክምችት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እየጨመረ መጥቶ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 28.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል። በዚህም የመንግስት የውጭ ብድር ክምችት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 23.8 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 26.6 በመቶ ከፍ ብሏል። የሀገር ውስጥ ብድርን ጨምሮ ጠቅላላ የመንግሥት ብድር ክምችት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 44.6 በመቶ በ2010 በጀት ዓመት ወደ 58.6 ከፍ ብሎ የነበር ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ግን ወደ 51 በመቶ ዝቅ ብሏል (ሠንጠረዥ 1.6)።

በአጠቃላይ የልማት አጀንዳዎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ፋይናንስ አስተማማኝና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለማሰባሰብ የውጭ ዕርዳታና ብድር ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ የመንግስት ጠቅላላ ገቢ በተለይ የታክስ ገቢን እንዲሁም የወጪ ንግድ ገቢን ማሳደግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 1.6፡ ያለፉት ዓመታት የብድር ክምችት አፈጻጸም

| | 2003 | አማካይ (በቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር) | | | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2003-2007 | 2008-2012 | 2003-2012 | |
| ጠቅላላ የብድር ክምችት | 15 | 22.8 | 48.7 | 35.7 | 54.9 |
| የውጭ የብድር ክምችት | 8 | 12.1 | 25.2 | 18.7 | 28.7 |
| የሀገር ውስጥ የብድር ክምችት | 7 | 10.7 | 23.5 | 17.1 | 26.2 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 33 | 49.9 | 88.8 | 69.3 | 107.7 |
| ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ) | | | | | |
| ጠቅላላ የብድር ክምችት | 44.6 | 45.2 | 54.9 | 50.1 | 51 |
| የውጭ የብድር ክምችት | 23.8 | 23.9 | 28.5 | 26.2 | 26.6 |
| የሀገር ውስጥ የብድር ክምችት | 20.8 | 21.3 | 26.4 | 23.8 | 24.3 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር


## 1.4 የገንዘብ ፖሊሲና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት

**የገንዘብ ፖሊሲ፦** ባለፉት አስር ዓመታት ሀገራዊ የዋጋ ሁኔታ የተረጋጋ እንዲሆን የተለያዩ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ከዚህ አኳያ የመሠረታዊ ገንዘብ ዕድገትን በመቆጣጠር የገንዘብ አቅርቦት ዕድገት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል። ከዚህ አንጻር የገንዘብ ፖሊሲ የመካከለኛ ግብ የሆነው የገንዘብ አቅርቦት አፈጻጸም በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 145 ቢሊዮን ብር የ24.5 በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 1.04 ትሪሊዮን ብር ደርሷል። ለዚህም የባንኮች የሀገር ውስጥ ብድር መጨመር ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። በአንጻሩ የባንኮች የተጣራ የውጭ ምንዛሪ ክምችት በተመሳሳይ ወቅት ቅናሽ አሳይቷል። ለዚህም የወጪ ንግድ የውጭ ምንዛሪ ግኝት መቀዛቀዝ በዋነኝነት እንደ ምክንያት ይጠቀሳል።

የገንዘብ ፖሊሲ አካል የሆነው የባንክ የወለድ ተመን የፋይናንስ ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሰራ ቆይቷል። ከዚህ አንጻር ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ለተቀማጭ ገንዘብ የሚከፈለው ዝቅተኛ የወለድ ምጣኔ የተሻሻለ ሲሆን በአንጻሩ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ በባንኮች እንዲወሰን ተደርጓል።

በዚህም መሠረት ባለፉት አስር ዓመታት ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት 14.4 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የምግብ ነክ ሸቀጦች ዋጋ ግሽበት 15.2 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች የዋጋ ግሽበት 13.7 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል (ሥዕል 1.2)። ለዚህም ዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ ግሽበት፣ በሀገሪቱ ውስጥ የሚታየው የተዛባ የገበያ ሥርዓት፣ የአቅርቦት መዋዠቅ፣ ከፍተኛ የሆነ የመንግሥት ኢንቨስትመንት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት በዋነኝነት እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ።

ሥዕል 1.2፡ ከ2003-2012 ሀገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ለውጥ ሁኔታ (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ

**የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት፡-** ባለፉት ዓመታት የባንኮች ሀብት፣ የማበደር አቅም እና የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት እየጨመረ መጥቷል። የባንኮች ቅርንጫፍ ብዛት በአማካይ በየዓመቱ የ26 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 682 በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 6,511 (የመንግሥት 1,927፣ የግል 4,584) ደርሷል። በዚህም የባንክ ደንበኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 50.7 ሚሊዮን ደርሷል። በተመሳሳይ ጊዜ የተበዳሪዎች ቁጥር ከ95,014 ወደ 296,411 አድጓል።

በዚህም ባለፉት አስር ዓመታት የባንኮች ተቀማጭ ገንዘብ በአማካይ የ27 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 98.6 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.04 ትሪሊዮን ብር አድጓል። በተመሳሳይ የባንኮች የብድር አቅም ከተቀማጭ ገንዘብ መጨመር ጋር ተያይዞ እያደገ በመምጣቱ የተከማቸ ብድር በአማካይ በ29.8 በመቶ በማደግ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 78.1 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.03 ትሪሊዮን ብር አድጓል።

በሀገሪቱ የባንክ አገልግሎት መስፋፋቱና የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ተሳትፎ መጨመሩ ለግል መድን ድርጅቶች መፈጠርና መስፋፋት ዋነኛ መንስኤ ነው። ከዚህ አኳያ የመድን ኩባንያዎች የቅርንጫፍ ብዛት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 194 በ2012 በጀት ዓመት ወደ 605 አድጓል። በተመሳሳይ ወቅት የካፒታል መጠናቸውም ከ955.7 ሚሊዮን ብር ወደ 9.7 ቢሊዮን ብር ከፍ ብሏል።

በተመሳሳይ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት፣ የሀብት መጠን እና የብድር አቅም በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል። ከዚህ አኳያ የአነስተኛ ፋይናንስ (microfinance) ተቋማት ቁጥርና ተደራሽነት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 30 ተቋማት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 41 ደርሷል። አጠቃላይ የካፒታል መጠናቸውም ከ2.9 ቢሊዮን ብር ወደ 19.4 ቢሊዮን ብር አድጓል።

# 1.5 የውጭ ንግድ ልማት

**የሸቀጦች የወጪ ንግድ፡-** የሸቀጦች የወጪ ንግድን ለማስፋፋትና የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ በመንግሥት በኩል የተለያዩ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል። የወጪ ንግድ ምርቶችን በአይነትና በጥራት ለማሳደግና በዓለም ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት በርካታ የማበረታቻ ስልቶች ተዘርግተው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ የወጪ ንግድ ምርቶችን በአይነት የማስፋፋትና ከፍተኛ ገቢ ሊያመጡ የሚችሉ የማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ሸቀጦችን የመፍጠር አቅም ደካማ ነበር። በእነዚህና በሌሎች ተጓዳኝ ተግዳሮቶች ምክንያት የሸቀጦች የወጪ ንግድ ዕድገት አፈጻጸምና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ዝቅተኛ ነው። በዚህም ምክንያት ባለፉት አስር ዓመታት የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ያሳየው አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 4.1 በመቶ ብቻ ሲሆን፣ በ2012 በጀት ዓመት ከሸቀጦች የወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢም 2.99 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነው። የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት በ2003 በጀት ዓመት የ8.4 በመቶ ድርሻ የነበረው ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ድርሻው ወደ 2.8 በመቶ አሽቆልቁሏል። በ2012 በጀት ዓመት ከተገኘው ገቢ ውስጥ ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ጥራጥሬ፣ ጫት፣ አበባ እና የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ ምርቶች 74.9 በመቶ ድርሻ አላቸው። እነዚህ የወጪ ንግድ ምርቶች በ2003 በጀት ዓመት ከተገኘው 2.75 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ 68 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ይህም የወጪ ንግድ ዘርፉ በአይነት መስፋፋት ደካማ መሆኑንና የዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በጥቂት የግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ መሆኑን ያመለክታል (ሥዕል 1.3)።

ሥዕል 1.3፡ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ከ2003-2012 በጀት ዓመት ከግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ በየዓመቱ በአማካይ 2.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ የዘርፉ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 4.5 በመቶ ሲሆን ለዚህም አስተዋጽዖ ያደረጉት ሀገሪቱ በመደበኛነት የምትልካቸው የምርት አይነቶች ናቸው፡፡ ከዋና ዋና የግብርና ወጪ ንግድ ምርቶች ውስጥ በአማካይ በየዓመቱ ከቡና 797 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ ከቅባት እህሎች 435 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ ከጥራጥሬ 229 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ ከጫት 275 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሁም ከአበባ ወጪ ንግድ 231 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

ባለፉት አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በየዓመቱ በአማካይ 357 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ አስገኝቷል፡፡ ምንም እንኳ ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ ያለው ድርሻ ዝቅተኛ ቢሆንም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ገቢ ከሌሎች ዘርፎች አንጻር ሲታይ ፈጣን ያለ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በዚህም መሠረት በአማካይ የ24.5 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች ለዘርፉ ከተሰጡ የፖሊሲ ድጋፎች በተጨማሪ የጨርቃጨርቅ እና የቆዳና የቆዳ ውጤቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ያሳዩት አንጻራዊ ተወዳዳሪነት እና ከኢንዱስትሪ ፓርኮች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ያሳየው መነቃቃት ናቸው፡፡ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ምርቶች ውስጥ ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች 102.2፣ ከጨርቃጨርቅ እና የጨርቃጨርቅ ውጤቶች 103.3፣ ከኤሌክትሮኒክስ 34.5፣ ከብረትና የብረታ ብረት ውጤቶች 2.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ አማካይ ገቢ ተገኝቷል፡፡


በሌላ በኩል ከማዕድን ዘርፍ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ባለፉት አስር ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ 24 በመቶ ዕድገት ቢያስመዘግብም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በሕገ ወጥ ንግድ መስፋፋት እንዲሁም በማበረታቻ እና በሌሎች የአሠራርና የፖሊሲ ክፍተቶች ምክንያት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ያም ሆኖ ዘርፉ በተመሣሣይ ጊዜ በአማካይ በየዓመቱ 340 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለሀገሪቱ አስገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ 94.25 በመቶ የሚሆነው ገቢ የተገኘው ከወርቅ የወጪ ንግድ ነው፡፡

**የሸቀጦች የገቢ ንግድ፦** ሀገሪቱ ከውጭ የምታስገባቸው በዋናነት የቴክኖሎጂና የካፒታል እቃዎች በመሆናቸው በዓለም ገበያ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በተጨማሪ ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ የፋብሪካ ጥሬ እቃ፣ መድሀኒት እና የመሳሰሉት የገቢ ንግድ ሸቀጦች ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ግብዓት በመሆናቸው የማያቋርጥ የውጭ ምንዛሪ ይከፈልባቸዋል፡፡ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ ጠቅላላ የሸቀጦች የገቢ ንግድ ፈጣን ዕድገት አሳይቷል፡፡ በዚህም በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በአማካይ በየዓመቱ በ6.1 በመቶ በማደግ በ2012 በጀት ዓመት 13.9 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል፡፡ ከ2003-2012 ድረስ በነበሩት ዓመታት የተመዘገበው የካፒታል ዕቃዎች ገቢ ንግድ አማካይ ዕድገት 5.3 በመቶ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ የሸቀጦች ገቢ ንግድ ውስጥ የ35.3 በመቶ ድርሻ ነበረው፡፡ ለእነዚህ እቃዎች ከወጣው ዓመታዊ አማካይ የ4.86 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች 75.2 በመቶ፣ የትራንስፖርት ዕቃዎች 22.9 በመቶ እንዲሁም የግብርና ዕቃዎች 1.9 በመቶ አማካይ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የፍጆታ ገቢ ንግድ ዕቃዎች የ6.4 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት ያሳዩ ሲሆን ከጠቅላላ የገቢ ንግድ ወጪም የ29.3 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከ4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ዓመታዊ አማካይ የፍጆታ እቃዎች ገቢ ንግድ ወጪ ውስጥ አላቂ የፍጆታ ዕቃዎች 69.4 በመቶ እንዲሁም አላቂ ያልሆኑ የፍጆታ ዕቃዎች 30.6 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ 1.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የነበረው የነዳጅ ገቢ ንግድ ወጪ የ7.6 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት በማሳየት በ2012 በጀት ዓመት

2.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል። ይህም ከጠቅላላ ዓመታዊ አማካይ የሸቀጦች ገቢ ንግድ ወጪ ውስጥ የ15.1 በመቶ አማካይ ድርሻ ነበረው። በሌላ በኩል የጥሬ ዕቃዎች ገቢ ንግድ በአማካይ 1.7 በመቶ ዓመታዊ ቅናሽ በማሳየት በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ከነበረበት 112.4 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 162.2 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ዝቅ ብሏል። ይህም ከጠቅላላ የሸቀጦች ገቢ ንግድ ክፍያ የ1.2 በመቶ ብቻ ድርሻ ነበረው።

**የሸቀጦች የንግድ ሚዛን፦** በሸቀጦች ወጪ ንግድ ዘርፍ የታየው ደካማ አፈጻጸምና የሸቀጦች ገቢ ንግድ ፈጣን ዕድገት የንግድ ሚዛኑን ለጉድለት ዳርጎታል። በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የ5.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉድለት በ2012 በጀት ዓመት 10.9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ደርሷል። ይሁን እንጂ የሸቀጦች ንግድ ሚዛን ጉድለት ከሀገራዊ ጠቅላላ ምርት የያዘው ድርሻ ከ16.8 በመቶ ወደ 10.1 በመቶ ወርዷል። ከሸቀጦች የወጪ ንግድ የተገኘው ገቢ የሸቀጦች ገቢ ንግድን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በአማካይ መሸፈን የቻለው 22.5 በመቶውን ብቻ ነው። በተለይም በቅርብ ዓመታት በዋነኛነት ከወጪ ንግድ መቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ የወጪ ንግድ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት 21.5 በመቶ ብቻ ሆኗል (ሥዕል 1.4)።

ሥዕል 1.4፡ የሸቀጦች የንግድ ሚዛን (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

# ምዕራፍ ሁለት

## የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

# 2.1 የግብርና ልማት

ከ2003 እስከ 2012 ባሉት ዓመታት ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚያደርግ የተጠበቀው አንዱና ዋናው ዘርፍ ግብርና ነው። ዘርፉ ለጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕድገትና ለድህነት ቅነሳ የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ከማሳደግ አኳያ በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ዕድገት በማምጣት የግብርና (የሰብል፣ እንስሳት፣ ደንና ዓሳ) ምርትንና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትን ማቀላጠፍ፣ በዘርፉ የገበያ ትስስርን ማሳደግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ማረጋገጥ፣ የህዝቡን ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ እና በዘርፉ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ነበሩ።

የግብርና አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (agricultural GDP) ዕድገት ከ2003 እስከ 2012 በጀት ዓመት በአማካይ በየዓመቱ የ5.3 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ በዕቅድ ከተያዘው ከ8 በመቶ በላይ አማካይ የዕድገት ምጣኔ ግብ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። በግብርና ውስጥ ከሚጠቃለሉት ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች መካከል የሰብል እና የእንስሳት ሀብት በአማካይ በየዓመቱ በቅደም ተከተል በ6.1 በመቶ እና በ3.7 በመቶ አድገዋል። በተመሳሳይ የደን ንዑስ ዘርፍ በአማካይ በየዓመቱ 3.4 በመቶ አድጓል። በዘርፉ የተመዘገበው አጠቃላይ ሀገራዊ የምርት ዕድገት በዕቅድ ከተያዘው ግብ አንጻር ዝቅ ያለ ቢሆንም ከሕዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ በመሆኑ ለገጠር ድህነት ቅነሣ አስተዋጽዖ አድርጓል። በመሆኑም በ2003 በጀት ዓመት በገጠር ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ሕዝብ መጠን 30.4 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት ወደ 25.6 በመቶ ዝቅ ብሏል።

የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ እንዲሻሻል ምርታማነትን የሚጨምሩ፣ ጥራትን የሚያሻሽሉና፣ የግብይት ሰንሰለቱን የሚያቀላጥፉ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በተጨማሪም የህብረት ሥራ ማህበራት የእሴት ጭመራና የወጪ ገበያ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በመሬት አቅርቦትና በሌሎችም አገልግሎቶች ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል። በዚህም ባለፉት 10 ዓመታት በአጠቃላይ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ ከተገኘው የውጭ የምንዛሪ ገቢ ውስጥ 73.8 በመቶ የሚሆነው የተገኘው ከግብርና ምርቶች ነው። በ2012 በጀት ዓመት የግብርና ምርት የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ 57 በመቶ እንዲደርስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም አፈጻጸሙ በሌሎች ዘርፎች የወጪ ንግድ ዕድገት በታቀደው ደረጃ ባለመሣካቱ የተነሳ የወጪ ንግድ ገቢ አሁንም ድረስ በዋነኛነት በግብርናው ዘርፍ ላይ የተንጠለጠለ ሆኖ ይገኛል።

በአነስተኛ ይዞታ የሚመረተው የዋና ዋና ሰብሎች የመኸር ምርት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 222 ሚሊዮን ኩንታል በ2012 በጀት ዓመት ወደ 335 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ብሏል። በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት የአገዳና ብርዕ ሰብሎች አጠቃላይ ምርት 297 ሚሊዮን ኩንታል፣ የጥራጥሬ ሰብል ምርት 30 ሚሊዮን ኩንታል፣ እንዲሁም የቅባት ሰብል ምርት 8.4 ሚሊዮን ኩንታል ደርሷል። ይህም የምርት ዕድገት የተመዘገበው በዘርፉ በታየው ከ20 በመቶ በላይ አማካይ የምርታማነት ጭማሪ ሲሆን፣ በተለይም በአብዛኛው የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ላይ የታየው የምርታማነት ጭማሪ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው።

በአነስተኛ ይዞታ የሚመረተው የአትክልትና ፍራፍሬ የመኸር ምርት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 22 ሚሊዮን ኩንታል በ2012 በጀት ዓመት ወደ 60 ሚሊዮን ኩንታል (አትክልት 10 ሚሊዮን ኩንታል፣ ሥራስር 42 ሚሊዮን ኩንታል እና ፍራፍሬ 8 ሚሊዮን ኩንታል) ከፍ ብሏል። ይህም የምርት ዕድገት የተመዘገበው በዋነኛነት

ባለፉት አስር ዓመታት በንዑስ ዘርፉ በታየው የምርታማነት ዕድገት ሲሆን፣ በተለይም በአትክልት ከ629 በመቶ በላይ፣ በሥራስር ከ100 በመቶ በላይ፣ በፍራፍሬ 9 በመቶ አማካይ የምርታማነት ጭማሪ ተመዝግቧል። ለዚህም የምርታማነት ዕድገት የግብርና ግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማስፋፋት እንዲሁም ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ዙሪያ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋጽዖ አደርገዋል።

የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ምርትን ከማሳደግ አኳያ በተከናወኑ የልማት ሥራዎች የተሻሻሉ ታላቢ ላሞችን ምርታማነት በማሳደግ የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 7 ቢሊዮን ሊትር ደርሷል። በተጨማሪም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከምርት ዕድገት አንጻር ዓመታዊ የሥጋ ምርት 1.7 ሚሊዮን ቶን፣ የእንቁላል ምርት በቁጥር 2.9 ቢሊዮን፣ የዶሮ ሥጋ ምርት 105 ሺህ ቶን፣ የቆዳና ሌጦ ምርት በቁጥር 23 ሚሊዮን፣ የማር ምርት 110 ሺህ ቶን እንዲሁም የዓሣ ምርት 59 ሺህ ቶን ደርሷል። ከምርታማነት አኳያም መሻሻሎች የታዩባቸው ሲሆን በግብርና አስተዳደራዊ መረጃ መሠረት ከሀገር በቀል የወተት ላም የሚገኝ አማካይ ዕለታዊ የወተት ምርት መጠን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 1.5 ሊትር በ2012 ወደ 2.6 ሊትር ከፍ ብሏል። ከአንድ የተዳቀለች የወተት ላም የሚገኝ አማካይ ዕለታዊ የወተት ምርት መጠን 12.1 ሊትር የደረሰ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው 10 ሊትር ዕለታዊ ምርታማነት ጋር ሲነጻጸር 21 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በተመሳሳይ ከአንድ ግመል የሚገኝ አማካይ ዕለታዊ የወተት ምርት መጠን 5.4 ሊትር የደረሰ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው 3.7 ሊትር ጋር ሲነጻጸር 44 በመቶ አድጓል። በተመሳሳይ ከአንድ ፍየል የሚገኝ አማካይ ዕለታዊ የወተት ምርት መጠን 0.4 ሊትር የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር 33 በመቶ ዕድገት አሳይቷል።

ከአንድ ዳልጋ ከብት የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት (carcas weight) በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 107 ኪሎ ግራም በ2012 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ 110 ኪሎ ግራም ደርሷል። ከአንድ በግ እና ፍየል የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት በ2012 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ በቅደምተከተል 11 ኪሎ ግራም እና 8 ኪሎ ግራም ደርሷል።

የመስኖ ልማት ከማስፋፋት አኳያ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ሽፋኑን 4.1 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ መሠረት የመስኖ መሬት ሽፋኑ እስከ 2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 790 ሺህ ሄክታር ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል። የተለያዩ የውኃ አማራጮችን ተጠቅመው በመስኖ የሚያለሙትን አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር 10 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የተጠቃሚው ቁጥር 4.3 ሚሊዮን ብቻ (ከዕቅዱ 43 በመቶ) መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የመስኖ ልማት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚፈልግ መሆኑና በዋጋ ግሽበት ምክንያት በመስኖ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ መጓተት መኖሩ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ለገጠሩ ህብረተሰብ የሥራ ዕድል በመፍጠር የገጠር የሥራ አጥነትን በመቀነስ በኩል በግብርናው ዘርፍ ባለፉት አምስት ዓመታት 6.7 ሚሊዮን የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። ይህም በአጠቃላይ የተፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2012 በጀት ዓመት 7.7 ሚሊዮን አድርሶታል። በከተሞች አካባቢ ወጣቱን ወደ ግብርና ዘርፍ በመሳብ የሥራ ዕድል ከመፍጠሩ በተጨማሪ ለከተሞች በቂ የግብርና ምርት ለማቅረብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል። በተለይም ወጣቱን ወደ ግብርና ዘርፍ ለመሳብና ተሳትፎው እየጨመረ እንዲሄድ ለማድረግ ግብርናን

የማዘመን ሥራዎች ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በእሴት መጨመር እንዲሁም በግብይት ሰንሰለት ልማት ላይ ሰፋፊ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። የተጐዱ አካባቢዎችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግ እንዲያገግሙ ተከልለው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገበት የመሬት መጠን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 4 ሚሊዮን ሄክታር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 21 ሚሊዮን ሄክታር አድጓል። በተጨማሪም የተፋሰስ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም ከፍተኛ የሆነ ዕድገት በማሳየት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.9 ሚሊዮን ሄክታር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 33.5 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ብሏል።

ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት ስትራቴጂ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ከማምጣት አንጻር ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ ቴክኖሎጂዎችን በመደበኛ የልማት ዕቅድ ውስጥ በማካተት እንዲተገበሩ ተደርጓል። ስትራቴጂው በግብርናው ዘርፍ በስፋት ተግባራዊ በተደረገባቸው ባለፉት አምስት ዓመታት (2008-2012) በአጠቃላይ 78.1 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ታቅዶ 36.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ አፈፃጸሙ 47.1 በመቶ ነው።

በዘርፉ የተመዘገበው አፈጻጸም በገጠር መቀነስ ካለበት የድህነት ምጣኔ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ግብዓትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ መጫወት ከሚጠበቅበት ሚና እንዲሁም ከፍተኛ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ እንደ አነስተኛ መሠረት እና ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ አንጻር ሲታይ አነስተኛ ነው። ዘርፉ ውስጣዊ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና ከመዘመን አንጻርም ክፍተቶች ያሉበት ሲሆን፣ ከዝናብ ጥገኝነት ባለመላቀቁም ድርቅ በሚከሰትባቸው ጊዜያት በዘርፉ የተሰማራው ማህበረሰብ መፈተኑ አልቀረም። ግብርና የሕይወት መሠረት በሆነበት በገጠሩ አካባቢ ቀላል የማይባል ቁጥር ያለው ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች ይገኛል።

በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ ከማድረግ፣ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ እና ለሌሎች ዘርፎች አስተማማኝ ግብዓቶችን ከማቅረብና ለምርቶች ገበያ ከመፍጠር አንጻር የግብርናው ዘርፍ ውስንነት ነበረበት። ዘርፉ የሀገሪቱን ሕዝብ የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ያልቻለ ሲሆን እስከ 25 ሚሊዮን ያህል ዜጎች በቂ ምግብ እንደማያገኙ ይገመታል። ከ15 ሚሊዮን የማያንሱ ዜጎችም በእለት ደራሽ እርዳታና በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ታቅፈው ይገኛሉ። የዘርፉን የሰው ኃይል ምርታማነት ዕድገትና የምርቶችን ምርታማነት ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ምርቶች የማሸጋገር ሂደቱ ደካማ በመሆኑ አሁንም የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል።

ያለፉት አስር ዓመታት አፈጻጸም እንደሚያሳየው ዘርፉ በምርትም ሆነ በምርታማነት መሻሻሎች የታዩበት ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥ፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሥርዓት ኋላቀርነት፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር፣ ያልዘመነ የምርት ገበያ፣ በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማትና ኢንቨስትመንት፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና ባለፉት አራት ዓመታት ጎልቶ የታየው የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ሁኔታ ዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም እንዳያሳይ ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች ነበሩ።

# 2.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት

ባለፉት አስር ዓመታት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት እና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሰራ የቆየ ቢሆንም በንዑስ ዘርፉ የተመዘገበው አማካይ ዓመታዊ የተጨማሪ ዕሴት ዕድገት 14.1 በመቶ ብቻ ነበር። በአጠቃላይ የግብዓትና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ዕጥረት፣ ደካማ የኢንዱስትሪዎች ትስስር፣ ዝቅተኛ የሰው ኃይል ምርታማነት፣ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውሱንነት እና ከፀጥታ መደፍረስ ጋር የተያያዙ ችግሮች የንዑስ ዘርፉን የማምረት አቅም አጠቃቀም ዝቅተኛ እንዲሆን አድርገውታል።

የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በተመለከተ ከጨርቃጨርቅ፣ ከስጋና ወተት፣ ከምግብ ማቀነባበሪያ እና ከፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት በ2003 ከነበረበት በቅደም ተከተላቸው 62.2፣ 67.4 እና 34.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር፤ እንዲሁም በ2012 ወደ 171.6፣ 72.5 እና 66.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያደገ ሲሆን፣ በአንጻሩ ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን ከ104.3 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወደ 72.6 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዝቅ ብሏል። ለዚህም የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዝቅተኛ አፈጻጸም፣ የውጭ ምንዛሪ እና የኃይል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመቅረብ እና ውሱን የገበያ ተወዳዳሪነት አቅም መኖር በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ለማሳለጥና የተጀመረውን የልማት እንቅስቃሴ ለማጎልበት የብረታ ብረትና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በተለይም የገቢ ምርቶችን ከመተካት አኳያ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። የገቢ ምርትን ከመተካት አንጻር በምርት መጠናቸው ከፍተኛ ድርሻ ይዘው የሚገኙት ስሚንቶ፣ የአርማታ ብረት፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና የሴራሚክስ ምርቶች ሲሆኑ የምርት መጠናቸውም በ2012 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል ወደ 17.1፣ 5.5፣ 1.5 እና 0.6 ሚሊዮን ቶን አድጓል። በተለይም የስሚንቶ ምርት ሀገራዊ ፍላጐትን ከማሟላት በዘለለ ለውጭ ገበያ እየተላከ የውጭ ምንዛሪ ማመንጨት ጀምሯል። በአጠቃላይ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማት ግብዓት በማቅረብ ረገድ ለምሳሌ በአርማታ ብረት፣ በቶቦላሬ፣ በቆርቆሮ፣ በሚስማር፣ በስሚንቶ፣ በሴራሚክ፣ በጂፕሰም፣ በእምነበረድና በቴራዞ ምርቶች የተሻለ ሀገራዊ አቅም እየተፈጠረ ነው። በተመሳሳይ ሀገራዊ የምግብ ዘይት ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት ለሟሟላት የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት 11 ፋብሪካዎች በማምረት ላይ ያሉ ሲሆን 8 ግዙፍ ፕሮጀክቶች በግንባታ ላይ ናቸው።

ከጠቅላላ የገቢ ንግድ ወጪ ውስጥ 20 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚወስደው የብረታ ብረት ምርት ሲሆን ይህም የሚያሳየው ዘርፉ ከውጭ በሚገቡ የግብዓት ምርቶች ላይ ጥገኛ መሆኑን ነው። ይህም የውጭ ምንዛሪ አቅርቦቱ ላይ ጫና ከመፍጠሩም ባለፈ በግብዓት አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ችግር በመፍጠሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ካላቸው ሙሉ አቅም ውስጥ ከ50 በመቶ በታች እንዲጠቀሙ አድርጓል። በተጨማሪም ጥጥ፣ ቆዳ እና ሌሎች ለአግሮፕሮሰሲንግ ግብዓትነት የሚውሉ የግብርና ምርቶችን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ፣ ዋጋ፣ መጠን እና ጊዜ ለኢንዱስትሪው ማቅረብ አልተቻለም።

ለዘርፉ ከአቅም በታች የማምረት ችግር በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ዘመናዊ የሥራ አመራርና የጥራት ሥርዓት የተጠናከረ አለመሆኑ፤ ኢንዱስትሪዎች ከዩኒቨርስቲ፣ ከምርምር

እና ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር ደካማ መሆኑ፤ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ቴክኖሎጂን የማሸጋገር ሥራ በሚፈለገው ደረጃ አለመሰራቱ፤ ለጥናትና ምርምር በቂ ፋይናንስ አለመመደቡ፤ ጥራት ያለው መሠረተ ልማት አለመስፋፋቱ እና የመሬት አቅርቦት እጥረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በአጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ዝቅተኛ ምርታማነት የሚስተዋልበት በመሆኑ ተወዳዳሪነቱም ደካማ መሆኑን የአፈጻጸም መረጃው ያሳያል። በመሆኑም በቀጣይ መሠረታዊ የብረታ ብረት ምርቶችን በሀገር ውስጥ ግብዓት በማምረት፤ የነባር ኢንዱስትሪዎችን የአቅም አጠቃቀም በማሻሻል፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እና ጥራት ያለው ኢንቨስትመንትን በመሳብ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውጤት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ አትኩሮ መሥራት እንደሚገባ አፈጻጸሙ ያመለክታል።

## 2.3 የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

ባለፉት አስር ዓመታት ከተሜነት በአማካይ በየዓመቱ በ3.7 በመቶ አድጓል። የከተሜኔት ደረጃ በ2012 በጀት ዓመት 21.4 በመቶ የደረሰ ሲሆን በከተማ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 23 ሚሊዮን እንደደረሰ ይገመታል። የከተሜነት ደረጃው ከአፍሪካ አማካይ (40 በመቶ) እና ከዓለም አማካይ (57 በመቶ) ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ሲሆን የከተሜነት ዕድገት ምጣኔ ግን ከአፍሪካ አማካይ (3.1 በመቶ) እና ከዓለም አማካይ (2.7 በመቶ) አንጻር ሲታይ ከፍ ያለ እንደሆነ መረጃው ያሳያል። ለከተሜነት ደረጃ እና የከተሜነት የዕድገት ምጣኔ ፈጣን መሆን ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት እና የከተሞች የሕዝብ ዕድገት ዋነኛ ምክንያቶች ሲሆኑ የገጠር ማዕከላት ወደ ከተማነት ደረጃ በማደጋቸው የሚፈጠር ለውጥ፣ የከተማ መስፋፋት፣ እንዲሁም አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶችን ተከትሎ የሚኖር የሕዝብ ዕድገት በዚሁ በቅደም ተከተል አስተዋጽዖ አድርገዋል።

የሀገራችን የአከታተም ሥርዓት ጤናማ ያልሆነና የተመጣጠነ ተዋረድ የሌለው ሆኖ ቀጥሏል። በዚህም ትልቁ ከተማ (አዲስ አበባ) ከመካከለኛ ከተሞች በ10 እጥፍ የሚበልጥ ሲሆን የመካከለኛ ከተሞችም ከአነስተኛ ከተሞች በተመሳሳይ ምጣኔ የተራራቁ ናቸው። ይህ አዝማሚያ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፉት ዓመታት የአዲስ አበባ የሕዝብ ብዛት ከአጠቃላይ የከተማ ሕዝብ ብዛት ከ23.9 በመቶ ወደ 21.7 በመቶ ቀንሷል። ይህ የአከታተም ሥርዓት አዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ከተማ በመሆን የኢንዱስትሪው ልማት ሞተር ሆና መቀጠሏ የማይቀር መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይህም የተመጣጠነ እና ፍትሐዊ አከታተምን በማረጋገጥ በየደረጃው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ሚና ያላቸውን ከተሞች ተመጋጋቢ ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ፣ የሁሉንም ከተሞች የዕድገት ዕድል ማስፋት እና የህዝቦችን የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ማረጋገጥ በቀጣይ በተቀናጀ መንገድ መከናወን ያለባቸው ሥራዎች መሆናቸውን ያመለክታል።

በ2003 በጀት ዓመት በከተማ ያለው የሥራ አጥነት ምጣኔ 18 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ2007 በጀት ዓመት ወደ 16.8 በመቶ ቢቀንስም በ2012 በጀት ዓመት ወደ 18.7 በመቶ ከፍ ብሏል። ባለፉት 9 ዓመታት 1.3 ሚሊዮን ኢንተርፕራይዞች የተፈጠሩ ሲሆን በ2011 በጀት ዓመት በተደረገው የኢንተርፕራይዞች የናሙና ቆጠራ መሠረት የኢንተርፕራይዞች የመክሰም ምጣኔ 25.3 በመቶ ነበር። ከሥራ ፈጠራ በተጨማሪ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አጋማሽ ላይ በተጀመረው የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም 582 ሺህ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

ከከተማ ልማት አኳያ የመሬት፣ የቤት ልማት፣ የኮንስትራክሽን እና የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ዘርፎች ተቋማዊ አደረጃጀቶችን እና ሕጋዊ ማዕቀፎችን የማጠናከር መጠነ ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል። የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ የሚመራበት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፤ ሀገራዊ የከተማ ልማትና አሰፋፈር ፕላን (National Urban Development Spatial Plan) ተዘጋጅቷል፤ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩቶች ተቋቁመዋል፤ እንዲሁም በየደረጃው ያሉ ከተሞች በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሠረት በፕላን የሚመሩባቸው ዕቅዶች መሠረታዊ መረጃዎች (Urban Profiles) ተደራጅተዋል። ከሀገራዊው የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ጋር የተጣጣሙ ዘጠኝ ክልላዊ የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላኖች (Regional Urban Development Spatial Plan) እና የከተሞች ክላስተር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቀዶ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ተፈፃሚ አልሆነም። በመሆኑም በቀጣይ የፌዴራል እና የክልሎች ከፍተኛ አመራሮችን ውሳኔ እና አቅጣጫ መሠረት በማድረግ የተቀናጀ ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ የማድረግ ሥራ በቂ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ከተሞችን ወደ ሊዝ ሥርዓት ከማስገባት አንጻር 842 ከተሞች ወደ ሥርዓቱ የገቡ ሲሆን ካሉት ከ2000 በላይ ከተሞች አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። የመሬትና መሬት ነክ ምዝገባ መረጃ ሥርዓት በ372 ከተሞች ለመዘርጋትና ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ በ23 ከተሞች ተግባራዊ ተደርጓል፤ የአየር በረራና የፎቶግራሜትሪ ሥራ ተሰርቷል፤ የመሬት ይዞታ ምዝገባን ለማስተግበር ለካዳስተር ካርታ ዝግጅት በግብዓትነት የሚያገለግሉ የመሬት ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን የማስፋፋት ሥራ ተሰርቷል፤ እንዲሁም በሳተላይት ስትሪዮ ምስል ለ44 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ተዘጋጅቷል። ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚሆን 144 ሺህ ሄክታር (96 በመቶ አፈጻጸም) መሬት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 26 በመቶ ለጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ተቋማትና ለኢንዱስትሪ፣ 19 በመቶ ለመሠረተ ልማት፣ 12.8 በመቶ ለመኖሪያ ቤት እና ቀሪው ለመዝናኛና ለሌሎች አገልግሎቶች የቀረበ ነው።

የቤቶች ልማትን በተመለከተ 580 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመንግስት ለመሥራት ታቅዶ 384,107 (66 በመቶ) የተገነቡ ሲሆን በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት 174 ሺህ ታቅዶ 152 ሺህ (87 በመቶ) ተገንብተዋል። እንዲሁም በሪል ስቴት አልሚዎች 70 ሺህ ታቅዶ 21,314 (30 በመቶ) ቤቶች ተገንብተዋል። የቤት አቅርቦቱ ካለው የቤት ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። በከተሞች ያለው የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ያልተጣጣመ መሆኑ አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ተገቢ ላልሆነ ወጪና መንገላታት በመዳረግ ለተወሳሰበ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ዳርጎታል። ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን የፋይናንስ እጥረት፣ የለማ መሬት አቅርቦት እጥረት፣ ወጪ ቆጣቢ የግንባታ ቴክኖሎጂ እና ዲዛይን ውሱንነት፣ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት እጥረትና ዋጋ መናር፣ የኮንስትራክሽን አቅምና የፕሮጀክት ሥራ አመራር ክህሎትና አቅም አናሳ መሆን፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን፣ ጠንካራ የቤት አስተዳደር ሥርዓት አለመኖር እና ጥቅም ላይ የዋሉ የቤት ልማት አማራጮች ውስን መሆን ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው። በመሆኑም የቤቶች ልማት ችግርን በዘላቂ ሁኔታ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉ ሰፊ አማራጮችን በቤቶች ልማት ላይ ተግባራዊ ማድረግ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን ይገባል።

የመሠረተ ልማትና አገልግሎት ግንባታን በተመለከተ 6,361 ኪ.ሜ የድንጋይ ንጣፍ መንገድ፣ 12,433 ኪ.ሜ የሚደርስ የጎርፍና የዝናብ ማስወገጃ መስመሮች ግንባታ፣ ከ3,406 በላይ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች (3 ደረጃውን የጠበቁ)፣ 502 የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቦታዎች እና 629 ቄራዎች (11 ዘመናዊ) ግንባታ ተከናውኗል። በከተሞች 141 ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን ለማዘጋጀት በታቀደው

መሠረት 101 (71 በመቶ) የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የተዘጋጁ ሲሆን 570 ሄክታር የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ቦታ የላንድስኬፕ ዲዛይኑን መሠረት አድርጎ እንዲለማ ተደርጓል። የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሽፋን ከ70 በመቶ ወደ 82 በመቶ ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በጥናት እንደተረጋገጠው ሽፋኑ በ2011 በጀት ዓመት 59 በመቶ ብቻ መሆኑን ያመለክታል። በተጨማሪም 49 አዳዲስና ነባር አረንጓዴ ፓርኮችን ለማልማት፣ 90 የውኃ አካላትና ዳርቻ ቦታዎች በስታንዳርድና ዲዛይን እንዲጠበቁና እንዲለሙ ለማድረግ እና 90 የዘላቂ ማረፊያ ቦታዎችን በስታንዳርዱና ዲዛይኑ መሠረት በመታሰቢያ ፓርክነት ለማልማት በዕቅድ ተይዞ በቅደም ተከተል 67፣ 30 እና 43 ቦታዎች እንዲለሙ ተደርጓል።

በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የፖሊሲ የማስፈጸሚያ የሕግና አሠራር ሥርዓት ለማጎልበት በዕቅድ ዘመኑ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የህንጻ አዋጅና ደንብ ማሻሻያ፤ የኮንስትራክሽን ኦዲት ደንብና መመሪያ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ አዋጅና ደንብ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። 11 የህንጻ ኮዶችና ስታንዳርዶች ሲከለሱ 3 ተጨማሪ ኮዶች (ማለትም የጤናና ደህንነት፣ የአርክቴክቸራልና የእሳት አደጋ መከላከያ) ተዘጋጅተዋል። እነዚህ የአሠራር ሥርዓቶች እና የሕግ ማዕቀፎች የተዘጋጁ ቢሆንም በተገቢ መልኩ ተግባራዊ ባለመደረጋቸው በግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በጠንካራና አስተማማኝ የሬጉላቶሪ ሥርዓት እንዳይመራ አድርጎታል።

ባለፉት አስር ዓመታት ዓለም አቀፍ  የተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው  የሥራ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን ለማፍራት ተችሏል። ይሁንና የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ባሉባቸው ድክመቶች እና ማነቆዎች ምክንያት አሁንም በሀገር ደረጃ ዓለም አቀፍ  ጨረታዎችና ኮንትራቶች በብዛት በውጭ ድርጅቶች ተይዘዋል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም ለመገንባት ግዙፍና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች የጥናትና የዲዛይን ማዕከል የሚሆንና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል ማበልፀጊያ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ተቋቁሞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ሀገሪቱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከተጠቀመችው አጠቃላይ ማሽነሪ ውስጥ በሀገር ውስጥ የተገጣጠመውና የተመረተው የማሽነሪ ብዛት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ የሀገር ውስጥ ምርትን ከማበረታታትና ከመጠቀም አኳያ በቀጣይ በትኩረት መሰራት እንዳለበት ያመለክታል።

## 2.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት

የሥነ ምድር መረጃ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነት፦ የሥነ ምድር መረጃ የማዕድንና ነዳጅ አለኝታ የሰፊ ክልል የጂኦሎጂና የሃይድሮ ጂኦሎጂ ካርታ ሥራዎች (በ1፡250000 መስፈርት) በ2009 በጀት ዓመት የተጠናቀቁ ሲሆን የጂኦኬሚስትሪ፣ የኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ፣ የጂኦፊዚክስና የጂኦተርማል ጂኦሎጂ እና የሰፊ ክልል ጂኦኬሚስትሪ ጥናትና ካርታ ሥራዎች ሽፋን አጠቃላይ አፈጻጸም 50 በመቶ  ደርሷል። ከዚህም በተጨማሪ የዝርዝር ሥራዎች (1፡50000-1፡10000) መረጃ መሰብሰብ እና የጥናት ቁፋሮዎችን ጨምሮ የክምችት ግመታዎች መጠን ከ30 በመቶ የዘለለ ባለመሆኑ ምክንያት የማዕድን ሀብትን አለኝታ የመለየት ሥራው እጅግ ዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ ይገኛል። ለዚህም በዘርፉ በቂ ልምድና ተሞክሮ ያዳበሩ ባለሙያዎች እጥረት፣ የካርታ ሥራው ከጂኦኬሚስትሪው ጋር ተቀናጅቶ አለመሰራት፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጥረት፤ የሥነ ምድር መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ አለመደራጀታቸው እና በክልሎች የሚሰበሰበው መረጃ የሰርቬይ መረጃ ቋቱ አካል አለመሆን ዋና ዋና ተግዳሮቶች ነበሩ።

የውጪ ምንዛሪና የሀገር ውስጥ ገቢ ማሳደግ፦ የማዕድን ንዑስ ዘርፍ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከሚጠበቀው አንጻር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም እንደ ምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው አለመረጋገትና የኮንትሮባንድ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ መስፋፋት ይገኙበታል። ባለፉት አስር ዓመታት ከልዩ ልዩ ማዕድናት ምርት ይገኝ የነበረው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ገቢ 3404 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ይህም በአማካይ በዓመት 340 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይሆናል። የውጪ ምንዛሪ ገቢ መጠኑ ከዓመት ዓመት የሚዋዥቅ ሲሆን በ2004 በጀት ዓመት 650 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሆነ ከፍተኛ ገቢ የተገኘ ቢሆንም በቀጣይ ዓመታት በተከታታይ ቅናሽ በማሳየት በ2011 በጀት ዓመት 48.93 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሶ ነበር። ለአፈጻጸሙ ማነስ በቅርብ ዓመታት የተከሰተው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ትልቅ የሚባለው የለገደምቢ የወርቅ ምርት መቆም፣ በግል ኩባንያዎች ወደ ምርት ሊሸጋገሩ የተዘጋጁ ከአምስት በላይ ትልልቅ ክምችቶች ቁፋሮና ምርት አለመጀመራቸው፣ ለግብዓት የሚፈለገው የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲሁም ከባህላዊ አምራቾች ይገኙ የነበሩ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርቶች በሕገወጥ ነጋዴዎች ኮንትሮባንድ ንግድ ሰንሰለት ውስጥ መግባታቸው ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።

የንዑስ ዘርፉን እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፦ እሴት ተጨምሮባቸው ወደ ገበያ ሊገቡ የሚችሉ በርካታ ማዕድናት በሰፊው መኖራቸው ይታወቃል። በዚህ ረገድ የስሚንቶ ፋብሪካዎች እንዲቋቋሙ የተደረገ ቢሆንም ከጥሬ ዕቃው ክምችት አንጻር የአምራች ኢንዱስትሪዎቹ ቁጥር በእጅጉ አናሳ ነው። በተመሳሳይ በቂ የጨው ክምችት እያለ በጨው ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ እንዲቀርብ በማድረግ በኩል ሰፊ ውስንነት ይስተዋላል። በሌላ በኩል በፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት የድንጋይ ከሰልና ፎስፌት ማዕድናትን ተጠቅሞ ለግብርና ልማት የሚውል ማዳበሪያ ለማምረት ባለመቻሉ የሀገሪቷ የማዳበሪያ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ የውጭ ገበያ ላይ ጥገኛ ሆኖ ቀጥሏል። የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ክምችትን እንዲሁም የባዮፊውል ልማትን ወደ ምርት የማሸጋገሩ ሥራም ገና በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ በአጠቃላይ የማዕድን ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር የተሻለ ገቢ ለማግኘት የተደረገው ጥረት ውጤታማ አለመሆኑን አፈጻጸሙ ያመለክታል።

በንዑስ ዘርፉ የተፈጠረ የሥራ ዕድል፦ በንዑስ ዘርፉ እስካሁን የተፈጠረው የሥራ ዕድል ከግማሽ ሚሊዮን ብዙም አይዘልም። ይህም የሚያመላክተው ንዑስ ዘርፉ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጥቅም ገቢ እንዲያስገኝና በሥራ ዕድል ፈጠራ አመርቂ ውጤት እንዲያስመዘግብ የዘርፎችን ቅንጅታዊ አሠራር መዘርጋት እና ሰላምና መረጋጋትን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ነው። በሰው ኃይል አቅርቦት ረገድ በንዑስ ዘርፉ አዳዲስ የሥነ ምድር ምሩቃን በዓመት ከ500 እስከ 600 የሚደርሱ መሠረታዊ የሥነ ምድር ትምህርት ተምረው ከ20 በማያንሱ ዩኒቨርሲቲዎች ሲመረቁ የነበረ ሲሆን ለእነዚህ ምሩቃን ተግባር ተኮር ሥልጠና በመስጠት ቀጣይነት ላለው ዕድገት ተዋናይ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ዕድል ተፈጥሮ ነበር። ይሁንና ከተቋማት ጋር ተናቦ በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻም ሆነ በተግባር ሥልጠና ብሎም የምርምር ሥራዎችን የመሥራት ባህል ስላልጎለበተ ተመራቂዎቹ ዘርፉ በሚፈልገው ብቃትና የሙያ ስብጥር ባለመመረቃቸው በዘርፉ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በአጠቃላይ በንዑስ ዘርፉ የሙያ ክህሎት ሥልጠና ተሰጥቶ ቀጣይነት ያለው አቅም የማጎልበቱን ዕድል ባለመጠቀማችን የሰለጠነ የሰው ኃይል ብክነት ተከስቷል።

## 2.5 የንግድ ልማት

በንግድ ዘርፉ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሠጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ለዚህም የንግድ አሠራሩን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ ከምዝገባ፣ ከዕድሳትና ከንግድ ስም ማጣራት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማስፋት አገልግሎቱን ፈጣንና  ቀልጣፋ ሊያደርጉ የሚያስችሉ ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሥራዎችን በማከናወን በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ይከሰቱ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅና ደንቦች በማሻሻል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በመስጠት፣ ከምዝገባና ማጣራት ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ቅድመ መስፈርቶችን በመቀነስ በምዝገባና በዕድሳት ዙሪያ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል።

በተጨማሪም በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ከሚሰጡ 1,134 ጣቢያዎች ውስጥ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት በመታገዝ ሲሰሩ የነበሩ 892 ጣቢያዎችን ወደ 1,049 ማድረስ የተቻለ ሲሆን በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሚገኘው ዋናው ሰርቨር ጋር በወረዳ ኔትወርክ እንዲገናኙ ተደርጓል። የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ ጥራቱን ያልጠበቀ ምርት ገበያ ላይ እንዳይውል ለመከላከልና የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓትን ለማስፈን በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ከዚህ አኳያ አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች በሚያመርቱ እና ለገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ዙሪያ የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን፣ የገቢና የወጪ ምርቶች ላይ  የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶች ወደ ሀገር እንዳይገቡ ጥረት የተደረገ ሲሆን ደረጃውን አሟልተው በማይገኙ አምራቾች እና አስመጪዎች ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ ተወስዷል።

በተመሳሳይ የጥራት መሠረተ ልማትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተቋማትን በማደራጀት የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለማስጠበቅና የኢኮኖሚውን የልማት ስትራቴጂ የሚያግዙ ስታንዳርዶች በማዘጋጀትና በትግበራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና የብሔራዊ ሥነ ልክ ላብራቶሪ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ለማሳደግ የአለካክ ወሰኖችን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 21 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 77 በመቶ ማድረስ ተችሏል። በተጨማሪም የዓለም አቀፍ  የላቦራቶሪ አክሬዲቴሽን ህብረት ሙሉ አባልነት በህክምና እና በፍተሻ ላቦራቶሪ ለማግኘት ተችሏል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን የዓለም አቀፍ  አክሬዲቴሽን ፎረም ስምምነቶችን በመፈረም አባል ሆኖ ተመዝግቧል። በአዳዲስ የአለካክ መስኮች ዓለም አቀፍ  ዕውቅና ለማግኘት በመስክ፣ በሚዛን አለካክ፣ በተንቀሳቃሽ ካሊብሬሽን ላብራቶር፣ በይዘት፣ በግዝፈት፣ በግፊትና በሙቀት አለካክ መስክ በጀርመን ዓለም አቀፍ የዕውቅና ሠርተፍኬት ተገኝቷል።

## 2.6 የባህልና ቱሪዝም ልማት

ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የባህልና የታሪክ ሀብት አንጻር የባህል ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና በትክክለኛው መስመር ለመምራት፤ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ፣ የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል እና የገጽታ ግንባታ ሥራ ለማሳደግ እና አዲሲቷን ኢትዮጵያ ያጤነ የፊልም ኢንዱስትሪ ለመገንባት ዘርፉን በፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጦ ማንቀሳቀስና መምራት ተገቢ በመሆኑ ሀገራዊ የፊልም ፖሊሲ በ2010 በጀት ዓመት ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል። በተመሳሳይ መልኩ ዜጎች ቋንቋዎቻቸውን በማልማት በሁለንተናዊ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማድረግ በ2012 የኢትዮጵያ የቋንቋ ልማት ፖሊሲ ተዘጋጅቷል።

ባለፉት አስር ዓመታት 5 የማይዳሰሱ ቅርሶች በዩኔስኮ (UNESCO) ለማስመዝገብ ታቅዶ አራቱን ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ከዚህ ቀደም በአጠቃላይ ከተመዘገቡት አስር የማይዳሰሱ ቅርሶች በተጨማሪ ሁለት ጥንታዊ የሥነ ጽሁፍ ሀብቶች በዩኔስኮ እንዲመዘገቡ ቀርበው በተጠባባቂ ዝርዝር (Tentative List) ውስጥ ገብተዋል፡፡ በተጠቀሰው የአስር ዓመታት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው 4,286 ቋሚ ቅርሶች ተመዝግበዋል፡፡ በተመሳሳይ 8,583 የኪነ ጥበብ እና ሥነ ጥበብ ሥራዎች ለታዳሚ የቀረቡ ሲሆን ይህም ለማቅረብ ከታቀደው የ83 በመቶ አፈጻጸም ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት አስር ዓመታት 65 በመቶ የሚሆኑ ቋንቋዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ለትምህርት አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ሀገራችን ከመስህብ ሀብቶች የምታገኘውን ጥቅም ለማሳደግ የቱሪዝም ገበያን ከማልማትና ተወዳዳሪነትን ከማሳደግ አኳያ በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በተለይም የግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚኖረውን ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ጥረት ተደርጓል፡፡ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የቱሪስት አገልግሎቶችን በአይነትና በመጠን ከማሳደግና የአገልግሎት ጥራትን ከማጎልበት አንጻር ፋይዳ ያላቸው በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እየጨመረ የመጣውን የቱሪስት ቁጥር ለማስተናገድና የአገልግሎት ጥራትን ለማጎልበት ያስቻሉ ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው የሆቴሎች ደረጃ ምደባ ሥርዓት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በዚሁ መሠረት ደረጃቸውን የጠበቁ 353 ሆቴሎች፣ 70 ሎጆች፣ 300 ሬስቶራንቶችና በሺዎች የሚቆጠሩ በደረጃ ያልታቀፉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተፈጥረዋል፡፡ በተጨማሪም ሕጋዊ እውቅና የተሰጣቸው አስጎብኝ ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት በቁጥር 600 ደርሰዋል፡፡

የውጭ ቱሪስት ፍሰትን ወደ 2.02 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ የዕቅዱን 42 በመቶ ብቻ ማሳካት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በቱሪዝም ዘርፍ ከተሰማራው ጠቅላላ የሰው ኃይል ውስጥ 23 በመቶ ብቻ የሚሆነው በዘርፉ የሰለጠነ መሆኑን በጥናት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሆቴልና ቱሪዝም ትምህርት ዘርፍ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጡ ከፍተኛ ተቋማት ቁጥር ወደ 10 ያደገ ቢሆንም አሁንም በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ክፍተት የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ ጊዜያት በትኩረት ሊሠራበት ይገባል፡፡ በአጠቃላይ በቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች የህብረተሰቡ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በተደረገው ጥረት ለበርካታ ዜጎች ቀጥተኛ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

በስፖርት ልማት ባለፉት አስር ዓመታት ከተመዘገቡ ጥንካሬዎችና ተግዳሮቶች መካከል የስፖርት አደረጃጀትና አመራርን በተመለከተ ስፖርቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የተለያዩ አዋጆች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጤናና አካል ብቃት እንቅስቃሴ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ከ148 ሺህ ወደ 6.3 ሚሊዮን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በዘርፉ ውስን የነበረውን የባለሀብት ቁጥር በማሳደግ በአሁኑ ወቅት 303 ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደው በዘርፉ 367.7 ሚሊዮን ብር የካፒታል መጠን ኢንቨስት በማድረግ ለዘርፉ ዕድገት አስተዋፅዖ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር ከፍ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን 27,542 የሚሆኑ ጥርጊያ ሜዳዎች፣ ጅምናዝየሞች፣ የመዋኛ ገንዳዎች፣ የስፖርት አዳራሾችና ስታዲየሞች እንዲሁም የሰውነት ማበልፀጊያ ማዕከላት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሥልጠና መስክም ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ብቸኛ ተቋም የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የስፖርት ሳይንስ ትምህርት በ26 ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በ2004 በጀት ዓመት 2,376 ዳኞችና 2,476 አሠልጣኞች የነበሩ ሲሆን ባለፉት ዓመታት በስፖርት አመራርነት፣ በኢንስትራክተርነት፣ በአሠልጣኝነት እና በዳኝነት የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት 30,625 ባለሙያዎችን ማፍራት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የመሠረተ ልማት አፈጻጸም

# 3.1 የትራንስፖርት ልማት

የመንገድ መሠረተ ልማት፦ መንግሥት መጠነ ሰፊ የሆነ የመንገድ አውታር የማስፋፋት፣ ደረጃ የማሳደግ እና የጥገና እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ባለፉት አስር ዓመታት 83,780 ኪ.ሜ ተጨማሪ መንገድ በመገንባት በሀገሪቱ ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉ መንገዶች ጠቅላላ ርዝመት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 53,997 ኪ.ሜ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 144,027 ኪ.ሜ ማድረስ ተችሏል። በዚህ መሠረት የመንገድ ጥግግት በቆዳ ስፋት (Road Density in km/1000 km2) በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 49 በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 130.9 ከፍ ያለ ሲሆን የመንገድ ጥግግት በሕዝብ ብዛት (Road Density in km/1000 population) ከ1 ወደ 1.31 ከፍ ብሏል። በተጨማሪም በአቅራቢያ ከሚገኝ ክረምት ከበጋ የሚያገለግል መንገድ ላይ ለመድረስ ይደረግ የነበረው ጉዞ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ3.4 ሰዓት በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1.3 ሰዓት ዝቅ ብሏል።

በአጠቃላይ በዘርፉ መልካም አፈጻጸም የተመዘገበ ቢሆንም ሁሉን አቀፍ የገጠር የተቀናጀ የመንገድ አቅርቦት ፕሮግራም (URRAP) ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ በማድረግ በኩል የአካሄድ ለውጥ በመደረጉ ክልሎች ጥቅል በጀት ሲመድቡና ለየዘርፉ ሲደለድሉ በቂ በጀት በመመደብ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻላቸው፤ በምህንድስና ግዥ፣ በዲዛይንና በግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደርና የኃብት አስተዳደር ሥርዓቶች ዙሪያ ዘመናዊና የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓትና ብቃት በተገቢ ደረጃ አለመኖር፤ የፕሮጀክቶች የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የክትትልና ቁጥጥር ጥራት ጉድለቶች፤ የግሉ ዘርፍ የመፈጸም አቅም ማነስ እና ከሙያ ታማኝነትና ሥነ ምግባር ጋር የተያያዙ ችግሮች ተፈጥረዋል። በተጨማሪም የግንባታ ግብዓቶችና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረትና የዋጋ መናር፤ የወሰን ማስከበርና ወጥና ተመጣጣኝ ያልሆነና ለብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆነ የካሳ ክፍያ አሠራር እና ከክልል መንገድ ተቋማት ጋር ተያይዞ በሕግ በተሰጡ ኃላፊነቶች ዙሪያ ግልጽ ግንዛቤና የአፈጻጸም ሂደት አለመኖሩ በዘርፉ የታዩ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው።

የባቡር ትራንስፖርት መሠረተ ልማት፦ የሀገራችን የባቡር መስመር ርዝመት 902 ኪ.ሜ ደርሷል። በዕቅድ ከተያዘው የ2,801 ኪ.ሜ የባቡር መስመር ዝርጋታ ሥራ ውስጥ የ609 ኪ.ሜ (22 በመቶ) የሚሆነው ተከናውኗል። በዕቅድ ዘመኑ ከተገነቡት ፕሮጀክቶች አጠቃላይ አፈጻጸም የመቀሌ-ሃራ ገበያ ፕሮጀክት 55 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን የአዋሽ-ኮምቦልቻ-ሃራ ገበያ ፕሮጀክት ደግሞ 92 በመቶ ደርሷል። አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ከሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ የፋይናንስ እጥረት፣ በመሠረተ ልማቱ ከመነሻ እስከ መድረሻ ድረስ (የጅቡቲ ወደብ፣ ደረቅ ወደቦች፣ የነዳጅ ዴፖዎች፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች) አገልግሎት መስጠት በሚያስችል ሁኔታ ግንባታ አለመከናወኑ፣ በባቡር ሴክተሩ የእውቀትና ልምድ ክምችት ያልዳበረ በመሆኑ ዘርፉ በውጭ ሀገር እውቀትና ቴክኖሎጂ ላይ ጥገኛ መሆኑ፣ ለፕሮጀክቶች ግንባታ ከወሰን ማስከበርና ከኃይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በሚፈለገው መጠን ያደገ አለመሆኑ በዋነኛነት ተጠቃሽ ናቸው።

በመሆኑም የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ በሚያስችል መልኩ ፋይናንስ ማፈላለግ፣ የግል ባለሃብቱን ማሳተፍ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ አሠራር በመዘርጋት የወሰን ማስከበርና የኃይል አቅርቦት ችግሮችን በልዩ ትኩረት መፍታት ይገባል። የአቪዬሽን መሠረተ ልማት፦ የኤርፖርት መሠረተ ልማትን ከማስፋፋት አንጻር አገልግሎት እየሰጡ የነበሩ ኤርፖርቶችን ከ20 ወደ 25 ለማሳደግና 5 ተጨማሪ ጥርጊያ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ለመገንባት ዕቅድ ተይዞ የ3 ኤርፖርቶች ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን የ6 ጥርጊያ ማረፊያዎችን ደረጃ በማሳደግም የሀገር ውስጥ ኤርፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል። የአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ተርሚናል 2 እያደገ ያለውን የመንገደኛ ቁጥር ለማስተናገድ የሚያስችል የማስፋፊያ ፕሮጀክት በመንደፍና በመተግበር አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። የኢትዮጵያ አቪዬሽን

አካዳሚንና የሲቪል አቪዬሽንን የሥልጠና ማዕከል ደረጃ በማሳደግና ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲያገኙ በማስቻል ከሀገር ውስጥ ፍላጎት በተጨማሪ ለውጭ ሠልጣኞችም ሥልጠና መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል። በንዑስ ዘርፉ ከሚታዩት ዋና ዋና ችግሮች መካከል ለዘርፉ መሠረተ ልማት ግንባታ የሚውል የበጀት እጥረት መኖሩ እና የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ የሚያበረታታ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ተጠቃሾች ሲሆኑ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት፦ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው የሀገር ውስጥ ትራንስፖርት ፍላጎት የሚስተናገደው በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሆን ይህንን አገልግሎት በጥራትም ይሁን በተደራሽነት ከነበረበት ደረጃ ለማሻሻል በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ከመንገድ ትራንስፖርት አቅርቦት አንጻር የህብረተሰቡን ፍላጎት ማሟላት ዋነኛ ትኩረት የሚፈልግ እንደ መሆኑ በ2003 በጀት ዓመት የተጓጓዙ ተሳፋሪዎች ቁጥር 148.1 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በሀገሪቱ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በሚደረግ ዓመታዊ ጉዞ (የከተማ ውስጥ ትራንስፖርትን ሳይጨምር) ሕዝብ የማጓጓዝ አቅም በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው 394 ሚሊዮን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 722 ሚሊዮን አድጓል። በዚህ መሠረት የህዝቡ የትራንስፖርት ተጠቃሚነትና የማጓጓዝ አቅም በየዓመቱ በአማካይ በ13.5 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በሌላ በኩል የአንድ አውቶቡስ አማካይ የኪሎ ሜትር ሽፋን በዓለም ባንክ መረጃ መሠረት 100 ሺህ ኪ.ሜ መሆን ሲገባው በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 64 ሺህ ኪሎ ሜትር ደርሷል። የከተማ ብዙኃን ትራንስፖርት አቅርቦት ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 14 በመቶ በ2012 መጨረሻ ወደ 34 በመቶ አድጓል። የሕዝብ ትራንስፖርት አማራጮች አማካይ የመጠበቂያ ጊዜ በ2003 ከነበረበት 45 ደቂቃ በ2012 መጨረሻ ወደ 11 ደቂቃ ዝቅ ብሏል።

በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት በትራፊክ አደጋ ሳቢያ የሞተው ሕዝብ ቁጥር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት በ10,000 ተሽከርካሪ 72 የሞት መጠን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 34.4 ሞት ዝቅ ብሏል። ሆኖም ይህ አፈጻጸም በ2012 በጀት ዓመት ለማድረስ ታቅዶ ከነበረው አንጻር እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ስታንዳርዱ መጠን (6.4/10,000) አኳያም ሲታይ አሁንም የሞት መጠኑ ከፍተኛ ነው። ለዚህም የአሽከርካሪዎች የብቃት እና የሥነ ምግባር ችግር፣ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ችግር፣ የእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ችግር እና የመንገድ ዲዛይንና ግንባታ ጥራት መጓደል ለትራፊክ አደጋ መከሰት ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው ተለይተዋል።

በአጠቃላይ የሕዝብ ትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም፣ የትራንስፖርት ስምሪትና ማኔጅመንት ሥርዓት ደካማ መሆን፣ በገጠርና በከተማ የሚስተዋሉ የተደራሽነት ክፍተቶች መኖር፣ የግል ባለሀብቱን የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖር፣ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት አለመስፋፋት እና አቅርቦቱና ድርሻው አነስተኛ መሆን እንዲሁም በተለዩ መስመሮች ላይ የሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎት አለመጀመርና የመሳሰሉ ክፍተቶች በዘርፉ ተስተውለዋል።

የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት፦ የመሠረተ ልማት ግንባታቸው ተጠናቆ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የጀመሩት የባቡር መስመሮች 34 ኪ.ሜ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር እና 756 ኪ.ሜ የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር መስመሮች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ነባሩ የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር አገልግሎት መስጠት በሚችለው 210 ኪ.ሜ የባቡር ሃዲድ ላይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር እና የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር መስመሮች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በዚህም መሠረት በባቡር ኦፕሬሽን ትግበራ በ2011 በጀት ዓመት 358 የሰው ማጓጓዣ ባቡሮችን (በቀን 0.5 ጥንድ) መስመር ላይ በማሰማራት 124 ሺህ መንገደኞችን ለማጓጓዝ እንዲሁም ብዛታቸው 1,080 የሚሆኑ የጭነት ማመላለሻ ባቡሮችን (በአማካይ በቀን 1.5 ጥንድ) በመስመር ላይ አሰማርቶ አገልግሎት በመስጠት ክብደታቸው 928.8 ሺህ ቶን የሚሆኑ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ አቅዶ የነበረ ሲሆን አፈጻጸሙ በመንገደኛ ብዛት 64 በመቶ እንዲሁም በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት 146

በመቶ ሆኗል። በነባሩ የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር በአሁኑ ወቅት በዓመት 57.6 ሺህ መንገደኞችን እና 62 ሺህ ቶን ደረቅ ጭነቶችን ማጓጓዝ ተችሏል። የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት በጀመረበት በ2008 በጀት ዓመት 30.1 ሚሊዮን መንገደኞች ያጓጓዘ ሲሆን በ2011 በጀት ዓመት ቁጥሩ ወደ 39.6 ሚሊዮን ከፍ ብሏል። በአጠቃላይ የትራንስፖርት አገልግሎት በሰጠባቸው አምስት ዓመታት ውስጥ 169.5 ሚሊዮን መንገዶች ማጓጓዝ ተችሏል። የቀላል ባቡር አማካይ የባቡር መጠበቂያ ጊዜን በተመለከተ በዲዛይን የተቀመጠው 6 ደቂቃ ቢሆንም አሁን ያለው አፈጻጸም 10 ደቂቃ ነው።

በአዲስ አበባ-ጅቡቲ እና በአዲስ አበባ ቀላል የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የነበሩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ከዲዛይንና ግንባታ ጋር የተያያዙ ክፍተቶች፣ የፀጥታ ችግሮች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ፣ ተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋዎች መከሰታቸው፣ የባቡር ጥገና መስጫ ወርክሾፕ አለመኖር እና በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የመለዋወጫ ግብዓቶችን ማግኘት አለመቻል ናቸው።

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፦ የአየር ትራንስፖርት መንገደኞችንና ዕቃዎችን በተለይም በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉትን ፈጥኖ ወደ ተፈለገበት ቦታ ከማጓጓዙም በተጨማሪ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገባት እና ንግድና ቱሪዝምን በመደገፍ ለሀገሪቷ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል። የመንገደኛ መቀመጫ አቅርቦትን በ2003 ከነበረበት 18 ቢሊዮን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 45.4 ቢሊዮን ለማድረስ ታቅዶ 60.1 (132 በመቶ) ማድረስ ተችሏል። ዓለም አቀፍ  የበረራ ጣቢያዎች ብዛት በቁጥር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 63 በ2012 በጀት ዓመት 123 ማድረስ ተችሏል። ከበረራ መዳረሻዎች አኳያ በ2003 በጀት መጨረሻ የነበሩትን 17 የሀገር ውስጥ መዳረሻ ጣቢያዎች ወደ 22 ማድረስ ተችሏል። የዓለም አቀፍ  መዳረሻዎች ቁጥር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 63 በ2012 በጀት ዓመት ወደ 127 ከፍ ብሏል። በአቪዬሽን ዘርፍ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ በተመለከተ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ቁጥራቸው 10 የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 24 ለማድረስ ተችሏል። ይሁን እንጂ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ ከሀገር ውስጥ የቱሪዝም መዳረሻዎች ጋር የአየር ትራንስፖረት መሠረተ ልማቶች አለመስፋፋት፣ ለሚበላሹ የግብርና ምርቶች በወቅቱ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ እና የተገነቡ አብዛኛዎቹ ኤርፖርቶች ወጪያቸውን መሸፈን የማይችሉ መሆናቸው በዘርፉ የታዩ ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸው።

የሎጂስቲክስ አገልግሎት፦ በዓለም ባንክ በሚዘጋጀው የሎጅስቲክስ አፈጻጸም መለኪያ መሠረት የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 104ኛ የነበረ ሲሆን የዕቅድ ዘመኑ ሲጠናቀቅ 57ኛ ደረጃ ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት በተገኘ መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ ከ160 ሀገራት 126ኛ ሆኗል። ወጪ እቃን በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጎ የመላክ አሠራር አንዱ ስትራቴጂ ሲሆን በኮንቴይነር ታሽጎ ወደ ውጪ በሚላከው የጭነት መጠን በመጀመሪያው የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ዘመን 11 በመቶ ብቻ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት መጠኑን ወደ 52 በመቶ ማድረስ ተችሏል። ከገቢ እቃዎች አኳያም የባህር ወደብ አማካይ ቆይታ ጊዜን ከ40 ቀናት ወደ 3 ቀናት ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎች ተወስደው አሁን የተደረሰበት አፈጻጸም በዩኒሞዳል የሚገቡ ኮንቴይነሮች ቆይታ ጊዜ በአማካይ 13 ቀናት እና በመልቲሞዳል የሚገቡ ኮንቴይነሮች ቆይታ ጊዜ  በአማካይ 6 ቀናት ሲሆን የሁለቱ አማካይ 9.5 ቀናት ሆኗል። የኮንቴይነር ጭነት በዚህ ደረጃ የቀነሰ ቢሆንም የሌሎች ጭነቶች የቆይታ ጊዜ ግን 40 ቀን ነው። በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት የሚጓጓዘውን የሀገሪቱን አጠቃላይ ጭነት ሽፋን ከ30 በመቶ ወደ 90 በመቶ ከፍ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን አፈጻጸሙ 48 በመቶ ሆኗል። የገቢ እና ወጪ ጭነቶችን ለማጓጓዝ ሀገሪቱ በ3 ወደቦች የምትጠቀም ሲሆን እነዚህም ጅቡቲ (98.6 በመቶ)፣ ሱዳን (0.3 በመቶ) እና በርበራ (1.1 በመቶ) ናቸው።

የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ ከዓለምአቀፉ ስታንዳርድ ጋር ሲነጻጸር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። የዕቃዎቹ የወደብ ላይ ቆይታ አፈጻጸም ከዓለምአቀፉ ስታንዳርድ (አማካይ 3 ቀናት) አንጻር ከ10 እጥፍ በላይ ነው። በገቢና ወጪ ዕቃዎች ከመነሻ እስከ መድረሻ ባለው ሂደት ውስጥ በርካታ ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪ አካላት አሉ። በእነዚህ አካላት የሚጠየቁ በርካታ የሰነዶች፣ የመረጃና የክፍያ ብዛት፤ የሥራ ሂደቱ የሚወስደው ጊዜ የተንዛዛ መሆን፤ ሥራው በሚጠይቀው ልክ በፋሲሊቲ፣ በመሣሪያና በሰው ኃይል የተሟላ ሆኖ አለመገኘት እና በሎጅስቲክስ ዘርፉ ተዋናዮች መካከል የተቀናጀ አሠራር አለመኖር ማነቆ ሆነው ተለይተዋል።

የአንድ ማዕከል የድንበር መቆሚያ የባህር ወደብ የሌላት ኢትዮጵያ የተቀላጠፈ የትራንዚት ትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንዲኖር ለማድረግ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በስምምነት ያቋቋመቻቸው ያገልግሎት ማዕከላት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል በሞያሌ፣ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል ደግሞ በደወሌ ተገንብተዋል። በሌላ በኩል በሎጅስቲክስ መሠረተ ልማት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ በአዲስ አበባ፣ በባህርዳርና በመቀሌ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ሦስት የቀዝቃዛ መጋዘኖች ተገንብተዋል።

በዘርፉ የትራንስፖርት አቅርቦትና ማኔጅመንት ችግር፣ ምቹ የሆነ የመንገድ መሠረተ ልማት አለመኖር፣ ያሉትም ቢሆኑ የመሠረተ ልማት ተደራሽነት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ የጭነት ማዕከላት እጥረት፣ ደረጃውን የጠበቀ የወደብ አገልግሎት አለመሟላት፣ በመንግስትም ሆነ በግል ዘርፍ በሀገር ውስጥም ሆነ በባህር ወደቦች የሎጅስቲክስ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች በዘርፉ ላይ ያላቸው ዕውቀትና ክህሎት በቂ አለመሆን፣ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጥረት፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራር ዘርግቶ በተጨባጭ በችግሩ ስፋት ልክ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ፣ የቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር እና ብልሹ አሠራር መኖር ዋነኞቹ ክፍተቶች ናቸው።

## 3.2 የኢነርጂ ልማት

በሀገራችን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለመደገፍ በቂ፣ አስተማማኝና ተመጣጣኝ የሆነ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መኖር ወሳኝ ነው። አጠቃላይ ሀገራዊ የማመንጨት አቅም በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 2,048.5 ሜጋ ዋት በ2012 በጀት ዓመት ወደ 4,478 ሜጋ ዋት ያደገ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 4,069 ሜጋ ዋት ከውኃ፣ 384 ሜጋ ዋት ከንፋስ እና 25 ሜጋ ዋት ከደረቅ ቆሻሻ የተገኘ ነው። የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋን 44 በመቶ የደረሰ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 33 በመቶው ከብሔራዊ ግሪድ የሚያገኝ ሲሆን ቀሪው 11 በመቶ ደግሞ ከብሔራዊ ግሪድ ውጪ ከሚገኝ ኃይል ተጠቃሚ ሆኗል። የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ጠቅላላ ርዝመት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 11,440 ኪሎ ሜትር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 18,400 ኪሎ ሜትር ለማሳደግ ተችሏል። የኤሌክትሪክ ኢነርጂን በማሰራጨትና በማከፋፈል ሂደት የሚደርሰውን የኢነርጂ ብክነት መጠን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 21 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 19.6 በመቶ ለመቀነስ ተችሏል። የኃይል ማመንጫዎችን በተመለከተ የታላቁ ህዳሴ ግድብንና የኮይሻ የውኃ ኃይል ማመንጫን ጨምሮ ሌሎች ፕሮጀክቶች (አይሻ 2 እና አሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ እና ቱሉ ሞዮ የጂዮተርማል ኃይል ማመንጫ) በትግበራ ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን የማመንጨት አቅምን ለማሻሻል ከፍተኛ ፋይዳ ይኖራቸዋል።

በኢትዮጵያ እስካሁን ያለው የኢነርጂ ዘርፍ አፈጻጸም መሻሻሎች ያሳየ ቢሆንም በሽፋንም ሆነ በመጠን ከተያዘው ግብ አንጻር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለዚህም እንደምክንያት ከሚቀርቡ ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሚመነጨው ኢነርጂ በውኃ ኃይል ላይ ጥገኛ መሆን፣ የዘርፉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በመጓተት የሚያደርሱት የገንዘብና የጊዜ ብክነት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ በዘመናዊ የኦፐሬሽን ቴክኖሎጂ ያለመታገዝ እና የሰለጠነና በሥነ ምግባር የታነፀ የሰው ኃይል እጥረት ናቸው።

# 3.3 የውኃ ኃብት ልማት

የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ንዑስ ዘርፍ፦ የመጠጥ ውኃ ሽፋንን በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በተደረገው ክለሳ መሠረት በገጠር ከ48.8 ወደ 98 በመቶ ማድረስ፣ በከተማ ከ74.6 ወደ 100 በመቶ ማድረስ እና ሀገራዊ ሽፋንን ከ52.1 ወደ 98.5 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን አፈጻጸሙን በተመለከተ በገጠር 82 በመቶ፣ በከተማ 91 በመቶ፣ ሀገራዊ ሽፋን ደግሞ 84 በመቶ ለማድረስ ተችሏል። በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በመጠጥ ውኃ አቅርቦት ስታንዳርድ መሠረት (ማለትም በገጠር ከ25 ሊትር በሰው በቀን ባላነሰና ከ1ኪ.ሜ ባልበለጠ ርቀት እንዲሁም በከተማ 100 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 1፣ ከ80 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 2፣ ከ60 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 3፣ ከ50 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 4 እና ከ40 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 5 ባላነሰ) የመጠጥ ውኃ ሽፋንን በ2007 መጨረሻ ከነበረበት በገጠር ከ59 በመቶ ወደ 85 በመቶ፣ በከተማ ከ51 በመቶ ወደ 75 በመቶ፣ አጠቃላይ ሀገራዊ ሽፋንን ከ58 በመቶ ወደ 83 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ በገጠር ወደ 54.9 በመቶ ዝቅ ሲል በከተማ ወደ 58.9 በመቶ ከፍ ቢልም በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ 55.7 በመቶ ዝቅ ብሏል። አፈጻጸሙ በ2007 በጀት ዓመት መነሻ ላይ ከነበረበት ሊወርድ የቻለው የማይሰሩ የገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማትን የብልሽት መጠን በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 11.2 በመቶ ወደ 8 በመቶ ለማውረድ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በ2012 በጀት ዓመት ወደ 19 በመቶ ከፍ በማለቱ ነው።

የሳኒቴሽንና ኃይጂን ንዑስ ዘርፍ፦ የመጠጥ ውኃን ለማቅረብ በከተማና በገጠር ከሚደረገው ተስፋ ሰጪ ጥረት በተቃራኒው በሳኒቴሽን ዙሪያ የተደረጉ ጥረቶች ዝቅተኛ ናቸው። በገጠር የሜዳ ላይ መጸዳዳትን ለማስቀረት በተደረጉ ጥረቶች ውጤቶች ቢመዘገቡም የሳኒቴሽን አገልግሎት መስጫ ተቋማት አቅርቦት ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ነው። የግለሰብ መፀዳጃ ቤቶች የግል ንጽህና መጠበቂያና መገልገያ የሌላቸው እንዲሁም በጥንቃቄ ያልተያዙና ለንክኪም የተጋለጡ ናቸው። በሜዳ ላይ መጸዳዳት በ1992 ከነበረበት 80 በመቶ በ2007 በጀት ዓመት 27 በመቶ ቢቀንስም በቅርብ ዓመታት የመቀነስ ምጣኔውን ማስቀጠል ያልተቻለ ሲሆን በተቃራኒው የተመዘገበው ውጤት ወደኋላ የመሄድ አዝማሚያ እንዳሳየ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በሀገራችን ካሉት 32 ሺህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 22 በመቶ ብቻ፣ 12 በመቶ የሚሆኑት የጤና ኬላዎች እና 53 በመቶ የሚሆኑት የጤና ማዕከላት ብቻ ንጽህናው የተጠበቀ ውኃ በግቢያቸው የሚያገኙ ሲሆን ይህ አፈጻጸም ከተቀመጠው ግብ አንጻር እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ በትምህርትና በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ተጽዕኖ እያደረሰ ይገኛል።

በአጠቃላይ በመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን ንዑስ ዘርፍ ባለፉት ዓመታት ውጤቶች ቢመዘገቡም አሁንም ንዑስ ዘርፉ በርካታ ክፍተቶች አሉበት። ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ፤ ውስን የገንዘብ አቅምና የአጠቃቀም ማነቆዎች፤ ውስን የሆነ የቴክኒክ አቅም፤ ዝቅተኛ የባለድርሻ አካላት እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ፤ ፈጣን የከተሞች መስፋፋት እና ጠንካራ የሳኒቴሽን ፖሊሲና ተቋማዊ ኃላፊነት አለመኖር ይገኙበታል። በመሆኑም በቀጣይ እነዚህን ፈታኝ ፈተናዎች ለማለፍ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል።

የተፋሰስ ልማትና የውኃ ሀብት አስተዳደር፦ የገጸ ምድር ውኃ ሀብትን በመጠቀም ረገድ እስከ አሁን በሁሉም ተፋሰሶች 34 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የገጸ ምድር ውኃ ሀብት መያዝ የሚችሉ ግድቦች ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን የታላቁ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ 89 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ የመያዝ አቅም ያላቸው ተጨማሪ ግድቦች በግንባታ ላይ ይገኛሉ። በተመሳሳይ ህዝቡን በማሳተፍ የውኃ አካላትን መሠረት አድርጎ ከ2003 ጀምሮ 1.1 ሚሊዮን ሄክታር ላይ የተቀናጁ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን የሥነ አካላዊ ሥራዎች በተሰሩባቸው ተፋሰሶች ውስጥም ከ2003 ጀምሮ 450 ሚሊዮን ያህል ችግኞች መትከል ተችሏል።

የመስኖ ልማት ንዑስ ዘርፍ፦ በሀገሪቱ በመስኖ የለማ መሬት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 159,277 ሄክታር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ብሏል። ከዚህ ውስጥ ሰፋፊና መካከለኛ የመስኖ አውታር በከፊልና ሙሉ በሙሉ የተገነባለት 490,000 ሄክታር ሲሆን በትክክል ሥራ ላይ ውሎ እየለማ ያለው ደግሞ ከዚህ ያነሰ ነው። እስከ አሁን በመስኖ የለማው መሬት አጠቃላይ እየታረሰ ካለው መሬት ከ8 በመቶ ያነሰ ሲሆን የመስኖ አለኝታ ተብሎ ከሚገመተው ከ5.8 እስከ 7.5 ሚሊዮን ሄክታር ውስጥ ደግሞ 20 በመቶ ያህሉ ብቻ ነው። ሀገሪቷ ካላት የውኃና የመሬት የመልማት አቅም አንጻር ሲታይ እስከ አሁን የተከናወነው የመስኖ ልማት በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል ውስን የሆነ ተቋማዊ አቅም፣ በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ዕጥረት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር አለመኖር፣ ውስን የቴክኖሎጂ አቅምና የገበያ ትስስር ይገኙባቸዋል።

## 3.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከድህነት ለመላቀቅ በምታደርገው ሁለንተናዊ ጥረት የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት የሚያስችሉትን የዲጂታል ኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት እና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ በመሥራት ላይ ይገኛል። የዘርፉን ተዋናዮች ለማስተባበርና ለማቀናጀት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን ትግበራውንም በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ተቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል። ባለፉት ዓመታት ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አቅም ግንባታ የሚያስፈልገውን የሰው ሀብት የሚያፈሩ በርካታ የትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የተገነቡ ሲሆን በአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ በሳይንሳዊ ዕውቀትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማጠናከርና ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ በዩኒቨርሲቲ፣ በኢንዱስትሪና በምርምር ተቋማት መካከል ትስስር እንዲፈጠር ሆኗል። በዚሁ መሠረት አንድ ሀገራዊ እና 17 ቀጠናዊ የትስስር ፎረሞች ተመስርተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረዋል። ተመራማሪና ፈጣሪዎችንም በማትጋት የምርምር አበርክቶን ለመጠቀምና ለማስፋት እንዲቻል ሥርዓት ተዘርግቷል። በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መስክ የግሉን ዘርፍ መሪነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ የድጋፍ ማዕቀፎችም እንዲኖሩ ተደርጓል። በተጨማሪም ዘርፉ የሚመራበት የረጅም ጊዜ የዕድገት አቅጣጫን የሚያሳዩ ፍኖተ ካርታዎች በ20 ልዩ ልዩ ዘርፎች ተዘጋጅተዋል።

በኢንፎርሜሽን ኮሙኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ እና በቴሌኮም አገልግሎት ንዑስ ዘርፎች የተደረሰበት የዕድገት ደረጃም ከዘርፉ የልማት መስኮች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው መሆኑ የተገመገመ ሲሆን፣ የዲጂታላይዜሽንና የዲጂታል አስተዳደር አገልግሎት በዋናነት የዲጂታል ኢኮኖሚውን የሚመራ መሳሪያ ሆኖ የህብረተሰቡን ዕውቀትና መሰረታዊ ፍላጎት ተከትሎ እንዲቃኝ የሚያስችል መደላድል ተፈጥሯል። ከዚህ አኳያ በ2012 በጀት ዓመት በሁሉም የቴሌኮም አገልግሎቶች 46.2 ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 44.5 ሚሊዮን የሚሆኑት የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው። በተመሳሳይ 23.8 ሚሊዮን ዜጎችን የኢንተርኔት እና ዳታ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት ከተመዘገቡት ተጨባጭ ቁሳዊ ሀብቶች መካከል 16 የልህቀት ማዕከላት፣ 10 የሳይንስ ካፌዎች፣ አንድ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ፣ አንድ ብሔራዊ የዳታ ማዕከል፣ የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ ማዕከላት፣ የኔትዎርክ ኦፔሬሽን ማዕከል፣ የዳታ ባክአፕ ማዕከል፣ የኮምፒዩተር መገጣጠሚያና ማሰልጠኛ ማዕከል፣ የገጠር ቴሌኮሙኒኬሽን ማሰራጫ ማዕከል እና የመሬት ምልከታ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ ተቋቁመው ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል። በፖሊሲ ደረጃ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ያገኘ አለመሆኑና በዚህም የዲጂታል መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት በሚፈለገው ደረጃ የተከናወኑ አለመሆኑ፤ የመንግሥት እና የግል ተቋማት የዲጂታል አገልግሎት አጠቃቀም ባህል፣ ልምድና አቅም አናሳ መሆን፤ የግሉን ዘርፍ የሚያበረታታ አሠራር አለመኖር እና በዘርፉ ጀማሪ የሆኑ የሥራ ፈጣሪዎች በቂ የሆነ ፋይናንስ አለማግኘታቸው የሚጠቀሱ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው።



# ምዕራፍ አራት

## የማህበራዊ ዘርፍ ልማት
## አፈጻጸም

# 4.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት

## 4.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት

የኢትዮጵያ ሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አብይ ጉዳይ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የዜጎች የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው። በፖሊሲው ላይ የተቀመጡ ዓላማዎችን ከማሳካት አኳያ ሠፊ እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን በውጤቱም የሕዝብ ቁጥር የዕድገት ምጣኔ በ2007 ከነበረበት 2.3 በመቶ በ2012 ወደ 2.2 ዝቅ እንዳለ ይገመታል። በሥራ ዕድሜ ክልል (ዕድሜው ከ15-64 የሆነ) ያለው ሕዝብ በተመሳሳይ ጊዜ ከ51.4 በመቶ ወደ 58.3 በመቶ ከፍ ብሏል። በውጤቱም ሀገሪቱ ከዲሞግራፊ ውጤት የሥራ ኃይል (labour force) አቅረቦትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ከፍ በማድረግ እስካሁን ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ እንደነበረው ጥናቶች ያመለከቱ ሲሆን ወደፊትም ለኢኮኖሚው ዕድገት አዎንታዊ አስተዋጽዖ ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በተመሳሳይ ጊዜም የዕድሜ ጥገኝነት ምጣኔ ከ77.6 በመቶ ወደ 42.8 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን በውጤቱም በቁጠባ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደነበረው ይገመታል። በመሆኑም ሀገሪቱ ከከፍተኛ የውልደትና የሞት ምጣኔ ወደ ዝቅተኛ ውልደትና ሞት ምጣኔ የተሳካ የዲሞግራፊ ሽግግር እያካሄደች ሲሆን በውጤቱም የሥነ ሕዝብ ትሩፋት (demographic dividend) ተጠቃሚ እየሆነች ነው። ኢትዮጵያ ከሥነ ሕዝብ ትሩፋት በሥራ ኃይል፣ በቁጠባና በሰብዓዊ ካፒታል ልታገኘው የምትችለውን ጥቅም ከፍ ለማድረግ የዲሞግራፊ ሽግግሩን ማፋጠን፣ ወደ ሥራ የሚገባው ሕዝብ በሰው ኃይል ገበያ ላይ የኢኮኖሚውን የመዋቅር ለውጥ ተከትሎ የሚፈለግ ክህሎት እንዲኖረው ማድረግና በዚህም መሠረት የሥራ ዕድልን ማስፋት ያስፈልጋል።

በሀገሪቱ የዲሞግራፊ ሽግግር ከከፍተኛ ውልደትና ሞት ምጣኔ ወደ ዝቅተኛ ውልደትና ሞት ምጣኔ የሚደረግ ጉዞ ነው። በዚሁ መሠረት የወሊድ ምጣኔ (total fertility rate) ወደ 4.1 ዝቅ ብሏል። ለውልደት ምጣኔ መቀነስ ዋናው ጉዳይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋን ከፍ ማለቱ ነው። ሴቶች በትምህርት ያላቸው ተሳትፎ እያደገ መምጣት፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻና የመሳሰሉ የባህል ተጽዕኖዎች ደረጃ በደረጃ እየተወገዱ መሄድ እና ሴቶች በሀብት ባለቤትናትና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የነበራቸው ተሳትፎ መሻሻል የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን አፈጻጸም የተሳካ እንዲሆን ያደረጉ ክንዋኔዎች ናቸው። የሥነ ሕዝብና ልማት ፖሊሲ ረጅም ጊዜ ያላስቆጠረ መሆኑ፤ በፌዴራልም ሆነ በክልል ያሉ የሥነ ሕዝብ አስተባባሪ አካላት ወጥነትና ጠንካራ አደረጃጀት የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑና ሥራውን በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወን ውስንነት መታየቱ እና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን የመከታተያና የመገምገሚያ ማዕቀፉ ደካማ መሆኑ እንደ ዋና ዋና ችግሮች የታዩ ናቸው።

## 4.1.2 የትምህርትና ሥልጠና ልማት

**አጠቃላይ የትምህርት ሽፋን፡-** የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት የ5.2 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 41.8 በመቶ ለማሳደግ ተችሏል። ሆኖም ይህ አፈጻጸም ከታቀደው የ80 በመቶ ድርሻ አንጻር ዝቅተኛ ነው። የአንደኛ ደረጃ (1-8) ንጥር ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 85.3 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 94.7 በመቶ አድጓል። በተመሳሳይ የአንደኛ ደረጃ 2ኛ ዕርከን (5-8) ንጥር የትምህርት ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት የ47.3 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 63.1 በመቶ ማሳደግ ተችሏል።

የሁለተኛ ደረጃ 1ኛ እርከን (9-10) ጥቅል ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 38.4 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 48.5 በመቶ ከፍ ብሏል። ሆኖም ታቅዶ ከነበረው የ74 በመቶ አኳያ እና ዝቅተኛ መካከለኛ የገቢ ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት ከደረሱበት የ84 በመቶ አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ 1ኛ እርከን (9-10) ንጥር ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 16.3 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 24.1 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህ አፈጻጸም ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት አማካይ የ64 በመቶ አፈጻጸም አኳያ ሲታይ አነስተኛ ነው። በተመሳሳይ የመሰናዶ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.1 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 14.8 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን ንጥር ተሳትፎንም በ2011 በጀት ዓመት ወደ 6.2 በመቶ ለማድረስ ተችሏል።

ይህ አፈጻጸም (በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተደረሰበት የ45 በመቶ እና ከሀገራችን የሰው ኃይል ፍላጎት አኳያ ሲታይ) በጣም ዝቅተኛ ነው። በ2000 በጀት ዓመት 1ኛ ክፍል የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት 3,680,681 የነበረ ሲሆን 8ኛ ክፍል የደረሱት 32.4 በመቶ እና በ2011 በጀት ዓመት 12ኛ ክፍል የደረሱት 7.8 በመቶ ብቻ ነበሩ። በተመሳሳይ የልዩ ፍላጎት ተሳትፎ በቅድመ መደበኛ፣ በአንደኛ ደረጃ (1-8) እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በ2011 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 1.3 በመቶ፣ 11 በመቶ እና 2.8 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርትን በተመለከተ በ2011 በጀት ዓመት ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት የሚችሉ ጐልማሶች 20.7 በመቶ ብቻ ነበሩ። ይህ አፈጻጸም (መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ከደረሱበት አማካይ የ76.4 በመቶ አንጻር) ዝቅተኛ ነው።

**የትምህርት ብቃት፣ ጥራትና አግባብነት ማረጋገጥን በተመለከተ፡-** ከ1ኛ ክፍል የማቋረጥ መጠን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 19.9 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 25 በመቶ ጨምሯል። በተመሳሳይ 5ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 69.1 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 41.7 በመቶ ቀንሷል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የማጠናቀቅ ምጣኔም በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 59.3 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 62.1 በመቶ ከፍ ብሏል። በሌላም በኩል ስንት ተማሪ በአንድ ክፍል እንደሚማር (የክፍል/ተማሪ ጥምርታው) በ2011 በጀት ዓመት በተገኘው መረጃ መሠረት ሀገራዊ አማካኙ 1 ለ 53 ሲሆን ይህም ወደሚጠበቀው 1 ለ 50 ምጣኔ የተጠጋ ቢሆንም በተለያዩ አካባቢዎች በተደረገው የመስክ ክትትል በአንድ ክፍል ውስጥ ከአማካዩ በጣም ከፍ ብሎ ከ80 በላይ ተማሪዎች እየተማሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

**የመምህራን ምልመላና ዝግጅት፡-** ከ2007 እስከ 2011 በጀት ዓመት ምዘናዎችን ከወሰዱ የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውስጥ መስፈርቱን በማሟላት ያለፉት እንደ ቅደም ተከተላቸው 24.3 በመቶና 26.2 በመቶ ብቻ ናቸው። በተጨማሪም የሙያ ፈቃድ ምዘናውን ከወሰዱ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች መካከል 24 በመቶ ምዘናውን አልፈዋል። በተመሳሳይም በ2009 በጀት ዓመት የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል የመግቢያ ፈተና ከተፈተኑ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን መካከል ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያመጡት 37.7 በመቶ ብቻ ነበሩ።

ባለፉት ዓመታት ተማሪዎች የሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማስቻል የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር በመቀየስና የቋንቋ፣ የሒሳብና የሣይንስ ትምህርቶች እንዲሁም በዝቅተኛ ክፍሎች የማንበብ፣ የመረዳትና የማስላት ክህሎትን ለማሳደግ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል። ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነቶች 50 በመቶና ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት አለባቸው ከሚለው መርህ አንጻር አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም በሁሉም የትምህርት ምዘና ጥናት ዓይነቶች የሴት ተማሪዎች ውጤትና የታዳጊ ክልል ተማሪዎች ውጤት ከሌላ ክልል ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

**የትምህርት ቤቶች ደረጃ ሁኔታ፡-** በትምህርት ኢንስፔክሽን ሥርዓት የትምህርት ቤቶች ደረጃ በ7 (25 በመቶ) የግብዓት፣ በ14 (35 በመቶ) የሂደት እና በ5 (40 በመቶ) የውጤት ስታንደርዶች መሠረት ከ50 በመቶ በታች ከሆነ ደረጃ 1 (ደረጃውን ያላሟላ)፣ ከ50-69.9 በመቶ ከሆነ ደረጃ 2 (ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ)፣ ከ70-89.9 በመቶ ከሆነ ደረጃ 3 (ደረጃውን ያሟላ)፣ 90 በመቶ እና ከዚያ በላይ ከሆነ ደረጃ 4 (ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ) ተብለው ደረጃ ይሰጣቸዋል። ከዚህ አኳያ የሀገራችን የትምህርት ቤቶች ሁኔታ ሲታይ 91.6 በመቶ የሚሆኑት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 83.7 በመቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች እና ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑ ናቸው።

**የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፡-** የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ተደራሽነት ከማስፋት አንጻር የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ቁጥር 672 የደረሰ ሲሆን የግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚመሩ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ቁጥር በድምሩ 950 (893 የግል እና 57 መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች) ደርሰዋል። በ2003 የሠልጣኝ ቅበላ ቁጥር 371,347 የነበረ ሲሆን በ2011 ወደ 283,968 ዝቅ ብሏል። በዘርፉ በየሙያ አይነቱ የበቃ አሠልጣኝ እጥረት መኖሩ እንደ ዋና ችግር ተለይቷል።

**የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ፡-** የዩኒቨርሲቲዎቻችን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 50 የደረሰ ሲሆን ይህም የከፍተኛ ትምህርት አቅርቦት እና ሽፋን ምጣኔ ከሀገሪቱ ሕዝብ አንጻር አንድ ዩኒቨርሲቲ ለ2.2 ሚሊዮን ሕዝብ እንዲደርስ አግዟል። በቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር የጠቅላላ ተማሪዎች ቁጥር በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 447,693 በ2011 በጀት ዓመት ወደ 790,932 ለማድረስ ተችሏል። የቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ተማሪዎች የመመረቅ ምጣኔ ባለፉት 5 ዓመታት በአማካይ 13 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በ2012 በጀት ዓመት የመምህር ተማሪ ጥምርታ 1 ለ 19፣ በዋና ዋና የትምህርት መስኮች የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታ 1 ለ 5፣ የላብራቶሪ መምህር ተማሪ ጥምርታ 1 ለ 25 ደርሷል። በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የመምህራን ምጣኔ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪ እና በሦስተኛ ዲግሪ ስብጥር በቅደም ተከተል 21 በመቶ፣ 65 በመቶ እና 14 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በተመሳሳይ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም እና በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ድርሻ በቅደም ተከተል በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 27 በመቶ እና 13.8 በመቶ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 37.7 በመቶ እና 14.6 በመቶ አድጓል። በተጨማሪም በ2003 በጀት ዓመት በሁለተኛ ዲግሪ የተማሪዎች ቁጥር 19,361 እና በሦስተኛ ዲግሪ 789 የነበረ ሲሆን በ2011 በጀት ዓመት በሁለተኛ ዲግሪ 86,457 እና በሦስተኛ ዲግሪ 4,355 ደርሷል። በተመሳሳይ የሴት መምህራን ተሳትፎ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 9.2 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት 15.2 በመቶ የደረሰ ሲሆን ሴት መምህራን በምርመር ላይ የነበራቸው ተሳትፎ በ2012 በጀት ዓመት 16.4 በመቶ ደርሷል። በ2011 በጀት ዓመት የታዳጊ ክልል ተማሪዎች ተሳትፎ ከአጠቃላይ ተማሪዎች 3 በመቶ የነበረ ሲሆን የታዳጊ ክልል የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከአዳጊ ክልል ጠቅላላ ተማሪዎች አንጻር 25.6 በመቶ ደርሷል። ልዩ ፍላጎት ያላቸው የአዳጊ ክልል ተማሪዎች ድርሻ ከአጠቃላይ ተማሪዎች ቁጥር 0.8 በመቶ ብቻ ነው።

### 4.1.3 የጤና ልማት

ባለፉት አስር ዓመታት በጤናው ዘርፍ ተግባራዊ የተደረገው በሽታን የመከላከል ስትራቴጂ ነበር። በተጨማሪም መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ተደራሽና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ጥረቶች ተደርገዋል። በመሆኑም የእናቶች ሞት ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 676 ከ 100,000 በ2009 በጀት ዓመት ወደ 401 ዝቅ ሲል ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት እና ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔን በቅደም ተከተል ከነበረበት 88 ከ 1,000 እና 59 ከ 1,000 ወደ 59 ከ 1000 እና 47 ከ 1,000 ዝቅ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ የመቀንጨርና መቀጨጭ ምጣኔን በቅደም ተከተል ከ44 በመቶና ከ10 በመቶ ወደ 37 በመቶና 7 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

በተመሳሳይ በቲቢ በሽታ ምክንያት የሚከሰት የሞት ምጣኔን በ15 በመቶ መቀነስ የተቻለ ሲሆን የወባ በሽታ ስርጭትን በመቀነስ የሞት ምጣኔውን በ84 በመቶ መቀነስ ተችሏል። በተመሳሳይ አማካይ በህይዎት የመኖር የዕድሜ ጣሪያ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 62 ዓመት በ2011 በጀት ዓመት ወደ 65.5 ዓመት አድጓል። በመሆኑም ጤናማ በህይወት የመኖር ዕድሜ ጣሪያም በተመሳሳይ ወቅት 58 ዓመት ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የዓለም ሀገራት እና ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት በቅደም ተከተል በተመሳሳይ ወቅት ካስመዘገቡት የ64 ዓመትና የ59 ዓመት ምጣኔ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው።

በጤና ዘርፍ አሁንም በውኃ፣ በግል እና በአካባቢ ንፅህና ጉድለት፤ በአልኮል መጠጥ፤ በስኳር እና ከአመጋገብ ሥርዓት ጋር ተይዘው በሚመጡ ችግሮች የሚከሰተው ሞትና በሽታ ችግር እንደሆኑ ቀጥለዋል። ከዚህ በተጨማሪም በሥራ ላይ የሚያጋጥም አደጋ እና ከፍተኛ የሆነ የደም ግፊት ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ ጭማሪ እያሳየ የመጣ ሲሆን ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አጣዳፊና ሥር የሰደደ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮች እጥረት ካለባቸው ሀገራት ውስጥም በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመታት እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል።

## 4.2 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የልማት ተሳትፎ፣ ሚናና ተጠቃሚነት

በግብርናው ዘርፍ የሴቶች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ወደ 27.4 በመቶ የደረሰ ቢሆንም ከወንዶች ጋር ሲነጻጻር በ52 በመቶ እንደሚያንስ መረጃዎች ያሳያሉ። በተመሳሳይ በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሴቶች ተጠቃሚነት ሲታይ 23 በመቶ ሲሆን ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። የመሬት ተጠቃሚነት መብትን ከማረጋገጥ አንጻር 14.8 ሚሊዮን ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በግብርና ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነትም እያደገ መምጣቱን ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአንጻሩ ሴቶች በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ በቂ ሥልጠናና የግብርና ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ ባለማግኘታቸው እስካሁን የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ አልቻሉም።

ባለፉት ዓመታት በተሰሩ የግንዛቤና ንቅናቄ ሥራዎች በህብረት ሥራ ማህበራት ከተደራጁ ጠቅላላ የህብረት ሥራ አባላት መካከል የሴቶች ድርሻ 30.5 በመቶ መድረሱን መረጃዎች ያሳያሉ። በተመሳሳይ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ በመደራጀት ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 41 በመቶ የሚሆነው የሴቶች ድርሻ ነው። በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ለሴቶች የማምረቻና የመሸጫ ቦታ አቅርቦት በስፋት አለመመቻቸት፣ የገበያ ትስስር በበቂ ሁኔታ አለመፈጠር፣ የሚሰጠው የሙያና የክህሎት ሥልጠና ዝቅተኛ መሆን፣ የብድርና ቁጠባ ባህል ያለመዳበር፣ የብድር አገልግሎት ተደራሽ አለመሆን፣ ሴቶች በቤቶች ልማት ፕሮግራም የመክፈል አቅም አነስተኛ መሆን ዋና ዋናዎቹ ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ነበሩ።

በሀገራችን በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ህፃናት ላይ ይፈፀማሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋና አስገድዶ መድፈር ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በዚህም መሠረት በ2008 በጀት ዓመት የሴት ልጅ ግርዛት እና 15 ዓመት ሳይሞላቸው የሚያገቡ ሴቶች ምጣኔ በቅደም ተከተል 65 በመቶና 6 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በተመሳሳይ የሴቶች አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ወሲባዊ ጥቃት ምጣኔ በቅደም ተከተል 23 በመቶ፣ 24 በመቶና 10 በመቶ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 33.8 በመቶ የሚሆኑት ጥቃቱ የደረሰባቸው በትዳር አጋሮቻቸው ነው።

የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተወሰዱ እርምጃዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በፌዴራል ደረጃ የሴቶችን ውሳኔ ሰጭነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 38.8 በመቶ፣ በሕግ ተርጓሚው 20.6 በመቶ፣ በከፍተኛ የአስፈጻሚ አካላት ደረጃ 50 በመቶ፣ በመካከለኛ አመራርነት ቦታ 22 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የህፃናትን መብት፣ ደህንነትና ጥበቃ ለማጠናከር ልዩ ልዩ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችንና አማራጭ ፕሮግራሞችን በመቅረጽና በመተግበር ባለፉት ዓመታት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 4.6 ሚሊዮን ህፃናትን በተለያዩ የሀገር ውስጥ አማራጭ ፕሮግራሞች ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል። የማህብረሰብ አቀፍ ፕሮግራሞችን ለማጠናከር በተሰራው ሥራ 5,225 የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶችን በማቋቋምና በማጠናከር በህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ በርካታ ሥራዎች የልደት ሰርቲፊኬት ያገኙ ህፃናትን ድርሻ 12 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

በተጨማሪም ጥቃት ለደረሰባቸውና በጎዳና ላይ ላሉ ህፃናት የሥነ ልቦና፣ የሕግ፣ የጤና እና የተሀድሶ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ 34 የተቀናጀ የአንድ መስኮት አገልግሎት ማእከላት፣ 6 የሆትላይን አገልግሎት ማእከላት፣ 100 የህፃናት ተስማሚ ችሎቶችና 4 የተሀድሶ ማእከላት ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምጣኔ በ2009 በጀት ዓመት ወደ 51 በመቶ አድጓል። ይህ ሁኔታ እየጨመረ በመምጣቱ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት ከመግባትና በአግባቡ ትምህርታቸውን ከመከታተል ይልቅ ወደ ሥራ እየተሰማሩ መሆናቸውን አመላካች ነው። በተጨማሪም አፈጻጸሙ ከሌሎች ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት እንዲሁም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት አንጻር ሲታይ እጅግ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይ ይህንን ለመቀነስ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል። ህፃናት በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ትርጉም ባለው መልኩ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የህፃናት አደረጃጀቶችና ልዩ ልዩ የህፃናት ኩነቶችን ማካሄድ ተችሏል። በዚህም መሠረት እስካሁን 63,939 የህፃናት አደረጃጀቶች (8,428 የህፃናት ፓርላማዎችና 55,511 የህፃናት ክበባት) እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ተደርጓል።

የወጣቶችን የኢኮኖሚ ችግሮች ከመፍታት አንጻር 4.5 ሚሊዮን ወጣቶች በሥራ ፈጠራና በንግድ ሥራ አመራር ሥልጠና እንዲወስዱ ሲደረግ 849,359 ወጣቶች ደግሞ የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በተመሳሳይ ለ481,126 ወጣቶች የቦታ አቅርቦት የተመቻቸላቸው ሲሆን ከዚህም ባሻገር 880,453 ወጣቶች በቁጠባ ላይ እንዲሳተፉ በመደረጋቸው 3 ቢሊዮን ብር መቆጠብ ችለዋል። በተጨማሪም ወጣቶችን በማህበራዊ ዘርፍ ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ባለፉት ዓመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ 2,854 የወጣቶች ስብዕና ልማት ማእከላት የተገነቡ ሲሆን 23 ሚሊዮን ወጣቶች በማዕከላቱ ከሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሆነዋል። ወጣቶች ለሱስና ለአደንዛዥ ዕጽ ያላቸውን ተጋላጭነት ለመከላከልና ከሱስ እንዲያገግሙ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም ችግሩን ከመቅረፍ አንጻር አሁንም ብዙ ርቀት መጓዝ እንደሚገባ ለመረዳት ተችሏል።

በተመሳሳይ በ2011 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ከተሞች በተከናወነ ጥናት መሠረት 4.4 በመቶ ታዳጊ ወጣቶችና ወጣቶች ሲጋራና ከሲጋራ ጋር የሚመሳሰሉ እፆችን፣ 36.6 በመቶ የሚሆኑ ወጣቶች ማንኛውንም አይነት አልኮል፣ 51 በመቶ የሚሆኑ ወጣቶች ጫት እንደሚጠቀሙ ያመለክታል። የወጣቶችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማስፋፋትና ባህል ለማድረግ በተከናወነው ተግባር የተሳተፉ ወጣቶች ቁጥር በ2002 ከነበረበት 3.5 ሚሊዮን በ2012 ወደ 21 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን በመስኩ በወጣቶች የተለያዩ ተግባራት በመከናወናቸው መንግስት በነሱ ሊያውል ይችል የነበረውን ሃብትና ንብረት ማዳን ተችሏል። የወጣቶችን የፖለቲካ ተሳትፎና ውክልና ለማሳደግ

በተከናወነ ተግባር በ2011 በጀት ዓመት በፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የወጣቶች ድርሻ 11.2 በመቶ እንዲሁም በሕግ ተርጓሚ አካላት 12.2 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በቀጣይ የዕቅድ ዘመን ወጣቶች በፖለቲካው መስክ ያላቸውን ተሳትፎና ተጽዕኖ ፈጣሪነት የበለጠ ለማጠናከር በርካታ የአሠራር ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል።

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት በህብረተሰቡ ዘንድ በሴቶች፣ በህፃናትና በወጣቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፤ ለሴቶችና ለወጣቶች የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በቂና ዘላቂ አለመሆናቸው፤ የሴቶች የመደራደርና የመወሰን አቅም ማነስ፤ የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ውክልና በዋና ዋና የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ማነስ፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኃይል ጥቃቶች መበራከት፤ የሴቶችና የወጣቶች ቁጠባ ባህል አለመዳበር፤ ነፃና ጠንካራ አደረጃጀቶች አለመፈጠራቸው፤ የሕግ አፈጻጸም ክፍተት፤ ወጥነት የሌለውና ተደራሽ ያልሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት መኖር፤ ሴቶችንና ወጣቶችን የመደገፍና ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጪነት የማምጣት ችግር እና የመንግስት ተቋማት የሴቶችን፣ የህፃናትንና የወጣቶችን ጉዳይ የዋና ሥራቸው አካል አድርገው አለመሥራት የታዩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመታት ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ተጠቃሚነታቸው፣ ውክልናቸውና ተሳትፎአቸው እንዲረጋገጥና በሀገር ልማት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል።

## 4.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት

የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎትን ከማስፋፋት አንጻር በ2003 ለ9,527 ድርጅቶች የሥራ ላይ ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ቁጥሩን ወደ 372,245 ማሳደግ ተችሏል። የማህበራዊ ምክክር አገልግሎትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሁለትዮሽ ምክክር ሥርዓትን የመዘርጋት ሥራ በ2003 ከነበረበት 108 ድርጅቶች በ2012 ወደ 9,739 ድርጅቶች በማሳደግ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ የሙያ ደህንነት ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ሥራ ላይ ውሏል። በሴክተሮች የሙያ ደህንነት ጤንነት ሥርዓት እንዲጠናከር ለማድረግ በታቀደው መሠረት  የኮንስትራክሽን ዘርፍ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። እንዲሁም ብሔራዊ የሙያ ደህንነት ጤንነት ካውንስል በማቋቋም ሥራ ለማስጀመር በታቀደው መሠረት የማቋቋሚያ ሰነዱ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በቀጣይ የሙያ ደህንነትና ጤንነት እንስቲትዩት ለማቋቋም ለተያዘው ዕቅድ አጋዥ ይሆናል።

በሀገር ውስጥ ድጋፍ ተደርጎላቸው በሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ብዛት በ2003 ከነበረበት 267,770 በ2012 በጀት ዓመት ወደ 15,062,128 ማሳደግ ተችሏል። ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በውጭ ሀገር በሥራ እንዲሰማሩ ከማድረግ አኳያ የዜጎችን መብትና ጥቅም ሊያስከብሩ የሚችሉ አዋጆችን የማዘጋጀትና የማፀደቅ፣ ከተቀባይ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ሥርዓት የመዘርጋት፣ የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት የማዘጋጀትና የሥልጠና ተቋማትን በማደራጀት የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት እንዲሳለጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተችሏል። በዚህም በውጭ ሀገር በሥራ የተሰማሩ ዜጎችን ብዛት በ2003 ከነበረበት 46,001 በ2012 ወደ 464,405 ከፍ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ የውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ስምሪት አገልግሎት በ2003 ከነበረበት 25899 በ2012 ወደ 328,483 ከፍ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በየደረጃው በመዘርጋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ባሉበት አካባቢ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችል በቀበሌ ደረጃ 13,500 አዳዲስ የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል። በተጨማሪም ለ1,944 የአረጋዊያንና ለ2,007 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እንዲቋቋሙ ተደርጓል።

የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶችን በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ባለፉት አራት ዓመታት በገጠርና በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ለ1,285,134 (በገጠር ለ1,192,014 እና በከተማ ለ93,120) ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 60 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል መሥራት የሚችሉ 19,218 (ወንድ 7,732 እና ሴት 11,486) ቤተሰቦችን ከተለያዩ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል። በተጨማሪም አካላዊ ተሃድሶና ሌሎች አገልግሎቶችን ያገኙ አካል ጉዳተኞችን ብዛት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 19,843 በ2011 በጀት ዓመት ወደ 412,867 በማሳደግ ከነበረባቸው የመንቀሳቀስ ችግር ተላቀው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል። በጎዳና ላይ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ከማድረግ አኳያ 24,003 ጎዳና ተዳዳሪዎች ወደ መጡበት ክልል እንዲመለሱ በማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን 5,430 ጎዳና ተዳዳሪዎች (3,204 አረጋውያን፣ 1,380 ህፃን የያዙ ሴቶችና 846 ወጣቶች) አገልግሎት እንዲያገኙ ውል ተፈፅሞ ወደ ሥራ ተገብቷል። ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊና የሥነ ልቦና ምክር ድጋፍ ከመስጠት አንጻር ለ695,873 የህብረተሰብ አካላት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን ለማሳደግ በተሰራው ሥራ ከ2003 ጀምሮ የ1,669,521 ሠራተኞች እና የ203,458 ድርጅቶች ምዝገባ ተካሄዷል። በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት 43.9 ቢሊዮን ብር የጡረታ መዋጮ ማሰባሰብ ተችሏል።

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት የቀጥታ ድጋፍ ሴፍቲኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎችን በመለየትና አገልግሎቱን በተቀመጠው ሥርዓት መሠረትና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር አፈጻጸሙ ደካማ መሆኑ፤ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሠሩ ሥራዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመፈፀማቸው፤ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሴት አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሕጻናት የሚሰጡ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፤ ወጣቶች የሱስና የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በቂ የሆነ የመከላከል ሥራ አለመሰራቱ፤ ሕጻናት ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ቤተሰብን የመደገፍና የማጠናከር ሥራ በሚፈለገው መጠን አለመሰራቱ፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ በጎዳና ላይ የሚተዳደሩ ሴቶችና ሕጻናት ወደ ጤናማ ማኅበራዊ ሕይወታቸው እንዲመለሱና ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ የትብብርና የቅንጅት አሠራሩ ያልተጠናከረ መሆኑ ማህበራዊ ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ መፍታት እንዳልተቻለ የአፈጻጸም ግምገማው ያሳያል።

# ምዕራፍ አምስት

## የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ

# 5.1 የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

ባለፉት ዓመታት የመንግስትን ዘርፍ የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት የተለያዩ የለውጥ ሥራዎች ተከናውነዋል። ይሁን እንጂ በህዝብ አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ያሉ አመራሮችና ሠራተኞች ደረጃውን የጠበቀ ሙያዊ አገልግሎት በመስጠት ዙሪያ ሰፊ ክፍተቶች ተስተውለውባቸዋል። በተመሳሳይ በህዝብ አገልግሎት ዘርፉ ዜጎችን ለማገልገል የተመደበውን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ያለማዋልና ሀብትን የማባከን ችግሮች ተከስተዋል። በመንግስት አግልግሎት ዘርፉ የመንግስትና የፓርቲ ሥራ መደበላለቅ የመንግስት ሰራተኛው ምደባ፣ የሥራ ሥምሪቱና ዕድገቱ በፖለቲካ ውሳኔ ጫና ሥር በመውደቁ የመፈጸም ብቃቱንና የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነቱን ጎድቶታል። በዘርፉ የሰው ሀብት ልማትን ከውጤት ጋር አስተሳስሮ ለመምራት የሚያስችል የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲ አለመኖሩ ችግሩን የባሰ ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል። በተማሳሳይ ተቋማትን በተደራጀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከማልማት ይልቅ የለውጥ መሳሪያዎችንና የሪፎርም አካሄድን በመከተላቸው ብቁ የሆኑ ተቋማትን መገንባት አልተቻለም።

የመንግስት ተቋማት፣ አመራሮችና  ባለሙያዎች ሙያዊ ነፃነት ስለሌላቸው አዲስ ሀሳብ በማመንጨት አሁን ካለው የለውጥ ጉዞ ጋር እኩል መራመድ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በአብዛኛው የመንግስት ዘርፎች ላይ ልዩነትን ያላገናዘቡ ተመሳሳይ የለውጥ ሀሳቦች፣ መሳሪያዎችና የመተግበሪያ ስልቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸው የአገልግሎት ሥርዓቱን በሚጠበቀው ልክ ለውጥ እንዳያመጣ አድርጎታል። የውጭ ተሞክሮዎችን ከሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አጣጥሞ ከመውሰድ እና ተሞክሮዎችን ከማስፋፋት አንጻር ጥረቶች ታይተዋል። የመንግስት ዘርፍም በአገልጋይነት መንፈስ የተሞላ ቀልጣፋ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማቅረብ ባለመቻሉ ሀገራዊ የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጥሯል። በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ያለው ሠራተኛ በከፊል የብቃት ክፍተት  ያለበትና በቂ ክፍያና ማበረታቻ የሌለው በመሆኑ የመፈጸም አቅሙ ክፍተት ስር የሰደደ እንዲሆን አድርጎታል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶችን ከማሳካት አንጻር የተሟላ የአገልጋይነት ስሜት ለመያዝና የለውጥ ሥራዎችን ለመተግበር በቁርጠኝነት እንዳይንቀሳቀስ አድርገውታል።

# 5.2 የፍትሕ ዘርፍ

ባለፉት ዓመታት የሕግና የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል ጠንካራ የፍትሕ ተቋማት ለመገንባት በተሰጠው ትኩረት መሠረት የፍርድ ቤቶች፣ የዐቃቤ ሕግ፣ የፖሊስና የማረሚያ ቤቶች አደረጃጀት እንዲስተካከል ማድረግ ተችሏል። የዜጎችን ሰብዓዊና ሕገ መንግስዊ መብቶች ላይ ለማክበርና ለማስከበር የሚያስችል የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ ውሏል። የተጠርጣሪዎችንና ታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት በማስከበር ረገድ የታራሚዎችን መብት በይበልጥ ሊያስጠብቅ የሚችል የማረሚያ ተቋማት ፍኖተ ካርታ እየተተገበረ ሲሆን በማረሚያ ቤቶችና በማረፊያ ቤቶች የታራሚዎችንና የተከሳሾችን አያያዝ የሚያሻሽሉ የለውጥ እርምጃዎች ተወስደዋል።

የሕግ ማስከበር ዘርፉን ሪፎርም በማድረግ የአስተሳሰብ፣ የአደረጃጀትና የስትራቴጂ ለውጦች በማካሄድ አቅም ተገንብቷል። በተለይም በሀገራዊ የፖሊስ ሪፎርም መነሻ በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፖሊስ ዶክትሪንና የማስፈጸሚያ ማንዋሎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ በመግባታቸው የፖሊስ ተቋምና አገልግሎት ዘመናዊ፣ ተደራሽና የሕዝብ ይሁንታ ያለው እንዲሆን የሚያስችል መደላድል ተፈጥሯል። የጦር መሳርያ ምዝገባና ቁጥጥር ሥርዓት የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። የቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ሥርዓት ከቀበሌ እስከ ፌዴራል በሚያስተሳስር መንገድ ተዘርግቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። የፖሊስ አገልግሎትን ዘመናዊ፣ ተደራሽና የሕዝብ

ይሁንታ ያለው እንዲሆን በቀልጣፋና ዘመናዊ የመረጃ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲደገፍ ተደርጓል። ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ ፖሊስ በከባድ እና ውስብስብ በሆኑ ከሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ከሙስና (ሌብነት) የወንጀል ጉዳዮች አንጻር ያከናወናቸው ስኬታማ የሆኑ የወንጀል ምርመራ ሥራዎች ተከናውነዋል።

የሕግና የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያውን ከመተግበር አኳያ በሕግ ዕውቀትና የሥራ ልምድ ያካበቱ የሕግ ምሁራን የተካተቱበት የሕግና የፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ምክር ቤት በማቋቋም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያግዙ አዳዲስ ሕጎች እንዲዘጋጁና ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ ተደርገው እንዲተገበሩ ተደርጓል። በዚህ መሠረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግ፣ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ፣ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የሽብር ድርጊትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተዘጋጁ ሕጎች፣ የጦር መሳሪያ አጠቃቀምና ዝውውር አዋጅ፣ የጥላቻ ንግግርንና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጁ ሕጎች ፀድቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርገዋል። የፌዴራል መንግስቱ ሕጎች ተግባራዊ መደረጋቸውንና አተገባበራቸውም ወጥነት ያለው መሆኑን ከማረጋገጥ እንዲሁም አስፈፃሚ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሥራቸውን በሕጉ መሠረት መሆኑን ከመፈተሽ ረገድ አዲስ አደረጃጀትና አሠራር ተቀርፆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ከመንግስት መስሪያ ቤቶችና ከልዩ ልዩ አካላት የሚቀርቡ የሕግ ምክርና እርማት ጥያቄዎችን በመቀበል ከሕገ መንግስቱና ሀገሪቱ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር መጣጣማቸውን እና የሴቶችንና የህፃናትን መብቶች ያከበሩ መሆናቸውን በመመርመር ተገቢውን እርማት በማድረግ ምላሽ ተሰጥቷል። በሕግ ጉዳይ ዓለም አቀፍ ትብብር አንጻር የሀገራችንንና የዜጎችን ጥቅም ባስቀደመና ባስጠበቀ ሁኔታ በወንጀል፣ በፍትሐብሔርና በንግድ ጉዳዮች ከተመረጡ የዓለም ሀገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ስምምነትና ትብብር እንዲኖር ውጤታማ ሥራዎች ተሰርተዋል። ሰብዐዊ መብት በመጣስ፣ በሙስናና በሌብነት፣ የሕዝብንና የሀገርን ሐብት በመመዝበር፤ የተደራጁ ወንጀሎችን በመፈጸም፣ የብሔር ተኮር ግጭቶችን በማነሳሳት፣ ሕገ ወጥ ጦር መሳርያና ገንዘብ በማዘዋወር እና ሌሎችንም የኢኮኖሚ ወንጀሎች በመሥራት የተጠረጠሩ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ተግባራት ማከናወን ተችሏል። በዚህም ባለፉት ዓመታት በተለያዩ አከባቢዎች በተፈፀሙ የተለያዩ ወንጀሎች 186,378 የወንጀል መዛግብት በመመርመር ውሳኔ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን የመዝገብ ፍሰቱም በየዓመቱ በአማካይ የ7 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። የዐቃቤ ሕግ መዛግብትን የማጥራት ምጣኔ 99.2 በመቶ፣ የዕርቅን ምጣኔ 80.98 በመቶ፤ የወንጀል ጉዳዮች የመርታትን ምጣኔ 93 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር የፍትሐ ብሔር ፍትሕ አስተዳደር እና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደርና የፍትሐብሔር ጉዳዮች አያያዝ ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን ከመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች የሕግ ክፍሎች ጋር በጋራ የውል ድርድሮችንና ዝግጅቶችን በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት አካላት እና በመደበኛ ፍርድ ቤት ውጤታማ ክርክሮችን በማከናወን የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የመርታት ምጣኔ 94 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

በተደራጀ መልኩ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን በሚገባው ደረጃ መከላከል አለመቻሉ፤ የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛነትና የሙያ ነፃነት ያልዳበረ መሆኑ፤ ወንጀሎችን ለመከላከልና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አቅም አለመገንባቱ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶችና በዚህ ሂደት ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ በተሟላ መልኩ ማቅረብ አለመቻሉ እና የሰብዐዊ መብት አያያዝና አጠባበቅ በሕገ መንግስቱና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት አለመከበሩ፣ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጽመው መሆኑ፣ ከፍተኛ የሙስና (ሌብነት) ተግባር የነበረ መሆኑ የአፈጻጸም ክፍተቶች ሆነው ተለይተዋል።

# 5.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ

የህዝብ ተሳትፎን ከማጠናከር አንጻር፦ ባለፉት ዓመታት በዕቅድ የተያዙና የፀደቁ ጉዳዮች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት መፈፀማቸውን ከመከታተል ባለፈ በጥራት፤ በብቃትና በቁጠባ መከናወናቸውን የመገምገም፤ የመደገፍና የመከታተል ተግባራትን አከናውኗል። በተጨማሪም የሚሰጡ ግብረ መልሶችና አቅጣጫዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን በዳግም ክትትል የማረጋገጥ ሥራ ለመሥራት ጥረት ተደርጓል። በሌላ በኩል ለየተቋማቱ በቋሚ ኮሚቴዎች የተዘጋጀ የመከታተያ ቼክ ሊስት በመጠቀምና ተግባራዊ በማድረግ ለመከታተልና ለመደገፍ ጥረት የተደረገ ሲሆን በዚህም የየተቋማቱ ድክመቶችና ጥንካሬዎች ተለይተው ድጋፍ እንዲደረግላቸው አግዟል።

የመገናኛ ብዙኃን በተመለከተ፦ ባለፉት ዓመታት የመገናኛ ብዙኃን በአንጻራዊነት በቁጥር ደረጃ የመጨመር ሁኔታ ያሰዩ ሲሆን፣ የመሠረተ ልማቶችም በመስፋፋት ላይ ናቸው። የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ሙያ ሥልጠና በመስጠት ባለሙያ ከማፍራ አንጻርም ጉልህ ድርሻ ነበራቸው። ለመገናኛ ብዙኃን መስፋፋት አጋዥ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ሥራ ለይ የዋሉ ሲሆን የመገናኛ ብዙኃን፣ የመረጃ ነጻነት፣ የብሮድካስት እና የማስታወቂያ አዋጅ ወጥተው ተግባር ላይ ውለዋል። በተጨማሪም የመገናኛ ብዙኃን በአንጻራዊነት የሥራ ነፃነት እየተፈጠረላቸው ይገኛል። ይሁን እንጂ አሁንም ለውጡን የሚመጥን የመገናኛ ብዙኃን ኮሙኒኬሽን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያለመኖር፥ በዘርፉ ማበረታቻ የማይሰጥ መሆኑ፥ ግብዓቶች ያለመሟላት፣ የመገናኛ ብዙኃን ለልማት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሀገሪቱ በምትፈልገው ልክና ደረጃ አበርክቶ ያለመስጠት፣ ጠንካራ የሚዲያ ማሕበራት ያለመኖር፣ በጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ሙያ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት ከሀገራዊ አውድ ጋር ያልተቃኘ መሆኑ፣ የዘርፉ ባለሙያዎች ብቃት ችግር፣ በክልልና በፌዴራል በመንግሥት የልማት ድርጅትነት የተቋቋሙ የመገናኛ ብዙኃን ነጻና ገለልተኛ ሆነው ሙያን ብቻ መሠረት በማድረግ ኃላፊነትና ተግባራቸውን አለመወጣቸው በዘርፉ የተስተዋሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስናን በተመለከተ፦ ባለፉት ዓመታት ያለድካም የራስ ያልሆነውን የህዝብና የሀገር ሀብት በመዝረፍ በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚደረጉ ሩጫዎች ከመቀነስ ይልቅ የዝርፍያ ዘዴዎችን በመንደፍ ጭምር እየተበራከቱ ይገኛሉ። ሚዲያዎች በህዝብ አገልግሎት ላይ እንግልት የሚያደርሱ እና በአቋራጭ ለመበልጸግ የህዝብና የሀገር ሀብትና ንብረት የሚዘርፉ አመራርና ሠራተኞች ~~አፍንጩ~~ የማጋለጥ እንዲሁም ዜጋው ከሌብነት ይልቅ በሥራ ለመበልጸግ ጥረት እንዲያደርግ ሥነምግባር በማስተማር ረገድ ከሚዲያ የጎላ ሚና ይጠበቃል። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት በኮሚሽኖች ፍላጎት ተዘጋጅተው የተለያዩ የሥነምግባርና ፀረ ሙስና መልክቶችን በተለያዩ ሚዲያዎች ተላልፈዋል። በተጨማሪም የፀረ ሙስና ትግሉ በተደራጀ መልኩ የነቃ የህብረተሰብ ተሳትፎ ታክሎበት ለመምራት ከ900 በላይ የተለያዩ ማህበራትን በ14 የፀረ ሙስና ጥምረት ስያሜ በማደራጀት የትግሉ ተባባሪና አጋር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በዚህም የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ተዕልኮ ተሰጥቶአቸው አቅደው ተንቀሰቅሷል፣ ለአባሎቻቸምው የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠናዎችን ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮችን በመለየት የቅድመ የመከላከያ ሥራዎችን በስፋት በማከናወን በብዙ ሚሊዮን ሀብትና ንብረት ከምዝበራ ለማዳን ተችሏል። ለጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ አሠራርና አደረጃጀቶችን በማሻሻል የመከላከል ሥራዎችን ሰርተዋል። በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ችግር የሚፈጥሩ አመራርና ሠራተኞችን በመለየት ከሥራ ቦታ ላይ ያነሱ፣

በዲስፕሊን እንዲቀጡ ያደረጉ፣ ከሥራ ያሰነበቱ ተቋማት ቁጥራቸው ብዙ ነው። ነገር ግን የተቋም አመራሮች በአብዛኛው ለፀረ ሙስና ትግል የተግባር ሰው ሆነው በጽናትና በትጋት ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ዝግጁነት በጣም ደካማ ነው። በሥልጣን አለግባብ የመጠቀም፣ አድላዊነትና ሌብነት አሁንም በተቋማት ውስጥ በስፋት አለ። በተለያዩ የመንግስት ግዥዎች፣ ግብርና ታክስ ስብስባ፣ ግንባታ ሥራዎች ላይ ግዙፍ የሙስና ወንጀል የሠሩ የመንግስት ኃላፊዎችና ሰራተኞች ቀላል የሚባሉ አይደለም። የሙስና መከላከል ሥራ እንዲያግዝ በቁጥር እስከ 500,000 የሚሆኑ ተመራጮች፣ ተሿሚዎችና የሚመለከታቸው የመንግስት ሠራተኞች ሀብትና ንብረት እንዲያስመዘግቡና እንዲያሳድሱ ተደርጓል።

የተወሰኑ የሀብት አስመዘገቢዎች መረጃ ለፍትሕ አካለት ሥራ አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል። ነገር ግን የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ አሠራር ካለመሆኑም በላይ በህጉ መሠረት ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ባለመከናወኑ ምክንያት ማስመዝገብ የሚገባቸው ያላስመዘገቡበት፣ ባለማስመዝገባቸው ደግሞ የማይጠየቁበት ሁኔታዎች ነበሩ። ለሙስና መከላከል ሥራ ከፍተኛ ዕገዛ እንዲያደርግ በደንብ ቁጥር 144/2000 መሠረት በተወሰኑ የመንግስት ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁና እንዲሟሉ ተደርጓል። አደረጃጀቶቹ በተቋማት ውስጥ የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርቶችን ሰጥተዋል፣ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስና ብልሹ አሠራር ተከላክለዋል። ይሁን እንጂ በሁሉም ተቋማት የተሟላ አረደረጃጀት በመፍጠር የሥራ ክፍሉ ለፀረ ሙስና ትግል ሊሰጥ የሚገባውን አስተዋዕዖ አቅም አሟጥጦ የመጠቀም ሥራ በአግባቡ አልተከናወነም። የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት ውስጥ ሥራ የሌለው የሥራ ክፍል ከመባል በተጨማሪ በራሳቸው በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራ ላይ ሚናቸውን በትክክል በመረዳት ያልተንቀሳቀሱበት ሁኔታዎች በብዛት ነበሩ።

# ምዕራፍ ስድስት

## የሰላም ግንባታና
## የውጭ ጉዳይ አፈጻጸም

# 6.1 የሰላም ግንባታ

ባለፉት አስር ዓመታት ሰላምን ለማስፈን በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። በመሆኑም በተመረጡ ወቅታዊ፣ ስርዓታዊና መዋቅራዊ የሰላም ማስረጽ ርዕሰ ጉዳዮች ተከታታይ የአቅም ግንባታ ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችና ተቋማት ተሰጥተዋል። በተጨማሪም በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ህብረተሰብና ሊሂቅ ተኮር ምክክሮች ማካሄድ የሚያስችሉ የምክክር የማስፈጸሚያ አሠራሮች ተዘርግተዋል። በዚህም ሊሂቃኑንና ማህበረሰቡን ያሳተፈ የዳበረ ዴሞክራሲን የማፅናት፣ የላቀ ብሔራዊ መግባባትን የመፍጠር፣ የሰላም ግንዛቤና ሁለንተናዊ ተሳትፎን የማሳደግ የምክክር መድረኮች ተካሂደዋል። በተጨማሪም ማህበራዊ ሀብቶቻችንንና ባህላዊ እሴቶቻችንን በመገንባት ሂደት በተለይም የሰላም እናቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት ተቋማት በባለቤትነት እንዲሳተፉና እንዲያግዙ በማድረግ ለዘላቂ ሰላም ምቹ ምህዳር ተፈጥሯል። ከሲቪክ ማህበረሰቡ ጋር በመሆን ሰላምን በማስፋፋት፣ ግጭትን በመከላከልና ዴሞክራሲን በማስፈን ላይ በቅንጅት ለመሥራት ተሞክሯል።

የጦር መሳርያ ምዝገባና ቁጥጥር ሥርዓት የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። የቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ሥርዓት ከቀበሌ እስከ ፌዴራል በሚያስተሳስር መንገድ ተዘርግቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። የፖሊስ አገልግሎትን ዘመናዊ፣ ተደራሽና የሕዝብ ይሁንታ ያለው እንዲሆን በቀልጣፋና ዘመናዊ የመረጃ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲደገፍ ተደርጓል።

በፌዴራልና በክልል እንዲሁም ክልል ከክልል ጋር የሚደረጉትን ተቋማዊና ማህረሰባዊ ግንኙነቶች ለማጠናከር የመንግስታት ግንኙነት የፖሊሲ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። ፖሊሲውን ማዕከል ያደረጉና በህብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር የሚያስችሉ ጥናቶችና የማስፈጸሚያ ምክረ ሃሳቦች ቀርበው ምክክር ተደርጎባቸዋል። በሌላ በኩልም የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶና በመንግስት ጸድቆ ተግባራዊ ተደርጓል። በተጨማሪም ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጉልህ ድርሻ ያለውና ስለዜጋው የተሟላ መረጃ የሚሰጥ ብሔራዊ መታወቂያ የመዘርጋት ሥራ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቆ በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል።

# 6.2 የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት

ከ2003 እስከ 2012 በነበሩ የበጀት ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ በናይል ተፋሰስ ሀገራት ዘላቂ ሰላም፣ ልማትና የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር እና የአፍሪካ ሕብረት ለአህጉሪቱ ልማት፣ ሰላምና ውህደት መሳሪያ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዲጠናከር ለማስቻል ሥራዎች ተሰርተዋል። በተጨማሪም በሁለትዮሽ ግንኙነትና በውክልና አድማሳችንን ለማስፋት እንዲሁም በባለብዙ ወገን መድረኮች ተደማጭነትን በማጠናከር የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የፀጥታ ግቦችን ለማሳካት ታቅዶ ሲሰራ ነበር። በዚህም ኢትዮጵያና ጅቡቲ በወደብ፣ በውኃና በኤሌክትሪክ አገልግሎቶችና በባቡርና በየብስ ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች እንዲተሳሰሩ ተደርጓል። በተመሳሳይ ከኤርትራ ጋር ስምምነቶች እንዲፈረሙ፤ በኤርትራ እና በጅቡተ መካከል ግንኙነት እንዲፈጠርና እንዲሻሻል፤ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ የሦስትዮሽ መድረክ እንዲፈጥሩ፤ በሱዳን የተከሰተውን ቀውስ ለመፍታት በተቀናቃኝ ወገኖች መካከል ስምምነት ላይ እንዲደረስ እና ከኬንያ ጋር ያለን ትብብር እንዲጠናከር ተሰርቷል። በተጨማሪም ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት በአሚሶም ማዕቀፍ የሶማሊያ የፌዴራል መንግስት አቅም እንዲጠናከር ድጋፍ በማድረግ፣ በኢትዮጵያና

ድቡብ ሱዳን መካከል የትብብር ስምምነቶች እንዲፈረሙና የደቡብ ሱዳን ግጭት በሰላም እንዲፈታ እና በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ ሰላጤ የውጭ ሀይሎችን ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችል አሠራር በኢጋድ ማዕቀፍ እንዲዘረጋ ተደርጓል። ስድስት የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ሲፈርሙ አራቱ ስምምነቱን አጽድቀዋል። በታላቁ ህዳሴ ግድብ ዙርያም የሦስትዮሽ ድርድር እንዲካሄድና በግብጽ በኩል ይቀርቡ የነበሩ የተዛቡ ሃሳቦችን በመመከት እንዲሁም የተለያዩ የቴክኒክ አጥኚ ቡድንና የሚኒስትሮች ቡድኖችን በማቋቋም በግድቡ ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮችን ለማለዘብና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲፈጠር በማድረግ በሶስቱም ሀገሮች የመርሆች ስምምነት (Declaration of Principles (DoP)) ተፈርሟል።

የአፍሪካ ህብረት የመሪዎቹ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ እንዲሆንና በቋሚነትም በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ተወስኗል። ከስትራቴጂያዊ አጋሮቻችን ጋር በመሪዎችና በሚኒስትሮች ደረጃ በርካታ የጉብኝት ልውውጦች በማድረግ የጋራ ኮሚሽንና የፖለቲካ ምክክሮች ተካሂደው የተለያዩ ስምምነቶች ተፈርመዋል። ፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ የመገናኛ ብዙሃንንና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን ድጋፍና አዎንታዊ አመለካከት ለማጎልበት ተሞክሯል። በገፅታ ግንባታ ረገድ የፓብሊክ ዲፕሎማሲ ካውንስል በመመስረት የከተሞችን፣ የተቋማትንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ግንኙነቶች ለማመቻቸት ጉልህ እንቅስቃሴ ተደርጓል። ዲያስፖራዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች እንዲደራጁ፣ ለትውልድ ሀገራቸው ልማት የሚያደርጉትን ተሳትፎ እንዲያሳድጉና መብታቸው እንዲጠበቅ በማሰብ በዕቅድ ዘመኑ አዳዲስ የኮምዩኒቲ፣ የልማትና የሙያ ስብስቦች የተፈጠሩ ሲሆን በዚህም 654 ነባር ስብስቦች እንዲጠናከሩ በማድረግ 274 አዳዲስ የዲያስፖራ ስብስቦች እንዲፈጠሩ ተደርጓል። 1,233 የዲያስፖራ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት 229,140 የዲያስፖራ አባላትን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን 6,527 ወጣት የዲያስፖራ አባላት ስለሀገራቸው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል።

# ምዕራፍ ሰባት

## የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ አፈጻጸም

የአካባቢ ደህንነት መብቶች፤ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና ተጠቃሚነት የሚረጋገጥባቸውን ሥርዓቶች በማዘጋጀትና መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ የአካባቢና የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሳታፊና ያልተማከሉ የአካባቢ መንከባከቢያ ሥርዓቶች እንዲዘጋጁ ተደርጓል። በሀገራችን የኢንዱስትሪና የከተሞች መስፋፋትና የኑሮ ለውጥን ተከትሎ እየመጣ ያለውን የአካባቢ ሃብቶች ብክነትና ብክለት በተገቢው ሁኔታ ለመከላከል በ146 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሕግን ለማስከበር የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተሰርቷል።

የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተግባራትን በማስተባበር፣ በመደገፍና በመፈጸም የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ ለአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን የሚቋቋም ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በአቅም ግንባታ፣ በአሠራር ሥርዓት ዝርጋታ፤ በቴክኖሎጂ ልየታና ሽግግር የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል። በዚህም ባለፉት ዓመታት 92.7 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የካርቦንዳይኦክሳይድ እኩሌታ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነስ ተችሏል።

ሀገራችን በዓለም አቀፍ  የአየር ንብረት ለውጥ ድርድሮችና በሌሎች ከፍተኛ ዓለም አቀፍ  የድርድር መድረኮች ባደረገችውና እያደረገች በምትገኘው ተሳትፎ የልማት አጋሮች ለዘርፉ የሚያደርጉት የገንዘብ፣ የአቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በዚህም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም የሚያስችል የፋይናንስ ምንጭና አቅርቦትን በማስፋት ከተለያዩ ምንጮች 618.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሀብት ማሰባሰብ ተችሏል።

በተመሳሳይ በ2003 በጀት ዓመት የነበረውን 11.8 በመቶ የደን ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 15.5 በመቶ ማድረስ ተችሏል። ባለፉት ዓመታት 0.7 ሚሊዮን ሄክታር የቀርቀሀና ሽመል ደኖችን በዘላቂነት በመጠበቅና በመንከባከብ 365.8 ሺህ ሜትር ኪዩብ ምርት ተመርቷል። የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ሽፋን ወደ 8.6 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን 16 የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን በመከለል ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቷቸው እንዲቋቋሙ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ክፍል ሁለት

## ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶችና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ



# ምዕራፍ አንድ

## ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ
## የልማት ተግዳሮቶችና
## መልካም አጋጣሚዎች

# 1.1 ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች

ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የማስመዝገብ ተግዳሮት፦ ባለፉት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና በዘርፎች መካከል ሊኖር ከሚገባው ትስስር አንጻር ሲታይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ክፍቶች ነበሩበት። ምንም እንኳ ባለፉት ዓመታት የድህነት መጠንን መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ጊዜ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ከ19 በመቶ በላይ የሚሆነው ዜጋ ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ይገመታል። ከዚህም ባለፈ በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት፣ ሥራ አጥነትና ልዩ ልዩ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶች ተከስተዋል። እነዚህም ክፍተቶች የዕድገቱን ቀጣይነት አጠራጣሪ ከማድረጋቸውም በዘለለ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የኑሮ ጫና እያሳደሩ ይገኛሉ። በመሆኑም በቀጣይ በኢኮኖሚው ውስጥ የተከሰቱ አንኳር ችግሮችን በመፍታት እና የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ በማስፈን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቱሩፋቱን ለህብረተሠቡ እንዲዳረስ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፤ የግለሠቦችን የኑሮ ደረጃ ተጨባጭ በሚባል ሁኔታ የሚያሻሽል፤ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚቀንስ፤ የዋጋ ግሽበትን፣ ሥራ አጥነትንና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶችን የሚያስተካክልና በኢኮኖሚ ዘርፎች ጠንካራ ትስስር ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ ለውጥን የሚያመጣ መሆን አለበት።

የውጭ ክፍያ ሚዛን መዛባት፦ በኢትዮጵያ አጠቃላይ ኢኮኖሚው አሁን ያለበት የምርታማነትና የተወዳዳሪነት ደረጃ በብዙ መለኪያዎች ሲታይ ዝቅተኛ የሚባል ነው። በተለይም ችግሩ በአምራች ዘርፉ ጎልቶ ይታያል። ይህም በመሆኑ የአምራች ዘርፉ በዓለም አቀፍ  ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ካለመቻሉ በተጨማሪ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ መሰል ምርቶች ጋርም ተወዳዳሪ መሆን አልቻለም። በመሆኑም ሀገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ሸቀጦች በአብዛኛው እሴት ያልተጨመረባቸው ውስን የግብርና ምርቶች ናቸው። በተጨማሪም ለሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑ ሸቀጦችን ፍላጎት በሀገር ውስጥ ምርቶች ማሟላት አልተቻለም። በመሆኑም የኢኮኖሚው የገቢ ዕቃዎች ፍላጎት ከዓመት ዓመት እየጨመረ በመሄዱ በወጪና በገቢ ንግድ መካካል ያለው ልዩነት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል። የውጭ ምንዛሪ እጥረቱም የክፍያ ሚዛኑን ከማዛበቱም በላይ ተጓዳኝ የገንዘብ ፖሊሲ አስተዳደራዊ ችግሮችን አባብሷል። በዚህ ረገድ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችት አቅም ማነስና በውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በጥቁር ገበያ መካከል ያለው ልዩነት ከሚጠበቀው በላይ ከፍተኛ መሆን የሚጠቀሱ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ነበሩ።

በቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ሚዛን መዛባት፦ ባለፉት ዓመታት ኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ተከስቷል። ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንት ፍላጎቱን በአጠቃላይ ቁጠባው ማርካት ባለመቻሉ የኢንቨስትመንትና ቁጠባ ሚዛን መዛነፍ ተስተውሏል። ከዚህ አኳያ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 17.3 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 20.9 በመቶ ጨምሯል። በተመሳሳይ ወቅት በኢኮኖሚው ውስጥ የፈሰሰው የኢንቨስትመንት መጠን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከ31.1 በመቶ ወደ 30.8 በመቶ ቀንሷል። ይህም በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ልዩነት በ2012 በጀት ዓመት 9.8 በመቶ ሆኖ መመዝገቡን መረጃው ያሳያል። ይህ ልዩነት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት የ13.8 በመቶ እየጠበበ የመጣ ቢሆንም ክፍተቱ አሁንም ከፍተኛ ነው።

የዋጋ ግሽበትን ማረጋጋት ፈታኝ መሆን፦ የዋጋ ግሽበት መንስኤዎች በርካታ ቢሆኑም ከፍተኛና ተከታታይነት ያለው የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚው ውስጥ መከሰት የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ምልክት ተድርጎ ይወሰዳል። ከዚህ አኳያ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የዋጋ ግሽበትን በአንድ አኀዝ የመገደብ የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫ የነበረ ቢሆንም በተግባር ግን ይህ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ከ2003 እስከ 2012 በነበሩት የበጀት ዓመታት የተመዘገበው ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት 14.4 በመቶ ሆኗል። ይህም በኢኮኖሚው ውስጥ በፍላጎት እና በአቅርቦት መካከል አለመጣጣም መኖሩን ከማሳየቱም በተጨማሪ የግብይት ሥርዓቱን የሚያዛንፋ ተቋማዊ ችግሮች መኖራቸውን ያመላክታል። ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት በዜጐች ላይ ካስከተለው የኑሮ ውድነት በተጨማሪ ዘላቂ ኢንቨስትመንት እንዳይኖር በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጓል።

የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር፦ የሥራ ስምሪት ሁኔታ የማክሮ ኢኮኖሚውን ጤናማነት ከሚያሳዩ አመልካቾች አንዱ ነው። ከዚህ አኳያ በሀገራችን ከ70 በመቶ የማያንሰው ሕዝብ እድሜው ከ50 ዓመት በታች እንዲሁም ከ50 በመቶ የማያንሰው ዕድሜው ከ30 ዓመት በታች መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህን መሰሉ የሥነ ሕዝብ መረጃ በርካታ ወጣቶች መኖራቸውንና ሥራ ፈላጊ መሆናቸውን ይጠቁማል። ከዚህ በተጨማሪ የግብርናው ዘርፍ መጠነ ሰፊ ስውር ሥራ አጥነትን (disguised unemployment) እንዲሸከም ተገዷል። በአንጻሩ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙ ውስን እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። እስካሁን የተሞከሩ የተለያዩ የሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች የተወሰነ ውጤት ያስገኙ ቢሆንም በቀጣይነት የሥራ ዕድል ለማስፋፋት ተስፋ የሚጣልባቸው አይደሉም። በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለሀገሪቱ ዜጐች በቂ የሥራ ዕድልም ሆነ አብዛኛው ዜጋ ሊደርስበት የሚችል የኑሮ ደረጃ መፍጠር አልቻለም።

አዝጋሚ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና ደካማ የዘርፎች ትስስር መኖር፦ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አዝጋሚ በመሆኑ የኢኮኖሚው ምርታማነት ዝቅተኛ ከሆነው የግብርናው ዘርፍ ምርቶች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው የግብርና ምርቶች እንዲሁም ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የመሸጋገር ሂደቱ ደካማ ነበር። በዚህም በግብርናው ዘርፍ የተሰማራውንና ምርታማነቱ ዝቅተኛ የሆነውን እምቅ የሰው ኃይል ሊቀበል የሚችል የዳበረ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መገንባት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል። ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መጠነኛ የሆነ መዋቅራዊ ሽግግር የታየ ቢሆንም ይህ ሽግግር የመጣው ከማኑፋክቸሪንግ ሳይሆን በአመዛኙ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ነው። የሸቀጦች የወጪ ንግድ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዋነኛነት በግብርና ምርቶች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች በመሸጋገር ቀጣይና አስተማማኝ የወጪ ንግድ ገቢ ማስገኘት ተስኖታል።

በተጨማሪም በዘርፎች መካከል ያለው ትስስር አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአምራች ማለትም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል። ለማስረጃ ያህል ከአጠቃላይ የማምረቻ ወጪዎች ውስጥ ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች ድርሻ ለማሽነሪ ንዑስ ዘርፉ 93.3 በመቶ ሲሆን፣ ለብረታ ብረት ንዑስ ዘርፉ ደግሞ 79 በመቶ ይደርሳል። በተመሳሳይ የጨርቃጨርቅና አልባሳት እንዲሁም የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፎች ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ ናቸው። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻም ከ30 በመቶ ያልበለጠ ነው። ይህም እውነታ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው የኢንቨስትመንት ድልድል የተጣጣመና የተቀናጀ እንዳልነበር ይጠቁማል።

ዝቅተኛ የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባበስብ አቅም፦ ባለፉት ዓመታት የሀገር ውስጥ የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከር ከታክስና ከሌሎች የሀገር ውስጥ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን በአግባቡ ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የታክስ ገቢ የመሰብሰብ አቅማችን በየዓመቱ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በዕቅድ

ተይዞ ከነበረው የታክስ ገቢ ግብ አኳያ ከፍተኛ ጉድለት ነበረበት። በዚህም ምንም እንኳ ሀገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ብታስመዘግብም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ባለፉት አራት ዓመታት እየቀነሰ መጥቷል። የመንግሥት ወጪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ያስገኘውን ውጤት ለመገምገም ብሎም ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማስያዝ የተሰጠው ትኩረትም አነስተኛ ነበር።

የፋይናንስ ድርጅቶች ተደራሽነት፦ የሀገራችን የባንክና የመድን ኩባንያዎች በተለመደው የፋይናንስ ተቋማት ጤንነት መመዘኛ ሲታዩ ደህና ቢመስሉም የአብዛኛዎቹ አቅም በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች የባንክና የመድን ኩባንያዎች አማካይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። የመንግስት ባንኮች መጠነ ሰፊ ብድሮችን ካለ በቂ አዋጭነት ጥናትና ክትትል ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በረዥም ጊዜ ብድር በመስጠታቸው የንግድ ባንኮችን የብድር ዓይነትና ጥራት አዛብቷል። የመድን ኩባንያዎችም በአብዛኛው በለመዱትና በሚቀላቸው አገልግሎት በመታጠር በሌሎች የመድን አገልግሎቶች ላይ በሰፊው ባለመሰማራታቸው የመድን ኢንዱስሪው እንዳይሻሻል አድርጎታል። በአጠቃላይ የፋይናንስ መሠረተ ልማቱ ባለፉት ዓመታት ዕድገት እያሳየ ቢመጣም ኢኮኖሚው ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የማይመጣጠንና በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ተደራሽነትም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል።

የመሠረተ ልማት አቅርቦትና የጥራት ጉድለት መኖር፦ ባለፉት ዓመታት በመንገድ፣ በባቡር፣ በኢነርጂና በመስኖ ግንባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም አቅርቦቱ ካለው የመሠረተ ልማት ፍላጎት አኳያ ሲታይ ከፍተኛ የሆነ ጉድለት ይስተዋልበታል። ከጥራት አንጻርም ሰፊ ጉድለት የሚታይበት ነው። ይህም ሀገሪቱ ያላትን ውስን ሀብት ለጥገናና ለመልሶ ግንባታ ወጪ እንድታውል ዳርጓታል። ከዚህ በተጨማሪ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራ በታቀደና ሀገራዊ አቅሞችን ከመጠቀም አንጻር በተቀናጀና  ቅደም ተከተል በማስያዝ በአግባቡ ባለመከናወኑ ዋና ዋና የልማት ኮሪደሮችንና አካባቢዎችን ከማስተሳሰር አንጻር ጉድለቶች ተስተውለውበታል።

የማህበራዊ አገልግሎቶች የጥራት ውስንነት መኖር፦ ባለፉት ዓመታት በማህበራዊ አገልግሎቶች ዙሪያ በተለይም በጤናና በትምህርት ዘርፎች ከአገልግሎት ጥራት ጋር የተያያዙ የአፈጻጸም ጉድለቶች ታይተዋል። በትምህርቱ ዘርፍ በቅድመ መደበኛ፣ በተግባር ተኮር የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርትና የልዩ ፍላጎትና የአካል ጉዳተኞች ትምህርት አገልግሎትን በተመለከተ ተደራሽነቱም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ከመከላከል አኳያ ቀድሞ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችን በነበሩበት ፍጥነት አጠናክሮ ያለማስቀጠል፤ ከሥነ ምግብ ጋር በተያያዘ በሕጻናት ላይ እየታየ ያለው የመቀንጨርና የመቅጨጭ ምጣኔ ትርጉም ባለው መልኩ አለመቀነሱ፤ የሕክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ሥርዓት ጠንካራ አለመሆን እና በሀገር ውስጥ የመድሃኒትና ሕክምና ቁሳቁስ የማምረት ውስንነት መኖሩ እያጋጠሙ ካሉ ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ከዚህ ባሻገር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነት በከተማና በገጠር ሰፊ የሆነ ልዩነት የሚታይበት ሲሆን ይህም ለዜጎች እኩል ዕድል ከመፍጠርና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯል።

የአቅም ውስንነትና ብልሹ አሠራር፦ ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡትን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር በተለያዩ ደረጃዎች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች ተስተውለዋል። በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት (በማቀድ፣ በመተግበር፣ በመከታተል፣ ኮንትራት በማስተዳደር) የአቅም ውስንነቶችና የቅንጅት ችግሮች ከመታየታቸውም በላይ የሀብት ብክነትና ሌብነትም ሰፍኖ የነበረ ሲሆን እነዚህን ሁኔታዎች የሚያስተካክልና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓትም በተገቢ መንገድ የተዘረጋ አልነበረም።

# 1.2 መልካም አጋጣሚዎች

ቀደም ሲል የሀገራችን ኢኮኖሚ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እንዳይችል የተጋረጡበትን ፈተናዎች ለማሳየት ተሞክሯል። ኢኮኖሚው በርካታ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ከነዚህ ችግሮች ተላቆ የዕድገትና ብልጽግና ጎዳናን ለመያዝ የሚያግዙ መልካም አጋጣሚዎች በቅርቡ በሀገሪቱ ከተካሄደው ፖለቲካዊ ለውጥ ጋር ተያይዞ መፈጠራቸው ግልፅ ነው።

የሰላምና ፍትሕ መስፈን ለመልካም አስተዳደርና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለኢኮኖሚና ማሕበራዊ ዕድገትና ብልጽግና እንዲሁም ለግሉ ዘርፍ ተሳትፎ መጠናከር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም በለውጡ ጊዜ የሀገራችንን ሕዝቦች ለቅሬታና ለምሬት የዳረጉ በርካታ ጉድለቶችን ለማረም የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ሀገራዊ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የተደረጉ ጥረቶችና ያስገኟቸው ውጤቶች አበረታች ናቸው። የሀገራችን የሰላም ግንባታ በተያዘው መንገድ እየተሻሻለ ከቀጠለ ሙሉ ትኩረትን ወደ ልማት በመመለስ የተስተዋሉ ጉድለቶችን በማረም በተሻለ የልማት ፍጥነት መንቀሳቀስ ይቻላል። እንዲሁም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ትውልድና ዜጋ በቀጣይ የተያዙ የልማት ግቦችን በተሻለ የመፈጸም አቅም ይኖረዋል።

ሀገራችን ያላት ተሰሚነትና ተቀባይነት ማደጉ፦ ሀገራችን ባለፉት ዓመታት በዓለም ማቀፍ፣ በአህጉራዊና ቀጠናዊ ጉዳዮችና መድረኮች ላይ ከነበራት ንቁ ተሳትፎ እንዲሁም በቀጠናው ሰላምን ከማረጋገጥ አንጻር ስታደርገው ከነበረው አስተዋጽዖ ተቀባይነትና ተሰሚነቷ እያደገ መጥቷል። በተጨማሪም ባለፉት ሁለት ዓመታት በነበረው ለውጥ ዓለም አቀፋዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ የኢትዮጵያን የለውጥ ተስፋ እያለመለሙ በመምጣታቸው  ጥረታችንን የሚያግዙ በርካታ ወዳጆች ማፍራት ችለናል። በዚህ ሂደትም በተገኘው አጋጣሚና ታስበው በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ለልማት ያለንን ቁርጠኝነት፤ መነሳሳትና ያጋጠሙንን ችግሮች ለማስረዳት በመቻሉ ሀገራችን ከብዙሃንና ከሁለትዮሽ ትብብሮች የፋይናንስ፤ የቴክኒክና የፖሊሲ ድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን ችላለች። ይህ ትብብር እንዲቀጥል በማድረግ ለልማት የሚያስፈልግ ፋይናንስ ማሰባሰብና ሌሎቹ አስፈላጊ ድጋፎችን ማግኘት ይቻላል።

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በልማት አጀንዳ እንዲሳተፉ ማድረግ መቻሉ፦ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በሀገራቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ የተደረገው ጥረት ውጤታማ በመሆኑ ከእነሱ የሚገኘው ልዩ ልዩ ድጋፍና ትብብር እየተሻሻለ መጥቷል። ይህ ተሳትፎ በቀጣይ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግ ለልማት የሚያስፈልገውን ሃብት፣ ክህሎትና ዕውቀት ከማሰባሰብ አንጻር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል።

ሕብረተሰቡ በሀገሩ የፖለቲካና የልማት እንቅስቃሴ ያለው ተሳትፎ መጠናከሩ፦ ባለፉት ዓመታት ዜጎች በሀገራቸው የፖለቲካና የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩት ተሳትፎ እያደገ ስለመምጣቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ። እነዚህም ሀገራዊ መግባባትን ለመፍጠር፤ የታክስ ገቢን ለማሳደግ፤ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጠን ፍትሐዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው አግባብ እንዲሆን የመከታተልና የመጠየቅ ባህልን ለማዳበር በተደረጉ ለውጦች የሚገለጽ ነው። በቀጣይ የዜጎችን ተሳትፎ ማጠናከር የልማት ዕቅድን በባለቤትነት ከመፈጸምና ከማስፈጸም እንዲሁም አስፈላጊውን ሀብት ከማሰባሰብ አኳያ ዋናው የልማት አንቀሳቃሽ ዜጎች እንዲሆኑ ያስችላል።

ያለፉ ስህተቶችን በማረምና ከነሱ በመማር ተገቢ አቅጣጫን መከተል፦ ካለፉት ስህተቶች ተሞክሮ ለመውሰድና እነዚህንም ስህተቶች በማረም ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በመሆኑም በቀጣይ በተሻለ የግልፅነትና ተጠያቂነት መንፈስ ሥራዎችን በማከናወን ውጤታማ ልማትን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው የልማት ዕቅድን በሚፈለገው አግባብ ለመፈጸም የሚያስችል መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት አስመዝግባለች። ዕድገቱ በዋነኛነት ከጥቅል ፍላጎት (aggregate demand) ዘመም የኢኮኖሚ ስርዓት የመነጨ ነው። ይህም በአብዛኛው ባለፉት ዓመታት በመንግስት ከፍተኛ ወጪ በተስፋፋ የመሠረተ ልማት ዕድገት አማካይነት የተመዘገበ ነው። ይህ የመንግስት ወጪ በከፍተኛ ብድር እና እርዳታ የተሸፈነ ነው። የመንግስት ወጪ ተግባራዊ የሆነበት አግባብና የተመዘገበው ዕድገት ለዓመታት የዋጋ ግሽበት ፈጥሯል። በተጨማሪም ዕድገቱ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል በተፈለገው መጠን በቋሚነት አልፈጠረም። በከፍተኛ የብድር ጫና ምክንያት ዕድገቱ ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ መፈጠሩ ከመንግስት ወጪና ብድር ባሻገር ዕድገቱ የሚቀጥልበት ሌላ አማራጭ የዕድገት ምንጭ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የኢኮኖሚ ዕድገቱን የሚያስቀጥል፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር የሚፈጥር እንዲሁም ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (homegrown economic reform) ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህም የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማዕቀፍ ገበያን መሠረት ያደረገ አቅርቦትን ለማስፋፋት በሚወሰዱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያዎች የሚገለጽ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውና ትኩረቱም የግል ክፍል ኢኮኖሚውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገት በሂደት በግሉ ዘርፍ ወደሚመራበት ዕድገት ማሸጋገር ሲሆን በዚህም ምክንያት በተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ውስጥ ዕድገቱ ወደ ኋላ ሳይመለስ የሚቀጥልና የተንሰራፋውን ሥራ አጥነትን የሚያቃልል ይሆናል። እነዚህም ማሻሻያዎች በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በክፍላተ ኢኮኖሚና በመዋቅራዊ ማስተካከያ ተለይተው የሚታዩ ናቸው።

## 2.1 የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ

ባለፉት ዓመታት የተስተዋለው የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት በቶሎ ተስተካክሎ ኢኮኖሚው ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ በጥብቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት እንዲመራ በመደረግ ላይ ይገኛል። የማክሮ ዘርፉን የሚመለከቱ የኢኮኖሚ ተግባራት በጥብቅ ክትትል እንዲደረግባቸው ተደርጓል። ከዚህ አኳያ በሚከተሉት የማክሮ ኢኮኖሚ የሪፎርም መስኮች በትኩረት በመሠራት ላይ ይገኛል።

የኢኮኖሚ ዕድገቱን ፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉን ዓቀፍ እንዲሆን የተቀናጀ ጥረት ማድረግ፦ በቅርብ ዓመታት እየተቀዛቀዘ የመጣውን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደ ቀድሞው ፍጥነቱ ለመመለስ የሚያስችሉ ጥረቶች በየዘርፉ በመከናወን ላይ ይገኛሉ። እነዚህም ጥረቶች መላውን ህብረተሰብ፣ ባለሀብቱን፣ የሲቪል ማህበረሰቡን፣ መንግሥትንና የልማት አጋሮቻችንን በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራዊ እየተደረጉ ነው። ይህም የሚከናወነው ያለፉትን ዓመታት የልማት ዕቅዶች አፈጻጸም በጥልቅ በመመርመር ከተገኙ መልካም አፈጻጸሞች እንዲሁም ከተስተዋሉ ድክመቶችና ተግዳሮቶች ልምድ በመቅሰም በህብረተሰቡ ተሳትፎ ተግባራዊ በሚሆነው የልማት ዕቅድ አማካይነት ይሆናል። ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻጸም ከዓይነት አንጻር ያለው አፈጻጸም በዝርዝር ጥናት ተገምግሞ በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የሪፎርም እርምጃዎች ለማመላከት እንደ ግብዓት ይወሰዳል። በዚህም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉን ዓቀፍ እንዲሆን የተቀናጀ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

የፊሲካል ፖሊሲን በተመለከተ የተጀመሩ የታክስ፣ የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር እንዲሁም የዕዳ አስተዳደር ማሻሻያዎች እና የታክስ አሰባሰብ ሥራውን በማዘመን የተሻለ ገቢ መሰብሰብ እንዲቻል ዜጎች በአግባቡ የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስችሉ አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። ሆኖም የሚጠበቅባቸውን ግብር በማይከፍሉት ላይ ሕጋዊ ዕርምጃ መውሰድ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ዕርምጃ የታክስ ሥርዓቱን ግልፅ በሆነ አሠራር እንዲቃኝ ያደርገዋል። የታክስ ገቢው አሰባሰብ ዝቅተኛ ቢሆንም ታክስ ከፋዩን በእኩል የማየትና በአግባቡ የማስተናገድ ችግር በጉልህ የሚታይ ነው። በመሆኑም የታክስ አስተዳደሩ ፍትሐዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን በርካታ አሠራሮች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን ይህም አበረታች ውጤቶች

በማሳየት ላይ ይገኛል። ኮንትሮባንድ የመንግሥትን ገቢ ከመጉዳቱም ባሻገር በአምራቹ፣ በንግዱ ማህበረሰብና በሸማቹ ላይ የሚኖረው አሉታዊ ገጽታ የከፋ መሆኑ ግልፅ ነው። የኮንትሮባንድ ንግዱ የሚከናወነው ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያ በምንልካቸው ምርቶቻችን ላይም ነው። በዚህ መሠረት ኮንትሮባንድ ለሀገራችን ወጪ ንግድ መዳከም አንዱ መንስዔ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ መሠረት የኮንትሮባንድ ንግድን ከምንጩ በማድረቅ ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን ለማበረታታት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በተጨማሪም የበጀት አስተዳደርና ቁጥጥር ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል። በዚህ ረገድ ጥብቅ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት በሕግ የተደነገገው በጀት በትክክል ለተፈለገው ዓላማ መዋሉ የሚረጋገጥበት ተቋማዊ የሆነ አሠራር እንዲኖር ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል። የመንግስት በጀት ኢኮኖሚው ትኩረት በሚሰጣቸው የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ትኩረት እንዲያደርግና ፕሮጀክቶችም ጥልቅ የአዋጭነት ጥናት ላይ ተመስርተው የሚመረጡ እንዲሆኑ አቅጣጫ ተይዞ በመሠራት ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቶቹም በተመደበላቸው በጀትና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ የሚያስችል የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥርና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ተደርጓል። የሚመደበው የወጪ በጀትም ያስገኘውን ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ አሠራሮችና በዚህም የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምቶችን ለመውሰድ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም፦ የግሉን ዘርፍ ምርታማነት ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ኢኮኖሚው የገጠሙትን መዋቅራዊ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ቁጠባን በማበረታታት ለግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የፋይናንስ አቅርቦትን ማስፋትና ፍትሐዊነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህንን ግብ ለማሳካት ገበያን መሠረት ያደረጉ የፋይናንስ ሴክተር ማሻሻያዎች ማድረግ ያስፈልጋል። ገበያ መር የወለድና የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ሥርዓት በሂደት የመገንባት፤ የገንዘብ ገበያ አክሲዮን ጥናትን መሠረት በማድረግ የማቋቋምና የማስፋፋት እና የብሔራዊ ባንክ የቁጥጥርና ክትትል አቅምን የማሳደግ ሂደቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

የሀገራችንን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመፈታተን ላይ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ የፖሊሲ እርምጃዎችን መወሰድ ተጀምሯል። በወጪ ንግድ ዘርፍ የሚታዩ መዋቅራዊ ችግሮችን በመለየት መሠረታዊ መፍትሔ የሚያመጡ የማሻሻያ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እየተሰራ ነው። በተወሰኑ የግብርና ምርቶች ላይ የተመሠረተውን የወጪ ምርቶችን ስብጥርና መጠን በማሳደግ፣ ከምርታማነትና ከማምረት አቅም ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመቅረፍ፣ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት ፈጥሮና የወጪ ንግድ ምርቶችን በዓይነትና በመጠን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን የኋሊት ጉዞ በመቀልበስ ዕድገት እንዲያሳይ የሚያስችሉ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

ሌሎች የውጭ ምንዛሪ ምንጮች፦ መንግሥት ከውጭ ሀዋላ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ የዲያስፖራው ህብረተሰብ ወደ ሀገር ቤት የሚልከውን ገንዘብ በባንክ ሥርዓት እንዲያልፍ ለማድረግ የተለያዩ የማበረታቻ ሥራዎችን በማከናወን አስፈላጊውንም ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል። የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም የሥራ ዕድልን ለማስፋት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ፍሰቱ የሚጎለብትበትን መንገድ የማመቻቸት ተግባራት በሰፊው በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም የውጭ ምንዛሪ አስተዳደሩንና ፖሊሲውን በጥናት በመፈተሽ አስፈላጊ ማሻሻያዎችን ለማድረግ መሰረታዊ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም የመንግስትን የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም በመገደብ የውጭ ምንዛሪው የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ላይ ብቻ እንዲውል ተደርጓል። የውጭ ዕዳ ጫናን ለመቀነስ የዕዳ ጫናቸው ከፍተኛ የሆኑ የብድር አይነቶች እንዳይወሰዱ የማድረግና እንዲሁም የተወሰዱ ተመሳሳይ ብድሮችን የዕዳ ክፍያ ጊዜ የማሸጋሸግ ሥራዎች ተከናውነዋል።

# 2.2 የክፍላተ ኢኮኖሚ ዘርፎች ማሻሻያ

ለአንዳንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች ልዩ ድጋፍና ትኩረት ማድረግ፦ ከዚህ ቀደም በወረቀትና በንግግር ትኩረት የሰጠነው ቢመስልም ግብርና ዘርፉ የሚመጥነውን ትኩረት አላገኘም። ለግብርና ዘርፍ ተዋናዮች የሚሰጠው ድጋፍ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሻሻል ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከዚህ አንጻር ለአርሶ አደሩ የሚቀርብ ግብዓት ግብይት የሚቀላጠፍበትና ከመንግስትም የተለየ ድጋፍ የሚያገኝበት ሁኔታ የታየ ሲሆን ለመስኖ ልማትና እርጥበት መቋጠር የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል። ለግብርና ልማት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት የግብርና ምርታችን በአስተማማኝ ሁኔታ በተከታታይ የሚያድግበት መንገድ እየተመቻቸ ሲሆን የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የቱሪዝም ዘርፎችም በተመሳሳይ ከፍተኛ ትኩረት እያገኙ ነው።

- አነስተኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፤
- ለግብርና ግበዓትና ፋይናንስ ማቅረብ፤
- የእንስሳት እርባታ ምርታማነትን መጨመር፤
- የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ የሁሉንም ትኩረትና ተሳትፎ አግኝቶ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- የግብርና አመራረት ዘዴን ማሻሻል፤
- ድህረ ምርት ብክነትን መቀነስ፤
- በጥናት ላይ የተመሠረተ የምግብ ዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ዋና ዋና ሰብሎችን በተለይም በአጭር ጊዜ ስንዴን፣ የቢራ ገብስን፣ የምግብ ዘይትና ጥሬ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ።

በማዕድን ልማት ዘርፍ፦ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በማሳተፍ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ከዓለምዓቀፍ ልምድ በመነሳት ማሻሻያ እየተደረገበት ይገኛል። የማዕድን ሀብታችንን መረጃ በማጠናቀርና ተደራሽ በማድረግ፣ በዚህም የባለሀብቶችን ተሳትፎ በማሳደግ፣ መንግሥትም በመሠረተልማት ዝርጋታ ላይ በሚያደርገው ኢንቨስትመንት ከልማቱ አክሲዮን ድርሻ እንዲኖረው በማድረግ መንግሥትን በፋይናንስ ተጠቃሚ ከማድረጉም በላይ የኢንቨስተሩን እምነት እንዲያጎለብት አቅጣጫ ተይዞ በመሠራት ላይ ይገኛል።

በቱሪዝም ልማት ዘርፍ፦ ሀገራችን በሌሎች ሀገሮች የማይገኙ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ቢኖሯትም ዕድሉን በአግባቡ ያልተጠቀመችበት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ዘርፍ ለውጭ ምንዛሪ ምንጭ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ቱሪስቶችን በተለያየ መልኩ ለመሳብ የሚያስችሉ ተግባራት በሰፊው በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ይህንንም ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም መንግሥት ለግል ባለሀብቱ ተሳትፎ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ይገኛል።

የተቀናጀ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ማረጋገጥ፦ የገቢና ወጪ ዕቃዎችን አጠቃላይ የትራንዚት ጊዜ እና ወጪ በመቀነስ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቻችን በዓለም አቀፍ  ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንዲሁም የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመደገፍ በሚያስችል መልኩ የሀገሪቱን የተቀናጀ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነት፤ የገቢና ወጪ ምርቶች የትራንስፖርት ኮሪደሮችን እና የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ጥራት፣ ቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማሳደግ አቅጣጫ ተይዞ በመሠራት ላይ ይገኛል። የተወሰኑ ገቢ ምርቶችን የመተካት ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ፦ በዓለም አቀፍ  ትስስር የሚመራው የኢኮኖሚ ስትራቴጂያችን በዋናነት ኤክስፖርት መር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣባቸው ያሉ ነገር ግን በትንሽ ጥረት ንጽጽራዊ አቅም ሊፈጠርባቸው የሚችሉ እንደ ምግብ ዘይት፣ ስንዴና የግብርና አግሮ ፕሮሰሲንግ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ

በማምረት የመተካት ስትራቴጂን በመከተል ሰፊ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ።

የሥራ ፈጠራንና የቢዝነስ ምህዳሩን ማሻሻል፦ የሀገር ውስጥ የሥራ ፈጠራንም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት መሠረተልማትን ያካተቱና እስካሁን የተሰሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣ የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታን የማሻሻል፣ አላስፈላጊ ቢሮክራሲን የማስወገድ እና የብድር አቅርቦት የማሻሻል ሪፎርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል።

የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ሚና ማሳደግ፦ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረውን ሚናና ያጋጠሙትን ፈተናዎች በዝርዝር በጥናት በመፈተሽ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡና በተሻለ ሁኔታ እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ የኢኮኖሚ ሪፎርም እርምጃዎች በቀጣይ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሀገሪቱን የቢዝነስ ከባቢያዊ ሁኔታ በማሻሻል ረገድ የሚሠራው ሥራ በትንሹ በመፍጨርጨር የሚታተረውን ቢሮክራሲያችንን ጠልፎ የሚጥል ሣይሆን የሚደግፍና የሚያሳድግ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ይህ ማሻሻያ በፋይናንስ ዘርፉ ከሚደረገው ማሻሻያ ጋር ተመጋግቦ ሀገሪቱ የፈጠራ ሥራዎች መፍለቂያ (startup nation) እንድትሆን ያደርጋል።

# 2.3 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ጉዳዮች ማሻሻያ

የመንግስትን ሚና ማሻሻል፦ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና የሚቀጥል ቢሆንም በአፈጻጸም ፖሊሲና ስልቶች ላይ እንደወቅቱ ሁኔታ ማሻሻያ ማድረግ ይገባል። የመንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ በተለይ በኢንቨስትመንት ጣልቃ አገባብ የተለየ አሠራር እንዲከተል ማድረግ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የገበያ ጉድለት መኖሩ በጠለቀ ጥናት እንዲፈተሽ በማድረግ የገበያ ክፍተት መኖሩ ከተረጋገጠና መንግሥት ጣልቃ መግባት ካለበት የፕሮጀክቱ አዋጭነት በበቂ ሁኔታ እንዲጠና እንዲሁም ጣልቃ ገብቶ ፕሮጀክቱን ለስኬት ለማብቃት በቂ የፕሮጀክት የማስፈጸሚያ አቅምና ሀብት ስለመኖሩ በቅድሚያ የማረጋገጥ አቅጣጫ ተይዞ በመሠራት ላይ ይገኛል። በፕሮጀክት ደረጃም እያለ ይሁን ፕሮጀክቱ ካለቀ በኋላ በቂ አቅም ያለውና ማስቀጠል የሚችል ባለሀብት መኖሩ ሲረጋገጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ ለግሉ ዘርፍ እንዲተላለፍ የሚደረግበት አሠራር ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል።

ከሀገር ውስጥ ባንኮች በመበደር የሚፈጸም ፕሮጀክት ባንኮች ለማበደር አዋጭ መሆኑን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል። መንግሥት ከባንኮች የሚወስደው ብድር የግል ባለሀብቱን የብድር ድርሻ የሚያኮስስ (crowding out) እንዳይሆን ጥንቃቄ በመወሰድ ላይ ይገኛል። የመንግስት የመጨረሻው ግብ ጠንካራ የግል ባለሀብት በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲፈጠር ስለሆነ ሂደቱ የግል ባለሀብትን የሚያኮስስ ሳይሆን የሚያጠናክርና የሚያስፋፋ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። የግል ባለሀብቶችን ጨምሮ ሁሉን የልማት ሀይሎች መንግስት መደገፍ ያለበት ለመንግስት ባላቸው ቅርበት ሳይሆን ባላቸው ውጤት ላይ ተመርኩዞ መሆን አለበት። መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ሲል የፈጠራቸው መንግስታዊ ድርጅቶች ከሌሎች የግል ተመሳሳይ ድርጅቶች የተለየ ድጋፍ የሚያገኙበት አግባብ እንዳይኖር ተደርጓል። በዚህ መሠረት ሁሉንም የኢኮኖሚ ተዋናዮች በእኩል የሚያሳትፍ፣ ፍትሐዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት የሰፈነበት የውድድር ሜዳ መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የመጫወቻ ሜዳውን ምቹ በማድረግና ለዚህ የሚያግዙ የፖሊሲና አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ዜጎች በነጻነት ሰርተው የሚኖሩባትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማበረታታት የሚወሰዱት የፖሊሲ እርምጃዎች ሁሉንም የሥራ መስክ የሚመለከቱ በመሆኑ በሚደረጉ የፖሊሲ ማሻሻያዎች በሙሉ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታቱና የሚደግፉ እንዲሆኑ በመሠራት ላይ ይገኛል።

የንግዱ ማህበረሰብ እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖረው በማድረግና በነጻ ለመደራጀትና ከመደራጀት በሚገኘው ጥቅም ላይ ትኩረት እንዲሰጥ መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ሰፊ የውድድር መንፈስ በመፍጠር በማምረትም ሆነ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሁሉ በውድድር ብቻ የጋራ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን ሊቀይር የሚችል ድምፅ ማሰማት የሚችልበት መድረክ ይፈጠራል፡፡

የግሉ ዘርፍ የማይተካ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ሚና ያለው በመሆኑ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የጎላ ሚና እንዲጫወት መንግስት አድሏዊ ያልሆነና የተመቻቸ ብድር በማቅረብ፣ አቅም በፈቀደ መጠንም የሚገኝ የውጭ ምንዛሪን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በማደላደልና ዘርፉም መንግሥት ቅድሚያ በሰጠባቸው የሥራ ዘርፎች ላይ እንዲሠማራ አቅጣጫ በማስያዝና አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችል የተሟላና ሁሉን ዓቀፍ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም በሚገነቡ የኢንዱስትሪና የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው አምራች የሚሆኑበትን ስልት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም የሥራ ዕድል መስፋፋትና ሥራ ፈጣሪነት ከኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ጋር የተጎዳኘና በሂደቱ የሚጎለብት በመሆኑ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የበለጠ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ መንግስት አስፈላጊ የሆነውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት ጥረት በማድረግ ላይ ነው፡፡

ግዙፍ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዜሽን ማፋጠን፦ መንግስት ወደ ግል እንዲዛወሩ የወሰነባቸው ድርጅቶች ፕራይቬታይዜሽን ሲጠናቀቅ በኢኮኖሚው ላይ በቅልጥፍናም ሆነ በአገልግሎት ጥራትና ብዛት የሚያመጣው ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ በተፋጠነ ሁኔታ ይህ ሂደት እንዲጠናቀቅ ትኩረት ተሰጥቶ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

የዓለም አቀፍና የአካባቢ የንግድ አካል መሆን፦ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን የንግድ ድርድሩን ከጀመረች በኋላ በተለያየ ምክንያት እየተስተጓጎለ አሁን ድርድሩን ሳታጠናቅቅ ረዥም ዘመን የቆየች ብቸኛ ሀገር የሚል ስም አግኝታለች፡፡ ኢኮኖሚያችንን ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ማስተሳሰሩ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ወደብ አልባ በመሆናችን የተለያዩ ወደቦችን በጋራ ለማልማት የጀመርነውን ተግባር አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡ በመሆኑም በምሥራቅ የጂቡቲን ወይም የበርበራን ወደብ፣ በምዕራብ የሱዳንን እንዲሁም በሰሜን የኤርትራን ወደቦች በመጠቀም ወጪ ከመቀነሳችንም ባሻገር አስተማማኝና ዘላቂ አገልግሎት ለማግኘት ይረዳል፡፡ የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ አማራጭን ማስፋት ይቻላል፡፡ የአካባቢ የንግድ ቀጠና አባል ለመሆን የፈረምነውም ስምምነት በጥብቅ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

ነጻ የሰው ኃይል ዝውውርን ማሳለጥ፦ በሀገራችን ያለውን ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በየዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ሥራ ወዳለበት አካባቢ በነጻነት ተዘዋውሮና መብቱ ተጠብቆ እንዲሠራ የሚያደርግ መርህ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የሲቪክ ማህበራት በሀገራችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በተደራጀ መልኩ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ አካላት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል በመቆም የሁለቱን የኢኮኖሚ ተዋናይነት ሚዛን እንዲጠብቅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ነፃ ሃሳብ የሚንሸራሸርበት እውነተኛ ዴሞክራሲ በመገንባት ሚዲያን ጨምሮ የሲቪክ ማሕበረሰቡን ሚና ማሳደግ የመንግሥትን ሚና የሚያቀጭጭ ሳይሆን የሚያጎለብትና ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዝ ነው፡፡ የዜጎችን ፖለቲካዊና ሞራላዊ ሥልጣን ያካተተ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አተያይ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ከዚህ በፊት ያጋጠሙንን ችግሮች ለማረምና በሀሳብ ነፃነት መንገስ ምክንያት የሚመጣውን የሕዝብና የሀገር አቅም አሟጥጦ ለመጠቀም ያግዛል፡፡ ሁሉንም ተዋናዮች እንደ አንድ የተዋሀደ አካል (integrated whole) ማየት ያስፈልጋል፡፡ ይህም አተያይ ሁሉም ተዋናዮች የሚጫወቱትን ቁልፍ ሚናና ያለውን ጥልቅ ትርጉም በዋናነት የማየትና የማድነቅ ዕድል ይሠጣል፡፡ ይህ ሲሆን ልማት በቁንፅል ቁሳዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ዘርፈ ብዙ ነፃነቶችን የሚያሰፋ የተሟላ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ ያግዛል፡፡

ነባር የልማት አጋሮቻችንን ማበረታታትና ወቅታዊ የልማት ፋይናንስ ምንጭ ማፈላለግ፦ የሀገራችን ሌላው የልማት አጋር የውጭ ዓለምአቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም መንግሥታት ናቸው። መንግሥት ከልማት አጋሮቹ ጋር በመተማመን በሚፈጥረው መድረክ የልማት ፋይናንስ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ የአፈጻጸም አቅም ለማጎልበት የሚረዱ የቴክኒክና የአሠራር ዕገዛዎችን ያበረታታል፤ በአግባቡም ተጠያቂነትና ግልፅነት በሰፈነበት መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል። የግሉን ዘርፍ ለማጎልበትም የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የልማት አጋርነት ሥርዓትን እንዲሁም በሙሉም ሆነ በከፊል ወደ ግሉ ዘርፍ የሚዞሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አተገባበር ላይ የልማት አጋሮቹ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የልማት አጋሮቻችን ከልማት እርዳታ ባሻገር የውጭ ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ በማድረግ በትብብር እንዲሰሩ ማበረታታት ይጠበቃል። በአሁኑ ወቅት የሚስተዋለው ዓለምዓቀፍ የልማት ፋይናንስ ፍሰት ነባሩን ሂደት የሚከተል አለመሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ቀደም ሲል የታዳጊ ሀገሮች የልማት ፋይናንስ ምንጭ የነበሩት ባለብዙ ወገን መድረኮችና የሁለትዮሽ የፋይናንስ ምንጮች አቅርቦት እየቀነሰ በአዳዲስ ሁለትዮሽ ለምሳሌም በቻይና፣ በግል በጎ አድራጊ (philanthropic) ድርጅቶችና በግለሰቦች ምንጭ እየተተካ መምጣቱ ይስተዋላል። ይህን ሁኔታም በመገንዘብ ሀገራችን ከወቅታዊ የልማት ፋይናንስ አቅርቦት ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማድረግ እየሰራ ነው።



# ምዕራፍ ሦስት

## የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ
## አስፈላጊነትና ልዩ ባህርያት

# 3.1 የሀገራችን የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ

የልማት ዕቅድ የማዘጋጀት ልምድ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በሀገራችን በተቀናጀ መልኩ ሥራ ላይ መዋል የጀመረው በ1940ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው። በሀገራችን በ1940ዎቹ መጀመሪያ ላይ እንደ እርሻና ደን፣ ኢንዱስትሪ ልማት፣ ትራንስፖርትና መገናኛ፣ ትምህርትና የውኃ ሀብት ልማት ለመሳሰሉት ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተናጠል የልማት ዕቅዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል። ሀገራችን ከ1949 እስከ 1965 በጀት ዓመት በነበረው ጊዜ የተለያዩ ዋና ዋና ዘርፎችን ያካተቱ ሦስት ሀገራዊ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅዶችን (የመጀመሪያው ከ1949-1954፣ ሁለተኛው ከ1955-1959፣ ሦስተኛው ከ1961-1965) በማዘጋጀት ሥራ ላይ አውላለች። አራተኛው የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ከ1967-1971 በጀት ዓመት የነበሩትን ዓመታት እንዲሸፍን ሆኖ ቢዘጋጅም በሀገሪቱ የየካቲት 1966ቱን ሕዝባዊ ንቅናቄ ተከትሎ በተደረገው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ምክንያት ሳይተገበር ቀርቷል።

ከ1967 እስከ 1983 በነበሩት አሥራ ሰባት ዓመታት መንግስት ያራምድ በነበረው ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያልተጣጣመ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ እንዲሁም በሀገሪቱ በተደጋጋሚ ከደረሰው አስከፊ ድርቅ እና ከተካሄደው አውዳሚ ጦርነት ጋር ተዳምሮ ኢኮኖሚውን ወደ ባሰ ቀውስ ደረጃ ላይ አድርሶት እንደነበር ይታወሳል። በወቅቱ የነበረው የተማከለ የኢኮኖሚ አስተዳደር የመንግስትን ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጠናከር በማድረግ ብቻ ሳይሆን የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና በሚያጠብ መልኩ የፖሊሲ እርምጃዎችን በመውሰድ ይመራ ነበር። በዚህ ረገድ በወቅቱ ከተወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎች ውስጥ መሬትን ጨምሮ ዋና ዋና የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የፋይናንስ ተቋማትን በመንግስት ቁጥጥር ስር ማዋል፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚገድቡ አዋጆችንና መመሪያዎችን ማውጣትና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ይሁን እንጅ ሀገሪቱ በዕዝ ኢኮኖሚ አመራርና አስተዳደር ሥርዓት ጥላ ሥር ሆናም ከ1966 ወዲህ የተለያዩ የረዥም ጊዜ ጠቋሚ እና የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶችን በማዘጋጀት ለመተግበር ሙከራ አድርጋለች። በዚህም ሂደት ስድስት ዓመታዊ የልማት ዕቅዶች (1971-1976) ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ከመዋላቸውም በላይ አንድ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድም (1977-1986) ተዘጋጅቶ ነበር።

በ1983 በጀት ዓመት የደርግ ሥርዓት መገርሰስን ተከትሎ ወደ ስልጣን በመጣው በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር መሪነት ኢኮኖሚው ገበያ መር ሥርዓት መከተል ጀመረ። በዚህም መሠረት በህዳር 1984 በጀት ዓመት የወጣው አዲሱ የሽግግር ዘመን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዓላማ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከዕዝ ኢኮኖሚ አመራር አላቆ በነፃ ገበያ ሥርዓት እንዲመራ ማድረግና የተፋጠነ ዕድገትን በማምጣት ሀገሪቱን ከድህነትና ከኋላቀርነት አረንቋ ማውጣት ነበር። የተወሰዱት የፖሊሲ እርምጃዎች ዋና ዓላማ በማክሮ ኢኮኖሚው ውስጥ ይታዩ የነበሩ መዛባቶችን ለማስተካከልና አለመረጋጋቱን በማርገብና ለገበያ መር ሥርዓት መጎልበት እንዲሁም ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ ማንሰራራትና መስፋፋት መሠረት ለመጣል የሚያስችል የመዋቅር ማስተካከያ ማድረግን ያካትታል። በዚህ ረገድ የተወሰዱት እርምጃዎች ዋነኛ ትኩረት የተዛባውን የገበያና የዋጋ ሥርዓት ማስተካከል፣ የምርት ግብዓቶች እንዲሁም ምርቶችና አገልግሎቶች በገበያ ሥርዓት እንዲመሩ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚገድቡ ሕጎችና ደንቦችን መለወጥ፣ በወጪ ክፍያና በበጀት ላይ የሚታየውን ጉድለት ማጥበብ፣ የንግዱን ዘርፍ ደረጃ በደረጃ ነጻ እንቅሰቃሴ እንዲኖረው ማድረግ እና ባጠቃላይም ኢኮኖሚውን መልሶ ማቋቋምን ያጠቃልላል።

ሆኖም ከ1984-1994 በጀት ዓመት ባሉት ጊዜያት መንግስት ሲከተለው የነበረው የኢኮኖሚ አመራርና አስተዳደር ስልት በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ደረጃ ዋና ዋና የፖሊሲ ባህሪያትን በቅርብ በመከታተል የኢኮኖሚ

መረጋጋትን ከማስፈንና በዓመታዊ የበጀት ዝግጅት አማካይነት የሀብት ድልድልን ከማስፈጸም ባሻገር ኢኮኖሚውን በረጅም ጊዜ ዕይታ ውስጥ በማስገባት የዕድገት ምንጮችንና አማራጮችን እንዲሁም የልማት ፋይናንስ ፍላጎትን መሠረት ያደረገና የግሉን ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከግምት ውስጥ ያስገባ የተቀናጀ የመካከለኛና የረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት አልተቻለም ነበር። ይህ ጊዜ በኢትዮጵያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪክ ክፍተት የነበረበት ወቅት ነበር። ይህንን በመገንዘብ መንግስት ከመልሶ ማቋቋሙ ፕሮግራም በኋላ ማለትም ከ1995-1997 ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ድህነት ተኮር በሆኑ ዘርፎች ላይ ያተኮረ የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (Sustainable Development and Poverty Reduction Program, SD-PRP) አዘጋጅቶ ተግባራዊ አድርጓል። ከዚህ በኋላም ሁለት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች ማለትም ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ማስወገድ (Plan for Accelerated and Sustainable Development to End Poverty - PASDEP 1998-2002) እና የመጀመሪያውና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (GTP I (2003-2007) እና GTP II (2008-2012)) ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ ተደርጓል።

በመቀጠልም በተመረጡ ዘርፎች ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች እንዲካሄዱ በማድረግና በግብዓትነት በመጠቀም የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የሆነች ኢትዮጵያን ለመገንባት ወሳኝ ሚና ያለው የ10 ዓመት (2013-2022) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱ በዘርፎች መካከል እርስ በእርስ የጎንዮሽ ኢኮኖሚ (በግብዓት፣ በፋይናንስ፣ በመሠረተ ልማት፣ በቴክኖሎጅ፣ በሰው ኃይል፣ በገበያና በመሳሰሉት) እንዲሁም ከማክሮ ጋር ወደ ላይ እንዲተሳሰር ተደርጓል። በተጨማሪም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከልማት ዕቅዱ ጋር በማስተሳሰር የዕቅዱ አካል ሆነው እንዲተገበሩ ለማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራ የፋይናንስ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ጥናቱ የየዘርፉን የልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲመግብም ተደርጓል። በአጠቃላይ የልማት ዕቅዱ የጋራ መግባባትንና ፍላጎትን እንዲሁም የዜጎችን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቅና የህዝቦችን ተሳትፎ ያረጋገጠ የልማት ዕቅድ እንዲሆን ሰፊ የሕዝብ ምክክሮች ተካሂደዋል።

## 3.2 የአስር ዓመት ዕቅዱ አስፈላጊነት

የአንድ ሀገር የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ሚና በዋናነት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በየምዕራፉ በሚዋሩ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች አማካይነት ሊተገበሩ የሚቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን፣ ዓላማዎችን፣ ግቦችንና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በማስቀመጥ የዕቅዶችን ተፈፃሚነት በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ለመከታተል የሚያስችል ነው። ይህም ማለት የልማት ዕቅዱ ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራተጂክ አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን በማስቀመጥ፣ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትንና ልማትን በረጅም ጊዜ ዕቅድ በመምራት፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የማምጣት ዓላማን ለማሳካት ብሎም ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በግልፅ በማስቀመጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና የጋራ ብልጽግናን ለማስፈን ያስችላል።

ከፍጹም ድህነት ወደማይቀለበስ ብልጽግና የሚደረግ ሽግግር የአንድና ከዚያ በላይ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል። በዚህም መሠረት በአንድ ትውልድ ዕድሜ ብልጽግናን በርዕይ ደረጃ ማመላከት የሚቻል ሲሆን ስኬቱ በትክክለኛ ጎዳና መሆኑን ለማመላከት በቂ ጊዜ ያስፈልገዋል። በተለይም በልማት ሂደት ውስጥ የዓመት፣ የአምስት ዓመት እና የአስር ወይም አሥራ አምሥት ዓመታት ዕቅዶች በእነዚህ ጊዜያት ሊፈጸሙ እንደሚገባቸው ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው።

በዝቅተኛ የድህነት ምጣኔ፣ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጽ የገቢ አቅም፣ በከፍተኛ የሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ፣ በዘላቂ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ በዘላቂ የከተማ ልማት፣ በኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ በፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና በመሳሰሉ ጉዳዮች የሚገለጹ ጥቅል የልማት ግቦች በአጭር ጊዜ የሚረጋገጡ ስላልሆኑ ከአስር ዓመት በማያንስ የጊዜ ሰሌዳ ይመለከታሉ። የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችም በረጅም ጊዜ ዕቅዱ የተመለከቱትን ግቦች ለማሳካት የሚተገበሩ ዝርዝር ዕቅዶች ናቸው።

የልማት ሂደትን የሀብት መፍጠሪያ አቅም መገንባት፣ ሀብት መፍጠር እና ሀብት በፍትሐዊነት መከፋፈሉን ማረጋገጥ በሚሉ ሦስት ደረጃዎች መከፋፈል ይቻላል። የሀብት መፍጠሪያ አቅም በኢንቨስትመንት ይረጋገጣል፤ ሀብት በኢኮኖሚ ዕድገት ይፈጠራል፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በፖሊሲ እውን ይሆናል። የእነዚህ ሂደቶች ትግበራም የተለያየ ጊዜ ይወስዳል። በአንድ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ስለኢንቨስትመንትና ተያያዥ ጉዳዮች፣ ስለ ዝርዝር የዘርፎች ተግባር እና በፖሊሲ ደረጃም ስለ ጥቅል ኢኮኖሚ መረጋጋት ሊታቀድ ይችላል። በአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ስለ መሠረተልማቶች ግንባታና ስለ ፈጣን የመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊታቀድ ይችላል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ዘላቂ ልማት እና ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም መዋቅራዊ ለውጥ ከአስር ዓመት ባነሰ የጊዜ ሰሌዳ ማቀድ አይቻልም።

ከዚህ አንጻር አስርና ከዚያ በላይ ዓመታት የሚወስዱ የረጅም ዘመን ዕቅዶች አመላካችና አቅጣጫ ጠቋሚ ሲሆኑ የአምስት ዓመት ዓይነት የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች በረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ የተመለከቱ ዋና ዋና ግቦችን ለማስፈጸም የሚታቀዱ ዝርዝር ጉዳዮች ይሆናሉ። በአስር ዓመት ሊደረስባቸው የሚገባቸውንና የሚችሉትን ግቦች ግምት ውስጥ ያላስገባ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ በብዙ መልኩ ግቡን የሚያሳካ ዕቅድ ሊሆን አይችልም።

ይህን ጉዳይ በምሣሌ ለማስረዳት የቡና ልማት ችግኝ ከማፍላት እስከ ምርት ባለው ሂደት የአምስት ዓመት ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል። በአንድ ዓመት ውስጥ ሊታቀድ የሚችለው ችግኝ አፍልቶ ከመትከልና ችግኙ መጽደቁን ከማረጋገጥ አይዘልም። ቡና በመትከል ተጠቃሚነትን ግብ ላደረገ ገበሬ ግን ትልቁ ዕቅድ የአምሥት ዓመት ዕቅድ ይሆናል። ገበሬው ስለሚኖረው የቡና ምርት መጠን፣ የቡናው ምርት ተሸጦ ስለሚገኘው ገቢና በገቢው ስለሚሟሉ ፍላጎቶች ከአምሥት ዓመታት ባነሱ ጊዜያት እንደሚሟሉ አድርጎ ማቀድ አይቻለውም። ይልቁንም እነዚህ ግቦች በአምሥት ዓመት ዕቅድ ከተመለከቱ በኋላ ዝርዝር አፈጻጸሞች የአምሥት ዓመት ግቦችን መሠረት አድርገው በአንድ ዓመት ተመጥነው ይታቀዳሉ።

## 3.3 የአስር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪያት

የልማት ዕቅድ ዝግጅቱ የዘርፎችን ትስስር ያማከለ እንዲሆን መደረጉ፦ የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አንዱ መለያ የዘርፎችን ትስስር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ነው። የዘመናዊ ግብርናን፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪንና የማዕድን ዘርፎችን አንዱ ለሌላው ግብዓትና ፍላጎት በመሆን እንዲደጋገፉ የንግድና የሎጅስቲክስ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎችን በማሳለጥ ምርትን ከገበያ ጋር የማገናኘት ሚና እንዲወጡ በልማት ዕቅዱ ዝግጅት ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል። በተመሳሳይ መሠረተ ልማቶች (መንገድ፣ ኢነርጂ፣ መስኖ፣ ሌሎች የትራንስፖርት መንገዶች፣ መገናኛዎች) ለሌሎች ዘርፎች መልማት መሠረት እንዲሆኑ እንዲሁም የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ የምርታማነት ወሳኝ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው የሁሉንም ዘርፎች ልማት በሚያሳልጡበት አግባብ ታቅዷል።

የዘርፎች ትስስር ወሳኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ምርታማነት፣ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም እና ሌሎች ዘርፎችን የማነቃቃት አቅም ያላቸውና ለበርካታ ዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል መሠረት የሚሆኑ ዘርፎች በቀጣይ አስር ዓመታት የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ዘመናዊ ግብርና፣ የአምራች ኢንዱስትሪና የማዕድን ዘርፎች በአምራች ዘርፍነት የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን እነዚህ ዘርፎችም በግብዓትና በፍላጎት የእርስ በእርስና ውስጣዊ ትስስር በሚደጋገፉበት አኳያ ታቅደዋል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዱ ኢትዮጵያ ባላት የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች ምክንያት የቱሪዝም ዘርፍ ለአገልግሎት ዘርፎች መጠናከር እንዲሁም ለአምራች ዘርፎችና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ወሳኝ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በማስገኘት ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከግምት ያስገባ እንዲሆን ተደርጓል። በተመሳሳይ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጭ እንዲሁም የሰው ሀብት መገንቢያ ለማድረግ የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል። እነዚህን ዘርፎች ለማልማትም መሠረተልማቶች ቁልፍ ሚና ስለሚኖራቸው የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በአብዛኛው ከዘርፎች ትስስር ጋር የተቆራኙ ነው። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በዘርፍ ተቋማት እንደመሆኑ ተቋማቱ ስለዘርፎች የመልማት አቅም፣ መሠረታዊ ክፍተቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የተሻለ ግንዛቤ አላቸው። በመሆኑም የልማት ዕቅድ ከላይ ወደታች የሚወርድ ሳይሆን በዘርፎች ተሳትፎ እንዲታቀድ ተደርጓል።

አሳታፊና ሀገራዊ የልማት ማዕከላትን የለየ መሆኑ፦ በሀገሪቱ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የሚደረጉ የልማት ዕቅዶችን ከሀገራዊ የልማት ዕቅድ ጋር የሚያስተሳስር ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት መኖር ለልማት ዕቅዱ ውጤታማነት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በክልሎችና ከክልሎች በታች ባሉ የመንግሥት አካላት የልማት ዕቅድን የሚመራ አቅምና በቂ ፋይናንስ እንዲኖር ማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሠረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሠት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አካባቢዎች የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይልና አቅሞችን በአግባቡ በመጠቀም ለልማት ዕቅድ መሳካት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ሀገራዊ የልማት ዕቅዱና የክልል መንግስታት የልማት ዕቅዶች ያላቸውን የመልማት እምቅ አቅም በመቃኘትና በማጣጣም እንዲሁም ሀገራዊ የልማት ማዕከላትን በመለየት የመሠረተልማት ዝርጋታዎች ከተመረጡ የልማት ማዕከላት ጋር የተቀናጁበትን አግባብ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ተደርጓል።

የሥርዓታትን ድክመቶች እንደ ዋና ተግዳሮት በመውሰድ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የሚደረግበት አቅጣጫ መያዙ፦ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በመዋቅራዊ ለውጥ ረገድ ለተስተዋለው ዝቅተኛ አፈጻጸም አንዱና ዋናው ምክንያት የሥርዓታት ድክመት እንደሆነ ታምኖበታል። የተቋማት ዝቅተኛ የማስፈጸም አቅም፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መላላት፣ የተጠያቂነት አለመስፈን፣ በግሉ ዘርፍ ያልተገቡ ባሕርያት መታየትና ከመንግሥት ተቋማት ብልሹ አሠራሮች ጋር መቆራኘት፣ እንዲሁም ከሀገራዊ የጋራ ስምምነቶች ይልቅ የተናጠል ፍላጎቶች ልቀው መገኘትና ለሠላም መደፍረስ መንስኤ መሆን የሥርዓታት ድክመት መገለጫ ሆነዋል። የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እነዚህን ክፍተቶች ከግምት በማስገባት የሥርዓታት መሻሻልና ለውጥ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን የለየ ሲሆን በዚህም የተሻሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ እንደሚውሉ ታሳቢ አድርጓል።

ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተነድፎ ወደ ተግባር መገባቱና ለዚህ ዕቅድ እንደመነሻ መወሰዱ፦ የሥርዓታትን ጉድለቶች ለማቃናት እንዲሁም የተዛባውን ኢኮኖሚ ለማስተካከል ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተነድፎ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህም በማክሮ ኢኮኖሚ መስክ የመንግስትን የፋይናንስ አስተዳደር የሚያጠናክር፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን የሚያሳድግ፣ የዋጋ ግሽበትን የሚቆቆጣጠር፣ የፋይናንስ ዘርፉን የሚያዘመንና አካታችነቱን

የሚያረጋገጥ እንዲሁም ዋና ዋና የልማት ምንጭ የሆኑትን እና አዳዲስ የዕድገት ምንጭ ሆነው ለተለዩት ዘርፎች ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ በመሆኑ አሁን ያለውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዘባት በመቅረፍ ለቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት መደላድል ይሆናል። በመሆኑም በኢኮኖሚ ማሻሻያው የተመለከቱ የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ የትኩረት መስኮችና የመዋቅራዊ ማሻሻያ ሥልቶች ለአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እንደመነሻም ተወስደዋል።

የግሉ ዘርፍ ዋና የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተር መሆኑን መቀበል የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ ትብብር የሚያጠናክር መሆኑ፦ ባለፉት አሥራ አምሥት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ ነበር። የመንግሥት የልማት ስኬቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚና በማሕበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ የተንጸባረቁ ሲሆኑ ዋና የዕድገት ምንጮቹም ፍላጎትን የሚያበረታቱ እነዚህ ዘርፎች ነበሩ። ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት መረጋገጥ የሚችለው በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሲሆን በቀጣዮቹ አስር የልማት ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግሉ ዘርፍ በተለይም የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በወሳኝ አምራች ዘርፎች ላይ እንደሚሰማራ ትልቅ ተስፋ ተጥሏል። ይህ ዕቅድ ዳር እንዲደርስም የግሉ ዘርፍ የመንግሥትን የልማት አቅጣጫ እንዲረዳና በምክክር ሲዳብርም እንዲገዛው እና መንግሥትም የግሉ ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በተቀላጠፈ መንገድ እንዲፈታ የማድረግ ዓላማ ያለው ሲሆን በልማት ሂደቱ የመንግሥትና የግሉ ዘርፎች እውነተኛ ትብብር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚሆኑ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ፣ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ማዕቀፍ፣ ሀገራዊ የተቀናጀ የልማት ማዕቀፍ እና የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ማዕቀፍ እየተዘጋጁ መሆኑ እንዲሁም ዘመናዊና ዲጂታል የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋቱ የልማት ዕቅዱን ልዩ ያደርገዋል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ክፍል ሦስት

## የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ

## 2013-2022



# ምዕራፍ አንድ

## የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

# 1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች

የልማት ዕቅድ የተሳካ ይሆን ዘንድ ወደፊት ሊደረስበት የሚታሰበውን ደረጃ፣ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ፣ ወደፊት ሊከሠቱ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። ከዚህ አንጻር የሀገራችን ርዕይ፣ እየተተገበሩ ያሉ እና በቀጣይ ተግባራዊ የሚሆኑ ሀገራዊ እና የዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ በቅርቡ እየተካሄደ ያለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም፣ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችና በትግበራው ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች፣ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም ከባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችና ለውጦች በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊያሳድሩት የሚችሉ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች በልማት ዕቅዱ እንደ መነሻ ተወስደዋል። ዋና ዋና የዕቅዱ መነሻዎች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

## 1.1.1 ሀገራዊ የረጅም ጊዜ የልማት ርዕይ

የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ መነሻ ያደረገው ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ማድረግ ነው። በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚረጋገጥ ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ አንዱ የብልጽግና ምንጭ እንጂ በራሱ የብልጽግና መለኪያ አይሆንም። ብልጽግና በቁሳዊ፣ ሰብዓዊና ማህበራዊ መልካም እሴቶች የሚገለጹ የማይዳሰሱ ባህሎቻችንንና ሀብቶቻችንን በማነጽ በምንፈጥራቸው አቅሞች፤ አቅሞቹም በሚፈጥሯቸው ጥሪቶች የተገነቡ ሥርዓታት፤ ጥሪቶቹና ሥርዓታቱ በሚያሟሏቸው የሰው ልጅ ፍላጎቶችና መሻቶች፤ እንዲሁም እነዚህን ፍላጎቶችና መሻቶች በማሟላት ረገድ የሚገለጽ የተድላ፣ የዕርካታና የምልዑነት ደረጃ ነው። በዚህም መሠረት ብልጽግና፦

1. ዜጎች ፍላጎቶታቸውንና መሻቶቻቸውን የሚያሟሉባቸው በየደረጃው በፍትሐዊነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችሉ የገቢ አቅምና ጥሪቶች እንዲሁም እነዚህን ጸጋዎች ለመፍጠር በሚያግዙ ቁሳዊ፣ ሰብዓዊና ተቋማዊ አቅሞች፤
2. ዜጎች ያላቸውን እምቅ ችሎታ በሚገባ ተጠቅመው ጸጋዎችን በፍትሐዊነት መፍጠርና መቋደስ በሚያስችሉ እንደ ትምህርት፣ ጤናና ሌሎች አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነት፤
3. ሁሉም ዜጎች የኢኮኖሚ አቅማቸው ፈቀደም አልፈቀደም ለመኖር መሰረታዊ የሆኑትን እንደ ተመጣጣኝ ምግብ፣ መጠለያ፣ ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ መሰረታዊ የጤናና ትምህርት አገልግሎቶች ተጠቃሚነት እና
4. ዜጎች የተለያዩ ማህበራዊ ማንነቶች ሳይገድቧቸው በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም ተጽዕኖ በእኩል ተሳታፊነታቸው በጋራ በሚገነቡ አዎንታዊ ሥርዓታት ይገለጻል።

ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት የሚከናወኑ የልማት ተግባራትና የሚመዘገቡ የልማት ውጤቶች ወደዚህ ሀገራዊ ርዕይ በአስተማማኝ ደረጃ የሚያደርሱን መሆን አለባቸው። ከዚህ አኳያ የማህበረሰባችንን ብልጽግና ለማረጋገጥ በአንድ በኩል አብዛኛው ማሕበረሰባችን ከራሱ መልካም እሴቶች በመነሳት የልማት ጥግ አድርጎ የሚወስዳቸውን ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት በየደረጃው በተደረሰባቸው አቅሞች ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በማስፈን በሌላ በኩል ሌላው ዓለም የደረሰባቸውን የብልጽግና ጫፎች ከራሳችን አድማስ ባሻገር በማየትና ሌሎች የሄዱባቸውን ጠመዝማዛ መንገዶች በማረም እኩል የዓለም ዜጋ የሚያደርገንን ፍኖት በመቀየስ አማካይ ገቢን ብቻ ሳይሆን ብልጽግናን እናቅዳለን።

በጥቅሉ ብልጽግና የሰዎችን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችሉ አቅሞች፣ በውጤቱ በታዩ የኑሮ ደረጃ መሻሻሎችና በሰዎች የእርካታ ደረጃ አመለካከት ሊገለጽ ይችላል። ከዚህ አንጻር የነፍስ ወከፍ ገቢና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ደረጃ፣ አንድ ዜጋ በሕይወት የሚቆይበት አማካይ ዕድሜ እና በተለያዩ የኑሮ ደረጃ መስፈርቶች የፍትሕና የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የነጻነት ጉዳዮች ላይ ዜጎች ያላቸው የእርካታ ደረጃ በመለኪያነት ይወሰዳሉ። በዚህም መሠረት ለብልጽግና ደረጃ መለኪያነት ሦሥት ዋና ዋና አመልካቾች የተመረጡ ሲሆን እነዚህም፦

- የሰብዓዊ ልማት አመልካች (Human Development Index)፤
- የፈርጀ ብዙ ድህነት አመልካች (Multidimensional Poverty Index) እና
- ዜጎች በኑሮአቸው ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ (Perception of Wellbeing) ናቸው።

### 1.1.2 የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች


ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ዋና ዋና ዓላማዎች የታለመውን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ሀገራዊ የረጅም ጊዜ የልማት ርዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል።

1. የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት (pragmatic market based economic system) በመከተል የግል ዘርፉን ጉልህ ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የበለጸገች ሀገር መገንባት፤
2. የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፤
3. አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነት፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጐልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ (structural economic transformation) ማረጋገጥ፤
4. የማህበራዊ አካታችነትን የሚያረጋግጡና ሌሎች የመሠረተ ልማቶች ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
5. ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ እና
6. ሰላምና ፍትሕን የሚያረጋግጡ ጠንካራ ሥርዓታት በመገንባትና የሕግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማስከበር የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥ ናቸው።

## 1.2 የልማት ዕቅዱ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች

የልማት ዕቅዱ የተመረጡ ቁልፍ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (strategic pillars) ያሉት ሲሆን እነዚህም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እና የጋራ ብልጽግናን ማረጋጋጥ፣ የኢኮኖሚ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማረጋጋጥ፣ የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት፣ ዘላቂ የዕድገት እና የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ፣ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት ማረጋገጥ፣ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የሥርዓታት ለውጥን ማረጋገጥ፣ የልማት ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ አካታችነትን ማረጋገጥ፣ የፍትሕ ተደራሽነት እና ውጤታማ የሕዝብ አገልግሎት ማስፈን እና ዘላቂ የሰላም ግንባታና ጠንካራ ቀጠናዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ማረጋገጥ ናቸው።

ሥዕል 1.1፡ የአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎችና የትኩረት መስኮች




## 1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እና የጋራ ብልጽግና

በልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ከማስቀጠል ባለፈ ጥራት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል። ባለፉት ዓመታት ፈጣን ዕድገት የተመዘገበ ቢሆንም ሰፊ የሥራ ዕድልን ከመፍጠር፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ለውጥን ከማምጣትና በዘርፎች መካከል ሊኖር ከሚገባው ትስስር አንጻር ሲታይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ክፍተት ነበረበት። ምንም እንኳ ባለፉት ዓመታት የድህነት መጠንን መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ሰዓት ከ19 በመቶ በላይ የሚሆነው ዜጋ ከድህነት ወለል በታች እንደሚኖር ይገመታል። ከዚህም ባለፈ በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት፣ ሥራ አጥነትና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶች በመከሠታቸው የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት አጠራጣሪ ከማድረጉም በዘለለ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የኑሮ ጫና እያሳደረ ይገኛል። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመታት የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት ላይ ያተኮረ ነው ሲባል ዕድገቱ በኢኮኖሚው ውስጥ የተከሰቱ አንኳር ችግሮችን በማስተካከል እና የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚን በማስፈን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቱሩፋቶችን ለህብረተሠቡ ማበርከት ማለት ነው። ስለሆነም በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን

የሚያረጋግጥ፤ የግለሠቦችን የኑሮ ደረጃ ተጨባጭ በሚባል ሁኔታ የሚያሻሽል፤ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚቀንስ፤ የዋጋ ግሽበትን፣ ሥራ አጥነትንና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን የሚያስተካክልና በኢኮኖሚ ዘርፎች ጠንካራ ትስስር ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ ለውጥን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት።

ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ከፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማህበራዊ ቱሩፋቶች ለመቋደስ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭን ማስተካከል ወሳኝ ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት ፍላጎትን (aggergate demand) በሚያበረታቱና ፍላጎትን ማዕከል በማድረግ በሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ሊመጣ ይችላል። ነገር ግን ፍላጎት ላይ ያተኮረ ዕድገት በአግባቡ ካልተመራ ዘላቂ ካለመሆኑም በላይ የተራዘመ የዋጋ ግሽበትን፣ ሥራ አጥነትን፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረትንና አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን ሊያመጣ ይችላል። ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥም ፍላጎትን በሚያበረታቱ ዘርፎች ላይ ትኩረት በመደረጉ የተለያዩ የኢኮኖሚ ችግሮች እንዲከሰቱ አድርጓል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ልዩ ትኩረት የተሰጠው የዕድገቱ ምንጭ በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው። ይህም አቅጣጫ ምርትን በማሳደግ የዋጋ ግሽበቱን ከመቆጣጠር በተጨማሪ በዘርፎች መካከል የሚደረግን የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስርን (backward and forward linkages) በማጠናከር የኢኮኖሚ ምህዳሩን በማስፋት፤ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ በመቀነስ ፍትሐዊ የልማት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያስችላል። በተጨማሪም በሀገር ውስጥ በዘርፎች መካከል የሚኖርን ትስስር በማጠናከር የሀገር ውስጥ ምርትን በግብዓትነት በመጠቀም፣ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎትን በመቀነስ፣ ምርታማነትን በማሻሻል የወጪ ንግድን በማጎልበት ዘላቂ የሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማረጋገጥ ታቅዷል።

ጥራት ያለው ዕድገት የሚኖረው ጤናማ የሆነና ተወዳዳሪነትን ማዕከል ያደረገ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ሲኖር ነው። በዚህም ኢኮኖሚው ጥራት ያለው የሥራ ዕድል (decent job) በመፍጠር ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል። በዚህ ዕቅድ የኢኮኖሚ ዕድገቱን መሠረተ ሰፊ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የዕድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታሳቢ ተደርጓል። ይህም የዘላቂ ልማት አጀንዳ ዋና መርህ ከሆነው “ዘላቂ ልማት ለሁሉም” (leaving no one behind) ጋር የተጣጣመ ነው።

## 2. የኢኮኖሚ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት

ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ብሎም የጋራ ብልጽግና ሊረጋገጥ የሚችለው ምርታማነትን በማሳደግ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ሲቻል ነው። ምርታማነት ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ በምርት ሰንሰለቱ ላይ አግባብነት ያለውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የግብዓት ብክነትንና ወጪን በመቀነስ እንዲሁም የማምረት አቅምን (production potential) አሟጥጦ በመጠቀም ነው። በተጨማሪም በኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር በማቀላጠፍና በማጥበቅ በምርት ሰንሰለቱ ላይ ምርታማነትን ከጥራት ጋር በማዋሃድ ተወዳዳሪነትን በጠንካራ መሠረት ላይ መጣል ያስፈልጋል።

በሀገራችን አጠቃላይ ኢኮኖሚው በተለይም የአምራች ዘርፍ ያለበት የምርታማነት እና የተወዳዳሪነት ደረጃ በብዙ መለኪያዎች ሲታይ ዝቅተኛ የሚባል ነው። ይህም በመሆኑ የአምራች ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ መሆን ካለመቻሉም በተጨማሪ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ መሰል ምርቶች ጋር ተወዳዳሪ መሆን አልቻለም። ኢኮኖሚው አመርቂ የሚባል መዋቅራዊ ለውጥ እና የምርታማነት ዕድገትን ባለማምጣቱ ሀገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ሸቀጦች በአብዛኛው እሴት ያልተጨመረባቸው የግብርና ምርቶች ናቸው። በዓለም ንግድ ሥርዓት ውስጥ ዋና ተዋናይ ለመሆን ምርታማነትን ማሳደግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። በመሆኑም

የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ በበዓለም አቀፍ የንግድ እሴት  ሰንሰለት ውስጥ በበቂ ደረጃ ለመሳተፍ በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ደረጃ፣ በተለይም የአምራች ዘርፎች ቅልጥፍናን በመጨመር እንዲሁም ብክነትን በማስወገድ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ የልማት ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው። ከዚህ አንጻር የግልና የመንግስት ዘርፍ ተናቦ መሥራት፣ መሠረተ ልማትን በጥራትና በመጠን ማቅረብ፣ በአጠቃላይ ኢኮኖሚውና በተለይም የአምራች ዘርፎች የሚፈልጉትን የሰው ኃይል ግብዓት ማቅረብ፣ ፈጠራን ማዕከል ያደረገ የአመራረት ዘዴን መከተል፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን ማረጋገጥ፣ በዘርፎች መካከል የሚኖር ትስስርን ጥራት ማዕከል ባደረገ መልኩ ማጠናከር ያስፈልጋል።

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ የቻሉ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው ቴክኖሎጂ እና ምርምር ለምርታማነት ወሳኝ ድርሻ አላቸው። የቴክኖሎጂ ለውጥ የሚመጣው በየዘርፉ ቀጣይነት ያለውን ምርምር በማድረግ የዘርፎችን ችግር መፍታት ሲቻል ነው። ከዚህ አንጻር ምርታማነትን ለማስቀጠል የቴክኖሎጂ ለውጥ ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት። በመሆኑም የዘርፎችን የቴክኖሎጂ ፍላጎት በማጤን ለምርታማነት ማደግ ጉልህ ሚና የሚኖረው የቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዲኖር ይሠራል። ለዚህም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ ቀጣይነት ያለውን የቴክኖሎጂ ለውጥ በማምጣት ምርታማነትን ማሳደግ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

የአምራች ዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ጥራት ያለው የሰው ኃይል ያስፈልጋል። እንዲሁም የእያንዳንዱን ዘርፍ ምርታማነት ለማረጋገጥ ከዘርፉ ጋር የተጣጣመ የሰው ኃይል ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ አቅርቦት ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የዘርፎች የሰው ኃይል አይነትና መጠን ከኢኮኖሚው ባህሪ ጋር የሚቀያየር በመሆኑ ዕቅዱ ይህን ታሳቢ በማድረግ የየዘርፉ የሰው ኃይል ፍላጎት የሚቀርብበትን ሁኔታ ይመቻቻል። በዚህም የትምህርት ዘርፉ የሚያቀርበውን የሰው ኃይል ከአምራችና ሌሎች ዘርፎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከሰተውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን ከማስወገዱ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ዘላቂ ምርታማነትን በማሳደግ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል።

የመሠረተ ልማት መስፋፋት ጥራትን በመጠበቅና በዋጋ ተወዳዳሪ በመሆን ምርታማነትን ለማሳደግና ተወዳዳሪ ለመሆን አዎንታዊ ሚና አለው።  ባለፉት ዓመታት የመሠረተ ልማት አቅርቦትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የኢኮኖሚ ትስስርን ከመፍጠርና የተቀላጠፈ የገበያ ትስስርን ከማረጋገጥ እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅምን በአግባቡ ከመጠቀም አኳያ ክፍተቶች ታይተዋል። ይህንን ከግምት በማስገባት በዕቅዱ ዘመን የመሠረተ ልማት አቅርቦት ከዕድገት ማዕከሎች (growth corridors) ጋር እንዲቆራኝና አቅርቦቱ እንዲያድግ የሚደረግ ይሆናል። በመሆኑም እያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ለዕድገት ማዕከል የሚያስፈልገውን መሠረተ ልማት በማቅረብ ምርታማነትን እንዲያሳድግና ተወዳዳሪነትን እንዲያበረታታ ማድረግ ይቻላል። በአጠቃላይ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዕድገት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ የዋጋ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥና ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ለማሳደግ ትልቅ ፋይዳ ስላለው የመንገድ፣ የባቡር፣ የደረቅ ወደብ፣ የአየር ትራንስፖርት፣ የኢነርጂ፣ የቴሌኮም፣ የውኃና የመስኖ ሥራዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲስፋፉ ይደረጋል።

በተጨማሪም ምርታማነትንና ተወዳደሪነትን ለማሳደግ ለኢኮኖሚው ዘርፍ የሚሰጠው ማበረታቻና ድጋፍ ኢንዱስትሪዎች በሚያስመዘግቡት የወጪ ንግድ አፈጻጸምና በሚፈጥሩት የሥራ ዕድል የሚወሰን ይሆናል። በመሆኑም በቀጣይ ለየዘርፎቹ የሚሰጡ ድጋፎችና ማበረታቻዎች አዎንታዊ አፈጻጸምን መሠረት ያደረጉ ይሆናሉ።

## 3. የቴክኖሎጂ አቅም እና የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ

ኋላቀርነትን በማስወገድ ከበለጸጉ ሀገሮች ተርታ ለመድረስና እኩል የዓለም ዜጋ ለመሆን አቋራጩ መንገድ በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ማሳደግ ነው። ከዚህ አኳያ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ከቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አድማስ በራቀ ሀገር ቴክኖሎጂን በመማር፣ በማሻሻልና በማምረት ብልጽግናን ዕውን ማድረግ እንደሚቻል የሀገሮች ተሞክሮ ያሳያል። በተለይም ከቴክኖሎጂ ዘርፍ ውስጥ የአይሲቲ ዘርፍ ሌሎችን ዘርፎች በማሳለጥ እንደመሠረተ ልማት እንዲሁም በራሱ እንደ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጣሪነቱና እንደ ሰው ሀብት መገንቢያ ዘርፍነቱ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል።

ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማልማትና ተደራሽነትን ማስፋት እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ ጉልበትን መሠረት ካደረገ የአመራረት ዘዴ በሂደት የቴክኖሎጂን ፈጣን ተለዋዋጭነት ታሳቢ ያደረገ የግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መሠረትን የመጣል፣ ቴክኖሎጂና ዕውቀት አከል የአገልግሎት ዘርፍ ኢኮኖሚን መገንባትና የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ይገባል።

## 4. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ

አንድ የልማት ዕቅድ ስኬታማነቱ የሚወሰነው በዕቅዱ ርዕይ፣ አዘገጃጀት፣ የግብ አመራረጥ እንዲሁም መንግስት ዕቅዱን ለመተግበር ባለው ቁርጠኝነት ብቻ ሳይሆን ዕቅዱን ለመፈጸም የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅርቦት መኖርና የተገኘውን ፋይናንስ በአግባቡ ለመጠቀም ሊወሰዱ በታቀዱ ፖሊሲዎች ጥራት ነው። ዕቅዱን ማዘጋጀት ከፍላጎት አንጻር የሚታይ ሲሆን ዕቅዱን ለማከናወን የሚያስፈልገው ዘላቂ ፋይናንስና ከፋይናንስ ጋር የተያያዘው ጉዳይ ከአቅርቦት አኳያ የሚታይ ነው። ዘላቂ ፋይናንስ ሲባል የሚሰበሰበው ፋይናንስ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን ለማስፈን ማስቻልና በዕቅዱ የተያዘውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚያስፈልገውን ኢንቨስትመንት ፋይናንስ ሊያደርግ የሚችል የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማረጋገጥ፣ የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ፣ የፋይናንስ ምርታማነትን ማሻሻልና የውጭ ዕዳ ጫና በዓለም አቀፍ መመዘኛ ሲለካ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ እንዲሆን ማድረግ ነው።

በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ከተስተዋለው የልማት ፋይናንስ ዕጥረት በላይ በልማት ፕሮጀክቶች መጓተት እንዲሁም ብልሹ አሠራሮች ምክንያት የተከሰተው ብክነትና ከዚህ ጋር የተያያዘው ዝቅተኛ የካፒታል ምርታማነት ከፍተኛ ነበር። በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ቁጠባ እና የውጭ ምንዛሪ ቁልፍ የፋይናንስ ምንጭ ናቸው። በመሆኑም ለልማት የሚውሉ ከፍተኛ የካፒታል ገቢ ዕቃዎችን ከውጭ ለማስገባት የሀገር ውስጥ የልማት ፋይናንስን ለማሳደግ ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሪ አቅሞች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል። ለዚህም ሀገራዊ የፋይናንስ አቅምን በውጭ ምንዛሪ አቅምና በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ማገዝ ይገባል።

የግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች የድርጅቶችና ኮርፖሬቶች ቁጠባ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ገቢ ለሀገር ውስጥ ፋይናንስ ወሳኝ ምንጮች ናቸው። የግለሰቦች ወይም የቤተሰቦች ቁጠባ ከሀገራዊ ምርት የ33 በመቶ ድርሻ ባለው የግብርናው ዘርፍ የሚኖረው ማሕበረሰብ ቁጠባን በሰብልና በቁም እንስሳት የሚይዝ በመሆኑና በአብዛኛው ከፍጆታ ስለማይወጣ ለልማት ያለው ፋይዳ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። በመሆኑም በቀጣይ የልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን ባንኮችና የአነስተኛ ቁጠባ ተቋማት የፋይናንስ ተደራሽነታውን በገጠርና ከተማ በማሳደግ የማህበረሰቡን የቁጠባ ባህል እንዲያበረታቱ ይደረጋል። በተጨማሪም የንግድ ድርጅቶችና

የፋይናንስ ተቋማትን ጨምሮ ኮረፖርቶች የሚያገኙትን ከፍተኛ ትርፍ ምርታማነትን በሚያሳድጉ አምራች ዘርፎች ላይ በመዋዕለ ንዋይ መልክ በማፍሰስ በዘርፎች ትስስር መዋቅራዊ ሽግግርን ያረጋገጠ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ እንዲወጡ ጥረት ይደረጋል። የግል የፋይናንስ ተቋማት ትርፋማነታቸው ረጅም ጊዜ ለሚጠይቅ የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ዘርፎች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

የፋይናንስ ፍላጎትን ለማሟላት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሌላው ዘርፍ የሀገር ውስጥ ገቢ ነው። መንግሥት ሀገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ ተግባራዊ ለሚያደርጋቸው ከፍተኛ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ድህነትን ለመቅረፍ በምግብ ዋስትና፣ በንጹህ ውኃ አቅርቦት፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በገጠር መንገድ ግንባታና በመሳሰሉት ለሚያወጣቸው ወጪዎች መሸፈኛ አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ የሀገር ውስጥ ገቢ ነው። ከሀገር ውስጥ ገቢ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ታክስ ከሀገራዊ ምርታችን በመቶኛ ሲሰላ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በጣም አነስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለዝቅተኛ የታክስ ምጣኔ አንዱ መሠረታዊ ምክንያት የኢኮኖሚው መዋቅር ነው። ለኢኮኖሚው የ33 በመቶ አስተዋጽዖ የሚያደርገው ግብርና በገጠር መሬት መጠቀሚያ ግብርና በገቢ ግብር የሚያመነጨው ገቢ አነስተኛ ነው። ማኑፋክቸሪንግም ገና ያልዳበረ በመሆኑ ከዚህም የሚሰበሰበው ታክስ የጎላ አይደለም። በፌዴራል ደረጃ ከሚሰበሰበው ታክስ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ከገቢ ንግድ ታሪፍ የሚሰበሰበውና በአብዛኛው በገቢ ዕቃዎች ላይ ከተመሠረተው የተዘዋዋሪ ታክስ ነው። ይህም መዋቅር ዘላቂ ያልሆነና የሀገር ውስጥ ገቢን ሳይቀር በውጭ ምንዛሪ አቅም ላይ እንዲንጠለጠል አድርጎታል። የኢኮኖሚ መዋቅሩ በሀገር ውስጥ ገቢ ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ በታክስ ሥርዓት መዛባትና በተለይም በታክስ ሥርዓት አለመዘመን ምክንያት ኢኮኖሚው አሁን ባለው አወቃቀር ማመንጨት የሚገባውን የታክስ ገቢ እያስገኘ እንዳልሆነ ይታመናል። በሀገር ውስጥ ገቢ ረገድ ለተስተዋለው ዝቅተኛ የታክስ ገቢ አፈጻጸም ዝቅተኛ የታክስ መሠረት፣ ለታክስ ሕግ ተገዥነት ዝቅተኛ መሆን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ውስንነት እንዲሁም የሰው ሃብት ብቃት ማነስና አርኪ ያልሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ዋና ምክንያቶች ናቸው። በመሆኑም በቀጣዮቹ አስር ዓመታት አስፈላጊ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያዎች ከማድረግ በተጨማሪም ታክስ በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማሳደግ፤ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓትን መገንባት፤ ኮንትሮባንድ፤ ታክስ ማጭበርበርና ኢ-መደበኛ ኢኮኖሚን ወደ ታክስ ሥርዓት ማምጣት፤ ምቹ የሥራ ከባቢ፣ ብቁ፣ ተነሳሽነት ያለውና ታማኝ የሆነ አመራርና ሠራተኛን መፍጠር የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ የሚተገበሩ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የፋይናንስ አቅሞችን ከጊዜያዊነት ይልቅ ዘላቂና ጥራት ወዳላቸው ምንጮች ማሸጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፋይናንስ የሚደረጉ የልማት መስኮችን ፋይዳ በአግባቡ መለየት እንዲሁም ብክነትን መቀነስና ቅልጥፍናን ማሳደግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

## 5. የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት

የኢኮኖሚ ዕድገትን ዘላቂ ለማድረግ በየዘርፉ የተሰማራው የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሊበረታታ ይገባል። አስፈላጊነት በጥናት ያልተረጋገጠ ከፍተኛ የመንግስት ሚና በኢኮኖሚ ውስጥ መኖር የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ከመፍጠሩም በተጨማሪ ብልሹ አሠራርን በማስፈን ለሀብት ብክነትና ለዝቅተኛ ምርታማነት ይዳርጋል። ይህንንም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለፉት ዓመታት ማየት ተችሏል። በመሆኑም ይህን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቀጣይነትና ጥራት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የግሉ ዘርፍ ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወትና የላቀ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ የዕቅዱ ልዩ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ይተገበራል። ሆኖም መንግስት የግሉ ዘርፍ ተወዳዳሪና የኢኮኖሚ ችግሮችን ፈቺ እንዲሆን የተለያዩ ማበረታቻዎችንና ለዕድገት ወሳኝ የሆኑ የመሠረተ ልማት ግብዓቶችን በማቅረብ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣን፣ ዘላቂና ጥራት ያለው

እንዲሆን ጉልህ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም በዕቅዱ የትግበራ ዘመን ጥራት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት መስመር በመከተል የግሉን ዘርፍ በማጎልበትና የመንግስትን ሚና ከግሉ ዘርፍ ጋር በማስተሣሠር የሀገሪቱን ብልጽግና እውን ለማድረግ እንደ አቅጣጫ ተይዟል። በዚህም የግሉ ዘርፍ ዋና የዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆንና በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት፣ በኢንቨስትመንት፣ በሥራ ሥምሪት፣ በውጭ ንግድና በቴክኖሎጂ ሽግግር ጉልህ ሚና እንዲኖረውና ብልጽግናን እንዲያረጋግጥ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል።

ባለፉት ዓመታት የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው ተሳትፎ አዎንታዊ ለውጥ ቢያሳይም በማኑፋክቸሪንግና በዘመናዊ ግብርና ውስጥ የነበረው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር። ለዚህም የግሉ ዘርፍ ያለበት መሠረት ጠባብ መሆኑና የቢዝነስ ተዋናዮች ከለመዱት የቢዝነስ አስተሳሰብና አስተዳደር ውጪ ለዕድገት መሠረት የሆኑና ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ዘመናዊ የቢዝነስ አስተሳሰብና አመራር ለመቅሰምም ሆነ የተሻለ አማራጮችን ለማየት የኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎታቸውን ለማበልጸግ የሚያሳዩት ዝንባሌ ዝቅተኛ መሆኑ አሉታዊ አስተዋጽዖ አድርጓል። በተጨማሪም መንግሥት ለግሉ ዘርፍ የሚያቀርበው አገልግሎት የተሟላና የተቀላጠፈ አለመሆኑ፣ የመንግሥት ኩባንያዎች ከግሉ ዘርፍ በተሻለ ሁኔታ የመንግሥት ድጋፍና አገልግሎት ማግኘታቸው፣ በገበያ ውስጥ የመንግሥትና የሥርዓት ጉድለት በስፋት መታየቱ፣ በጋራ ቢዝነስ የመሥራት ልምድ አናሳ መሆንና የሕጎችና አሠራሮች አለመሻሻል የግሉ ዘርፍ በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት እንዳያድግ አድርጎታል።

በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመታት ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ የተያዘውን ርዕይ ዕውን ከማድረግ አኳያ የግሉ ዘርፍ ወደ ላቀ የዕድገት ምዕራፍ እንዲሸጋገር ይደረጋል። ከዚህ አንጻር የግሉ ዘርፍ አሁን ያለበትን የአቅምና የአመለካከት ችግር በመቅረፍ እንዲሁም የወደፊቱን እንቅስቃሴ የሚገቱ ማነቆዎችንና ከመንግሥት የሚያስፈልጉ ድጋፎችን በመለየት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በወሳኝ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል። በተጨማሪም ጥራት ያለው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በማበረታታትና የመሠረተ ልማት አቅርቦትንና ጥራትን በማሳደግ ኢትዮጵያ ለግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ዝግጁ መሆኗ ይረጋገጣል። በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከሚስተዋሉት ማነቆዎች በላይ መሠረታዊው ችግር ዘርፉ ለሀገራችን የረጅም ጊዜ ባህል ባለመሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻችንን ወደ ‹ኢንዱስትሪያሊስትነት› ደረጃ ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል። ለዚህም የቴክኖሎጂ ሽግግር ወሳኝ ነው።

በተጨማሪም መንግስት የግሉ ዘርፍ በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ጉልህ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ የፖሊሲ፣ የአስተዳደርና የተቋም ማሻሻያና ማበረታቻዎች በማድረግ ለግሉ ዘርፍ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር አቅጣጫ ይዞ ይሠራል። የግሉን ዘርፍ ልማት የሚያሳልጥ የግሉ ዘርፍ የልማት ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ ይደረጋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር የሚያስችል ሁኔታን በመፍጠር፣ የኢንቨስትመንት አዋጁን በየወቅቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና የአሠራር ማነቆዎችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በማሻሻል፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ ፖሊሲን በማሻሻል፤ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደርንና የገቢና የወጪ ንግድ ሥርዓትን ግልፅና ቀልጣፋ በማድረግ የግሉን ክፍል ኢኮኖሚ ተሳትፎ የማጎልበት ሥራ ይሠራል።

## 6 . ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚ

የሀገራችን ኢኮኖሚ ለሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ስጋትና ክስተት ተጋላጭነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በልማት ዕቅዱ ዘመን ሊከሰቱ የሚችሉ የሰው ሠራሽና የተፈጥሯዊ አደጋዎችን በመለየት፣ በመተንበይና በመተንተን የዕቅዱ አካል ማድረግ ያስፈልጋል። የአየር ንብረት ለውጥ የዝናብን መጠን በማዛባት የግብርና ዘርፉን ከመጉዳቱም በተጨማሪ የውኃ መጠንን በመቀነስ በኃይል አቅርቦትና በመስኖ እርሻ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥና የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንዲከሠቱ

ያደርጋል። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በድርቅና ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ በሚገለፅ የአየር ንብረት ለውጥ ተገላጭ ሆና ቆይታለች። ስለሆነም ዘላቂነት ያለው፣ ፍትሐዊና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት ወሳኝ ነው። ከዚህ አንጻር በልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን የአካባቢ መራቆቶችን በመለየት የተፋሰስ ልማት ሥራ በማጠናከር በረሃማነትን መከላከልና በበረሃማነት፣ በድርቅና በጎርፍ፣ የተጎዱትን ጨምሮ የተራቆቱ መሬቶችን እና አፈርን ወደ ነበረበት መመለስና ከአከባቢ መራቆት ነጻ የሆነች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። ዘላቂ የፍጆታና የአመራረት ስልቶችን ማረጋገጥ፣ ደንን መጠበቅና ማልማት፣ የከባቢ ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀትን በመቀነስ ለምግብ ዋስትናና ለአርሶና አርብቶ አደሩ ገቢ መሻሻል በሚረዳ ሁኔታ የሰብልና የእንስሳት ምርትን ማሻሻል፣ ከታዳሽ የኃይል ምንጭ የኤሌክትሪክ ኃይልን በሠፊው በማመንጨት ለሀገር ውስጥና ለቀጠናው ገበያ ማቅረብና ዘመናዊና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በትራንስፖርት፣ በኢንዱስትሪና በሕንጻ ኮንስትራክሽን ዘርፎች መጠቀም የተለየ ትኩረት የሚሠጣቸው ይሆናሉ። በተመሳሳይ ሀይቆችንና ወንዞችን ከተለያዩ ብክነቶች ለመከላከልና በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ፣ ዳርቻዎችን ስርዓተ ምህዳሮችን በዘላቂነት ለመያዝና ለመጠበቅ፣ ጤናማና ምርታማ ሀይቆችንና ወንዞችን እውን ለማድረግና ወደ ነበሩበት ለመመለስ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የሀገሪቷ ተፋሰሶች በወጣላቸው የልማት ዕቅድ መሠረት እንዲተዳደሩና እንዲለሙ ይደረጋል።

ለማንኛውም አደጋ ጊዜ ምላሽ የመስጠት አቅምን በመገንባት፣ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራዎችን በህብረተሰቡ ዘንድ ማስረፅ፣ ለአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ተግባራት የሚውል ሃብትን ማሰባሰብና ለተግባራቱም የሚውልበትን አደረጃጀት መፍጠር እንዲሁም ለአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የሚውሉ የተለያዩ ተቋማትንና መሳሪያዎችን ወቅቱ ከሚፈልገው የአደጋ ክስተት አኳያ በማሟላት ለአደጋ ተጋላጭ ያልሆነችና አደጋም ቢከሰት የተሻለ የመቋቋም አቅም ያላት ሀገር ለመገንባት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። የሚከናወኑ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ተግባራት ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ስምምነት ከገባንባቸው መርሆች ጋር ተዛማጅነት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ለአደጋ ምላሽ የሚሆን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ የክምችት አቅምን ስትራቴጂክ በሆኑ ቦታዎች በበቂ መጠን ማከማቸት፣ የተሟላ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማስቻል፣ ወሰን ተሻጋሪ አደጋዎችን ለመቆጣጠር፣ ለመከላከልና ጉዳትን ለመቀነስ የሚያስችል ስልቶችን መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸው ሥራዎች ይሆናሉ።

በተጨማሪም በአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ በመረዳዳት፣ በመቻቻልና በአብሮነት ዙሪያ ያሉ እሴቶችን በማጎልበትና በመጠቀም ለሚከሰት አደጋ በጥናት የተደገፈ ሀገር በቀል መፍትሄ በማፍለቅ ለአደጋ አይበገሬነትን ማሳደግ፣ የአደጋ ጊዜ ጥሪ የማድረግ ሥልጣንን እስከ ታችኛው አስፈጻሚ አካል መወሰን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንዲሁም የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ተቋማትን ከፌዴራል እስከ ዝቅተኛው አስፈጻሚ አካል ቴክኒካዊ ብቃቱ እንዲጎለብት ይደረጋል። ለአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ደጋፊ የሆኑ የአሠራር ልማዶችን፣ ኃላፊነቶችንና የሀብት ምንጮችን በመለየትና በማጠናከር ውጤታማ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርን ማሳደግ፣ በጎ ፈቃደኞችን በማሰልጠን በአደጋ ወቅት ትብብር የሚያደርጉበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ሁሉን አቀፍ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ተግባራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ በተደጋጋሚ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች የእያንዳንዱን አካባቢ ልዩ ባህሪይ ያገናዘበ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስልቶችን ነድፎ መሥራትና ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰቦች አካባቢን በጥናት በመለየትና ከሌሎች የልማት አካላት ጋር በማቀናጀት ከአደጋ በፊት አማራጭ መተዳደሪያ እንዲኖራቸው ለማስቻል ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።

## 7. የሥርዓታት ለውጥ

ሥርዓታት የሕብረተሰብን አመለካከት፤ የመንግሥትን ሚና፣ የማሕበረሰብን ግንኙነቶች፤ የመንግሥትንና የሕብረተሰብን መሥተጋብሮች የሚዳኙ ተቋማት፥ በተቋማቱ የሚወጡ ገዢ ሕጎች፤ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች እና የባሕልና የዕምነት ሕግጋትን እንዲሁም የፖለቲካ ሥርዓትን የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። ከእነዚህ መስተጋብሮች የሚመነጩ የሰብዓዊ መብቶች፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰላም፣ ፍትሕና ነፃነት በራሳቸው ትልቅ ግቦችና የብልጽግና አምዶች ሲሆኑ እንደ ገቢና ጥሪት እንዲሁም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ለመሳሰሉ የብልጽግና መለኪያዎች ግብዓት ናቸው። በተመሳሳይም መልካም አስተዳደር፣ ሰላም፣ ፍትሕና ነጻነት የሚያስገኙ የማህበረሰብ መልካም እሴቶች፣ የመንግሥት ተቋማት፤ የማሕበረሰብ ተቋማትና ገዢ ሕጎች፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ለሌሎች የልማት አቅሞች መሟላት መሠረት ናቸው።

በዚህም መሠረት በመንግሥትና ማሕበረሰብ እንዲሁም በፖለቲካ ልሂቃን መካከል በዴሞክራሲያዊ አግባብ የሚፈጠሩ ስምምነቶችና የመንግሥት ቅቡልነት ለልማት መሠረት ለሆኑት ሰላም መስፈን፣ የማሕበረሰብ ትጋት፣ በመንግሥት ተቋማት በተለይም የሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ለሚፈጠር የአገልጋይነት መንፈስና ትጋት ትልቅ አቅም ይፈጥራሉ።

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚደረጉ ትብብሮች በገበያ መር መርህ የሚገነባ ጠንካራ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንዲረጋገጥ ያግዛሉ። ከዚህ አንጻር የመንግሥት ሚና የሀገራቱን የልማት ጥረቶች ለማፋጠን የሚያስችል የተለየ የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ መዋቅር መፍጠር የሚያስችል የፖለቲካና ኢኮኖሚ ቅንጅት ማስፈን፤ በቀን ተቀን የፖለቲካ ጉዳዮች ያልተጠመደ፤ በግሉ ዘርፍ መደለያዎች ያልተበገረ፤ ግን ደግሞ የምርታማነትና የተወዳዳሪነት ግቦችን ለማሳካት ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚተባበር፤ እንዲሁም በልማት ውስጥ የወሳኝ ተዋናዮችን መስተጋብር የሚያሳልጥ በተወዳዳሪነት መርህ በተመረጡ ባለሙያዎች የተሞላ ቢሮክራሲ እንዲኖር ማድረግ ነው። በተጨማሪም ሲቪል ሰርቪሱን ለማትጋት የሚያምንበትና በካርዱ የመረጠው መንግሥት መኖሩን ከማረጋገጥ ባሻገር የትምህርት ዝግጁነትን፣ ክህሎትንና ትጋትን የሚያበረታታ ነገር ግን አጉዳይነትን፣ ሌብነትንና ስንፍናን ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት ማስፈን ተገቢ ነው።

የትምህርት ተቋሞቻችን ከልጅነት ጀምሮ የመልካም ዜጋ መፍለቂያ እንዲሆኑ ከቤተሰብ፣ ከማህበረሰብና ከመምህራን ጋር የተቀናጀ ጥረት ማድረግና ትምህርትን መሸለም ታሳቢ ይደረጋል። ቤተሰብን፣ የማሕበረሰብ መሪዎችንና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር የዕምነት ተቋሞቻችንና አስተምህሮቶቻቸው ከድህነት ለመላቀቅ ለምናደርገው ጥረት ምርኩዝና ተስፋ እንጂ የስንፍናችን መደበቂያ እንዳይሆኑ በጋራ ይመከራል። ሲቪክ ማህበራት ለሀገርና ሥርዓታት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። የመንግሥትንና ሕብረተሰብን እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎችና በሌሎች ተቋማት ያሉ ግንኙነቶችን የሚበይኑት ግለሰቦች ወይም አውራ የፖለቲካ ተቋማት ሳይሆኑ በጋራና በስምምነት የምናቆማቸው ሥርዓታት ይሆናሉ።

## 8. የሴቶች ተሳትፎ እና ማህበራዊ አካታችነት

በልማት ዕቅዱ ዘመን የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥና የግለሠቦችን የኑሮ ደረጃ በተጨባጭ የሚያሻሽልና ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚቀንስ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት በልማት ተጠቃሚነት ወደኋላ የቀሩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ክልሎች ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት

ያስፈልጋል። በመሆኑም የሴቶችን፣ ህፃናትና ወጣቶችን ጉዳይ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች እንዲካተት በማድረግ፣ በማሕበረሰቡ አመለካከት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በዘላቂነት በማስረፅ ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን ሴቶችና ወጣቶች በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ያላቸውን ሚና እንዲወጡና አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠርላቸዋል። በተጨማሪም የሴቶችንና ህፃናትን ጥበቃ ሥርዓት በማጠናከር ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን ማስጠበቅ፣ መብታቸውን ማስከበር፣ ሴቶችንና ወጣቶችን በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ፍትሐዊ ተሳትፎና ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።

በተመሳሳይ በማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተለዩ የልማታዊ ሴፍቲኔት፣ የማህበራዊ መድንና የሥራ ዕድል ማስፋፋት እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎችም የሕግ ጥበቃ እና ድጋፍ ይደረጋል። የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት አካታችነትና እና ተደራሽነትን ማሻሻል ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋዊያንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አካታችነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ  ስምምነቶችና ሀገር በቀል የአሠራር ስልቶች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የጎዳና ተዳዳሪነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራት ተፈጻሚ ይደረጋሉ።

የአርብቶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ ማዕከል ያደረገ የመሠረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎቶትን አቅርቦት በማስፋፋት የማህብረሰቡ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ማድረግ ትኩረት ይሰጠዋል። በተለይ የሰውና እንስሳት የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ማሳደግ፣ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ልማት ማስፋፋት፣ የውኃና አማራጭ ኢነርጂ ኃይል ልማት ማስፋፋትና ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫ ናቸው። ምርታማነትን ለማሳደግ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ግብዓቶችን በማቅረብ በአንድ አካባቢ ተሞክረው ውጤት ያመጡ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሁሉም ተጠቃሚዎችና አካባቢዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል። በተጨማሪም የህብረተሰቡን አቅም በመገንባትና ተሳትፎውን በማሳደግ የልማት ሥራዎችን በባለቤትነት መንፈስ መፈጸም እንዲችል ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። የግል ባለሃብቱን በማበረታታት እንዳስፈላጊነቱ ከመንግስት ጋር በአጋርነት (partnership) እንዲሰሩ በማድረግና ሌሎች አማራጮችን በማስፋት አመቺ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

## 9. የፍትሕ ተደራሽነት ሕና ውጤታማ የሕዝብ ኦገልግሎት

የወንጀል ሕግን አፈጻጸም ውጤታማነት በማረጋገጥ፣ እሴት የማይጨምሩ ሥራዎችን በማስወገድ ሥራዎችና አገልገሎቶች በፍጥነትና በጥራት እዲሠሩ እንዲሁም በአነስተኛ ወጪና በቅርበት እንዲሰጡ ማድረግ፣ የስትራቴጂክ አመራርና ማስፈፀም አቅም ማሳደግ፣ ፍትሐዊ፣ ተደራሽና ጠንካራ የዴሞክራሲና የፍትሕ ተቋማት እንዲኖሩ ማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ሁሉንም የተደራጁ የወንጀል ዓይነቶችን መከላከል፣ በደልን፣ ብዝበዛን፣ ሕገ ወጥ ዝውውርንና በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ማናቸውንም የኃይል ጥቃቶች ማስቆም፣ ሕገ ወጥ የገንዘብና የጦር መሳሪያ ዝውውርን በከፍተኛ መጠን መቀነስ፤ በማንኛውም የኃይል ጥቃትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚደርሱ የሞት መጠኖችን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ እና አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን በልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን ትኩረት ተደርጎባቸው ይሠራል።

በተጨማሪም በሀገራዊና በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት መሰረታዊ ነጻነቶችን መጠበቅ፣ ጥቃትን ለማስቆምና ሽብርተኝነትንና ወንጀልን ለመከላከል በዓለም አቀፍ  ትብብር ጭምር አግባብነት ያላቸው ሀገራዊ ተቋማትን በማጠናከር እንዲሁም ሁሉንም በእኩልነት የሚያዩ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን በማስፋፋትና

ተፈጻሚነታቸውን አስገዳጅ በማድረግ ዘላቂ ልማት ለሁሉም" "leaving no one behind" የሚለውን የዘላቂ ልማት አጀንዳ ዋና መርህ ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ሥራ አመራር ሥርዓትን ማሻሻል፤ የህዝብ ሠራተኞችን እሴት መገንባትና ሥነምግባርን ማሻሻል፣ ውጤታማ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ በሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት በሀገራዊው የልማት ጉዞ ጉልህ ሚና እንዲጫወት ማድረግ በልማት ዕቅዱ የትግበራ ዘመን ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም ሲቪክ ማህበረሰቡም በሀገሪቱ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በሚደረገው ጥረት ዙሪያ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ማበረታታት፣ ሙስናንና ጉቦን በሁሉም መልካቸው በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፣ ውጤታማ፣ ተጠያቂና ግልፅ ተቋማትን በሁሉም እርከኖች መፍጠር፣ ምላሽ ሰጪ፣ አካታች፣ አሳታፊና ወካይ ውሳኔ አሰጣጥን በሁሉም እርከኖች የማረጋገጥ ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

## 10. ዘላቂ ሰላም እና ጠንካራ ቀጠናዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብር

ፈጣንና ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ አዎንታዊ ሰላምና የዳበረ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ ማህበራዊ ሀብቶችን፣ እሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን ማሳደግ፣ ሕግ ማስከበር፣ የሰብአዊ ደህንነት አቅምንና ታአማኒነትን፤ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን፣ እንዲሁም ሕዝብ ተኮርና ሥራን በዕውቀት የመምራት ሥርዓትን ማጎልበት ያስፈልጋል። ለዚህም ስለ ሰላም አስፈላጊነት በትምህርት ሥርዓት፣ በሚዲያና በጥበብ ውስጥ እንዲካተት በማድረግ የትውልዱን ሥነ ልቦና መገንባት፤ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰቡ አዎንታዊ ሰላምን ማስረጽ፤ ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶችን በማቋቋምና በማጠናከር ሀገራዊ ጉዳዮችንና ብሔራዊ ጥቅሞችን መለየትና የጋራ መግባባት መፍጠር፣ መጠበቅ፣ መንከባከብና ማሳደግ፤ የማህበራዊ ሀብቶችና ባህላዊ እሴቶችን እንዲሁም የጥናት ውጤቶችን ወደ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ ማሣደግ እና ብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማሕበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራምን በመተግበር አዎንታዊ ሰላምን ለመገንባት ይሠራል። በተጨማሪም የሕግ ማስከበርና የሰብዓዊ ደህንነት ተቋማት ምላሽ ሰጪ፣ ተአማኒ፣ ዘመናዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆነው እንዲገነቡ በማድረግ የሕግ የበላይነት በህብረተሰብ ደረጃ ልዕልና እንዲያገኝ የምክክር መድረኮችን በማካሄድ፣ የግጭት ክስተትና የሁነት መረጃዎች በመተንተን ለውሳኔ ሰጪ አካላት በማድረስና ምላሽ በመስጠት አለመግባባቶች እንዲመክኑ የሚደረግ ሲሆን የሲቪክ ማህበራትም ግጭትን በመከላከልና ሰላም በማስፈን ዙሪያ የበኩላቸውን እንዲወጡ ይደረጋል።

በተጨማሪም ማህበራዊ መስተጋብር፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስርና የጋራ ብልጽግና ለማምጣት የሚያስችል ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም፣ ማህበራዊ መስተጋብርና የኢኮኖሚ ትስስርን ለማጠናከር ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በኢጋድ (IGAD) ማዕቀፍ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ፣ የድንበር ጉዳዮችን በሰላማዊ መንገድ እልባት መስጠትና የድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችን ፍትሐዊ አጠቃቀም ማስፈን፣ ለአፍሪካ ህብረት የሰላም፣ የብልጽግናና የውህደት አጀንዳዎች መሳካት ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት በህብረቱ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ማሳደግ፣ የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከርና አጋሮችን ማበራከት፣ በባለብዙ ወገን መድረኮች ተደማጭነታችን እና ጥቅሞቻችንን ማሳደግ፣ በዓለማቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ የሀገራችንን መልካም ገፅታ መገንባት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰትንና የወጪ ምርቶችን ገበያ ማሳደግ፣ የቱሪስት ፍሰትንና የልማት ፋይናንስ ዕድሎችን ማሳደግ፣ የዜጎችን መብትና ጥቅም ማስከበር፣ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያንን ተሳትፎና የሀብት ፍሰት ማሳደግ በትኩረት የሚሰራባቸው ይሆናሉ።

# 1.3 የልማት ዕቅዱ የትኩረት መስኮች

በልማት ዕቅዱ የተካተቱ ሁሉም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ሌሎች ዘርፎች ለሀገሪቱ የልማት ርዕይ መሳካት የማይተካ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ቅድሚያ ሰጥታ (priorty focus areas) ልትፈታቸው ካሰበቻቸው ማነቆዎች፣ ዘርፎች ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚና፣ በትንሽ ጥረት ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ያላቸው አቅም፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ባላቸው ትስስርና በእነዚህ ዘርፎች ላይ በሚያመጡት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ፣ ሀገሪቷን ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ ያላቸው አቅም፣ እንዲሁም ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ ያላቸው የጎላ ድርሻ መሠረት በማድረግ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 1. ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት

ፈጣን፣ ዘላቂና መሠረተ ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስመዝገብ የኢኮኖሚያዊ ብዝሃነት (economic diversification) ዕሳቤ እንደ ስትራቴጂ ይተገበራል። ኢኮኖሚያዊ ብዝሃነት ከአንድ የገቢና የዕድገት ምንጭ ይልቅ ወደ ብዙ የዕድገት ምንጮች (diversified sources of growth) የማተኮር ሂደት ነው። በዚህም መሠረት ግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ጨምሮ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የከተማን ዕድገት መሠረት ያደረገ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጮች ተደርገው ተለይተዋል።

የግብርና ዘርፍ ልማት፦ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የግብርና ዘርፍ አፈጻጸም አበረታች የነበረ ቢሆንም ዘርፉን በአስተማማኝ ደረጃ ከማዘመን አንጻር ከፍተኛ ክፍተቶች ተስተውለዋል። ከ2003 እስከ 2012 በነበሩት አስር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግብርናው ዘርፍ ተጨማሪ እሴት በአማካይ በየዓመቱ በ5.3 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። ይህም በተመሳሳይ ወቅት ከተመዘገበው ከሕዝብ ዕድገት ምጣኔ በላይ በመሆኑ አስቸጋሪ የአየር ንብረት በተከሰተባቸው ዓመታት ዘርፉ ከመፈተኑ በስተቀር በገጠር አማካይ የኑሮ መሻሻል እንዳለ ማስተዋል ይቻላል። ከዚህም በላይ ግብርናው ለሌሎች ዘርፎች ዕድገት መፋጠን የበኩሉን ድርሻ ያበረከተ ሲሆን በተለይም 77 በመቶ ለሚሆነው የሀገሪቱ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ምንጭ ሆኗል። ይሁን እንጂ ዘርፉ ውስጣዊ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣትና ከመዘመን አንጻር አሁንም ከዝናብ ጥገኝነት አለመላቀቅ፣ የዘርፉ አቅሞች ከበሬ እምብዛም ያልዘለሉ መሆን፣ ለአጠቃላይ መዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ ከማድረግ አኳያ በተለይም ለሌሎች ዘርፎች በቂ ምግብና አስተማማኝ ግብዓቶች ከማቅረብ እንዲሁም ገበያ ከመፍጠር አንጻር የግብርናው ዘርፍ ውስንነት አለበት። የሀገሪቱን ዜጎች የምግብ ፍላጎት ማሟላት ካለመቻሉ በተጨማሪ የዘርፉ የሰው ኃይል ምርታማነትም ዝቅተኛ ነው።

የግብርናው ዘርፍ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ፈጣን እንዳይሆንና የግብርና ትራንስፎርሜሽን እንዳይረጋገጥ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የመዋቅራዊ ሽግግር የተሻለ አስተዋጽኦ እንዳያበረክት የሚገድቡ ማነቆዎች ከቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት፥ ከዝቅተኛ የግብርና ኢንቨስትመንት ብሎም ከዝቅተኛ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዙ በሦስት አበይት ጉዳዮች የሚጠቃለሉ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶችም የመስኖ ልማት በተገቢው መጠን አለመስፋፋትና በቴክኖሎጂ ያልታገዘ መሆን፣ የተቀናጀ የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት አለመኖር፣ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ማመንጨት፣ ብዜትና ስርፀት ሥርዓት አለመዳበር፣ የግብርና ፋይናንስ እንዲሁም ኢንሹራንስ እና ኢንቨስትመንት በበቂ ሁኔታ አለማደግ፣ የግብርና ግብይት ሥርዓት ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና ሕጋዊ ሆኖ ያለመገንባት፣ በግብርና መስክ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖርና የግብርና ዘርፍ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዘም

የዕውቀት፣ ክህሎትና ተነሳሽነት አነስተኛ መሆን፥ ወጥነት ያለውና የተናበበ አደረጃጀትና አሠራር አለመኖር ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማሻሻልም የግብርና ዝመና አማራጭ የሌለው የዕቅዱየትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል።

የግብርና ዝመና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማሳደግ በቀጣዮቹ አስር ዓመታት ድርብርብ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ መመገብ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የመዋቅራዊ ሽግግርን እውን ማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ምግብ፣ ግብዓትና የሰው ኃይል ማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት ማጎልበትና የሥራ ዕድል መፍጠር ከግብርናው ዘርፍ በቀጣይ የሚጠበቁ ሚናዎች ናቸው። በመሆኑም የግብርና ዝመናን ለመተግበር ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶች በወሳኝ መልኩ መፈታት ይኖርባቸዋል። አጠቃላይ የግብርና ልማት አቅጣጫው በባሕላዊው የአመራረት ሥርዓት ከሚካሄዱ የተለመዱና እነዚህንም ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥረቶች ጎን ለጎን ግብርናን እንደ ህይወት ማቆያ አድርጎ የሚወስድ ሳይሆን እንደ አንድ ትርፋማና አዋጭ ኢንዱስትሪ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት በማበረታታት በሂደት የባሕላዊውን የግብርና ዘይቤ መተካት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በልማት ዕቅዱ የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ፣ ከጉልበት አጠቃቀም እስከ ተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች የሚዘልቅ ሜካናይዜሽን በሁሉም የግብርና ንዑስ ዘርፎች ለማስፈን፣ በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ ገበሬዎችን የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው ማገዝና ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስተርነት ለማሳደግ፤ የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማጎልበት እና በዘርፉ የባለሀብቱን ተሳትፎ ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

ለዚህም የግብርና ሥነ ምህዳርን (agroecology) ማዕከል ያደረገ የግብርና እንቅስቃሴን መከተል፣ የአመራረት ሥርዓትን ማዘመን፤ በተለይም የኤክስቴሽን አገልግሎቱን የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት በማድረግ የክትትል ሥርዓትን ማዘመን፣ ሁለንተናዊ የግብርና አቅሞችን ማጎልበት፤ የምርምር፣ የሠው ኃይል፤ የግብርና መሠረተ ልማት፤ የቴክኖሎጂ ሥርፀትን ማሻሻል፣ በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ በሂደት አስቻይ ፖሊሲዎችን መተግበር፤ የኮንትራት የግብርና አሠራርን ማስፈንና ሕጋዊ ዋስትና መስጠት፣ የግሉ ዘርፍ በአስተማማኝ የመሬት ይዞታ ላይ ግብርናውን እንዲያዘምን ማድረግ በትኩረት ሊተገበሩ የሚገባቸው ዋና ዋና ርምጃዎች ይሆናሉ። በእንስሳት ሀብት ዙሪያም የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ፣ መኖ እና ጤና ላይ በትኩረት ለመሥራት ግቦች ተጥለዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፦ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት እና ለተለያዩ አሉታዊ ተጽዕኖዎች የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ጠንካራ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መኖር ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት ቢኖርም ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከ7 በመቶ በታች ሲሆን ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ ውስጥ ያለው ድርሻም ከ13 በመቶ ያልበለጠ ነበር። ዘርፉ በአጠቃላይ ሲቃኝ በቀላል ማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች የተዋጠ ከመሆኑም በተጨማሪ አዝጋሚ ለውጥ የታየበት ዘርፍ ነው። ዘርፉ ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ያለው ተጽዕኖና ፋይዳ ደካማ ነው። በዘርፉ ከአጠቃላይ የማምረቻ ወጪዎች ውስጥ ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች ድርሻ ለማሽነሪ (machinery and equipment) ዘርፍ 93.3 በመቶ ሲሆን ለብረታ ብረት (iron and steel) ዘርፍ ደግሞ 79 በመቶ ይደርሳል። በተመሳሳይ የጨርቃጨርቅና አልባሳት እንዲሁም የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፎች ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ ናቸው። ከቆዳና ከጨርቃጨርቅ ዘርፎች ውጭ ያሉ የአምራች ዘርፎች ከሚያመርቱት ምርት ውስጥ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የቻሉት ከ2 በመቶ በታች ነው። በተጨማሪም የማኑፋክቸሪንግ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻም ከ30 በመቶ ያልበለጠ ነው። በተመሳሳይ የማኑፋክቸሪንግ የማምረት አቅም በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ፤ ያሉት ማኑፋክቸሪንግ ከሌሎች ላዕላይ ኢንዱስትሪዎች (up-

stream industries) ጋር ያላቸው ቁርኝት ዝቅተኛ መሆኑ፣ የመሠረተ ልማት በተለይም የኃይል አቅርቦት መጓደል ብቁ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የተንዛዛና ገዳቢ የመንግስት ቢሮክራሲ እና ከግሉ ዘርፍ አቅም ውስንነት ጋር ተዳምሮ የዘርፉን የማምረት አቅም ከ50 በመቶ በታች አድርጎታል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ምርታማነትና ቅልጥፍናን በማሳደግ መዋቅራዊ ሽግግርን ዕውን ማድረግ ወሳኝ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተወስዷል።

የማኑፋክቸሪንግ ልማት ወሳኝ ከሚሆንባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በከፍተኛ የዘርፎች ትስስር በሚፈጠር ሰፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አማራጭ ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ መቻሉ ነው። ከዚህ አንጻር የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት የሀገሪቱን የእንስሳት ሀብት፥ የቅባት እህሎች፥ የቃጫና የፍራፍሬ ሀብቶች በአግባቡ መጠቀምን ቅድሚያ ይሰጣል። የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ከግብርናው ዘርፍ ግብዓትና በቂ ምግብ በማግኘት ተጠቃሚ እንደሚሆን የመታሰቡን ያህል በአጸፋው ዘመናዊ ግብርና ግብዓቶችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን በመፈብረክ እንዲሁም ከግብርና ዘርፍ ለሚመረት ትርፍ ምርት ገበያ በመፍጠር በዘርፎች ትስስር የኢኮኖሚ ዕድገትንና መዋቅራዊ ለውጥን የማረጋገጥ አቅጣጫ ይከተላል።

የእስካሁኑን የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት እየመራ ለሚገኘው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ 70 በመቶ የሚሆነው ግብዓቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተከፍሎባቸው ከውጭ ከሚገቡ ዕቃዎች ነው። በመሆኑም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት የኮንስትራክሽን ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ማምረት ሌላው ትኩረት የሚደረግበት ነው። በአጸፋውም የኮንስትራክሽን ዘርፍ በማኑፋክቸሪንግ የግንባታ ሂደት ውስጥ አዲስ ሚና ይኖረዋል። የአምራችና የኮንስትራክሽን ዘርፎችም የማዕድን እንዲሁም ለኃይል ምንጭነት የሚውሉ ሀብቶችን በመጠቀምና ዙሪያ መለስ የዘርፎች ትስስርን በመፍጠር በማኑፋክቸሪንግ፥ በማዕድን፥ በውኃና በኤሌክትሪክ፥ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፎች የሚፈጠረውን ተጨማሪ እሴት በማሳደግ አጠቃላይ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ልማት እንዲያፋጥኑ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል። በእነዚህ ጥረቶች ከውጭ የሚገቡ መሠረታዊ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፣ በአዲስና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አዲስ ምርትና አዲስ ፍላጎት መፍጠር፥ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ በመሆን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ ሥራ አጥነትን በመቀነስ እና በሂደቱ የተስተካከለ የንግድ ሚዛን ማረጋገጥ የዘርፉ ዋነኛ ግብ ነው። በተጨማሪም በመጪው አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ባለፉት ዓመታት ማኑፋክቸሪንግን ለማስፋፋት የተጣሉ መሠረተ ልማቶችን ታሳቢ በማድረግ ማኑፋክቸሪንግ ከሌሎች ዘርፎች የተነጠለ እንዳይሆን፣ የትስስር ሠንሠለቱን በማንሠላሰልና ከሌሎች ዘርፎች ፍላጎት ጋር በማጣመር የአምራች ዘርፎችን ማስፈንጠር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ማኑፋክቸሪንግን ተወዳዳሪ ለማድረግ አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በማሟላት ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል።

የኢትዮጵያን የሸቀጦች የወጪ ንግድ የገበያ መዳረሻ በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት አንጻር ሲታይ በተወሰኑ ሀገራት ላይ የተንጠለጠለ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ያላትን አቅም በመፈተሽ፣ የአለምን ነባራዊ ለውጥ አቅጣጫ በማጤንና በመተንተን ከዘልማዳዊ የወጪ ንግድ ገበያ በመላቀቅ አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ማፈላለግ የትኩረት አቅጣጫዋ ነው። በተጨማሪም በቀጣይ አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ትግበራ የዕድገት ማዕከልን (growth corridors) መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ልማት ልዩ ትኩረት የሚያገኝ ይሆናል። ከመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪ ግንባታው ጎን ለጎን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የሥራ ዕድልን ከመፍጠር በተጨማሪ ለመካከለኛና ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ግብዓቶችን የማቅረብና በሌሎችም ጉዳዮች በማስተሳሰር በትብብር እንዲሰሩ ማድረግ ትኩረት ይሰጠዋል። ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በጊዜ፣ በአይነትና በመጠን ስለሚለያይ የኢኮኖሚውን አጠቃላይ ገጽታ ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተፈላጊውን የሰው ኃይል ግብዓት ቀድመው በማቀድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል። በተጨማሪም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ

የመሠረተ ልማቶችን በዕድገት ማዕከላት አማካይነት በማቅረብና ምርታማነትንና ቅልጥፍናን በመጨመር የማኑፋክቸሪንግ ልማት ዕውን ይደረጋል።

የማዕድን ዘርፍ ልማት፦ በኢትዮጵያ ትርጉም ባለው ደረጃ ዘመናዊ የማዕድን ልማት የሚታየው በወርቅ ማዕድን ነው። ይህም የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት፣ ለዜጎች የሥራ ፈጠራና የገቢ ምንጭ ከመሆን፤ በገንዘብ ተቋማት እንደ ሀብት መያዢያነት ከመቆጠር፤ እንዲሁም በሀገር ደረጃ እንደ አንድ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ጎልቶ ከመውጣት አንጻር  ብዙ ርቀት አልተሄደበትም። ኢትዮጵያ ማዕድናትን ጨምሮ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር መሆኗ የታወቀ ሆኖ ሳለ፣ የተፈጥሮ ሀብቶቿ በተለይም ማዕድናቶቿ በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ መገኘታቸው ሀገሪቷ ከሌሎች የበለጸጉ ሀገሮች አንጻር በልማት ወደኋላ የመቅረቷ አንድ ምክንያትም፣ መገለጫም ነው። ለዚህም በዋነኝነት በዘርፉ ያለው ኢንቨስትመንት በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ዝቅተኛ መሆን፤ በሀገሪቱ የማዕድን አለኝታ ሽፋን መረጃ በዝርዝርና በጥራት በበቂ ደረጃ አለመኖር፣ መረጃው በሚገኝበትም ጊዜ መረጃ ከማቅረብ፣ የተቀላጠፈና ፈጣን የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከማስፈን፣ ከማስተዋወቅና አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች ከመሳብ ጀምሮ ዘርፉን የማስተዳደር አቅም ውስንነት፤  በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ አቅም ደካማ መሆን፣  የዘርፉን ልማት ከሌሎች ዘርፎች ልማት ነጥሎ የማየት ችግር ወይም በተገቢው ደረጃ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የሥልቶች ግልጽና ወጥ አለመሆን፣ ከማኅበረሰብ እስከ ፖሊሲ አውጪ ባሉ ተቋማት ስለማዕድን ሀብትና በዘርፉ ስለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የተያዙ ገንቢ ያልሆኑ ግንዛቤዎችና አመለካከቶች፣ የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የማዕድን አስተዳደር የዘርፉን ሕጎች ለመተግበር የአቅም ውስንነት መኖር ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ትግበራ ዘመን እነዚህም ተግዳሮቶች በማስወገድ የማዕድን ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የማዕድን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ካለው ትስስር አኳያ የአሸዋ፣ የኢግኒምብራይት፣ የባዛልትና የመሳሰሉ ድንጋዮች፣ የዕምነ በረድ፣ የግራናይትና የኖራ ድንጋይ ማዕድናት ለኮንስትራክሽንና ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ጠቃሚ ግብዓቶች ናቸው። ነገር ግን የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት እየመራ የሚገኘው የኮንስትራክሽን ዘርፍ እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ግብዓት በማዕድናት ላይ እሴት ተጨምሮባቸው ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶች በመሆናቸው የኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍ ሊሞላው የሚገባ ክፍተትና አቅም መኖሩን ያሳያል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ለወጠነችው የመዋቅራዊ ሽግግር ዕቅድና የመካከለኛ ገቢ ሀገር የመሆን ትልም መሳካት ወሳኝ እንደሆኑ የታመነባቸውን የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ዝመና ስትራቴጂዎች ከማፋጠን አንጻር ከማዕድን ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ሚና ይጠበቃል።  በመሆኑም በልማት ዕቅዱ የተያዘው አቅጣጫ የማዕድን ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግርን በማፋጠን አጠቃላይ አቅም መፍጠር ሲሆን በተለይም የዘርፎች ትስስርን ማጠናከር፣ የማኑፋክቸሪንግና የግብርና ዝመናን ለማፋጠን ከውጭ የሚገቡ የግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ግብዓቶችን በመተካት ማዕድናትን በግብዓትነት መጠቀም፣ ተጨማሪ እሴት በዘርፉ በመፍጠር ለኢኮኖሚው ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ፣ ለዘላቂ ማኅበራዊ ለውጥ አጋዥ ዘርፍ እንዲሆን በማድረግ የማኅበረሰብ የሀብትና የልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጫ መስክ እንዲሆን ማድረግ እና ተወዳዳሪ የማዕድን ኢንዱስትሪ በመፍጠር መዋቅራዊ ለውጥን ማምጣት ትኩረት ይሰጠዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ ልማት፦ የቱሪዝም ዘርፍ ለአንድ ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ በጣም ከፍ ያለ ነው። ኢትዮጵያ  ታሪክ፣ በውብና ማራኪ የተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም በአስደናቂ የባህል ፀጋ የታደለች የአፍሪካ መዲና ናት። እነዚህ ብርቅዬ ሃብቶቿ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነጻጸሩ በጣም ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ናቸው።  ሆኖም ባለፉት ጊዜያት እነዚህን ሃብቶች በአግባቡ ከመጠቀም አንጻር  ሰፊ ክፍተቶች ታይተዋል። በተለይም የቱሪስት መዳረሻዎች  በተገቢው መልኩ በጥናት ተለይተውና ለምተው፣ ለሀገር ጥቅም ሊያስገኙ በሚችሉበት ቁመና ላይ አይገኙም። መስህቦቻችን ያላቸው ደረጃ እጅግ ከፍ ያለ

ቢሆንም ለጎብኝዎች በሚመች፣ ተወዳዳሪና ሳቢ በሆነ ሁኔታ የለሙ አይደሉም። በቱሪስት መዳረሻዎቻችን በቂና የሁሉንም ፍላጎት ሊያስተናግድ በሚያስችል መጠን የመጓጓዣ፣ የመኝታ፣ የምግብ፣ የቴሌኮም፣ የባንክ፣ የመንገድ ዳር ማረፊያዎች፣ የመታጠቢያ ቤቶች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የእግር መንገዶች የተሟሉ አይደሉም። በተጨማሪም ማህበረሰቡም ከቱሪዝም ተጠቃሚ የሚሆንባቸው በቂ አሠራሮች አልተዘረጉም። በዘርፉ ለተሰማሩና መሰማራት ለሚፈልጉ በተለይም ከማዕከል ወጣ ባሉ የመስህብ ቦታዎቻችን መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ማበረታቻዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸውና የቱሪዝም ዘርፉን ተወዳዳሪ ሊያደርግ በሚችል መልኩ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለኢንዱስትሪው እየቀረበ አለመሆኑ በቱሪዝም ዘርፍ ያለውን ከፍተኛ የሆነ እምቅ አቅም ጥቅም ላይ እንዳይውል አድርገዋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች በመፍታት ከዘርፉ የሚጠበቀውን እምቅ አቅም ሀገራችን በአግባቡ እንድትጠቀም ማስቻል ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል።

በቀጣይ አስር ዓመት የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኝታዎች በአግባቡ በመለየትና በማልማት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት በማጠናከር፣ በሀገሪቱ የሚገኙ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን በማልማት፣ ነባር መዳረሻዎችን በማጎልበትና የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነት በማስፋፋት የዘርፉን ተወዳዳሪነት በማሳደግ፤ ውጤታማ የገበያ ትስስር፣ የብራንዲንግና ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን መፍጠርና በነባር የቱሪስት አመንጪ ሀገራት ያለንን የገበያ ድርሻ በማሳደግ፤ በዘርፉ ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ በመፍጠር እና የማበረታቻ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት እንዲሁም በተወሰኑ ግብዓቶችና የመሠረተ ልማት ጥረቶች ሌሎች በርካታ ዘርፎችን በማነቃቃት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚኖረው ከፍተኛ ሚና ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል።

አይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ፦ ብዘሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕሳቤ ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ዘመኑን በሚመጥን ለፈጣን የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር ወሳኝ በሆኑ አይሲቲን በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ መሰማራት የግድ ነው። አይሲቲና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር ገብተው የሌሎች ዘርፎችን ልማት ከማሳለጥ ይልቅ እንደ አንድ የኢንዱስትሪ መስክ በማበልጸግ የኢኮኖሚ ዕድገትና የልማት ግስጋሴን እንዲያፋጥኑ በትኩረት ይሠራል። በተጨማሪም የዲጂታል ኢኮኖሚ መገንባት፤ በሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ኢገቨርናንስ ተግባራትን (e-governance)፣ ወረዳ ኔት፤ የገጠር ኮኔክቲቪቲ ፕሮግራምና የገጠር መንግሥታዊ ኢንተርኔት አቅርቦት ማዕከል የመሳሰሉትን ማጎልበት)፣ የቴክኖሎጂ ግብይት፣ ፋይናንስና ሎጂስቲክስ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የአይሲቲ ፓርክንና ኢኮሲስተምን ማበልጸግ፤ በአይሲቲ ዕውቀትን የሙያና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቶችን ማስፋፋት በትኩረት ተይዘው የሚሰሩባቸው ይሆናል። በተጨማሪም "ምርታማነት ከቴክኖሎጂ ጋር" የሚል ወሳኝ የዕድገት አቅጣጫ በትኩረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

## 2. ዘላቂ እና ተደራሽ የፋይናንስ ዘርፍ ልማት

ባለፉት ዓመታት የመንግስት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ሳይካሄድ በበጀት ውስጥ እንዲካተቱ መደረጉ አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደታቸውን አጠናቀው በወቅቱ ወደ ምርትና አገልግሎት ባለመግባታቸው የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የዕዳ የመክፈል አቅም ላይ ችግር አስከትሏል። ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ወጪና ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው ምክንያት ከተስተዋለው የልማት ፋይናንስ እጥረት በላይ በልማት ፕሮጀክቶች መጓተት፣ እንዲሁም ብልሹ አሠራሮች ምክንያት የተከሰተው ብክነትና ከዚህ ጋር የተያያዘው ዝቅተኛ የካፒታል ምርታማነት ይገዝፋል።

በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመት ልማት ዕቅድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሪፎርም ማካሄድ፣ ጠንካራ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደርን ተግባራዊ ማድረግ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀብት የማሰባሰብ አቅምን ማጎልበት፣ የመንግስትና የግል አጋርነትን ማጠናከር፣ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን ማጎልበት እንዲሁም በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት የሚመራ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ሥራዎች ይሆናሉ። በዚህም የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ማሳደግ፣ በንግድ ባንኮች የበላይነት የተያዘው ዘርፍ በሌሎች የባንክ አይነቶችና የፋይናንስ ድርጅቶች እንዲኖሩ በመሥራት የፋይናንስ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ዲጂታል የፋይናንስ ሥርዓትን ማሳለጥ፣ የካፒታል ገበያ (capital market) የሚቋቋምበትን አሠራር መዘርጋት እና የፋይናንስ ምንጭ ለማሳደግና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ለማጎልበት ከወለድ ነጻ የሆኑ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ አሠራሮችን የበለጠ ማስፋፋት ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል። በተጨማሪም የፋይናንስ አቅሞችን ከጊዜያዊ ወደ ዘላቂና ጥራት ወዳላቸው ምንጮች ማሸጋገር፣ የፋይናንስን ጥራትና ፋይዳ መጨመርና ብክነትን መቀነስ፣ ቅልጥፍናን ማሻሻል፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባን ከገጠር እስከ ከተማ ባሉ ተቋማት ማሳደግ፣ ሀገራዊ የፋይናንስ አቅምን በውጭ ምንዛሪ አቅምና በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ማገዝ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ገቢን በዘመናዊ የታክስ ሥርዓት መደገፍ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

## 3. የሥነ ሕዝብ ለውጥ ትሩፋት

የአንድ ሀገር ትልቁ ኃብት የሰው ኃይል ነው። ዘላቂ ልማትን እንዲሁም ብልጽግናን ለማረጋገጥም ዋናው መሠረት የሠው ኃይል ነው። በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለያዝነው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ ልማትና ማህበራዊ ልማት እንደ ጽኑ መሠረት የሚወሰድ ነው። በመሆኑም ለሰው ሀብት ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት የሥነ ሕዝብ ትሩፋትን ማረጋገጥ ወሳኝ ይሆናል።

በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ ባለፉት ዓመታት በርካታ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ከጥራት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከተደራሽነት እንዲሁም ከተገቢነት አንጻር ሰፊ የአፈጻጸም ክፍተቶች ተመዝግበዋል። በትምህርት ዘርፍ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ፣ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን ንጥር ተሳትፎ፤ በሁለተኛ ደረጃ ጥቅልና ንጥር ተሳትፎ፤ በመሰናዶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥቅልና የንጥር ተሣትፎ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት ከዓለም አቀፍ  ስታንዳርድ አንጻር አነስተኛ ነው። በተጨማሪም በመጠነ መድገምና በመጠነ ማቋረጥ የተመዘገቡት ዝቅተኛ የሆነ አፈጻጸም በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው። በተመሳሳይ በጤናው ዘርፍ ተግባራዊ የተደረገው በሽታን የመከላከል ስትራቴጂ የህብረተሰቡን የጤና ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት እንደሚያስችል በተጨባጭ ማየት ተችሏል። ከዚህ ስትራቴጂ በተጓዳኝ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ተደራሽና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ጥረቶች ተደርገዋል። ይህም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አፈጻጸም የተሻለ ውጤት እንዲኖራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት በመቆጣጠር የህጻናትን ሞት መቀነስ የተቻለ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል። በተጨማሪም ወደ ጤና ተቋም ሄደው የማይወልዱ እናቶችን ቁጥር በመቀነስ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶችን ምጣኔ መቀነስ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ሰፊ ክፍተቶች አሉበት።

ባለፉት ዓመታት በዘርፉ በዋናነት የተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ጉድለት፤ የዘርፉ የቁጥጥር ሥርዓት ጠንካራ አለመሆን፤ የአገልግሎት ተቋማት ከስታንዳርድ በታች መሆን፤ ዘርፉ በሚገባው መልኩ በቴክኖሎጂ አለመደገፉ፤ የፋይናንስና የግብዓቶች በቂ አለመሆን፤ የማህበረሰቡና የባለድርሻ አካላት የዘርፉ ተሳትፎ፣ ዕውቀትና ክህሎት ውስንነት፤ ቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት አለመኖር፤ የአመራርና የአስተዳደር የብቃት ችግሮችና የተጠያቂነት አሠራር ደካማ መሆን እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አናሳ መሆን ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ናቸው።

የሠው ኃብት ልማት ዘርፍ በቀጣይ ጤናማ፣ በዕውቀትና በክህሎት የዳበረና ርዕቱ አመለካከት ያለው የሰው ኃይል በመፍጠር የኢኮኖሚ ዕድገትንና አስፈላጊውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ሀገራችን በቀጣዮቹ ዓመታት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአምራች ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ የሰው ኃይል እንደሚኖራት ጥናቶች ያመለክታሉ። በመሆኑም ይህን አምራች የሰው ኃይል ጤንነቱን በመጠበቅ የዕድገት ምዕራፉ የሚፈልገውን ሙያና ክህሎት ማዳበር የሚያስችሉ አቅሞችና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሥነ ሕዝብ ለውጥ ትሩፋት ይረጋገጣል። ለዚህም የትምህርት አገልግሎት ተደራሽነትን፣ ጥራትንና ፍትሐዊነትን ማሳደግ ትኩረት ይሰጠዋል። በተጨማሪም የዘርፉን አገልግሎት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነትና ጥራት የሚያስጠብቁ ሥርዓታትን መዘርጋት፣ መከታተልና መቆጣጠር፤ ከሌሎች የዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በትብብር መሥራት፣ መደገፍ፣ ምርምሮችን ማካሄድና የቴክኖሎጂ፣ የምርምርና የሳይንስ ውጤቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ከዚህም አኳያ በቀጣይ አስር ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን በሁሉም ደረጃ ጥራት፣ ተገቢነትና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ ልዩ ትኩረት ያገኛሉ።

## 4. ጥራትን፣ ተደራሽነትንና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያገናዘበ መሠረተ ልማት

የልማት ዕቅዱን ርዕይ በተሟላ መልኩ ለማሳካት እና ዜጎችን በዘላቂነት ከልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ጥራት ያለው፣ ተደራሽ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያገዘበ የመሠረተ ልማት ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ትኩረት ከተሰጣቸው ቁልፍ መስኮች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፤ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት፣ የኢነርጂ መሠረተ ልማት እና የመስኖና የውኃ መሠረተ ልማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፦ ከአጭርና የመካከለኛ ዘመን ያለፉ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ አፈጻጸሞች በተለይም የኢኮኖሚ ዕድገት ከምንም በላይ በቴክኖሎጂ ልህቀት የሚወሰኑ ናቸው። ያደጉ ሀገሮች ሁለንተናዊ ውድድር በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ የመሆኑን ያህል ኋላቀርነትን በማስወገድ ከበለጸጉ ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍና እኩል የዓለም ዜጋ ለመሆን አቋራጩ መንገድ በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ማሳደግ ነው። ከዚህ አኳያ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ከቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አድማስ የራቀ ሀገር ቴክኖሎጂን በመማር፣ በማሻሻልና በማምረት ሂደቶች ብልጽግናን ዕውን ማድረግ እንደሚቻል የሀገሮች ተሞክሮ ያሳያል። በተለይም ከቴክኖሎጂ ዘርፍ ውስጥ የአይ. ሲ. ቲ. ዘርፍ የሌሎችን ዘርፎች በማሳለጥ እንደ መሠረተ ልማት እንዲሁም በራሱ እንደ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጣሪነቱና እንደ ሰው ሀብት መገንቢያ ዘርፍ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል። በልማት ዕቅዱ ዘመን የዲጂታል ኢኮኖሚን የመገንባት ለዚህም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማልማትና ተደራሽነትን ማስፋት እንዲሁም የአይ. ሲ. ቲ. አገልግሎቶችን ማሳደግ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

ጉልበትን መሠረት ካደረገ የአመራረት ዘዴ በሂደት የቴክኖሎጂን ፈጣን ተለዋዋጭነት ታሳቢ ያደረገ የግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መሠረትን የመጣል፣ ቴክኖሎጂና ዕውቀት አከል የአገልግሎት ዘርፍ ኢኮኖሚን የመገንባት፣ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ተወዳዳሪነትን የማሳደግ ሥራዎች የዘርፉ የትኩረት መስኮች ናቸው። በተመሳሳይ ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ ልማቶችን መገንባትና ማደራጀት፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት የሚውል የሰው ሀብት አቅምን ማሳደግ፤ ምርትንና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ምርምሮችን ማካሄድ፤ ቴክኖሎጂዎችን ማልማት፣ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ፤ የለሙ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋትና በኢኮኖሚው ውስጥ ጉልህ ሚና የሚኖራቸውን የምርምርና የኢኖቬሽን ውጤቶችን ማበረታታት፤ ቴክኖሎጂን መሠረት በማድረግ የሥራ ዕድል መፍጠርና የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር ሀብት ማፍራት በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናሉ።

የትራንስፖርት መሠረተ ልማት፦ በሀገራችን የመንገድ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት መንግሥት ከፍተኛ ትኩረትና ቅድሚያ በመስጠት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ምክንያቱም መንገድ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደ ደም ሥር የሚቆጠር መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። በዚህም ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ የሀገሪቱን መንገዶች ጠቅላላ ርዝመት በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ተችሏል። ሆኖም ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት አንጻር ሲታይ ያለው የመንገድ አውታር በቂ ካለመሆኑም በላይ ተደራሽነቱም ሌሎች ሀገሮች ከደረሱበት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። ለማስረጃ ያህል በኢትዮጵያ ያለው የመንገድ ጥግግት (road density) በእያንዳንዱ 1,000 ካሬ ኪ.ሜ 130.9 ኪ.ሜ ገደማ ሲሆን፣ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች በአማካይ 140 ኪ.ሜ፣ በዓለም ደረጃ ደግሞ በአማካይ 394 ኪ.ሜ ገደማ ነው። ይህም እንደ ሀገር ያለን የመንገድ አውታር በቂ አለመሆኑንና ተጨማሪ መንገድ በስፋት መሠራት እንዳለበት ያመለክታል።

በትራንስፖርት መሠረተ ልማት ረገድ ማነቆ ከሆኑት መካከል ግንባታው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑና እንዲሁም የማስፈጸም አቅም ውሱንነት በዋንኛነት ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም በግንባታው ሂደት የሚያጋጥሙ የወሰን ማስከበር፣ የካሣ ክፍያና የመሳሰሉት ችግሮች በመሠረተ ልማቱ ግንባታ ፍጥነትና ወጪ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይታወቃል። በተለይም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያስኬዱ የገጠር መንገዶች አማካይነት ከወረዳዎች ጋር ለማገናኘት ታቅዶ የተጀመረውና በክልሎች አስፈጻሚነት ተግባራዊ የሚደረገው “ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም” (URRAP) በፋይናንስ እጥረት፣ ተገቢውን ቅድሚያ ባለማግኘቱ እና በአጠቃላይም በማስፈጸም አቅም ውሱንነት ምክንያት አፈጻጸሙ እጅግ ደካማ ሆኖ ቆይቷል።

በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ዘላቂነትና ፍትኃዊነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን ከፍተኛ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ከወዲሁ ታሳቢ ያደረገ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ ማፋጠን፣ የነባር መንገዶችን እንክብካቤና ወቅታዊ ጥገና ማጠናከር፣ እንዲሁም የመሠረተ ልማቱን ጥራት፣ ፍትኃዊነትና ተደራሽነት ማረጋገጥ የዘርፉ ቀዳሚ ተግባራት ሲሆኑ ክልሎች በቀጥታ በመንገድ ልማትና አስተዳደር ሥራዎች ላይ በጉልህ የሚሳተፉ እንዲሆኑም ታቅዷል። በተጨማሪም የባቡር መሠረተ ልማትን በማስፋፋትና ጥራትን በማረጋገጥ የሀገሪቱን የባቡር መሠረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል።

የኢነርጂ መሠረተ ልማት፦ በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ የኢነርጂ ፍላጎት በፍጥነት እየጨመረ መጥቷል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገትም የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። የኢነርጂ መሠረተ ልማት ከሌሎች ልማቶች ቀድሞ መገኘት ያለበት፣ ሌሎች የልማት ሥራዎችን የሚያነቃቃና የሚስብ መሠረተ ልማት በመሆኑ በቂና አስተማማኝ የሆነ የኢነርጂ መሠረተ ልማት አቅርቦት ለዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ስለ ሀገራዊ ልማት ሲታሰብ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ሀገራችን ከተለያዩ ምንጮች (በዋንኛነት ውኃ፣ ንፋስ፣ ፀሐይ፣ እንፋሎት) ለኢነርጂ ማመንጫ ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ እምቅ ሀብት ያላት ሲሆን እስከ አሁን በሥራ ላይ የዋለው እጅግ አነስተኛው ክፍል ነው። በአሁኑ ጊዜ የዘመናዊው ኢኮኖሚ ዋነኛ የኢነርጂ ምንጭ ውኃ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ኢነርጂን ከንፋስ፣ ከፀሐይ እንዲሁም ከጂኦተርማል ምንጮች ማመንጨት ተጀምሯል፣ ድርሻቸውም እያደገ በመሄድ ላይ ነው።

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ በኢነርጂ ዘርፍ ያለው ሁኔታ ሲታይ ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት የኃይል አቅርቦትን በፍጥነት ለማሳደግና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በማስፈጸም አቅም ውሱንነት፣ በፋይናንስ እጥረት፣ በሰለጠነና በሥነ ምግባር የታነፀ

የሰው ኃይል እጥረትና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት በዕቅድ የተያዙ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ታይተዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በቂና ጥራት ያለው የኃይል አገልግሎት ለማቅረብ ያለመቻል ችግሮች (ለምሳሌ የኃይል አቅርቦት መቆራረጥ እንዲሁም ከፍተኛ ብክነት) ሲያጋጥሙ ከመስተዋሉም በላይ በአገልግሎቱ ዝቅተኛ ተደራሽነትና ኢፍትኃዊነት ይንፀባረቅበታል። በልማት ዕቅዱ ዘመን የኢነርጂ መሠረተ ልማት ዋና ትኩረት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያስፈልገውን መሠረተ ልማት በመገንባት ጥራት ያለው የኃይል አገልግሎት በወቅቱና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀርብ ይደረጋል።

የመስኖና ውኃ መሠረተ ልማት፦ የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የመስኖ ልማትን በተመለከተ ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በቀጣይ የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ እንዲሁም ለሌሎች ዘርፎች በበቂ ሁኔታ ግብዓት በሚሆን ደረጃ ለማድረስ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታን በማካሄድ የመስኖ ልማትን ማስፋፋትና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል። የመሠረተ ልማት አቅርቦትና ዝርጋታ በራሳቸው የሚኖራቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በአካባቢዎች ላይ ያለውን እምቅ የመልማት አቅም በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ለአካባቢውና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የሚኖረውን ፋይዳ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸውል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመት የሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶች የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ፣ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራርን እውን ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

በተጨማሪም የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ለሁሉም ዜጎች እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ተቋማትና ለእንስሳት ለማዳረስ የመጠጥ ውኃ መሠረተ ልማት ግንባታ የሚካሄድ ይሆናል። ለዚህም የንጹህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሥራ ማስፋፋት፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ መሠረተ ልማቶች ዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ የታዳሽ ኃይል አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፣ የከተሞች ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ማሳደግና ድንበርና ድንበር ተሻጋሪ የውኃ ሀብት ጉዳዮች ፍትሐዊ አጠቃቀም ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ተሠጥቶ ይሠራል። በተጨማሪም በሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ የሳኒቴሽንና ሃይጅን አቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት በማከናወንና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ወጥና ዘላቂ ድጋፍ በማድረግ ይሠራል።

## 5. ዘላቂ ከትመት (Sustainable Urbanization)

የኢትዮጵያ የከተማ ህዝብ ብዛት ከጠቅላላ ህዝብ ቁጥር አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ የሚባል ቢሆንም ሀገራችን ከተሜነት በፍጥነት ከሚያድግባቸው ሀገሮች ውስጥ አንዷ ናት። ሆኖም እየታየ ያለው የከተሜነት ዕድገት በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርና በምርታማነት ዕድገት የታገዘ ባለመሆኑ መልካም ዕድል ሳይሆን ስጋት ሊሆን ችሏል። የከተሞች መስፋፋት በዕቅድ ሊመራ የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ መልካም ዕድል የሚፈጥር ነው። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ በፈጣን የሥነ ሕዝብ ሽግግር (rap-id demographic transition) እየተመዘገበ ካለባቸው ሀገሮች መካከል አንዷ ስትሆን ባለፉት 20 ዓመታት የሀገሪቱ አምራች የሰው ኃይል ቁጥር በሁለት እጥፍ ማደጉ አንዱ የሥነ ሕዝብ ሽግግሩ ማሳያ ነው። በዚህም ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት እየጨመረ በመምጣቱ

በከተሞች የሥራ አጥ ቁጥር ጨምሯል። በከተማ ልማት ዘርፍ ከተሜነትን በብቃት ለመምራት የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ አለመኖሩ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰውን የሰው ኃይል ወደ ሥራ ለማስገባት በቂ የሥራ ዕድል አለመኖርና የከተማ ፋይናንስ አቅም ውስንነት በዘርፉ የተስተዋሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

ከተሞች የሥራ ዕድልን በስፋት እንዲፈጠሩ በማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንዲሁም የብልጽግና ጉዞን ለማፋጠን ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተጨማሪም ከተሞችን ማልማት ለሥራና ለኑሮ ሳቢ በማድረግ ለመዋቅራዊ ሽግግሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከዚህ አኳያ በአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ዘመን ከዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የከተማ መሬትን ምርታማነት ለመጨመር የይዞታ ማረጋገጫ ሥርዓትን ማሻሻል፣ ለልማት የሚሆኑ የመሬት አቅርቦቶችን ማሻሻልና በመልሶ ማልማት ሂደት ዘላቂ የከተማ ልማትን ማረጋገጥ፣ ከተሞችን ከዙሪያቸው ካለ ልማት ጋር በማስተሳሰርና ከሌሎች የልማት ማዕከሎች ጋር በማቆራኘት ምርታማነትን ማሳደግ፣ የመንግስትና የግል አጋርነትን በመጠቀም የቤቶችን ዕጥረት መፍታት፣ ያልተማከለ የከተማ ልማትን ማጠናከር፤ የከተሞችን የመሠረተ ልማት ፍላጎት ማሟላት ይገኙበታል። በተጨማሪም ብቃትና የሥራ ተነሳሽነት ያለው የሰው ኃይል አቅርቦትና ቴክኖሎጂ በስፋት፤ በጥራትና በተመጣጣኝ ወጪ የማቅረብና ቅንጅታዊ አሠራር የማዳበር እንዲሁም የመረጃ ልውውጥን ወደ ዲጂታል የማሳደግ ተግባራት ከቀጣይ የትኩረት መስኮች ውስጥ ናቸው።

## 6. ሰላም፣ ፍትሕና አካታች ሥርዓታት

ባለፉት ዓመታት በሀገራችን የሰላም፣ የፍትሕ፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደር እና የአካታችነት ችግሮች ማጋጠማቸው ይታወቃል። የፍትሕ ዘርፍ ከመንግስት የለውጥ ፍጥነትና ከህዝቡ መሰረታዊ የፍትሕ እና በእኩል የመጠቀም ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አንጻር ሲመዘን ገና ጅምር ላይ መሆኑ፤ የዜጎች በመብትና ግዴታ፣ በነጻነትና ሃላፊነት መሃል ያለውን ሚዛን አለመጠበቅና የመብት ጥያቄን በኃይል ለማስፈፀም የሚያደርጉት የተደራጁ የሕገ ወጥ ተግባራትና የሥርዓት አልበኝነት አዝማሚያዎች መታየታቸው፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶችና በዚህ ውስጥ የተሳተፉ ወንጀል ፈፃሚዎችን በተሟላ መልኩ ለሕግ አለማቅረብ በፍትሕ ሥርዓት እና የሰላም ሁኔታ ላይ የተወሰኑ ክፍተቶችን ፈጥረው ቆይተዋል።

በቀጣይ አስር ዓመት ፍትሐዊ፣ ተደራሽ እና ጠንካራ የፍትሕ አገልግሎትን በማስፈን የኢኮኖሚ ዕድገቱንና ልማቱን ማገዝ፣ ብቃት ያለው የህዝብ አገልግሎት ሥርዓትን መገንባት፣ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ሥራ አመራር ሥርዓትን ማሻሻል፣ ሀገራዊ ጉዳዮችንና ጥቅሞችን አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በብዙሃን ተሳትፎ መለየትና የጋራ መግባባትን መፍጠር፣ የህዝብ ሰራተኞች እሴት ግንባታና ሥነ ምግባርን ማሻሻል እንዲሁም የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናሉ። በዚህም ለኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ ሁኔታን ለመፍጠር እንቅፋት የሆኑ የሰላም፣ የሕግ፣ የፍትሕ፣ የፖሊሲና የተቋም አሠራሮችን በማሻሻል ሀገራችን በዓለም አቀፍ ያላትን የንግድ ምቹ ከባቢ ደረጃ ማሻሻልና በዚያውም ሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ይሠራል።

# 1.4 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ስምምነቶች እና የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ትስስር


የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 እ.ኤ.አ. በመስከረም 2015 የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት መሪዎች በኒውዮርክ ባደረጉት ስብሰባ ፀድቆ ይፋ የሆነና በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ቋት የተተካ ነው። ይህ የልማት አጀንዳ የማይነጣጠሉና ሁሉን አቀፍ (Universal) ባህሪያት ያሏቸው 17 ግቦችን፣ 169 ኢላማዎችና 230 አመልካቾችን ያካተተ ነው። የዘላቂ ልማት ግቦችን ከመፈፀምና ከማስፈፀም አኳያ በዓለም አቀፍ ደረጃ አስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ ባይኖርም የዓለም ሀገራት መሪዎች የጋራ የቃልኪዳን ሰነድ ሆኗል። ይህም የየሀገራቱን ልማት የበለጠ ለማፋጠን እና ስኬታማ ለማድረግ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት በአህጉራዊ ግብዓትነት የተወሰደውን እና "Common African Position on Post 2015 Development Agenda" የተሰኘውን የአፍሪካ የጋራ አቋም ሰነድ ለማዘጋጀት የከፍተኛ ኮሚቴ አባል ሆነው እንዲሠሩ ከተመረጡ 10 የአፍሪካ ሀገራት መካከል የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በመወከል ተመርጣ አስተዋጽዖ አድርጋለች።

የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የማስተሳሰር ሥራ ተሰርቷል። የዘላቂ ልማት ግቦች ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዝግጅት እንደ አንድ መነሻነት የተወሰዱ ሲሆን በልዩ የትኩረት መስኮች፣ በመሠረታዊ አቅጣጫዎች፣ በማክሮ-ኢኮኖሚ ዕቅድ፣ በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በማስፈፀሚያ ፋይናንስ ዕቅድ፣ በመሠረተ-ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በሰው ኃብት ልማትና በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዕቅድ፣ በልማታዊ መልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ እንዲሁም በባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድ እንደየአግባቡ የማስተሳሰር ሥራ ተሰርቷል። በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ን እንዲካተት ተደርጓል። ዕቅዱን በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማፀደቅ የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራና የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የህግ አስገዳጅነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ባለፉት አምስት ዓመታት ሲተገበር ቆይቷል።

የዘላቂ የልማት ግቦች በቀሪዎቹ አስር ዓመታት ተግባራዊ የሚሆኑ በመሆናቸው በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ እደተደረገው ሁሉ ከአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ጋር ሙሉ በሙሉ ለማስተሳሰር እና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች አኳያ መተግበር ያለባቸውን ተግባራት በመለየት ግቦቹን ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ የዘላቂ የልማት ግቦች ትግበራ የፋይናንስ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል። ጥናቱን በግብዓትነት በመጠቀም ሁሉንም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገሪቱ የረጅም ጊዜ ርዕይ፣ ከልማት ዕቅዱ ዓላማዎችና ምስሶዎች ጋር በግብ ደረጃ እንዲተሳሰሩ ተደርጓል (ሥዕል 1.2)። በተጨማሪም በክትትልና ግምገማ ማትሪክስ ሰነድ ውስጥ በኢላማና አመላካች ደረጃ ሙሉ በሙሉ እንዲተሳሰሩ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ወቅትና ድርድሮች ላይ የአፍሪካ ህብረት 2063 አጀንዳ ተቀባይነት እንዲኖረው ተጽዕኖ መፍጠር ችላለች። በዚህም 17ቱ የዘላቂ ልማት ግቦች ከአፍሪካ አጀንዳ 2063 ውስጥ ካሉ 20 ግቦች ጋር ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እንዲካተቱ ተደርጓል። በመሆኑም የዘላቂ የልማት ግቦችን ከአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰሩ ሲደረግ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ም እንደተሳሰረ ታይቷል።

ሥዕል 1.2፡ የዘላቂ ልማት ግቦች ከአስር ዓመቱ ዕቅድ ምሰሶዎች ጋር ያላቸው ትስስር





# ምዕራፍ ሁለት

## የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ

የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ሀገራዊ ርዕይን ለማሳካት ወሳኝ በሆኑት የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በዚህ መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፤ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ፤ የኢኮኖሚውን የዕድገት ቀጣይነትና ዘላቂነት ማረጋገጥና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ናቸው።

## 2.1 የኢኮኖሚ ዕድገትና የድህነት ቅነሳ

የድህነት ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7 በመቶ መቀነስን፤ የተገነቡና ሊገነቡ የታሰቡ ጥቅል ሀገራዊ አቅሞችን፤ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲሁም በእያንዳንዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ያሉ አቅሞችንና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ የምርታማነት መነሻዎች ታሳቢ በማድረግ ኢኮኖሚው ከ2013 እስከ 2022 ባሉት አስር ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ በ10 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል።

በተጨማሪም በቀጣይ የልማት ዕቅድ ዘመን የሀገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማረጋገጥ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መርነት ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መርነት ማሸጋገርን፤ የሀገሪቱን በዓለም አቀፍ የገበያ ተወዳዳሪነት በማሳደግ በወጪ ንግድ ገቢ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብን እንዲሁም የልማት ፋይናንስ ምንጭን በአብዛኛው ከግሉ ዘርፍ እንዲሆን በማድረግ የልማት ፋይናንስን ዘላቂነት ብሎም የኢኮኖሚውን ዕድገት ቀጣይነት ማረጋገጥ ታሳቢ ተደርጓል።

የቁሳዊና ሰብዓዊ ካፒታል ክምችትን ከማሳደግ ጎን ለጎን በአጠቃቀማቸው ከፍተኛ ምርታማነት ወደላቸው ዘርፎች ማሸጋገርን፤ ቅልጥፍናንና ምርታማነትን ማዕከል ያደረገ ስልትን ታሳቢ በማድረግ የካፒታል ክምችት (capital accumilation) እና አጠቃላይ ምርታማነት (total factor productivity) ለዕድገቱ የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ በቅደም ተከተል 55 በመቶ እና 45 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። የኢኮኖሚ ዕድገቱ በክፍላተ ኢኮኖሚ ሲታይ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ በየዓመቱ የ5.9፣ የ13 እና የ10.6 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግቡ ታቅዷል (ሠንጠረዥ 2.1)።

ሠንጠረዥ 2.1፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አማካይ ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶ)

| | 2008-2012 | አማካይ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 |
| ግብርና | 4.1 | 5.5 | 6.2 | 5.9 |
| የሰብል ምርት | 4.8 | 4.6 | 4.6 | 4.6 |
| የእንስሳት ምርት | 2.5 | 8.5 | 10.1 | 9.3 |
| ኢንዱስትሪ | 15.2 | 11.4 | 14.6 | 13 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 13 | 18.4 | 22.9 | 20.6 |
| ኮንስትራክሽን | 17.3 | 8.5 | 9.2 | 8.9 |
| አገልግሎት | 8.2 | 10.4 | 10.7 | 10.6 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 8.9 | 11.3 | 11.8 | 11.6 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 11.5 | 14.6 | 14.8 | 14.7 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 12.5 | 9.9 | 7.8 | 8.8 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 8.2 | 9.2 | 10.9 | 10 |

ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

የ10 በመቶ አማካይ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማሳካት የሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት ምጣኔ (gross capital formation) ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በልማት ዕቅድ ዘመን በአማካይ 36.9 በመቶ እንደሚሆን ተገምቷል። ይህም ባለፉት የልማት ዕቅዶች የትግበራ ወቅት ተመዝግቦ ከነበረው የኢንቨስትመንት ምጣኔ ጋር የሚስተካከል ሲሆን ባለፉት ዓመታት በተለይም በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የታየውን የሀብት ብክነት የበዛበትና የተንተተ አፈጻጸም የማረም አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ በማስገባት የካፒታል ምርታማነትን በመጨመር እንደሚካካስ ታሳቢ ተደርጓል። ከጠቅላላ የኢንቨስትመንት ምጣኔ ውስጥ 64.8 በመቶ የሚሆነው ከግሉ ክፍል ኢኮኖሚ ኢንቨስትመንት የሚጠበቅ ሲሆን ይህም በልማት ዕቅዱ የተቀመጠውን የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ልማት መሪነት የማረጋገጥ አቅጣጫ የተከተለ ነው። ቀሪው 35.2 በመቶ የመንግስት ኢንቨስትመንት ድርሻ ይሆናል። ከመንግስት ኢንቨስትመንት ድርሻ ውስጥ 63.1 በመቶ በመንግስት የካፒታል በጀት አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ቀሪው 36.9 በመቶ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኢንቨስትመንት ድርሻ ነው።

ሠንጠረዥ 2.2፡ የመጨረሻ ጠቀሜታ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ ፍጆታ | 79.1 | 72 | 70 | 71 | 69.3 |
| የግል ፍጆታ | 64.8 | 61.1 | 56.8 | 58.9 | 55.2 |
| የመንግሥት ፍጆታ | 9.5 | 10.9 | 13.2 | 12.1 | 14 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ | 20.9 | 28 | 30 | 29 | 30.7 |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | 30.8 | 36.8 | 37 | 36.9 | 37.3 |
| የግል ኢንቨስትመንት | 22.1 | 22.4 | 25.4 | 23.9 | 26.9 |
| የመንግስት ኢንቨስትመንት | 8.2 | 14.4 | 11.6 | 13 | 10.3 |
| በመንግስት ካፒታል በጀት | 4.2 | 7.7 | 8.6 | 8.2 | 8.4 |
| የመንግስት የልማት ድርጅቶች | 4 | 6.7 | 3 | 4.8 | 1.9 |
| ጠቅላላ የወጪ ንግድ | 7.1 | 11.9 | 12.9 | 12.4 | 12.9 |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ | 16.9 | 20.7 | 19.9 | 20.3 | 19.4 |
| ሀብት ክፍተት | (9.9) | (8.9) | (7) | (7.9) | (6.5) |


ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

በተጨማሪም የወጪ እና የገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ በ2022 በቅደም ተከተል 13 እና 19.4 በመቶ እንደሚሆን ታቅዷል። በዚህም የሀብት ክፍተት (ማለትም በሀገር ውስጥ ቁጠባና በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት መካከል ወይም በወጪ ንግዱ ገቢና በንግዱ ወጪ መካከል ያለው ልዩነት) ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ለዕቅዱ ዘመን እየቀነሰ እንደሚመጣ ታቅዷል።

# 2.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 32.7 በመቶ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 22 በመቶ እንደሚቀንስ ታቅዷል። በአንጻሩ በዚሁ ጊዜ የኢንዱስትሪ ድርሻ ከ29 በመቶ ወደ 35.9 በመቶ ሲያድግ በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ ከ39.5 በመቶ ወደ 42.1 በመቶ ከፍ እንደሚል ታቅዷል። ከኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተናጠል ሲታይ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.9 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 17.2 በመቶ እንደሚያድግ ታቅዷል (ሠንጠረዥ 2.3 እና ሥዕል 2.1)።

ሥዕል 2.1፡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ (በመቶኛ)




ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

ሠንጠረዥ 2.3፡ የኢኮኖሚ ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | 2017 | 2022 |
|---|---|---|---|
| ግብርና | 32.7 | 27.2 | 22 |
| የሰብል ምርት | 21.3 | 16.6 | 12.4 |
| የእንስሳት ምርት | 8.5 | 8.5 | 8.2 |
| ኢንዱስትሪ | 29 | 30.4 | 35.9 |
| የማኑፋክቸሪንግ | 6.9 | 10.3 | 17.2 |
| የኮንስትራክሽን | 21.1 | 19.3 | 17.9 |
| አገልግሎት | 39.5 | 42.4 | 42.1 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 14.3 | 16.2 | 16.9 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 5.3 | 6.7 | 8 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 3.3 | 3.3 | 2.9 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት* | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን (*የተጣራ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት፣ FISIM ተቀንሶ)

በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ዘርፍ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በአማካይ በየአመቱ የ1.6 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በአንጻሩ የኢንዱስትሪና አግልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል የ4 መቶኛ ነጥብ እና የ4.4 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል (ሠንጠረዥ 2.4)።


ሠንጠረዥ 2.4፥ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የሚኖራቸው አስተዋጽዖ (በመቶኛ)

| | 2008-2012 | አማካይ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 |
| ግብርና | 1.5 | 1.7 | 1.6 | 1.6 |
| የሰብል ምርት | 1.1 | 0.9 | 0.7 | 0.8 |
| የእንስሳት ምርት | 0.2 | 0.7 | 0.9 | 0.8 |
| ኢንዱስትሪ | 3.4 | 3.2 | 4.8 | 4 |
| የማኑፋክቸሪንግ | 0.8 | 1.5 | 2.9 | 2.2 |
| የኮንስትራክሽን | 2.6 | 1.7 | 1.7 | 1.7 |
| አገልግሎት | 3.3 | 4.3 | 4.6 | 4.4 |
| ጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 1.3 | 1.7 | 2 | 1.9 |
| ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን | 0.6 | 0.9 | 1.1 | 1 |
| የፋይናንስ ኢንዱስትሪ | 0.4 | 0.3 | 0.2 | 0.3 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 8.2 | 9.2 | 10.9 | 10 |

ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ኮሚሽን

**የሸቀጦች የወጪ ንግድ በዋና ዋና ዘርፎች፡-** በልማት ዕቅድ ዘመን ከታቀደው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ የሸቀጦች የወጪ ንግድም መዋቅራዊ ወይም የስብጥር ለውጥ እንደሚኖረው ታቅዷል። በዚህ መሠረት የሸቀጦች ወጪ ንግድ ከጠቅላላ ወጪ ንግድ ያለው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 39 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 53.9 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ የግብርና፣ የማኑፋክቸሪንግና የማዕድን ዘርፎች የወጪ ንግድ ድርሻዎች በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበሩበት 77፣ 13.3 እና 6.9 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 36.4፣ 48.4 እና 11.3 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በአጠቃላይ የግብርና ምርቶች በወጪ ንግድ ገቢ ውስጥ ያላቸው ድርሻ እየቀነሰ እንደሚሄድና በአንጻሩ የኢንዱስትሪና የማዕድን ምርቶች ድርሻ እየጨመረ በመሄድ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ታቅዷል (ሥዕል 2.2)።


ሥዕል 2.2፥ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ስብጥር በዋና ዋና ዘርፎች (በመቶ)




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

**የዘርፎች የሠራተኛ ስምሪት ድርሻ ለውጥ፦** ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ የሰው ኃይል ስምሪት ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወደላቸው ዘርፎች እንደሚሸጋገር ይጠበቃል። በዚህ መሠረት በዕቅዱ ዘመን በግብርናው ዘርፍ የሚሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ በ2005 በጀት ዓመት ከነበረበት 72.7 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 42 በመቶ ዝቅ እንደሚል ይጠበቃል። በአንጻሩ በዚህ ጊዜ በኢንዱስትሪ (ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን እና ማዕድን) የተሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ ከ7.5 በመቶ ወደ 19 በመቶ ከፍ ሲል በአገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራው የሰው ኃይል ድርሻ ደግሞ ከ19.8 በመቶ ወደ 39 በመቶ እንደሚጨምር ታቅዷል።

ሥዕል 2.3፡ የዘርፎች የሠራተኛ ኃይል ስብጥር በ2022 (በመቶ)




ምንጭ፦ የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# 2.3 የፊሲካል ፖሊሲ

በልማት ዕቅዱ ዘመን የመንግስት ገቢና ወጪን ጤናማና ዘላቂ ለማድረግ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢን የሚያሳድግና በአንጻሩ የሀገራችን የዕዳ ጫናን ለመቀነስና በዘላቂነትም ጤናማ የብድር ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት በታክስ ፖሊሲና ሕጎች ዙሪያ ማሻሻያ በማካሄድ፤ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን በማዘመን፤ የታክስ መዋቅሩን በማሻሻልና ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴን በመከላከል ጠቅላላ የመንግስት ገቢን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 395 ቢሊዮን ብር በአማካይ በየዓመቱ በ26.1 በመቶ በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.9 ትሪሊዮን ብር ለማድረስ ግብ ተቀምጧል። ይህን ግብ ለማሳካትም ከታክስ የሚገኘውን ገቢ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 312 ቢሊዮን ብር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.5 ትሪሊዮን ብር ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን በዚሁ ጊዜም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ ከ9.2 በመቶ ወደ 18.2 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። ጠቅላላ የመንግስት ወጪን በተመለከተም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 480 ቢሊዮን ብር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4.5 ትሪሊዮን ብር ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት ጠቅላላ የመንግስት ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት 23.4 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በተመሳሳይ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የካፒታልና የመደበኛ ወጪዎች ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በቅደም ተከተል ወደ 36 በመቶ እና 64 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

ሠንጠረዥ 2.5፡ ጠቅላላ የመንግስት ገቢና ወጪ ዕቅድ

| | 2012 | አማካይ (በቢሊዮን ብር) | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ የመንግስት ገቢ | 395 | 764 | 2,547 | 1,655 | 3,934 |
| የሀገር ውስጥ ገቢ | 354 | 720 | 2452 | 1,586 | 3,818 |
| የታክስ ገቢ | 312 | 637 | 2223 | 1,430 | 3,492 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | 43 | 83 | 229 | 156 | 326 |
| የውጭ ዕርዳታ ገቢ | 41 | 44 | 94 | 69 | 116 |
| ጠቅላላ ወጪ | 480 | 927 | 2,944 | 1,936 | 4,490 |
| የካፒታል ወጪ | 204 | 424 | 1,164 | 794 | 1,617 |
| የመደበኛ ወጪ | 276 | 504 | 1,781 | 1,142 | 2,874 |
| የበጀት ጉድለት | (85) | (164) | (398) | (281) | (556) |
| የወጪ አሸፋፈን | 85 | 164 | 398 | 281 | 556 |
| የሀገር ውስጥ የታክስ ገቢና የበጀት ጉድለት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶ) | | | | | |
| የታክስ ገቢ | 9.2 | 11.6 | 16 | 13.8 | 18.2 |
| የበጀት ጉድለት | 2.5 | 3 | 2.9 | 2.99 | 2.9 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር

የመንግስት በጀት ወጪ ድልድልም ድህነት ተኮርና ለዘላቂ ልማት መሠረት ለሆኑ ለሰው ሀብት ልማት፣ ለመሠረተ ልማት ማስፋፋትና ለአምራች ዘርፎች ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም አዳዲስ የዕድገት ምንጭ ለሆኑ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት ይሆናል። በተጨማሪም የመንግስትን ወጪ ውጤታማነት ለማሳደግ በዕቅዱ የትግበራ ዓመታት የሪፎርም ሥራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የመንግስት የበጀት ጉድለት ብር 556 ቢሊዮን ሆኖ እንደሚመዘገብ የተተነበየ ሲሆን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻም 2.9 በመቶ ይሆናል። የበጀት ጉድለቱ አሸፋፈን በአብዛኛው ከሀገር ውስጥ ምንጮች እንደሚሆን አቅጣጫ ተቀምጧል። ለዚህም በገበያ ሥርዓት የሚመራ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቦንድና የአክሲዮን ገበያን ለመመስረት መንግስት በትኩረት ይሠራል። በዚህም መሠረት በልማት ዕቅድ ዘመን በአማካይ 79 በመቶ የሚሆነው የበጀት ጉድለት ለዋጋ ግሽበት በማያጋልጡ የሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 21 በመቶ ከውጭ ሀገር በሚገኝ ብድር ይሸፈናል።

በሌላ በኩል በዕቅድ መነሻ ወቅት ያለውን ከፍተኛ ሀገራዊ የዕዳ ክምችት ከማቃለል አኳያ የመካከለኛ ዘመን የብድር ስትራቴጂን በመከተል ጤናማ የብድር ሁኔታ ለመፍጠር የሚሰራ ይሆናል። በዚህም ጠቅላላ ሀገራዊ የዕዳ ክምችት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረውን ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 51 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 48.6 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

# 2.4 የገንዘብ ፖሊሲና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ልማት

የገንዘብና የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች እንዲሁም የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ልማት ማክሮ ኢኮኖሚውን በማረጋጋት ሀገሪቱ በልማት ዕቅዱ ዘመን ላቀደችው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ብሎም ለጤናማና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች መሳካት የማይተካ ሚና አላቸው። ከዚህ አኳያ የዋጋ ግሽበት በአማካይ ከነጠላ አሃዝ የዘለለ እንዳይሆን ለማድረግ የገንዘብ ፖሊሲው ይህን ግብ በሚያሳካ መልኩ ይቃኛል። በተጨማሪም የመንግስት የበጀት ጉድለት የዋጋ ግሽበትን በማያስከትል መልኩ እንዲሸፈን ገበያ መር የመጀመሪያና የሁለተኛ የሰነዶች ሽያጭ ገበያ እንዲሳለጥ በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የመንግስት የበጀት ጉድለት በዋናነት ከገበያ እንዲሸፈን ይሠራል።

የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመንን ለማረጋጋጥ እና የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት የሚመራ የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር ይደረጋል። የፋይናንስ ኢንዱስትሪው የታቀደውን መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያግዝ ለማድረግ የወለድ ምጣኔ ተመን በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት እንዲመራ የማድረግ እና ዲጂታል የፋይናንስ ሥርዓት የሚዘረጋ ይሆናል። ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ የካፒታል አካውንት ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግና የተሳለጠ የካፒታል ገበያን በመፍጠር አማራጭ የልማት ፋይናንስ ምንጮችን ለማስፋት የሚሰራ ይሆናል።

የተረጋጋና በነጠላ አሃዝ የተገደበ የዋጋ ሁኔታን ከማረጋገጥ አንጻር በዕቅድ ዘመኑ አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦት መጠንን (broad money) በአማካይ በየዓመቱ በ21 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በተመሳሳይ በዕቅድ ዘመኑ የመሰረታዊ ገንዘብ (base money) የመስፋፋት ምጣኔ በአማካይ በየዓመቱ በ19 በመቶ በማደግ መሠረታዊ ገንዘብ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት በነበረበት 7.3 በመቶ ለማቆየት ግብ ተጥሏል (ሠንጠረዥ 2.6)። ይህም ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲን በመከተል የዋጋ ግሽበትን በነጠላ አሀዝ ለመገደብ ከተያዘው አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ነው።

ሠንጠረዥ 2.6: የገንዘብ አቅርቦት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 |
|---|---|---|---|---|
| መሠረታዊ የገንዘብ አቅርቦት | 7.3 | 7.3 | 7.3 | 7.3 |
| ጠቅላላ የገንዘብ አቅርቦት | 30.8 | 34.3 | 36.8 | 35.5 |

ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ከበጀት ውጪ ለሚከናወኑ በግሉ ዘርፍና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ለሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትልቅ የፋይናንስ አቅምን ከማረጋገጥ አንጻር በልማት ዕቅዱ ዘመን የባንኮች ዓመታዊ ቁጠባ በአማካይ በ28.6 በመቶና የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ዓመታዊ ቁጠባ በአማካይ በ30 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በዚህም አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን (deposit position) በ2012 ከነበረበት ብር 1.04 ትሪሊዮን በአማካይ በየዓመቱ በ22.4 በመቶ በማደግ በ2022 ወደ ብር 7.9 ትሪሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

# 2.5 የልማት ፋይናንስ

የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ በኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ በዘላቂ ሰላም፣ በመልካም አስተዳደር፣ በፍትሕና ቀጠናዊ ትስስር ግንባታ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ ፋይናንስ ነው። የፋይናንስ ዕቅድ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህም በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድና ከበጀት ውጭ የሆነ የፋይናንስ ዕቅድ ናቸው።

**በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድ፡-** በመንግሥት ገቢና ወጪ ትንበያ መሠረት በልማት ዕቅዱ ዘመን ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ የውጭ እርዳታን ጨምሮ የጠቅላላ ወጪን 88.7 በመቶ እንደሚሸፍንና ቀሪው 11.2 በመቶ በበጀት ጉድለት እንደሚታይ ትንበያው ያሳያል። ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ በዕቅድ ዘመኑ ብር 19.3 ትሪሊዮን የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ውስጥ መደበኛ ወጪ ብር 11.4 ትሪሊዮን እና የካፒታል ወጪ ብር 7.9 ትሪሊዮን እንደሚሆን የመንግሥት ገቢና ወጪ ትንበያ ያመለክታል።

በዕቅድ ዘመኑ በየዘርፉ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ በዘርፍ ተነጥሎ ሲታይ ለእቅዱ ዘመን ከተተነበየው ብር 7.9 ትሪሊዮን ከጠቅላላ የመንግስት የካፒታል ወጪ ውስጥ የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች የ24.8 በመቶ እና የመሠረተ ልማት ዘርፎች የ43.3 በመቶ ድርሻ እንደሚኖራቸው ትንበያው ያሳያል። የሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ከጠቅላላ የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ ውስጥ 21.9 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይወስዳል። ሌሎች በዕቅዱ ውስጥ የተካተቱ የልማት ሥራዎች ቀሪውን 10 በመቶ የካፒታል ወጪ ድርሻ እንደሚይዙ የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያው ያሳያል። ዝርዝሩ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 2.7 ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 2.7፡ የበጀት ነክ የካፒታል ወጪ ፍላጎት ትንበያ በዘርፍ ከጠቅላላ የካፒታል ወጪ ያለው ድርሻ (በመቶኛ)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ኢኮኖሚ ልማት | 12.9 | 24.5 | 25 | 24.8 | 23.6 |
| መሠረተ ልማት | 52.8 | 41.6 | 45 | 43.3 | 49.7 |
| ሰው ሀብት ልማት | 23.1 | 23.8 | 20 | 21.9 | 16.7 |
| ሌሎች ዘርፎች | 11.2 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| ጠቅላላ የካፒታል ወጪ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር

**ከበጀት ውጪ የሆነ የፋይናንስ ምንጭና የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ፍላጎት፡-** በአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን፣ ከበጀት ውጭ የሆነ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ፋይናንስ ከባንክና ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቁጠባ፣ ከሌሎች ቁጠባ ምንጮች በጠቅላላ 18 ትሪሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል። ከዚህ ውስጥ ባንኮችና አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት በቁጠባና ብድር ተመላሽ የሚሰበስቡት ብር 15.6 ትሪሊዮን ሲሆን ይህም የ86.5 በመቶ ድርሻ አለው። ቀሪው ብር 2.4 ትሪሊዮን (13.5 በመቶ) ከግምጃ ቤት ሰነድ፣ ከመንግስት ቦንድ ሽያጭ፣ ከካፒታል ገበያ (equity market) እና ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮች እንደሚሰበሰብ ትንበያው ያሳያል።

ሠንጠረዥ 2.8፡ በጀት ነክ ያልሆነ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ የፋይናንስ በምንጭ (በቢሊዮን ብር)

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ተቀማጭ ሒሳቦች | 144.6 | 334.8 | 1061.7 | 699 | 1588 |
| ባንኮች | 141.8 | 328.2 | 1037.1 | 683 | 1549.2 |
| አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | 2.8 | 6.6 | 24.6 | 16 | 38.8 |
| ከብድር የተሠበሠበ | 200.7 | 417.1 | 1299.6 | 858 | 1947 |
| ባንኮች | 183.3 | 376.2 | 1147.9 | 762 | 1707.4 |
| አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | 17.4 | 40.9 | 151.7 | 96 | 239.6 |
| ሌሎች የፋይናንስ ምንጮች | 59 | 128.8 | 357.8 | 243 | 526.6 |
| አጠቃላይ የፋይናንስ ምንጭ | 404.3 | 880.7 | 2719.1 | 1800 | 4061.6 |

ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ከበጀት ውጭ የሚቀርበው ጠቅላላ የብድር ፋይናንስ በልማት ዕቅዱ ዘመን ብር 14 ትሪሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለግብርና ዘርፍ ብር 3.4 ትሪሊዮን ብድር ለማቅረብ ዕቅድ ተይዟል፡፡ ይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት 24.3 በመቶ ይሆናል፡፡ ለኢንዱስትሪ ብር 5.7 ትሪሊዮን (40.7 በመቶ) እና ቀሪው ብር 4.9 ትሪሊዮን (35 በመቶ) ለአገልግሎት ዘርፍ እንደሚውል ዕቅድ ተይዟል፡፡

በሠንጠረዥ 2.9 እንደተመለከተው የፋይናንስ ድልድሉ በተቋማዊ ባለቤት ሲታይ ብር 12.2 ትሪሊዮን (87.2 በመቶ) የግሉን ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ለማሟላት የሚውል ሲሆን ብር 1.8 ትሪሊዮን (12.8 በመቶ) በመንግስት የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወጪ ለመሸፈን እንደሚውል በዕቅድ ተይዟል፡፡ በአጠቃላይ በአስር ዓመት የልማት ዕቅዱ ዘመን የታቀደውን የኢንቨስትመንት ምጣኔ ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት፣ ከካፒታል በጀት፣ ከውጭ ቁጠባና ከራስ ጥሪትና ከሌሎች የኢንቨስትመንት ምንጮች በሚገኝ የልማት ፋይናንስ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ 2.9፡ የሀገር ውስጥ ብድር ድልድል

| | 2012 | አማካይ | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ጠቅላላ ብድር አቅርቦት | 290.8 | 591.0 | 2214.2 | 1402.6 | 3262.1 |
| ለግብርና | 34.2 | 122.0 | 553.68 | 337.9 | 880.8 |
| ለኢንዱስትሪ | 155.1 | 289.3 | 857.9 | 573.6 | 1295.1 |
| ለማኑፋክቸሪንግ | 27.2 | 137.3 | 683.36 | 410.3 | 1131.2 |
| ለአገልግሎት | 101.5 | 179.7 | 802.6 | 491.1 | 1086.2 |
| የብድር አቅርቦት (በተቋማዊ ባለቤትነት በቢሊዮን ብር) | | | | | |
| ጠቅላላ ብድር | 290.8 | 591 | 2214.2 | 1402.6 | 3262.1 |
| ለመንግስት ዘርፍ | 96.1 | 115.22 | 242.92 | 179.07 | 326.2 |
| ለየግሉ ዘርፍ | 194.7 | 475.76 | 1971.3 | 1223.53 | 2935.9 |

ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

ሠንጠረዥ 2.10፡ የኢንቨስትመንት ምንጮች (በቢሊዮን ብር)

| | አማካይ (በቢሊዮን ብር) | | | 2022 |
|---|---|---|---|---|
| | 2013-2017 | 2018-2022 | 2013-2022 | |
| ኢንቨስትመንት | 1,994 | 5,017 | 3,506 | 7,149 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት | 591 | 2,214 | 1,403 | 3,262 |
| ከካፒታል በጀት | 424 | 1,163 | 794 | 1,617 |
| የውጭ ሀብት ቁጠባ | 467 | 944 | 705 | 1,250 |
| ከራስ ጥሪትና ከሌሎች የኢንቨስትመንት ምንጮች | 512 | 696 | 604 | 1,020 |
| የኢንቨስትመንት (ፋይናንስ) ምንጮች ድርሻ (በመቶኛ) | | | | |
| ኢንቨስትመንት | 36.8 | 37 | 36.9 | 37.3 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር አቅርቦት | 10.6 | 16.1 | 13.4 | 17 |
| ከካፒታል በጀት | 7.7 | 8.6 | 8.2 | 8.4 |
| የውጭ ሀብት ቁጠባ | 8.9 | 7 | 8 | 6.5 |
| ከራስ ጥሪትና ከሌሎች | 9.7 | 5.3 | 7.5 | 5.3 |

ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

# ምዕራፍ ሦስት

## የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

# 3.1 የግብርና ልማት

የግብርናው ዘርፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለማሳደግ ድርብርብ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ለቀጣዮቹ አስር ዓመታት የሚኖረውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የህገሪቱን ሕዝብ የመመገብ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ የማስገኘት፣ የመዋቅራዊ ሽግግርን እውን የማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች በቂ ምግብ፣ ግብዓትና የሰው ኃይል የማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት የማጎልበትና በስፋት የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራ ከግብርናው ዘርፍ ይጠበቃል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የግብርና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፦ የሀገራችን የግብርና ምርት በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለዝቅተኛ ምርታማነት የተጋለጠ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የምርት መጠን ከዝናብ መጠን መዋዠቅ እና በየጊዜው ከሚከሰቱ የድርቅ አደጋዎች ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ውጣ ውረዶች ይታዩበታል። ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ በቂ ስላልሆነ ለመስኖ ልማት ትኩረት መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም በቀጣይ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ አነስተኛ፣ መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ ልማቶች በመንግስት፣ በልማት አጋሮች፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በማህበረሰቡ ትብብር የሚገነቡ ይሆናል። ይህን የመስኖ መሠረተ ልማቶች ተጠቅሞ በዓመት ውስጥ ያሉንን የምርት ወቅቶች ወደ 3 ወይም 4 ከፍ በማድረግ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥም በላይ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲኖረው ይደረጋል። የመስኖ ግንባታዎች ኢንቨስትመንት ቅደም ተከተል በሚሰጡት ጥቅምና በመረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል። በአጠቃላይ ለመስኖ ሥራ ትኩረት በመስጠት በቤተሰብ ደረጃ የውኃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

○ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፦ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። ለሀገራችን መልከዓ ምድርና አግሮኢኮሎጂ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነታቸውን ለአርሶ/አርብቶ አደር በማረጋገጥ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተና የአርሶ/አርብቶ አደሩን አቅም ያገናዘበ ሀገር በቀል የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ፈጠራና ስርጭት ሥርዓትን በማጎልበት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ አደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል። የግብርና ዘርፍ የሚጠቀማቸውን ማናቸውንም የቴክኖሎጂ ግብዓቶችና ማሽነሪዎችን ከግብር ነጻ በማድረግና የሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ሥርዓት በመገንባት ግብርናን ለማዘመን በትኩረት ይሠራል። በዚህም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማቋቋም ከፍተኛ ዕገዛ ይኖረዋል። በተጨማሪም ምርታማነትና የምርት ጥራትን በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የሥራ ዕድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና ለመሳብ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዋና ምሰሶ የግሉ ዘርፍ መሆኑ ቢታወቅም የመንግስት ዘርፍ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የቁጥጥርና ፍተሻ እንዲሁም ክትትል ሥራዎችን ይሠራል። የግሉን ዘርፍ ለማሳተፍ በሚደረገው ጥረት መንግስት የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን ይጠቀማል።

○ በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮችን የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው በማገዝ ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስተርነት ማሳደግ፦ በሀገራችን የአርሶ አደሮች የመሬት ይዞታዎች እጅግ አነስተኛ፣ የተበጣጠሱ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ በመሆናቸው የእርሻ ሜካናይዜሽንንና ሌሎች የተሻሻሉ

የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አዋጪ ካለመሆኑም በላይ የድህረ ምርት ማሰባሰብና ጥራት ቁጥጥር ሥራዎችን ለመሥራትም አዳጋች አድርጎታል፡፡ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ዘርፉን ለማዘመን አርሶ አደሮች በመሬታቸው የመጠቀም መብትን እንዲሁም መሬት ነክ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በማይነካ ሁኔታና አሠራሩ አዋጭ በሆነባቸው አካባቢዎች ኩታ ገጠም መሬቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ (land consolidation) የኩታ ገጠም ይዞታ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በረቂቅ የመሬት አጠቃቀም አዋጁ ላይ የተጠቀሱትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀምና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የገጠር መሬት የኩታ ገጠም ይዞታ አሠራርን የማሻሻልና የኮንትራት እርሻ አሠራርን የማጎልበት ሥራ በልማት ዕቅዱ ዘመን በስፋት ይሠራል፡፡

○ የእንስሳት ሃብት ልማትን፤ መኖ ልማትንና ጤናን ማሻሻል፦ የእንስሳት ኃብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ሥርዓትን ከማሻሻልና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል፡፡ በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የኳራንቲን ማዕከላትን አጠናክሮ ወደ ሥራ ማስገባትና ሌሎች ከግብይት ጋር የተያያዙ መሠረተ ልማቶችን በመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሽርክና ማሟላት፤ ዘመናዊ የምርት ዱካ ሥርዓትን መተግበር፤ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ሥርዓቶችን ማሻሻል፤ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ከእንስሳት በሽታዎች የፀዱ ማድረግና ሕገወጥ ንግድን ትርጉም ባለው መልኩ መቆጣጠር በቀጣይ ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡ በተያያዘም በኤክስፖርት ቄራዎችና በአርቢዎች መካከል ቀጥታ የምርት ግብዓት ግንኙነቶችን ማዳበር ትኩረት ይደረግበታል፡፡

○ ሆርቲካልቸር ልማት፦ በክላስተር የተደራጁ አነስተኛ አርሶ አደሮችና ትላልቅ የግል አምራቾች የሆርቲካልቸር ልማት ዋና ምሶሰዎች ናቸው፡፡ የሆርቲካልቸር ልማት ዋና የትኩረት አቅጣጫ የግብዓት አቅርቦት ሥርዓቱን ማዘመን ነው፡፡ ይህም ማለት ገበያ ተኮር የሆነና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟሉ ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዝርያዎችን ማፍለቅና ማሰራጨት እንዲሁም በዘርፉ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግን ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም የዘመናዊ ችግኝ ማፍያ ልማት ስትራቴጂያዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማጠናከር፤ የግብይት ማዕከላትን ለአርሶ አደሩ ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች ማደራጀት፤ የማቀዝቀዣ ማሽኖችን መሠረተ ልማት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማመቻቸት እንዲሁም ከገበያ ትስስር ጋር በተያያዘ በትላልቅ የሆርቲካልቸር ምርት ሰብሳቢዎችና በአርሶ አደሮች መካከል ቅርበት የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

○ በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፦ ባለሀብቱ በዘርፉ ያለውን ተሳትፎ እንዲያሳድግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል፡፡ ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርትና በግብይት መሠረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፎችንና ማበረታቻዎችን በመስጠት በዘርፉ የባለሀብቱ ተሳትፎ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

○ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅምን መገንባት፦ የዘርፉን የማስፈጸም አቅምና ክህሎት ለማሳደግ በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ደረጃ የሰው ኃብት ሪፎርም እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ይህ ሥራ የአገልግሎት ጥራትና ጊዜን የሚያፋጥንና የውሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፍ ነው፡፡ ይህንን ጅማሮ ወደክልል፣ ወደዞንና ወደወረዳ ለማውረድ በቀጣይ የሚሰራ ሲሆን የተቋማዊ መስተጋብሩም ጎን ለጎን እንዲቀናጅ ይደረጋል፡፡

○ የሥራ ዕድል መፍጠር፦ በገጠር የሚኖሩ ሥራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሐዊ፣ ዘላቂና ውጤታማ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ ከዚህም አንጻር በተለይም የተማረ አርሶ አደርና አርብቶ አደርን ለመፍጠርና የዘመነ ግብርናን እውን ለማድረግ

በሜካናይዜሽን አገልግሎትና በመጀመሪያ ደረጃ እሴት አከል ሥራዎች ላይ ወጣትና የተማረ የግብርና አግልግሎት ሰጪዎችን ለመፍጠር እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

○ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት ማካሄድ፦ የአየር ንብረት ለውጥ የዝናብን መጠን በማዛባትና የግብርና ዘርፉን በመጉዳት የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ከማድረጉም በላይ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችና ፀረ ሰብል ተባዮች እንዲከሠቱ ያደርጋል። በመሆኑም በቀጣይ የግብርና ልማት ዘላቂነትን በማረጋገጥና ከግብርና ልማት የሚወጣውን የከባቢ ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት መጠንን በመቀነስ የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

○ በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ ዓላማዎች ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፣ ለኢኮኖሚው መዋቅራዊ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ በተለይም ግብርናን በማዘመን ሀገራዊ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፍላጎትን ማሟላት፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ማቅረብ፣ እሴት መጨመርና በገጠር በቂ የሥራ ዕድል መፍጠር ናቸው። እነዚህን ጥቅል ዓላማዎች ዕውን ለማድረግም ዋና ዋና ስትራቴጂክ ዓላማዎች የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ገበያ ተኮር የእንስሳትና የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ እንዲሁም ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ማሻሻል ናቸው።

○ የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይትን ማሳደግና ማዘመን እንዲሁም በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በግብርና ምርምር፣ በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትና በህብረት ሥራ ማኅበራት የሚገለጹ ቁልፍ የስኬት መስኮችም የዘርፉን ስትራቴጂክ ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ዋና ዋና የውጤት መስኮች ናቸው። የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በተለይም የምግብ ዋስትና፣ የሥርዓተ ምግብ ዋስትናና የሥርዓተ ፆታ ነክ ጉዳዮችን ማሻሻል፣ የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን መቀነስ፣ እንዲሁም የሥራ ዕድል መፍጠር ተጨማሪ ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የእህል ሰብል ምርትና ምርታማነት፦ በሁሉም የአመራረት ሥርዓቶችና የሰብል ዓይነቶች የሰብል ምርትን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት ከ543 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 925 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ የአዝርዕት ምርትን ከ362 ወደ 662 ሚሊዮን ኩንታል፣ የሆርቲካልቸር ምርትን ከ181 ወደ 261 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

○ ከአመራረት ሥርዓቶች በአነስተኛ ይዞታ የሚመረተው ምርት እንዲሁም ከምርት ወቅቶች የመኸር ወቅት ምርት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፣ ከአጠቃላይ አነስተኛ ይዞታ የሰብል ምርት የአዝርዕት ምርት ከ60 በመቶ በላይ ድርሻ የሚሸፍን ነው። ከአዝርዕት ምርት ውስጥ በመኸር ወቅት የሚመረተውን ከ333 ወደ 586 ሚሊዮን ኩንታል፣ በበልግ የሚመረተውን ከ21 ወደ 37 ሚሊዮን ኩንታል፣ በመስኖ የሚመረተውን ከ8 ወደ 38 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ ግብ ተይዟል። የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች የጤፍ፣ ገብስ፣ ስንዴና በቆሎ ምርት በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 57.36 ሚሊዮን ኩንታል፣ 23.78 ሚሊዮን ኩንታል፣ 53.15 ሚሊዮን ኩንታልና 96.28 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 85.48 ሚሊዮን ኩንታል፣ 30.97 ሚሊዮን ኩንታል፣ 87.92 ሚሊዮን ኩንታልና 177.34 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል። ከአጠቃላይ የሰብል ምርት ውስጥ የመካከለኛና የሰፋፊ ባለሀብት እርሻ ምርት ከተደረሰበት የ4 በመቶ ድርሻ ወደ 16 በመቶ የሚያድግ ይሆናል።

○ ከምርታማነት አኳያ የመኸር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች የጤፍ፣ የገብስ፣ የስንዴና የበቆሎ ምርታማነት በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 18.5፣ 25፣ 29.71ና 42.39 ኩንታል በሄክታር በ2022 ወደ 27.21፣ 32.65፣ 48.86ና 74.78 ኩንታል በሄክታር የማድረስ ግብ ተጥሏል። የቡና ምርታማነት በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 6.5 ኩንታል በሄክታር በ2022 ወደ 12 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ የቡና ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 5.6 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 14 ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። የቅድመና ድህረ ምርት ብክነትን ከመቀነስ አኳያ የሰብል ድህረ ምርት ብክነትን በተመለከተ የተቀናጀ ተባይ መከላከል ዘዴን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በማሳደግ በ10 የተመረጡ ሰብሎችና ተባዮች ላይ መከላከል እንዲካሄድ በማድረግ ሊባክን የሚችለው የምርት መጠን በቀጣይ አስር ዓመታት በ1 በመቶ ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

○ የሰብል ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ፦ የምርጥ ዘር አቅርቦት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1.09 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 2.3 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ የአፈር ማዳበሪያ ሥርጭት በ2012 ከደረሰበት 16.1 ሚሊዮን ኩንታል በ2022 ወደ 32.9 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ በዕቅድ ተይዟል። ከዚህ ጎን ለጎን እንደ ኮምፖስት ያሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግና የመሬት አጠቃቀምን በማሻሻል የኬሚካል ማዳበሪያ ፍላጐትን ለመቀነስ መጠነ ሰፊ ጥረት ይደረጋል። በተጨማሪም ጥቅም ላይ የሚውሉ የፀረ አረም፣ ፀረ ፈንገስ፣ ፀረ ተባይ መጠን በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት የ2.5፣ 1.2 እና 0.6 ሚሊዮን ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6.7፣ 0.89 እና 1.8 ሚሊዮን ሊትር በማሳደግ በነዚህ ምክንያቶች ምርት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ ውጥን ተይዟል። በዚህ ረገድ አረምን፣ ፈንገስንና ተባዮችን በዘላቂነት ለመከላከልና በመከላከሉ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውለው የኬሚካል መድሃኒት አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርስ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ዘዴዎች በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላሉ።

○ የተዛማች ተባዮች ፀረ ተባይ መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 15,387 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 100 ሺህ ሊትር ከፍ በማድረግ ተባዮቹ በሰብል ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከ2 በመቶ በታች እንዲሆን ማድረግ፤ የመደበኛ ተባዮች ፀረ ተባይ መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 4.9 ሚሊዮን ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 5.5 ሚሊዮን ሊትር ከፍ በማድረግ የተባዮቹ ጉዳት ከ5 በመቶ በታች እንዲሆን ማስቻል፤ መደበኛ ተባዮች በወረርሺኝ መልክ በሚከሰቱበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውለው የፀረ ተባይ መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 397 ሺህ ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 500 ሺህ ሊትር ከፍ በማድረግ ተባዮቹ በሰብል ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከ10 በመቶ በታች እንዲሆን ማድረግ በልማት ዕቅዱ ዘመን የተያዙ ግቦች ናቸው።

○ የሆርቲካልቸር ምርትና ምርታማነት፦ ለሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ልማት ለባለሃብት የተላለፈ መሬት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 17,595 ሄክታር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 43,091 ለማሳደግ ታቅዷል። ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የሆርቲካልቸር ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 272.8 ሺህ ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1.05 ሚሊዮን ቶን የማድረስ ግብ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከንዑስ ዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢም በዚሁ ጊዜ ከ326.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የ6.7 በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በማስመዝገብ ወደ 950 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማድረስ ታቅዷል። የአነስተኛ ይዞታ የሆርቲካልቸር ምርት በመኸር ከ68 ሚሊዮን ወደ 112 ሚሊዮን ኩንታል፣ በበልግ ከ47 ሚሊዮን ወደ 54 ሚሊዮን ኩንታል፣ በመስኖ ከ65 ሚልዮን ወደ 95 ሚሊዮን ኩንታል የምርት ዕድገት ለማስመዝገብ ግቦች ተቀምጠል።

- የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት፦ በልማት ዕቅድ ዘመን የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማትን በአንድ በኩል ዝቅተኛ ምርታማነትን በዝርያ፣ በአያያዝ፣ በአመጋገብና በጤና አጠባበቅ በማሻሻል የምርት ዕድገት ለማሳየት የታሰበ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በሀገር ውስጥ ከኢንዱስትሪ መስፋፋትና ከኢኮኖሚ መሻሻል ጋር በተያያዘ በሚፈጠር የምርት ፍላጎት የእንስሳት ምርት መጠንና አይነትን ለማሳደግ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።

- የወተት ምርትና ምርታማነት፦ የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 4.37 ቢሊዮን ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 11.8 ቢሊዮን ሊትር ለማድረስ ግብ ተቀምጧል። ከዚህም ውስጥ የላም ወተት ምርት፣ የፍየል ወተት ምርትና የግመል ወተት ምርት በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከደረሱበት 3.63 ቢሊዮን ሊትር፣ 0.1 ቢሊዮን ሊትር እና 0.65 ቢሊዮን ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 9.9 ቢሊዮን ሊትር፣ 0.2 ቢሊዮን ሊትር እና 1.6 ቢሊዮን ሊትር ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ ከአንድ የሀገር በቀል የወተት ላም የሚገኝ ዕለታዊ የወተት መጠን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 1.45 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2.02 ሊትር ለማድረስ እና በአንድ አለባ ወቅት የሚገኘውን አማካይ የወተት ምርት መጠን (lactation milk yield) ከ261 ሊትር ወደ 423 ሊትር ለማሳደግ ታቅዷል። በአነስተኛ ስፔሻላይዝድ ወተት ከብት እርባታ ከተዳቀለች ላም የሚገኘውን ዕለታዊ አማካይ የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 6 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10.7 ሊትር ለማሳደግና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት መጠን በዚሁ ጊዜ ከ1,620 ሊትር ወደ 3,222 ሊትር ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል።

- በተመሳሳይ ሙሉ በሙሉ የውጭ ዝርያ የሆኑ ላሞችን ዕለታዊ የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 13 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 17 ሊትር ለማሳደግና እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት ከ3,920 ሊትር ወደ 5,085 ሊትር ለማሳደግ ግቦች ተቀምጠዋል። በአጠቃላይ የላሞች ወተት ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርብበትን ሥርዓት በማጠናከር የላም ወተት ይደርስበት የነበረውን የ2.6 በመቶ የድህረ ምርት ብክነት ወደ 1.3 በመቶ ለመቀነስና እንዲሁም ጥራቱና ደህንነቱ ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርብ የወተት ምርት ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 46 በመቶ በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 67 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። በተጨማሪም የግመልና የፍየል ወተት ምርታማነትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት በቀን በአማካይ በቅደም ተከተል 2.9 ሊትርና 0.5 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.4 ሊትርና 0.5 ሊትር ለማድረስ ግብ ተቀምጧል።

- ከወተት ላሞች የሚገኘውን ዓመታዊ የወተት ምርት በታቀደው መጠን ለመጨመር እንዲሁም የወተት ላሞች ጥቅል ምርታማነት ትርጉም ባለው መልኩ እንዲጨምር ይረዳ ዘንድ ዝርያቸው የተሻሻሉ እንስሳት ብዛት ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.7 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 17 በመቶ ከፍ እንዲል ይደረጋል። በዚህም በእያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር እጅ ከሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው ላሞች በ2012 በጀት ዓመት በአጠቃላይ 11.5 ሚሊዮን የነበሩት የታላቢ ላሞች ቁጥር በየዓመቱ በ2 በመቶ በመቀነስ በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 9 ሚሊዮን ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል።

- የሥጋ ምርትና ምርታማነት፦ የሥጋ ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 295 ሺህ ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1.7 ሚሊዮን ቶን ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። በተጨማሪም ሥነ ምህዳርን መሠረት ያደረገ የሥጋ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን በመጠቀም የዳልጋ ከብት፣ የበግ፣ የፍየልና የግመል ሥጋ ምርታማነት በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 110፣ 10.5፣ 8.4 እና 250 ኪሎ ግራም ካርካስ ክብደት በቅደም ተከተል በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 120፣ 12፣ 10 እና 278 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዷል።

○ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት፦ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ሥነ ምግብ ፍላጎትን በማሟላት የወጪ ንግድን ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮዎች አያያዝ የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስፔሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚታቀፉትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ማሳደግን መሠረት ያደረገ ሥራ በልማት ዕቅድ ዘመን ይሠራል። በዚህ ረገድ የእንቁላል ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 2.8 ቢሊዮን እንቁላል በ2022 ወደ 5.5 ቢሊዮን እንቁላል የማሳደግ ግብ ተቀምጧል። የዶሮ ስጋ ምርትን በተመለከተም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 48 ሺህ ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 106 ሺህ ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት ከአንድ ስፔሻላይዝድ የተሻሻለ የቤተሰብ እና የባህላዊ ዶሮ እርባታ በዓመት የሚገኘውን የእንቁላል ምርት በቅደም ተከተል 200፣ 188 እና 65 በ2022 ወደ 340፣ 213 እና 115 ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት ከአንድ ዶሮ በዓመት የሚገኘውን የዶሮ ስጋ ምርት ከስፔሻላይዝድ ከተሻሻለ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 2፣ 1.5 እና 1.3 ኪሎ ግራም በ2022 ወደ 2.3፣ 2 እና 2 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዷል።

○ የዓሣ ምርት፦ የዓሳ ምርትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ የምግብና ሥነ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከመደበኛ ውኃ አካላት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት የ59 ሺህ ቶን ምርት በ2022 በጀት ዓመት ወደ 247 ሺህ ቶን ለማድረስ ታቅዷል። ከአኳካልቸር (aqua farming) በ2022 በጀት ዓመት 13 ሺ ቶን ለማድረስ ታቅዷል።

○ የማር ምርትና ምርታማነት፦ የማር ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 59 ሺህ ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 152 ሺህ ቶን ለማድረስ የታቀደ ሲሆን፣ ከአንድ ባህላዊ ቀፎ በአንድ ቆረጣ የሚገኝ የማር ምርት መጠንን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 5.2 ኪሎ ግራም በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 15.4 ኪሎ ግራም ለማሳደግ ታቀዷል። ዘርፉን ለማዘመንና ሽግግር በማምጣት የአርሶአደሩን ግንዛቤ በማሳደግና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን በማሻሻል በ2012 በጀት ዓመት 4 በመቶ የነበረው የተሻሻለ ዘመናዊና ሽግግር ቀፎ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 43 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዷል።

○ የድህረ ምርት ብክነትን መቀነስ፦ የእንስሳትና ዓሣ ምርት የድህረ ምርት ብክነትን የሚቀንሱ መሠረተ ልማቶችን በማመቻቸት የላም፣ የፍየልና የግመል ወተት የድህረ ምርት ብክነትን በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 2.6 በመቶ፣ 10 በመቶ እና 10 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.3 በመቶ፣ 5 በመቶ እና 5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል። የበሬ ሥጋ ድህረ ምርት ብክነትን ከ0.5 በመቶ ወደ 0.3 በመቶ፣ የበግ ሥጋ ድህረ ምርት ብክነትን ከ3 በመቶ ወደ 1.5 በመቶ፣ የፍየል ሥጋ ብክነትን ከ3 በመቶ ወደ 1.5 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል። በተመሳሳይ የግመል ሥጋ ድህረ ብክነትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረት 8 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4 በመቶ ለማውረድ ታቅዷል።

○ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም፦ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ አርሶ/አርብቶ አደሩን የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጅዎችንና የተሻሻሉ አሠራሮችን ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ዓመታዊ የአፈር ብክለትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 20.5 ቶን CO2E በሄክታር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 15.8 ቶን CO2E በሄክታር ዝቅ ለማድረግ፣ እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ ዓመታዊ ተጨማሪ የባዮማስ መጠንን ከ27 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ካርበን ወደ 75.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ካርበን ከፍ ለማድረግ በዕቅድ ተይዟል። በዚህም በየዓመቱ ተጨማሪ የአፈር ካርቦናዊ ቁስ ይዘት በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 1.8 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2.2 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን ለማሻሻል ለ10,000 ተፋሰሶች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት ተቋቁመው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ግብ ተቀምጧል።

○ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥራዎችን በመደበኛ ሥራዎች ዕቅድ ውስጥ በማካተትና በመተግበር በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 36.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 125.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። ለዚህም በሰብል ልማት ዘርፍ በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 7.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅነሳ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 37.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማድረስና በእንሳሳት ልማት ዘርፍ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ሥራዎችን በመደበኛነት በመሥራት ከ12.1 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅነሳ ወደ 48 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ከፍ ለማድረግ ታቅዷል። በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የተጎዱ ቦታዎችን በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራ በማልማትና ተመልሰው እንዲያገግሙ በማድረግ ዓመታዊ ተጨማሪ የተገለለ የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ከተደረሰበት 17.5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የካርበን እኩያ የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ ወደ 40 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተቀምጠዋል፦

○ ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን፦ ግብርና ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በግብርናው ዘርፍ ለማሳካት የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚችል ተቋማዊ መዋቅር፤ የሰው ሃብትና ክህሎት እንዲኖረው ይደረጋል። በፌዴራልና በክልል ደረጃ መልሶ ማቋቋም ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህም ለተቋሙ ከተለዩት የሪፎርም አጀንዳዎች ውስጥ አንዱና ወደ ተግባር የሚተረጎም ሲሆን አደረጃጀቱና የሰው ኃይል ፍላጎቱ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምዘናና የማበረታቻ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር (ለአርሶ/አርብቶ አደሩና ለግሉ ባለሃብት፣ ለማህበራት፣ ለመንግስት ባለሙያዎች) ስትራቴጂ በመቅረፅ ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል።

○ የግብርና ልማትን ዲጅታላይዝ ማድረግ፦ የግብርና ልማትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የግብርና ባለድርሻ አካላት የሚጠቀሙበት የግብርና መረጃ መረብ መሠረተ ልማት (AgriNet) በመዘርጋት የግብርና ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ ጥራት ያለውና ቀልጣፋ አገልግሎትን ለደንበኞቹ መስጠት እንዲቻል ይደረጋል። በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ምክር አገልግሎት፣ የግብዓት ማሰባሰቢያና ስርጭት ክትትል ሥርዓት፣ የግብርና በሽታና አደጋ ክትትልና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት፣ የግብርና ገበያ መረጃ ሥርዓት፣ የግብርና ምርቶች አመራረት ዱካ ሥርዓት፣ የተቀናጀ የግብርና መረጃ ሥርዓት፣ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትና የተሞክሮና እውቀት አስተዳደር ሥርዓት ትኩረት የሚደረግባቸው የማስፈፀሚያ ስልቶች ይሆናሉ።

○ የፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች፦ በሀገር ደረጃ እየተሰራ ያለውን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ መሠረት በማድረግ ግብርናም በዘርፍ ደረጃ የፖሊሲ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች በጥናት በመለየት የዘርፉን ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች ሊፈቱ የሚችሉና ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ስምንት ጉዳዮች እንዲለዩ ተደርጓል። ለዚህም የአሠራር ማሻሻያ የስትራቴጂ ለውጥን እንዲሁም የፖሊሲና የሕግ ለውጦችና ማሻሻያዎችን በማድረግ የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥና ዘርፉ ለጥቅል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ያለውን አስተዋጽዖ በተገቢው መንገድ እንዲወጣ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት ይሠራባቸዋል። በተለይም የግብርና፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ የቴክኖሎጂና

ግብዓት አቅርቦት፣ የግብርና ፋይናንስና ኢንሹራንስ፣ የሀገር ውስጥና የወጪ ንግድ ግብይት፣ አዋጭ የመስኖ ልማትና የውኃ አጠቃቀም፣ አዋጭ የግብርና አገልግሎት መሠረተ ልማት፣ የግል ዘርፍ ተሳትፎን ማሳደግና የግብርና ዘርፍ የማስፈጸም አቅምን የማጠናከር ሥራዎች የፖሊሲ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ይሆናሉ።

○ የገጠርና ከተማ ትስስር፦ የግብርና ልማትን በማፋጠን ሀገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ የገጠርና ከተማ ትስስር ወሳኝ በመሆኑ የተሟላና ውጤታማ የግብርናና ገጠር ልማት ላይ በትኩረት ይሠራል። ለዚህም የተቀናጀ ቤተሰብ ተኮር አሠራሮችን በሙከራ ደረጃ በመፈተሽ በልማት ዕቅዱ ዘመን በስፋት ለመተግበር አቅጣጫ ተቀምጧል። በተለይም በሙከራ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የዘርፈ ብዙ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን ውጥን ማስፋት ላይ በትኩረት ይሠራል። ይህም ቤተሰቦች የተሻለ ገቢ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ የእውቀት ደረጃና ጤናማ ቤተሰብ እንዲኖሯቸው የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል። በተጨማሪም ለአካባቢያቸው ሁለንተናዊ ደህንነት በባለቤትነትና አብሮነት መንፈስ እንዲተጉ የትብብር አውዶችን የሚያመቻችና ለህበረተሰቡ የቀረበ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ልምምድን የሚፈጥር መርሃ ግብር ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም የመንግስት ተቋማትን፣ የህብረተሰቡን፣ የግሉን ዘርፍና መንግሰታዊ ያልሆኑ አጋር አካላትን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችል አሠራርን በዘላቂነት ለመዘርጋት የሚያስችል ሲሆን፣ የመንግስት ተቋማት ተናቦና ተቀራርቦ መሥራትን በሁሉም ደረጃና በተለይም ለህብረተሰቡ ቅርበት ባላቸው አካላት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራትን ዕቅዱ በቅድሚያነት ይዟል።

○ በዚህ የልማት ስልት ተመጋጋቢ የገጠርና የከተማ መስተጋብርን ለመፍጠር የተሻሻለ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፤ አማራጭ የሥራ ዕድል ፈጠራ፤ የተሻሻለ መሰረተዊ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፤ የተጠናከሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ቁልፍ ተግባራት ናቸው። ይህ የልማት ሥርዓት የገጠርና የከተማ መስተጋብር ምርታማነትን በማሻሻል፤ የገበያ አማራጮችን በማስፋት፤ አገልግሎትን በማሳለጥና አመጋገብን በማሻሻል ጤናማና ዘላቂነት ያለው ዕድገት እንዲመዘገብ የራሱን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ አሠራር በተጨማሪም የህብረተሰቡን እምቅ የልማት ኃይልና የማደግ ፍላጎትን አዋህዶ የቤተሰብ ለውጥን በማሳለጥ፣ የቀበሌ፣ ወረዳ፣ ክልልና ሀገራዊ ለውጥን በአጭር ጊዜ በማምጣት የዘላቂ ልማት ግቦችን አካታች በሆነ መልኩ ለማሳካት የሚያስችል ነው።

## 3.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ በየደረጃው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፤ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፤ የነባር ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤ የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያና የመድሃኒት ምርቶችን ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ በማምረት የሀገር ውስጥ ፍላጎቶችን ማሟላትና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤ የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን ለሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አምራቾች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት፤ የወጪ ንግድ ምርቶችን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ማሳደግና የማኑፋክቸሪንግን የእሴት ሰንሰለት፣ ትስስርና ተመጋጋቢነት ማጠናከር ከማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ልማት አንጻር ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ናቸው። በተጨማሪም በጥናት ላይ የተመሠረቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በዘርፉ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በብዛት፣ በጥራትና በአይነት መሳብ፣ ለዚህም የግሉን ዘርፍ ሚናና አጋርነት ማሳደግ፤ የዘርፉን ትስስር ለማሳለጥ በቀጣይ ከባድ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣

የኬሚካልና የፋርማሲቲካልስ እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ልማት ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር፤ የክላስተር አደረጃጀትን ማጠናከር፤ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና በሂደት ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ምቹ መደላድል መፍጠር እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

○ ሀገሪቱ ያላትን የሰው ኃይል፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ ምርቶችን ለማምረት የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ፣ ምርቶቹ በዓለምና በሀገር ውስጥ ገበያ ያላቸውን ተፈላጊነት እንዲሁም በዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር ግምት ውስጥ በማስገባት በልማት የዕቅዱ የመጀመሪያ አምስት ዓመታት (2013-2017) የግብርና ምርቶችን በጥሬ ዕቃነት በሚጠቀም ማኑፋክቸሪንግ ላይ በማተኮር አስተማማኝ የኢንዱስትሪ መሠረት ለመገንባት የሚሰራ ይሆናል። ከዚህ አኳያ በዓለም አቀፍና በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ፣ በተለይም በምግብና ተያያዥ ምርቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል። በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ሀብትና አቅም ሊመረቱ የሚችሉ እንደ አግሮፕሮሰሲንግ በተለይም በምግብ፣ መጠጥ፣ ስኳር፣ ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ላይ ትኩረት በመስጠት ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ይሠራል። የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በተለይም ማዳበሪያና ሌሎች ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። በተጨማሪም እያደገ የመጣውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለማስቀጠል በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን በተለይም ብረታብረትና ሲሚንቶ የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት ትኩረት ይደረጋል። ከዚህ አኳያ በመጀመሪያዎቹ አምስት የልማት ዕቅዱ ትግበራ ዓመታት ቀላል ቴክኖሎጂዎችንና ብዙም የተማረ የሰው ኃይል በማይጠይቁ ዘርፎች ላይ በማተኮር የሚሰራ ሲሆን በተለይም ሀገሪቱ በስፋት ከውጭ የምታስገባቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ለመቆጠብና ሠፊ የሥራ ዕድል መፍጠር በሚያስችሉ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

○ በልማት ዕቅዱ ሁለተኛ አምስት ዓመታት (2018-2022) በቂ ዝግጅት በማድረግ ከፍተኛ ካፒታልና የሰለጠነ የሰው ኃይል ወደሚጠይቁ የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች በመሸጋገር ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚን ለመገንባት ጥረት ይደረጋል። ከዚህ አኳያ ሁለተኛው የአምስት ዓመት የኢንዱስትሪ ልማት ሁለት መልክ ይኖረዋል። አንደኛው በመጀመሪያው የአምስት ዓመት የኢንዱስትሪ ልማት መርሐ ግብር የተተገበሩ ኢንዱስትሪዎችን በማሻሻል ጥራታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ከፍተኛ እውቀትና ካፒታል ላይ የተመሠረቱ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ነው። ከዚህ አኳያ ሀገሪቱ ከውጭ የምታስገባቸውን የካፒታል ምርቶች በሀገር ውስጥ በመተካት ዘርፉን የማበረታታትና የማዘመን ሥራ ትኩረት ይሰጠዋል። በዚህም መሠረት የትራንስፖርት እቃዎችን፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በተለይም ብረታብረትንና ሌሎች ትላልቅ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ሀገሪቱ በኢንዱስትሪ የበለፀገች እንድትሆን የሚሰራ ይሆናል።

○ በአጠቃላይ በዕቅዱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት መርሐ ግብር በውጭና በሀገር ውስጥ ገበያ ያለውን ተፈላጊነት፤ ምርቶቹን ለማምረት የሚያስፈልገውን የቴክኖሎጂ ደረጃ፤ የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅማቸውን፤ ያላቸውን የፊትዮሽና የኋልዮሽ የዘርፎች ትስስርን፤ የወጪ ንግድ ምርቶች ስብጥር ማስፋፋትን፤ የሚጠይቁትን የሙያ ክህሎት ደረጃ፤ የሚያስፈልጋቸውን ካፒታል መጠንና የመሠረተ ልማት ፍላጎትን ታሳቢ በማድረግ በሠንጠረዥ 3.1 በተመለከቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

ሠንጠረዥ 3.1፡ የተመረጡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የትግበራ ቅደም ተከተል ዕቅድ

| ለመጀመሪያው አምስት ዓመታት (2013-2017) | ለሁለተኛው አምስት ዓመታት (2018-2022) |
|---|---|
| ○ አግሮ ፕሮሰሲንግ | ○ ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች |
| ○ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች | ○ ብረታ ብረትና የኢንጂነሪንግ ውጤቶች |
| ○ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት | ○ የትራንስፖርት መሳሪያዎች (አውቶሞቲቭ) |
| ○ መሰረታዊ ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች | ○ የማምረቻ ማሽኖች (የጨርቃጨርቅና የቆዳ) |
| ○ ፋርማሲቲካል እና የሜዲካል እቃዎች | ○ የወረቀት |
| ○ የግንባታ ግብዓቶች (ሲሚንቶና ብረታብረት) | ○ ፕላስቲክ (ፖሊመር) |
| ○ የወረቀትና ህትመት ሥራዎች | ○ የሜዲካል እቃዎች |
| ○ የእንጨት ውጤቶች | ○ የኢንፎርሜሽንና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) |
| ○ የግብርና ግብዓቶች (ማዳበሪያና ፔስቲሳይድ) | ○ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ክፍሎችን ማምረት |
| ○ ስኳርና ሞላሰስ | |
| ○ የፕላስቲክ ውጤቶች | |
| ○ ኤሌክትሮኒክስ የመገጣጠም ሥራ ዎች | |

የቀጣይ አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

○ የነባር አምራቾችን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል፤ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ዘርፉ ለሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማስቻል፤ ስትራቴጂያዊ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፤ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ማምረትና የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በስፋት እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ማሳደግና የንዑስ ዘርፉ ከሀገሪቱ ዘላቂ ልማት ከዘላቂና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን አማካይ የማምረት አቅም አጠቃቀም በ2012 ከነበረበት 50 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ ስትራቴጂክ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶችን በማስፋፋት የሀገር ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶችን ጠቅላላ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ከ30 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 60 በመቶ ማሳደግ፣ የምርት ጥራት ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ሥራን በማሻሻል የንዑስ ዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ታቅዷል።

○ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19 ሺ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 81 ሺ ማሳደግ፣ ጥራት ያለው ኢንቨስትመንት በመሳብና ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውጤት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ አትኩሮ በመሥራት ቅድሚያ በተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችና በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 171,830 በልማት ዕቅዱ ዘመን የ14 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት እንዲያስመዘግብ ማድረግ፣ በአጠቃላይ በልማት ዕቅዱ ዘመን በዘርፉ በድምር የሚፈጠረው አዲስ የሥራ ዕድል ከ5 ሚሊዮን በላይ እንዲሆን ማድረግ የንዑስ ዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚሰማራውን የሰው ኃይል ከኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰርና የሥራ ላይ ሥልጠና በመስጠት የሠራተኛው ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና የኢንዱስትሪ ሥራ ባህል እንዲዳብር ይደረጋል።

○ ተቋማዊ አደረጃጀቶችና ቅንጅታዊ አሠራሮች ለዘርፉ ግቦች ስኬት በሚጠቅም መልኩ ይቃኛሉ። የዕድገት ኮሪደርን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶች አቅርቦት ከፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይደረጋል።

○ የምርትና ምርታማነት እንዲሁም የምርት ስብጥርና ጥራት ማሻሻያ ሥራዎች በስፋት ይከናወናሉ። የጥራት ደረጃውን ያሟላ፣ ያልተቆራረጠ፣ በቂና ፈጣን የምርት ግብዓት አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል። ከዚህ አንጻር አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን እርስ በእርስና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ግብዓት እንዲያቀርቡ የሚደረግ ሲሆን፣ በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የማይችሉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ ለማስገባት የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ቅድሚያ እንዲሰጠው ይደረጋል።

○ የምርምርና ሥርፀት፣ የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና፣ የጥራት ሥራ አመራር፣ የቤንችማርኪንግ፣ የኢንዱስትሪ እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ጨምሮ ትስስር እንዲጎለብትና እንዲጠናከር ይደረጋል። የተጠናከረ ሥራ አመራርና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን የዘርፉ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ይደረጋል።

○ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብና በኮንስትራክሽን፣ በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሠማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲገቡ ምቹ መደላድል ይፈጠራል። ከዚህ አኳያ የተቀናጀ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት፤ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት፤ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ማሻሻያ፤ አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃ ሥርዓት ግንባታና አዳዲስ በውጤት ላይ የተመሠረቱ የኢንዱስትሪ ማበረታቻዎችን ወደ ተግባር ማስገባት ትኩረት ይሰጠዋል።

# 3.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የተሳለጠ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፦ ሥራን ለማሳለጥ ማስተካከያ ከሚፈልጉ ዋና ዋና ጉዳዮች በኮንስትራክሽን ዘርፍ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ሲሆን ከሴክተሩ ውጪ ያሉ ሆኖም ግን በሴክተሩ የሥራ ማሳለጥ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ጉዳዮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት በመሥራት ማስተካከያዎች ይደረጋሉ። ከዚህም ባሻገር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የህብረተሰቡንና የአካባቢ ደህንነትና ጤንነትን ያረጋገጠ እንዲሆን የሚያስችሉ የአሠራር ስርዓቶች ተጠንተው ተግባራዊ ይደረጋሉ።

○ ሥነ ምግባር የተላበሰ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት፦ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ የዲዛይን ጥራት፣ ግልፅነት የጎደለው የጨረታ መስፈርት አወጣጥና የጨረታ አገማገም፣ ተገቢነት የጎደለው የኮንትራት አስተዳደር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የክፍያ አሠራር የግንባታ አፈጻጸም እንዲሁም በጥቅሉ የግልጸኝነትና ተጠያቂነት አሠራር ጉድለት ምክንያት ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጠ አድርጎታል። ይህም ሁኔታ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት እየጎዳ ይገኛል። ስለሆነም በኢንዱስትሪው ያለውን ብልሹ አሠራር የሚያስወግድና ኢንዱስትሪው በሥርዓት እንዲመራ የሚያስችል ግልፅና ተጠያቂነት ያለውን አሠራር የሚያሰፍን ሥርዓት በጥናት ላይ በመመስረትና በማዘጋጀት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

○ በሀገር አቀፍና በክፍለ አህጉር ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት፦ በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከሚፈልገው አንጻር ሲታይ ያሉት የተቋራጮች ብዛት አነስተኛ መሆንና በአቅም ውስንነቶች ምክንያት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛና የገበያ ድርሻቸውም አነስተኛ ነው። ስለሆነም የሀገር በቀል ኩባንያዎች ተሳትፎና የገበያ ድርሻ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲያድግ ለማስቻል የተወዳዳሪነት አቅማቸውን መገንባት የሚያስችሉ አሠራሮች ተጠንተው ተግባራዊ ይደረጋሉ።

○ ሰፊ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ምርታማ የሆነ ፍትሐዊ ገቢ የሚፈጥር፣ ምቹና አዳጊ የሥራ ዕድል መፍጠር፦ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ከዝቅተኛና ከፊል ክህሎት ከሚጠይቁ ወደ መደበኛ ክህሎት የሚጠይቁ የኮንስትራክሽን ሙያዎች እንዲያድጉ ክህሎት ያለው በቂ የሰው ኃይል ለማቅረብ በዕቅድ ዘመኑ የክህሎት ማበልጸጊያ ፕሮግራም በመቅረፅ፣ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪው በስፋት ገብተው የሥራ ዕድል የሚፈጥሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ከውጭ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር በትብብርና በሽርክና እየተቀናጁ እንዲሰሩ በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የ10 ዓመት ትላልቅ (flagship) ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጠር ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ሀገራዊ አቅም በመገንባት በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የሀገር ውስጥ ገበያውን 75 በመቶና የክፍለ አህጉሩን 25 በመቶ የገበያ ድርሻ በሀገር በቀል ኩባንያዎች እንዲሸፈን ማድረግ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ግብዓት ውስጥ ከውጭ የሚገቡ 60 በመቶ ዋና ዋና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ውስጥ 80 በመቶውን በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተኩ በማድረግ ኢንዱስትሪው ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማድረግ፣

ኢንዱስትሪው ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥር ማድረግ፣ እንዲሁም በጥናትና ምርምር በመታገዝና የውጭውን ዓለም የቴክኖሎጂ ዕውቀት በመቅሰም የኮንስትራክሽን ግንባታዎችን የጥራት፣ የወጪና የጊዜ ተወዳዳሪነት ቀጣይነት ባለው መንገድ ማሻሻል ዋና ዋና የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው።

በቀጣይ አስር ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፦

○ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የህብረተሰቡንና የአካባቢ ደህንነትና ጤንነትን ያረጋገጠ ምቹ የሥራ ሁኔታን ለመፍጠርና በጎ ገጽታ ለመገንባት እንዲችል የዘርፉ ተዋናዮችን እርካታ ወደ 75 በመቶ ለማሳደግ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከሚከሰቱ ግጭቶች ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት ሳይደርሱ በስምምነት መፍትሄ የሚሰጣቸው አለመግባባቶችን 75 በመቶ ለማድረስ፣ በጥንቃቄና በጥራት ጉድለት በሰውና በንብረት ላይ የሚፈጠር አደጋ 80 በመቶ ለመቀነስ፣ በዓለም አቀፍ መመዘኛ እንደ ሀገር በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው አማካይ 49.06 በመቶ የተሳለጠ የአሠራር ሥርዓት አፈጻጸም በ2022 በጀት ዓመት ወደ 75 በመቶ ከፍ ለማድረግ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን ብልሹ አሠራር ለመቀነስ በተመሳሳይ ወቅት እንደ ሀገር የተመዘገበውን የአረዳድ ምዘና (Corruption Perception Index) ውጤት ከ114ኛ ደረጃ (37 ነጥብ) ወደ 35ኛ ደረጃ (60 ነጥብ) ከፍ ለማድረግ ይሠራል።

○ የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሀገር አቀፍና በክፍለ አህጉር ደረጃ ያላቸውን ተወዳዳሪነት አቅም በማሳደግ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻቸውን ወደ 75 በመቶና በክፍለ አህጉር ደረጃ ወደ 25 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል። የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት የጊዜ ብክነት በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ እንዲቀንስ እንዲሁም በተመሳሳይ ወቅት በኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውን የዋጋ ተገማችነት በማሻሻል ወደ 50 በመቶ እንዲቀንስ ይደረጋል።

○ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያለውን አስተዋጽዖ በዘላቂነት በማስቀጠል በዕቅድ ዘመኑ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የሥራ ዕድል ፈጠራ በዓመቱ 16.6 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል። በዚህም ከኮንስትራክሽን ዘርፍ በቀጥታ በየአመቱ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 710 ሺህ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3.3 ሚሊዮን እንዲሁም በተመሳሳይ ጊዜ በተዘዋዋሪ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከ1.78 ሚሊዮን ወደ 8.3 ሚሊዮን የሚጨምር ይሆናል። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መሠረታዊ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት በሀገር ውስጥ ምርት ሽፋን 80 በመቶ የሚደርስ ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፦

○ ምቹ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሁኔታ ለመፍጠርና ለማጠናከር የተሳለጠ የአሠራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ የአሠራርና ሥነ ምግባር ኮድ የማዘጋጀት፣ ተቋማዊ አደረጃጀትና የኮንትራት አስተዳደርን የማጠናከር፣ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሠራርን የማስፈን እንዲሁም የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ ለብልሹ አሠራር ተጋላጭነት የመቀነስ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

○ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት አቅም ለማሳደግ እንዲቻል የውጭ ኩባንያዎች ለሀገር ውስጥ ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በቂ ልምድና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያደርጉበት ሥርዓት ይዘረጋል። ትላልቅ የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች በተወሰኑ ሥራዎች ላይ መለስተኛ የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮችን በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሚያሳትፉበትን የሕግ ማዕቀፍ በጥናት ተለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል። የኮንስትራክሽን ሊዝን ጨምሮ ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችና የሽሙር አሠራር ይዘረጋል።

○ ከዲዛይን ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፕሮጀክቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን የቁጥጥር ሥርዓት የሚያጠናክር የኮንትራት አስተዳደርና የፕሮጀክት ማኔጅመንት አሠራርን የማዘመን ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል። የአቅም ግንባታና የመንግስትና የግል አጋርነትን በማጠናከር የግሉን ዘርፍ ሚና የማሳደግ ጥረቶች በስፋት ይከናወናሉ።

○ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያለውን አስተዋጽዖ ለማሳካት እንዲቻል በዕቅድ ዘመኑ ሥራ አጥ ዜጎችን በየአካባቢያቸው በማደራጀትና ተገቢውን የክህሎት ሥልጠና በመስጠት በየአካባቢው በሚከናወኑ የግንባታ ግብዓት ምርትና በተለያዩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በቀጥታ ተሳታፊ ለማድረግ ለአዳዲስ ምሩቃን ተግባር ተኮር ሥልጠና በመስጠት በቀጥታ በግንባታ ሥራ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ይደረጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትም በግንባታ መሳሪያዎች አቅርቦት በስፋት እንዲሳተፉ ይደረጋል። መሰረታዊ የኮንስትራክሽን ግብዓት የሆነው ብረትና የማጠናቀቂያ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱና በገበያው ተፈላጊ እንዲሆኑ የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል።

○ ለሀገር ውስጥ አነስተኛ ድርጅቶች የሙያ ፍቃድና የቁጥጥር ሥርዓትን በመዘርጋት የሥራ ዕድል የማስፋት፣ የግብዓት አቅርቦት ባለቤትነት ሥርዓትን የማስተካከል፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች አቅርቦት ፕሮግራምን የመቅረፅና የማቀናጀት ሥራዎችን ታሳቢ ያደረጉ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

# 3.4 የማዕድንና ነዳጅ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የማዕድንና ነዳጅ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የውጭ ምንዛሪ ግኝትና የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ፦ የወጪ ንግድ ማዕድናት (ወርቅ፣ ጌጣጌጥና የከበሩ ማዕድናት፣ ዕብነበረድ፣ ፖታሽ፣ ታንታለምና ሌሎችም)፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ለዓለም ገበያና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በዓይነት፣ በብዛትና በጥራት የሚቀርቡ ሲሆን፣ ለዚህም የቤተ ሙከራ፣ የቤተ መሳሪያና የመረጃ ማሰራጨት አገልግሎቶች ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ይደረጋሉ። በማዕድናትና ነዳጅ ምርምርና ልማት ጥናት ወቅት ባለሀብቱ የሚያወጣቸው ወጪዎች አግባብነት ያላቸውና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ እንዲሆኑ በማድረግ የሀገራዊ ሀብት ብክነት የመቀነስ፣ የገቢ ምንጮችን አሟጦ የመጠቀም፣ እሴትን የመጨመርና የማጣሪያ ወጪዎችን ለመቀነስ ሀገራዊ አቅም የማሳደግ፣ ምርትና ምርታማነትን የማጎልበት እንዲሁም በዘርፋ የልማት ሥራዎች የገቢ አሰባሰብ ሂደት ላይ ግልፅ የሆነ አሠራርን የመከተል ሥራዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል። የባህላዊና አነስተኛ ማዕድናት አምራቾች እንዲደራጁ ድጋፍ በማድረግ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግና የማዕድናት ምርትና የምርት ውጤቶች ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል።

○ በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና ማጎልበት፦ በዘርፉ ሰፊ ልምድ ያላቸው ዓለም አቀፍ ባለሀብቶች ከሀገር በቀል ባለሀብቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር በሽርክና እንዲሰሩ የማስማማት፤ በማዕድን ሥራዎች ፖሊሲ የተለዩ አምስቱ የማዕድን መስኮች ላይ የምርምርና ሥርጸት ሥራዎችን የማካሄድ፤ የዘርፉ ፕሮጀክቶች በተገቢው የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወኑና ምርታማነታቸው እንዲጨምር የማድረግ፣ የባዮፊውል ቴክኖሎጂን የማስፋፋት፣ የግሉ ዘርፍ ደፍሮ የማይገባባቸውን መስኮች በመለየት በመንግሥት መሪነት የግሉን ዘርፍ በማበረታታት ኢንቨስትመንት የማመቻቸት፤ ለግሉ ዘርፍ ጥናት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ሥርዓት የመዘርጋት፣ የሀገር በቀል አነስተኛና መካከለኛ ባለሀብቶች በብዛት እንዲፈጠሩ በማድረግ ከከፍተኛ ደረጃ ባለፈቃዶች ጋር በትስስር እንዲሰሩ የማድረግ እንዲሁም በዘርፉ ግጭቶችን ለማስወገድ ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ሥራዎች የሚሰሩ ይሆናል። ከማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ የሚጠበቀው ከሀገራዊ ፍጆታና ፍላጎት አንጻር ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መልማት ያለባቸው የዘርፉን ሃብት ክምችት ለይቶ የቅድመ አዋጭነት ጥናት በማካሄድ ለመንግሥትም ሆነ ለግሉ ዘርፍ የኢንቨስትመንት አማራጮች በስፋት እንዲቀርቡ ይደረጋል።

○ በዘርፉ እሴት የሚጨምሩ የማኑፋክቸሪንግ ሥራዎች ኢንዲስፋፉ ማድረግ፦ እምቅ ክምችት መኖሩ በተረጋገጡ ማዕድናትና የተፈጥሮ ጋዝ እሴት ተጨምሮ ለገበያ ማቅረብ እንዲቻል የኢንዱስትሪ ግብዓት ማዕድናትን በተገቢው አይነት፣ መጠንና ጥራት እንዲቀርብ ማድረግና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወይም ወደ ውጪ ተልከው ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ የማዕድን የማኑፋክቸሪንግ ሥራዎች እንዲቋቋሙ የቅድመ አዋጭነት ጥናት በማድረግ ለግሉም ይሁን ለመንግስት የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዲቀርቡ ይደረጋል። የማዕድንና ነዳጅ ምርት አቅራቢ ባለሀብቶች በግላቸው ወይም ከሌላ ባለሀብትና መንግሥት ጋር በመንግስትና የግል አጋርነት በማስተሳሰር የምርት አቅርቦት እሴት ሰንሰለት እንዲጎለብት ይደረጋል። እንዲሁም ዘርፉን ከባለድርሻ አካላትና ከሌሎች አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ጋር ለማስተሳሰር ተገቢውን ጥናት በማከናወንና በመለየት ከማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ ሥራዎች ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል። በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመረቱ የዘርፉ ምርቶች ተገቢው እሴት ተጨምሮ ለገበያ እንዲቀርቡ ቴክኖሎጂ የማላመድ፣ የእሴት ማበልጸጊያ ማዕከላትን የማቋቋምና ሌሎች የድጋፍ ሥራዎች በስፋት ይሰራሉ።

○ የሥራ ዕድል መፍጠር፦ ለሥራ ፈላጊ ዜጎች በማዕድንና ነዳጅ እንዲሁም የነዳጅ ተቋማት ጥናት፣ ልማትና የምርት እንደዚሁም የግብይት ሥራዎች ላይ የሥራ ዕድል ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችና ባህላዊ የዘርፉ አልሚዎች የሥነ ምድር መረጃ ተደራሽ የማድረግና በዘርፉ ሥራዎች ዙሪያ ቴክኒካል ሥልጠናዎችን መስጠትና ከተመረጡ የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር ለማዕድን ዘርፍ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የሰው ኃይል አቅርቦት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብና የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማዕድንና ነዳጅ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዋና ዓላማ የማዕድንና ነዳጅ ሀብቶችን ለይቶ በማወቅ፣ በማልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጡን ማፋጠንና ሀገራዊ ሃብትን ማሳደግ እንዲሁም ዘርፉ ለውጭ ምንዛሪ ግኝትና ሀገር ውስጥ ገቢ የሚኖረውን አስተዋጽዖ በማጉላት፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማስፋፋት፣ ለማኑፋክቸሪንግ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የዘርፉን ምርቶች እሴት እንዲጨምሩ በማድረግና የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፋይዳውን ማሳደግ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማዕድንና ነዳጅ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል።

○ የውጪ ምንዛሪ ግኝትንና የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ በዘርፉ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 160 በ2022 ወደ 660 ለማሳደግ፤ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 50 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1,050 ለማሳደግ፤ በዘርፉ በአገልግሎት መስክ የሚሰማሩ ኢንቨስትመንቶችን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 1,700 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6,700 ለማሳደግ ግብ የተጣለ ሲሆን በኩባንያዎችና ባህላዊ አምራቾች በ2012 በጀት ዓመት ይመረት የነበረውን የወርቅ ምርት መጠን ከነበረበት 3.2 ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 137 ቶን ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

○ ከሥነ ምድር መረጃ ጋር በተያያዘ የማዕድናትን ክምችት ሃብት ማደራጀት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 10 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 40 በመቶ በማሳደግ ለኮንስትራክሽን፣ ለኬሚካል፣ ፔትሮኬሚካል፣ ለኃይል ማመንጫና ሌሎች ተዛማጅ ምርቶች ግብዓት የሚሆን የአለኝታ ክምችት ቦታዎችን በመለየትና በማጥናት ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,600 ጥናቶች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6,000 ጥናቶች ለማድረስ ግብ ተይዟል።

○ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን እሴት የሚጨምሩ የማኑፋክቸሪንግ ሥራዎችን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 30 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 130፣ እንዲሁም በዚሁ ጊዜ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማኑፋክቸሪንግ ብዛት ከ1,500 ወደ 6,500፣ ለኬሚካልና ፔትሮኬሚካል ምርት የሚረዱ ማዕድናትን የሚያመርቱ የማኑፋክቸሪንግ ተቋማትን ብዛት ከ100 ወደ 1,100 ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል። በተጨማሪም የኃይል ምንጭ ማዕድናት ማኑፋክቸሪንግ በ2012 በጀት ዓመት ምንም ያልነበረ ሲሆን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10 ለማድረስ እንዲሁም የጨው ምርት ጥራትና መጠን በመጨመር ከውጭ የሚገባውን የጨው ምርት በ2022 በጀት ዓመት ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት ግብ ተጥሏል።

○ በዘርፉ የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 200 ሺህ የሥራ ዕድሎች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1.8 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማዕድንና ነዳጅ ልማት ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፡

○ የዘርፉን የልማት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የማዕድንና ፔትሮሊየም የፖሊሲዎችና የሕግ ማዕቀፎች ጥናትን መሠረት በማድረግ ይዘጋጃሉ። ዘመናዊ የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ሥርዓትን በመዘርጋት፣ የካዳስተር ሥርዓትን በመተግበር፣ የፔትሮሊየም ዳታ ቤዝን በማዘመን፣ ዘመናዊ የጂኦሳይንስ ኢንፎርሜሽን አገልግሎት ሥርዓትን በመገንባት፣ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጥን በመጀመር እንዲሁም የማዕድን ስኮር ካርድ እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ፣ የዘርፉን የሰው ኃይል አቅም በመገንባትና አደረጃጀቱን በማዘመን እንዲሁም የነዳጅ ጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪ እንዲቋቋም በማድረግ የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ ይደረጋል።

○ የማዕድን ኢንቨስትመንት ሥራ ከአካባቢ ብክለት የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፣ ተግባራዊ ማድረግና በሚለማው ማዕድን አካባቢ የሚገኘውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እንዲሁም በየክልሉ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ቅርንጫፍን በማቋቋም የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል። የቤተሙከራ፣ መሳሪያና ጥናት ማዕከላት በዘመናዊ መልክ ይደራጃሉ።

ከከፍተኛ ትምህርትና ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር ለዘርፉ ጥናት፣ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ባለሙያዎችን የማፍራት እንዲሁም ብቁና በቂ ባለሙያዎችን በዘርፉ ማቆየት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል። የወርቅ ማጣሪያ መሣሪያና ደረጃ ማስጠበቂያ፣ የሳተላይት ምስል መቀበያና መተንተኛ፣ የጂኦሳይንስ ዳታ መተንተኛና ማሰራጫ ሶፍትዌር ፕሮግራም፣ የድሮን፣ የማዕድን ኢንተለጀንስ ትግበራ፣ የማምረቻና የማበልጸጊያ ማዕከላት ይገነባሉ።

# 3.5 የንግድ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የንግድ ዘርፍ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የመፈጸምና የማስፈጸም ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ፣ የዘርፉን ዕድገት ማሳለጥ የሚያስችሉ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፣ የንግድ አሠራሮችን ማዘመን፣ የወጪ ንግድ የምርት መጠን፣ ስብጥርና ጥራትን ማሳደግ፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት አመቺ የሆነ የንግድ ሥርዓት መዘርጋትና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማረጋገጥ ትኩረት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ዘመናዊ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት የምርትና አገልግሎት ጥራትና ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

○ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን፤ ከአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና ሙሉ ተጠቃሚ መሆንና ከተመረጡ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ ለሀገራችን ምርቶች ሰፊ የገበያ ዕድል መፍጠር ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ። ከዚህ በፊት የነበረውን የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት ሪፎርም በማድረግና የንግድ ተወዳዳሪነትን በማስፈን የሸማቹን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በተጨማሪም የምርት ጥራት ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ሥራን በማሻሻል ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ አስፈላጊው ሥራ ይሠራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የንግድ ዘርፍ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ በሀገር ውስጥ ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ አሠራርና የግብይት ሥርዓትን ማስፈን፣ በእሴት ጭማሪ የላቁ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ለዓለም ገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የዓለም አቀፍና ከባቢያዊ ትስስርን የሚያጎለብቱ የንግድ ስምምነቶችን በማጠናከር የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ ለዕቅዱ ዘመን የተቀመጡ የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የንግድ ዘርፍ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል።

○ የንግድ ሥራን ለመጀመር ያለ አመቺነት ነጥብን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 48 በ2022 ወደ 80 ከፍ በማድረግ ኢትዮጵያን በ2022 በጀት ዓመት ከቀዳሚ 50 ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ ታቅዷል። በሀገር ውስጥ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን በመቆጣጠር የምርት ጥራታቸውን፣ ደህንነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ በቁጥር በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 300 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 610 ለማሳደግ ታቅዷል።

○ በሀገር ውስጥ ለተመረቱና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አስገዳጅ የሆኑ ምርቶች የሚደረግ የቁጥጥር ሥራን ከ28 የምርት ዓይነቶች ወደ 68 የምርት ዓይነቶች ለማሳደግ፤ በገቢ ምርቶች ላይ የሚደረግ የምርት

ጥራት ፍተሻን ከ2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ወደ 3.5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ከፍ ለማደረግ፤ የወጪ ምርቶች ላይ የሚደረግ የምርት ጥራት ፍተሻን ከ650,000 ሜትሪክ ቶን ወደ 1.1 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ተግባርን በቁጥር ከ1.1 ሚሊዮን ወደ 2.1 ሚሊዮን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

○ ለሀገራችን ምርቶች የገበያ ዕድል ለማስፋት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድሮችን የማጠናቀቅና የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቶችን ተግባራዊ የማድረግ እንዲሁም ከተመረጡ 7 ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነቶችን የመፈራረም ግቦች ተቀምጠዋል። ከዚህ አንጻር የንግድ ድርድሮችን፣ ግንኙነቶችንና የገበያ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በማከናወን ዋና ዋና የውጭ ገበያ መዳረሻዎችን በልማት ዕቅዱ ዘመን በቁጥር ከ37 ወደ 96 ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

○ የዓለም አቀፍ ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ደረጃዎችንና ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ በፍላጐት ላይ የተመሠረቱ 3,055 ሀገራዊ አዳዲስ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዷል። ፀረ ውድድር የንግድ ተግባራትንና የሸማች መብት ጥሰቶችን በመከላከል የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ የገበያ ግልፀኝነት ሽፋንን ከ40 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ እንዲሁም የሀገር ውስጥና ድንበር ተሻጋሪ የቅድመና የድህረ ውህደት ቁጥጥር አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ከ96 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

○ በአጠቃላይ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 18.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከግብርና 6.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ 9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ ከማዕድን 2.1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላርና ከኤሌክትሪሲቲና ሌሎች 0.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የንግድ ዘርፍ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ ዘርፉ በአሠራር፣ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት እንዲጠናከር ይደረጋል። ከዚህም አንጻር ቅንጅታዊ አሠራርን የማጎልበት፤ የሥራ አመራርና የቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባትና የንግድ አሠራር ምቹነትና የሪፎርም ሥራዎችን ውጤታማ የማድረግ ሥራዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ። በተጨማሪም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን የማዘመንና በጥናት ላይ የተመሠረተ የግብይት ሰንሰለትና የጥራት ቁጥጥር ሬጉላቶሪ ሥራዎች ሪፎርም ይካሄዳሉ። በዚህም የተሟላና የተጠቃለለ የንግድ ፓሊሲ ይቀረጻል። ሕገ ወጥ ንግድን በተጠናከረ መልኩ ለመቀነስ የተሻሻለ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል። አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃ ሥርዓት ይገነባል። እንዲሁም ዘመናዊ የምርት ማቆያ፣ የማዘጋጃና የግብይት ማዕከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል። የምርት ጥራት ደረጃዎች መወሰኛ ስትራቴጂን ቀርፆ ተግባራዊ በማድረግ ምርቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችን የማውጣትና የመቆጣጠር ሥራ ይሠራል።

○ ንግድን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች (Ease of Doing Business) እንዲዘምኑ፣ ዲጂታል መር የሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍንና መሰረታዊ የሆኑና ለንግድ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ አስፈላጊው ፋይናንስ እንዲቀርብ ይደረጋል። በሌላ መልኩ ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር የመንግስት ግዥ ለሀገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ የሚሰጥበት ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል።

# 3.6 የከተማ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የከተማ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ በሀገሪቱ የሚታየው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አንዱ የከተሞች የልማት ገፅታ ነው። ከዚህ አኳያ ከተሞች የኢኮኖሚ ልማትና የሥራ ዕድል ፈጠራ ምንጭ እንዲሆኑ በከተሞች ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለከተማ ግብርና፣ ለማዕድንና ለቱሪዝም ልማት ትኩረት ይሰጣል። በዚህም መሠረት የሥራ ፈጠራ ክህሎትንና የቢዝነስ መፈልፈያና ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በማደራጀት ብሎም የፋይናንስ አቅርቦትና የገበያ ትስስርን በማጠናከር የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕድገትን ማፋጠን ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል። በተጨማሪም የካፒታልና የሰው ኃይል ፍልሰትን በየአካባቢው በመግታት የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማስፋፋትና አነስተኛና መካከለኛ ከተሞችን ለማልማት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የከተሞችን ልማት ለማፋጠንና ፍትሐዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመሬት አቅርቦት በበቂ መጠንና በዘላቂነት እንዲቀርብ ይደረጋል።

○ ከተሞች ልማትን የሚያፋጥን እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው በሚያስችል መልኩና ሚዛኑን የጠበቀና ያልተማከለ የአከታተም ሥርዓትን የሚያጠናክር ዕቅድና ትግበራ በሁሉም ደረጃ እንዲኖር በማድረግ በከተሞች የሚስተዋለውን የቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ለማጥበብ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የተለያዩ የቤት ፕሮግራሞችና የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች እንዲኖሩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የገጠር ማዕከላት መኖሪያ ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይደረጋል። የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማትና አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ የከተማ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ጥገና ደረጃ ወጥቶላቸው በበቂ ሁኔታ እንዲቀርቡና በዕቅድ፣ በዲዛይንና በድርጊት መርሐግብር እንዲቀናጁ ይደረጋል። በተጨማሪም በከተማ መሠረተ ልማት አቅርቦት የግሉን ዘርፍ ሚና በማጎልበትና የከተማ መሠረተ ልማት አማራጭ ፋይናንስን በማስፋት፣ አረንጓዴ ልማትን የሚያፋጥን የልማት ስትራቴጂ እንዲሁም ከተሞች ያልተማከለና መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን ዘመናዊ አደረጃጀት ብሎም የአመራርና የባለሙያ ስምሪት እንዲኖራቸው የሚያስችል አቅጣጫ ተግባራዊ ይደረጋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የከተማ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የከተማ ልማት ዋና ዓላማ የከተሞች ልማትንና የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን እንቅስቃሴ በከተማና በገጠር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ በመተግበር ከተማነትን ማሳደግ እንዲሁም ከተሞች አሳታፊና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ ተዋረድ ባለው የተሟላ ዕቅድና ባልተማከለ የከተማ አስተዳደር እንዲመሩ በማድረግ የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕድገትን ማፋጠን ነው። ከዚህ አኳያ የከተሞችን የመሬትና የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳዳር ሥርዓት ውጤታማነት በማሻሻል ምቹ የመኖሪያ አካባቢ የመፍጠር፣ ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ መሠረተ ልማትና የአገልግሎት አቅርቦትን ማሻሻል፣ የከተሞችን ጽዳት አገልግሎትና የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋንና ተደራሽነትን በማሳደግ ከተሞች ለኑሮ ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮሎጂያዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ ማድረግ ነው። በገጠር ማዕከላት የመኖሪያ ቤቶችን ስታንዳርድ ማስያዝ፤ የከተሞችን ኢኮኖሚ በማሳደግ ለኢንዱስትሪ መሠረት የሚጥል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተራፕራይዞች ልማት ሥራዎችን በማስፋፋት ሥራ አጥነትን መቀነስ እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና ሥርዓትን በማስፋት ድህነትን መቀነስ፤ መልካም አስተዳደር በከተሞች ጥልቀት እንዲያገኝ ማድረግ፤ የከተሞችን የፋይናንስ አቅም፣ አስተዳደርና የሃብት አጠቃቀም በማሻሻል በቂና ውጤታማ የከተማ ልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ተጨማሪ ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የከተማ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ በከተሞች ለ15 ሚሊዮን ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የከተማ ሥራ አጥነት ምጣኔን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት የ18.7 በመቶ ምጣኔ በየዓመቱ በአማካይ በ1 በመቶኛ ነጥብ በመቀነስ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 9 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል። በተመሳሳይ ወቅት 2 ሚሊዮን አዳዲስ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲፈጠሩ በማድረግና ከዚህም ውስጥ 10 በመቶ የሚሆኑትን ወደ አነስተኛ ደረጃና 1 በመቶ የሚሆኑትን ወደ መካከለኛ ደረጃ ማኑፋክቸሪንግ በማሸጋገር ለኢንዱስትሪ ዕድገት የሚኖራቸው አስተዋጽዖ እንዲያድግ ይደረጋል።

○ በልማት ዕቅዱ ዘመን 4,000 የሚጠጉ ከተሞችና 14,000 የገጠር ልማት ማዕከላት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የአካባቢያዊ ልማቶችና አገልግሎቶች በተቀናጀ የከተሞች ዕቅድ እንዲመሩ ይደረጋል። በተጨማሪም መሬትን በቁጠባ ለመጠቀም እንዲቻል የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና የካዳስተር ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 60 በመቶ በማሳደግ ከተሞች የመሬት ሀብታቸውን ሙሉ በሙሉ የሚያወቁበትና የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት ይዘረጋል። በዚህም ከሚኖረው ጠቅላላ የከተማ መሬት ፍላጎት ውስጥ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆነው መልሰ እንዲያገኝ ይደረጋል። መሬት ለልዩ ልዩ ልማት የሚቀርብበትን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ በጨረታ የሚቀርበው መሬት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 5 በመቶ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 40 በመቶ እንዲያድግና በተመሳሳይ ወቅት በመንግስት ምደባ የሚቀርበው ድርሻ ከ95 በመቶ ወደ 60 በመቶ እንዲቀንስ ይደረጋል። በተጨማሪም ሁሉም ከተሞች በዕቅድ መመራታቸውን በማረጋገጥ የደቀቁ ከተሞችን መልሶ በማልማት የከተማ ዕቅድን የማያሟሉ የከተማ ክፍሎችን ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 74 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 30 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ይሠራል።

○ በዕቅድ ዘመኑ ከ4.4 ሚሊዮን በላይ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት የከተሞች የቤት አቅርቦት ምጣኔን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 64 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል። የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች 600,000 (በአጠቃላይ ለመገንባት ከታቀዱት ቤቶች 14 በመቶ) የሚጠጉ የመኖሪያ ቤቶች ይገነባሉ። በተመሳሳይ የገጠር ማዕከላት የመኖሪያ ቤቶችን ስታንዳርድ በማስያዝ 2.8 ሚሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች የሚገነቡ ሲሆን ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆኑ አዳዲስና 50 በመቶ የሚሆኑ ነባር ግንባታዎች የጥግግት ስታንዳርድን እንዲያሟሉ ይደረጋል።

○ ለከተሞች ልማት የሚያስፈልግ የፋይናንስ ፍላጎት በዕቅዱ ዘመን ቢያንስ 60 በመቶ የሚሟላ ይሆናል። ከዚህም ውስጥ በከተሞች ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች 10 በመቶ በህብረተሰብ መዋጮ እንዲሸፈን ይደረጋል። ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓትን በመዘርጋት ከልማት ፋይናንስ ወጪያቸው 60 በመቶውን በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ እንዲሁም የከተሞች የበጀት አፈጻጸም 95 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል። አዲስ አበባና ሌሎች የተሟላ ካዳስተር ሊኖራቸው የሚችሉ 6 ከተሞች ቦንድ አሳትመው በመበደር የመሠረተ ልማት በጀት ክፍተታቸውን እንዲሸፍኑ ይደረጋል። የከተሞችን ጽዳት አገልግሎትና የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋንና ተደራሽነትን በማሳደግ ከተሞች ለኑሮ ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ከ20 ሺህ በላይ ሕዝብ ባላቸው ከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት ከ1 በመቶ ያልበለጠ ሽፋን ወደ 50 በመቶ፣ የደረቅ ቆሻሻ ሽፋንን በተመሳሳይ ከ30 በመቶ ወደ 80 በመቶና በሁሉም ከተሞች ደረጃውን የጠበቀና ተደራሽ የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋንን በዕቅድ ላይ ከተቀመጠው የመሬት ድርሻ 30 ከመቶ ሆኖ እንዲለማ በማድረግ በ2012 በጀት ዓመት ስታንዳርዱን ካሟሉ 6 ከተሞች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 200 ከተሞች የሚደርስ ይሆናል።

○ በሀገር አቀፍ ደረጃ 972 ከተሞች በምግብ ዋስትና ሥርዓት እንዲታቀፉ ይደረጋል። በዚህም የመሥራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 3.62 ሚሊዮን የከተማ ነዋሪዎች የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል። በተመሳሳይ የመሥራት አቅም ለሌላቸውና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ለተጋለጡ በጥቅሉ 689,195 ለሚሆኑ የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማንና ህጻናት እንዲሁም ወደ 44,000 ለሚጠጉ የጎዳና ተዳዳሪዎች የማህበራዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍና መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ይደረጋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የከተማ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ ከተሞች የኢኮኖሚ ልማትና የሥራ ፈጠራ ምንጭ እንዲሆኑ በ972 ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሥራ ፈጣራ ማጎልበቻ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ይደረጋል። የኢንተርፕራይዞችን የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ችግሮች ለመፍታት ህንፃዎችና ሼዶች የሚገነቡ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ከተማ አንድ አዲስ ምርት የፈጠራ ሥራ ፕሮጀክት ተግባራዊ ይሆናል። ለዚህም ለኢንተርፕራይዞች አስተማማኝና ውጤታማ የብድር አቅርቦትና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጉ ይደረጋል።

○ በቀዳሚነት መልማት የሚገባቸውና ሀገራዊ ዕድገቱን ከማፋጠን አንጻር ከፍተኛ ሚና ያላቸው ከተሞችና የልማት ቀጠናዎች ተለይተው የርብርብ ማዕከል የሚደረግባቸው ይሆናል። የተቀናጀ ልማትን ለማረጋገጥ የከተማና የአካባቢው ቅንጅት ዕቅድና ትግበራ እንዲኖር ይደረጋል። የመሬት አቅርቦት ለማኑፋክቸሪንግ ቅድሚያ እንዲሰጥ ይደረጋል። በተመሳሳይ የመሬት አቅርቦትን ለማሻሻል ባለይዞታዎች ተጠቃሚ በሚሆኑበት መልኩ የማበረታቻ እንዲሁም በመንግስትና የግል አጋርነት መሬት እንዲለማ የሚደርግበት ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል። በመልሶ ማልማት የባለይዞታዎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ፓኬጆችም ተግባራዊ ይደረጋሉ። በተጨማሪም ገለልተኛና ፍትሐዊ የካሳ ግመታ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል።

○ በከተማና በገጠር ማዕከላት ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለማሳደግ የሚያስችል የቤት ልማት የፋይናንስ ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት አቅርቦት አማራጮችን የማስፋት ሥራ በአዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ይደረጋል። በተመሳሳይ ሀገራዊ የከተማ መሠረተ ልማት ቅንጅት ማስተር ፕላን፤ የከተሞች በጂኦግራፊያዊ መረጃ የታገዘ የመሠረተ ልማት የሀብት ምዝገባና አመራር እንዲሁም የካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ ማኔጅመንት ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል። በተጨማሪም የመሠረተ ልማትና አገልግሎት ሀብት ምዝገባና አስተዳደርን ከካዳስተር መረጃ ምዝገባ ሥርዓት ጋር የማስተሳሰር ሥራ ይሠራል።

○ የግል ዘርፉ በሽርክና በመሠረተ ልማት ፋይናንስ አቅራቢነት፣ በግንባታ፣ ጥገናና አስተዳደር እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ሥርዓት ይዘረጋል። የከተሞችን የፋይናንስ አቅም ለማሳደግ የራሳቸውን ገቢ መጠቀም እንዲችሉና ለከተሞች የመበደር መብት የሚሰጥ የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያ የሚደረግ ሲሆን የከተሞች መሠረተ ልማት ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል። በተጨማሪም የከተሞችን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት የከተሞች ያልተማከለ ተቋማዊ አስተዳደር በጥናት ላይ ተመስርቶ ተግባራዊ ይደረጋል።

○ ቆሻሻን ከምንጩ የመቀነስ፣ መልሶ የመጠቀምና የመልሶ ኡደት መርሆዎችን እንዲሁም ማካካሻ ሥርዓትን መሠረት ያደረጉ የሕግ ማዕቀፎች ይዘጋጃሉ። የግሉ ዘርፍ በአረንጓዴ መሠረተ ልማትና ቆሻሻ አስተዳደር፣ በፋይናንስ አቅራቢነት፣ በግንባታና በጥገና እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ሥርዓት ይዘረጋል። በምግብ ዋስትና ትግበራ የከተማ ነዋሪው የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል ተቋማዊ ሥርዓት ይተገበራል። በተጨማሪም በከተሞች የምግብ ዋስትና ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል።

# 3.7 የባህልና ቱሪዝም ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የባህል ሀብቶችን በማጥናት፣ በመንከባከብና በመጠበቅ ለሀገር ልማት አስተዋጽዖ ያላቸው ማህበራዊ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀምና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ለይቶ ጥቅም ላይ ለማዋል በትኩረት ይሠራል።

○ የሀገሪቱን የቱሪዝም አለኝታዎች በአግባቡ መለየትና ማልማት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ማጠናከርና ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን በማልማትና ነባር መዳረሻዎችን በማጎልበት ብሎም የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነትና መጠን በማስፋፋት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ ውጤታማ የገበያ ትስስር፣ ብራንዲንግና ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን መፍጠርና የገበያ ድርሻን ማሳደግ፣ ዘርፉን በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር በመደገፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

○ በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በዕውቀትና በክህሎት በማብቃት የአገልግሎት አሠጣጡን ማሳለጥ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ ወጥ በሆነ አደረጃጀት ማዋቀር፣ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ ማዘመን እንዲሁም የመንግስትን ሚና መቀነስና የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር ትኩረት ይሰጣቸዋል።

○ በልማት ዕቅዱ ዘመን በዘርፉ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማረም ለሀገር ሁለንተናዊ ብልጽግና አስተዋጽዖ ማበርከት የሚያስችል ዘርፉን በማደራጀት መምራት ይጠበቃል። የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብዝኃ ባህላዊ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ ለመልካም ገጽታ ግንባታና ለዘላቂ ፍትሐዊና ተደራሽ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ማዋል፤ የሀገራችን የቱሪዝም ሃብቶች በባለድርሻ አካላትና በማህበረሰቡ ተሳትፎ በማልማት፣ ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በመፍጠርና የቱሪስት አገልግሎቶችን ጥራት በማጎልበት እንዲሁም ጠንካራ የገበያና ፕሮሞሽን ስትራቴጂዎችን በመተግበር ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግና ከዘርፉ የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ማጎልበት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

○ በልማት ዕቅዱ ዘመን በስፖርት ንዑስ ዘርፍ የህብረተሰቡን የስፖርት ተሳትፎ በማጎልበት ብቁ እና ተወዳዳሪ ዜጋን በማፍራት በዓለም አቀፍ መድረክ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ስፖርቱ ለሀገራዊ ማህበራዊ ልማት እና ብልጽግና እንዲውል ትኩረት ይሰጠዋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የቅርስ እንክብካቤና ጥበቃን ማሳደግ፣ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣ የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት ተሳትፎን ማሳደግ፣ የስፖርት ማዘውተሪያና ማሰልጠኛ ማዕከላትን ማስፋፋት፣ ከአበረታች ቅመሞች የጸዳ የስፖርት ማህበረሰብ መፍጠር፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ የሀገር ውስጥ የጉብኝት ባህል ማሳደግ፣ በዘርፉ የሚፈጠረውን የሥራ እድልን ማሳደግ፣ ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ፣ ሀገራችን በዘርፉ ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚኖራት የዲፕሎማሲ የሁለትዮሽና የሦስትዮሽ ግንኙነቶችን ማጎልበት፣ የመረጃ አስተዳደር ስራዓት ማሳደግ እንዲሁም የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ በዘርፉ ትኩረት የተሰጣቸው ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል።

○ በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ ትምህርትና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገቡ ቅርሶችንና የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን በቅደም ተከተል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ9 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 19 ማሳደግና በዩኔስኮ የተመዘገቡ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶቻችንን ብዛትም በዚሁ ጊዜ በቁጥር ከ4 ወደ 13 ለማድረስ ታቅዷል።

○ የተፈጥሮና የባህል ሀብታችንን ለመንከባከብ የሚያስችል አንድ ሀገራዊ ስትራቴጂና አካታች ብሔራዊ የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሰነድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ በፌዴራል ደረጃ የሚሰሩ ሙዝየሞችን በቁጥር ከ1 ወደ 6 ማሳደግ፣ የተመዘገቡ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በቅደም ተከተል ከ4,286 ወደ 8,800 እና ከ37,950 ወደ 862,000 ለማድረስ ታቅዷል።

○ ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገላቸው የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ቁጥር በልማት ዕቅዱ ዘመን ከ61,674 ወደ 345,229፣ የቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀም ሥራን የሚያሻሽሉ ተግባራትን ከ53 ወደ 73 ቋንቋዎች ለማሳደግ ታቅዷል። በኪነ ጥበብ ዘርፍ በ90 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በ2,800 ወረዳዎች ለማቋቋም እንዲሁም የኪነ ጥበብ አገልግሎትን የሚያገኝ የሕዝብ ቁጥር ከ5.8 ሚሊዮን ወደ 10 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል። የእውቀት ሀብትን ለመጠቀም የሚያስችሉ የተሰበሰቡና የተደራጁ የመረጃ ሀብቶችን በተመለከተ እንደየቅደም ተከተላቸው ከ111,540 ወደ 1.77 ሚሊዮንና ከ82 ሺህ ወደ 1.54 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም የባህልና ጥበባት አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ የባህልና ዕደ ጥበብ ማዕከላት የሚገነቡ ሲሆን፣ የትውፊታዊ መንደር፣ ሁለገብ ብሔራዊ ሙዝየም፣ የቋንቋ ጥናትና ምርምር ተቋም ይመሰረታል።

○ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,348 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2,696 ለማሳደግ እንዲሁም በዚሁ ጊዜ የጎብኝዎችን እርካታ መጠን ከ50 በመቶ ወደ 75 በመቶ ለማሳደግ ግቦች ተቀምጠዋል። በተጨማሪም 59 አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማልማትና በ40 ነባር መዳረሻዎች ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል። የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን በማስተዋወቅና የጉብኝት ባህል እንዲዳብር በማድረግ የጎብኚዎችን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት 23.7 ሚሊዮን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 70 ሚሊዮን ማሳደግ፣ እንዲሁም በሆቴልና ቱሪዝም የሰለጠነ የሰው ኃይልን ቁጥር በማሳደግ ሰልጥነው አገልግሎት የሚሰጡ ሙያተኞችን ከ23 ወደ 59 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል። በተጨማሪም ዘርፉን በማልማትና በማሳደግ ለዜጎች የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ1.64 ሚሊዮን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 5.2 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

○ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የጎብኚዎችን ቁጥር በዚሁ ጊዜ ከ850 ሺህ ወደ 7.3 ሚሊዮን በማሳደግ ከቱሪዝም የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል። ይህንን ግብ ለማሳካት የሚያስችል የዘርፍ አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻያዎች የሚደረጉ ሲሆን የመዳረሻ አስተዳደር ተቋም የመመስረትና የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከልን ወደ ኢንስቲትዩት የማሳደግ ሥራዎች ይከናወናሉ።

○ በስፖርት ዘርፍ ህዝባዊ እና መንግስታዊ የስፖርት አደረጃጀቶች ለማጠናከር በቅደም ተከተል ከ1,257 ወደ 1,579 እና ከ122,904 ወደ 180,631 ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር ከ 27,539 ወደ 51,378 ለማድረስ፣ በግል የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከ3 ወደ 44 ለማሳደግ እንዲሁም ሀገር አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከ63 ወደ 529 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በጤና እና አካል ብቃት የሚያደርግ ህብረተሰብ ክፍል ከ5.6 ወደ 20 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

○ በታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ሥልጠና ፕሮግራም ተተኪ ስፖርተኞች ብዛት ከ2,735 ወደ 49,624 እንዲሰለጥኑ ይደረጋል። በስፖርት ተሳትፎ ከሚደረግባቸው 17 የስፖርት ዓይነቶች ውስጥ ውጤት የሚመዘገብባቸው የስፖርት ዓይነቶች ከ9 ወደ 11 ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ደረጃ በተደረጉ መድረኮች የተሳታፊ አትሌቶች ብዛት ከ1,208 ወደ 3,500 ለማሳደግ እንዲሁም በቀጣዩ 10 ዓመት ውስጥ ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ 3 ውድድሮችን ለማዘጋጀት እና በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚዘጋጁትን የስፖርት ውድድር መድረኮች ከ300 ወደ 1,970 በማሳደግ የተሳታፊዎችን ቁጥር ከ22,000 ወደ 50,000 ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል።

○ የስፖርት ማህበራዊ ልማትና ዲፕሎማሲን ለማሳደግ ስፖርት ከባህልና ቱርዝም ጋር ተሳስሮ ለሀገር ገጽታ ግንባታ፣ ለሥራ ዕድል ፈጣራ፣ ሕዝብ ለሕዝብ ትስስርና አንድነት ለማጠናከር በስፖርት በጎ ፍቃድ አገልግሎት የተሰማሩትን የህብረተሰብ ቁጥር ከ8300 ወደ 103,956 ማድረስ፣ የሴቶችን እና አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በቅድመ ተከተል ወደ 500,000ና 50,000 ለማድረስ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የባህልና ቱሪዝም ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ የአስር ዓመቱን የዘርፍ ዕቅድ ለማሳካት ፖሊሲዎችን ወቅታዊ ማድረግ፣ የፖሊሲ ማስፈፀሚያ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ፣ የባህልና የቋንቋ ጥናት ማዕከላትን በማቋቋም የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃና ልማት፣ የትውን ጥበባት አዳዲስ ፖሊሲዎችን ማውጣትና የዕደ ጥበብ ልማት፣ የባህል ልማት፣ የመዳረሻና የቱሪዝም ምርት ልማትና አስተዳደር ስትራቴጂ ማውጣት የዕቅዱ መተግበሪያ መንገዶች ይሆናሉ።

○ የቱሪዝም የሰው ኃብት ልማት፣ የገበያና ፕሮሞሽን፣ የቱሪዝም አገልግሎቶች ልቀት፣ የቱሪስት መረጃ ስርጭት፣ የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ በቱሪዝም ልማት የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት፣ ፍትሐዊ የቱሪዝም ንግድን ማረጋገጥ፤ የቱሪስት ደህንነትና ጥበቃ ማቋቋም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ማሻሻያ ሥራ፣ የቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ማሻሻያና የቅርስ ጥበቃና ልማት ማሻሻያ፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት፤ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የማሻሻያ ሥራዎች የሚከናወኑ ሲሆን የማስፈፀሚያ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ማስተካከያዎችን ማውጣትና መተግበር እንዲሁም በዘርፉ የሚካሄዱ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችና የአደረጃጀት ለውጦች የማስፈፀሚያ ስልቶች ይሆናሉ።

○ በመጠናቀቅ ላይ ያለው የስፖርት ፖሊሲ ክለሳ እና የስፖርት ሕግ እንዲሁም የስፖርት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ፣ የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያ ፕሮግራም እና የፀረ አበረታች ቅመሞች ስትራቴጂ እና ልዩ ልዩ ሰነዶች ተዘጋጅተው ይተገበራሉ።

# ምዕራፍ አራት

## የመሠረተ ልማት ዕቅድ

# 4.1 የትራንስፖርት ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የትራንስፖርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት አቅርቦትንና ጥራትን ማሻሻል፦ በቀጣይ ልማት ዕቅዱ ዘመን የመንገድ ዝርጋታዎች ልማት ኮሪደሮችን መሠረት አድርገው እንዲገነቡ የሚደረግ ሲሆን ሁሉን አቀፍ የመንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም (URRAP) አጠናክሮ በማስቀጠል ሁሉም የሀገሪቱ የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ ከሚያገለግሉ የገጠር መንገዶችና ከዋና ዋና መንገዶች ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል። በተጨማሪም የመንገድ የመንገደኛ ማስተናገጃ ተርሚናሎች፣ ዴፖዎች፣ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎች፣ የበረራ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እና ሌሎች የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ በማድረግ የመንገድና ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ሃብቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ለሕጻናትና ለነፍሰጡሮች ምቹ እና እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል። እነዚህን መሠረተ ልማቶች በአግባቡ በማስተዳደር እና ደህንነታቸው በተከታታይ ጥገና በማድረግ በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንገድ እና ሌሎች የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ድርሻ እንዲያድግ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በሀገሪቷ ዋና ዋና ከተሞች ለብዙሃን ትራንስፖርት እና ለሞተር አልባ ትራንስፖርት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ መንገዶች በመስቀለኛና ዋና ዋና መንገዶች ላይ እንዲኖሩ በማድረግ የተሽከርካሪ ፍሰቱ በማይዋዥቅ ሁኔታ እንዲቀጥል እና ደህንነቱ በዘላቂነት የተጠበቀ የተሽከርካሪ እና የእግረኛ እንቅስቃሴ እንዲኖር ይደረጋል። በሌላ በኩል በትራንስፖርት መሠረተ ልማት ዝርጋታ የተስተዋሉ የመንገድ ወሰን ማስከበር፣ በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ማስፈን፣ የእግረኛ መንገድ ግንባታው በሚፈለገው ደረጃ ማድረግ፣ የመንገድ ግንባታው በወቅቱና በጥራት ማከናወን፣ የመንገድ ሃብት ደህንነትና ሙብት እንክብካቤ ማጎልበት ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

○ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ጥራት ማሻሻል፦ በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሠጡት አገልግሎቶች በዋነኝነት ደህንነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ተደራሽነትን፣ ጥራትንና ቅልጥፍናን እና ግልፅነትን ባጣመረ መልኩ እንዲፈፀሙ ይደረጋል። የመንገድ ልማት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት በማረጋገጥ እና ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም አጠናክሮ በማስቀጠል የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ይበልጥ ይስፋፋል። የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎቱ የግል ባለሃብቱን ባሳተፈ መልኩ እንዲስፋፋ እና ተደራሽ እንዲሆን የሚደረግ ይሆናል። በተለይም በከተማ የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር በመፍጠር እና በትራንስፖርት ዘርፉ መዋቅራዊ የአገልግሎት ለውጥ በማድረግ በዋና ዋና ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎቱን ከአነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ወደ ብዙሃን ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች እንዲሸጋገር እንዲሁም እነዚህ የትራንፖርት አገልግሎቶች ታዳሽ ኃይል እንዲጠቀሙ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከዚህም ተጨማሪ በታዳሽ ኃይል የሚሰሩ የብዙሃን ትራንስፖርት ስልቶችን የማስፋፋትና፣ የትራንስፖርት አቅርቦቱና አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ የተደገፈ እንዲሆን ይሠራል።

○ የሎጂስቲክስ ችግሮችን በመፍታት ቅልጥፍናንና ምርታማነትን ማረጋገጥ፦ የሀገሪቱን ገቢና ወጪ ጭነት የማሳደግ፤ በዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ ሀገሪቷን ያለችበትን ደረጃ የማሻሻል፣ የተቀላጠፈና አስተማማኝ የጉምሩክና የትራንዚት ሥርዓት በመዘርጋት የሎጅስቲክስ ሥራው የተሳለጠ እንዲሆን የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ። የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን ከዲዛይን አቅሙ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን በማድረግ በሎጂስቲክስ ዘርፍ ጉልህ ሚና እንዲወጣ ይደረጋል። በተጨማሪም የአየር ትራንስፖርት

መዳረሻዎችን በማስፋትና በተለይም የካርጎ አቅምን በማሳደግ የሀገራችንን ሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪ ይበልጥ የማሻሻልና የማዘመን ተግባራት ይከናወናሉ።

○ የግል ባለሀብቱ በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ ማሳደግ፦ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ እና አገልግሎት አቅርቦት የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም ለዘርፉ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመንግስት በጀት ብቻ መሸፈን የማይቻል በመሆኑ አማራጭ ፋይናንስና ደጋፊ የገቢ ምንጮችን ለማጎልበት፣ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሳደግ ያሻል። የግሉ ባለሃብት ተሳትፎ ከፋይናንስ አቅም ባሻገር የቅልጥፍናና ውጤታማነት እንዲሁም በአዳዲስ አሠራሮች የዳበረ ተሞክሮ ያለው በመሆኑም በትራንስፖርት ዘርፍ የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ የማሳደግ፣ የመንግስትና የግል አጋርነት ሥርዓትን የማጠናከርና ተግባራዊ በማድረግ በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት ይሰጠዋል።

○ የዘርፉን የማስፈጸምና የመፈጸም አቅምን ማሳደግ፦ የትራንስፖርት ዘርፉን የሰው ኃይል በዘላቂነት በመገንባት የዘርፉን ማስፈፀም አቅም ለማሳደግ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ እንደገና መደራጀት ለሚገባቸው የዘርፉ ተጠሪ ተቋማት ውጤታማ መዋቅራዊ አደረጃጀት በፍጥነት በመፍጠር እና የሰው ኃይሉን በማሟላት የተጀመረውን ለውጥ በተሻለ ደረጃ ማስቀጠል፣ እንዲሁም የተዘረጉ ነባር አደረጃጀቶች፣ ፖሊሲዎች፣ የሕግ ማዕቀፎች እና አሠራሮችን ከወቅታዊ ሁኔታ እና ከህብረተሰቡ አዳጊ ፍላጐት አንጻር በመቃኘት ለህዝቡ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገልጋይ ተኮር እንዲሆኑ ይደረጋል። በተጨማሪም በየደረጃው የሚገኘው አመራር እና ፈፃሚ በዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡ ዓላማዎች እና ግቦችን ማሳካት የሚያስችል ቁመናን እንዲይዝ በክፍተት ላይ የተመሠረተ እና ተከታታይ የሆነ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠና በመስጠት የማስፈጸም አቅም ለመገንባት ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትራንስፖርት ዘርፉን በስርዓተ ትምህርታቸው እንዲያካትቱ በማድረግ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦቱን ማሳደግ እንዲሁም በተጠሪ ተቋማቱ ላይ የሚገኙ የአቅም ግንባታ ማዕከላት ወደ ልህቀት ማዕከላት (Center of Excellence) ደረጃ እንዲያድጉ በማድረግ የዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲበራከት እና የሀገር በቀል አማካሪዎችና የሥራ ተቋራጮች አቅም እንዲጎለብት ጥረት ይደረጋል። ከዚሁ ጎን ለጎን የተቋማትን አሠራር ለማሳለጥ እንዲሁም አገልግሎቱን ለማቀላጠፍ እና ተደራሽ ለማድረግ ለሚያስችል የቴክኖሎጂ ዝርጋታ እና ትግበራ ሥራዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል። የማዘመንና ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን (modernization and institutional transformation) የአሠራር ሥርዓትን ማጎልበት፣ የአየር እና የየብስ ትራንስፖርት የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አሠራሮችን በመዘርጋት አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ የሚያስችል በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም መገንባትም ትኩረት ይሰጠዋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትራንስፖርት ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ ማድረግ፣ የሎጀስቲክስ አገልግሎት ቀልጣፋና አስተማማኝ ማድረግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ እና የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነት እንዲያድግ ማድረግ የትራንስፖርት ዘርፍ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትራንስፖርት ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል።

○ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ፍትሐዊነትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፦ የሀገራችን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ካለበት 144,027 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 245,942

ኪሎ ሜትር ለማሳደግ ታቅዷል። የፍጥነት መንገድ ግንባታን አሁን ካለበት 301 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1650 ኪሎ ሜትር ለማድረስ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ (URRAP) ግንባታ አሁን ካለበት 55,808 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 108,797 ኪሎ ሜትር ለማድረስ እንዲሁም በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መንገዶችን ከ58 ወደ 87 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል። በዚህም ወደ ክረምትና ከበጋ መንገድ ለመድረስ የሚወስደውን ጊዜ በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት አማካይ 1.31 ሰዓት በ2022 በጀት ዓመት ወደ 0.54 ሰዓት ዝቅ ለማድረግ፤ ክረምት ከበጋ ከሚያስኬዱ መንገዶች ከ2 ኪሎ ሜትር በላይ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን ምጣኔ ከ64.6 በመቶ ወደ 47.9 በመቶ ዝቅ ለማድረግ፣ የመንገድ ጥግግትን ከ130.9 ኪሎ ሜትር ወደ 214.3 ኪሎ ሜትር/1000 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

○ ከመንገድ ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ አንጻር፦ተጨማሪ የሕዝብ ትራንስፖርት መናኻሪያዎችን በመገንባት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 690 በ2022 ወደ 732 ለማሳደግ ግብ የተጣለ ሲሆን፣ የከተማ ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች (ዲፖዎች፣ ተርሚናሎች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች እና ፓርኪንግ) ከነበረበት 1008 በ2022 ወደ 2106 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። የጭነት ትራንስፖርት ተርሚናሎችን ከ1 ወደ 23፣ የደረቅ ወደቦች አሁን ካሉበት 8 ወደ 11 ለማሳደግ እንዲሁም በተለዩ ቦታዎች የቀዝቃዛ መጋዘን በመገንባት አሁን ካለበት 3 ወደ 6 ለማሳደግ ታቅዷል።

○ በባቡር መሠረተ ልማት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተጀምረው የነበሩ ሀገራዊ የባቡር ኔትዎርክ ግንባታዎች እንዲጠናቀቁ እንዲሁም አዳዲስ የባቡር መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በመገንባት የሀገሪቱን የባቡር መሠረተ ልማት ሽፋን ከ902 ኪ.ሜ ወደ 4,199 ኪ.ሜ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል። ይህንን በማድረግ ሂደት በዕቅድ የተያዘው የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታ ቀደም ብሎ የተሰራው የባቡር መሠረተ ልማት ማስተር ፕላን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አዋጭነት ከለሳ ተደርጎላቸው የሚሰሩ ይሆናል። በተጨማሪም ነባሩን የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር በሚመለከት አነስተኛ ጥገናና ማሻሻያ ተደርጎበት 200 ኪሎሜትር ተጨምሮበት በድምሩ 410 ኪሎ ሜትር አገልግሎት ላይ ይውላል።

○ በአቪየሽን ዘርፍ ተጨማሪ ደረጃቸውን የጠበቁ ኤርፖርቶችን በመገንባት በ2012 ከነበረበት 22 በ2022 ወደ 28 ለማሳደግ ግብ የተጣለ ሲሆን 6 የመንገደኛ ማስተናገጃ ተርሚናሎች እና 10 ጥርጊያ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ይገነባሉ። በተጨማሪም የሀገር ውስጥ የውኃ ትራንስፖርት መሠረተ ልማት በጣና፣ ባሮ፣ አባያ፣ ጫሞ፣ ህዳሴ ግድብና ጊቤ ወንዝ ላይ በመገንባት የውኃ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዷል።

○ የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ ማድረግ፦ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሕዝብ ትራንስፖርት የተጓጓዙ ተሳፋሪዎች ብዛት በ2012 ከነበረበት 722 ሚሊዮን በ2022 ወደ 1.5 ቢሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል። የትራንስፖርት አገልግሎቱን የተቀናጀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ ለማድረግ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ከ50 ሺህ ሕዝብ በላይ ነዋሪ ባላቸው 69 ከተሞች ላይ የብዙሃን እና ሞተር አልባ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ይደረጋል። በገጠር መንገዶች መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋንን ከነበረበት 67 በመቶ ወደ 100 በመቶ፣ የከተማ ብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሕዝብ የማጓጓዝ ድርሻ 2012 ከነበረበት 34 በመቶ በ2022 ወደ 70 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል። በተጨማሪም ከጎረቤት ሀገራት የሕዝብ ትራንስፖርት ትስስር ብዛትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6 ለማሳደግ ታቅዷል። ሀገር አቋራጭ የባቡር ትራንስፖርት አቅርቦትን በማሻሻል የመንገደኛን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 79.19 ሺህ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 448.6 ሺህ ለማሳደግ እንዲሁም የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን በቀን የማጓጓዝ አቅም ከ75 ሺህ ተሳፋሪ ወደ 200

ሺህ ተሳፋሪ ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የአየር መንገደኞችን ቁጥር በ2012 መጨረሻ ከተደረሰበት ከ10.2 ሚሊዮን በ2022 ወደ 48.4 ሚሊዮን እና የሀገር ውስጥ የአየር መንገደኞችን ቁጥር በ2012 ከተደረሰበት 2 ሚሊዮን በ2022 ወደ 11.8 ሚሊዮን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

○ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፦ በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርስ የሰው ሞት በ10 ሺህ ተሽከርካሪ በ2012 ከነበረበት 34.4 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10 ዝቅ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፣ በባቡር አደጋ ምክንያት የተከሰተ የሞት አደጋን በዓመት በሚሊዮን ኪሎ ሜትር ጉዞ በ2012 ከነበረበት 12 ወደ 1 ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሏል። በዓለም አቀፉ የማሪታይም የሴፍቲ ኦዲት ግኝት በ2012 ከተደረሰበት 3 በ2022 ወደ 0 መቀነስ የታቀደ ሲሆን በዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን የሴፍቲ ኦዲት ደረጃ በ2012 ከተደረሰበት 90 በመቶ በ2022 ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ ታቀደል።

○ የሎጀስቲክስ አገልግሎት ቀልጣፋና አስተማማኝ ማድረግ፦ የሀገሪቱን ገቢና ወጪ ጭነት የማንሳት አቋም አሁን ካለበት 17.7 ሚሊዮን ቶን ወደ 30.41 ሚሊዮን ቶን ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ (LPI) ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት 126ኛ ደረጃ ወደ 40ኛ ደረጃ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

○ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፦ በቀጣይ አስር ዓመታት ከመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ የሚወጣውን የ14 ሚልዮን ቶን ካርበን ተመጣጣኝ (carbon equivalent) ጋዝ ልቀትን በ2022 በ13.2 ሚልዮን ቶን በመቀነስ ሊደርስ ከሚችለው 41 ሚሊዮን ቶን የካርበን ልቀት ወደ 27.8 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ ታቅዷል። በተጨማሪም የማበረታቻና የማትጊያ ሥርዓት በመዘርጋት ለአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ የሆኑ የብዙሃን ተሽከርካሪዎችን እና የግል ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ለማሳደግ ታቅዷል።

○ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም በመገንባት የዘርፉ ውጤታማነት ማሳደግ፦ የመንገድ ዘርፍ የማስፈጸም አቅም በማሳደግ የግንባታ ኘሮጀክቶች ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም አሁን ካለበት 35 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ፣ የመንገድ የፈንድ ገቢ አቅምን በ2012 ካለበት 2.97 ቢሊዮን ብር ዓመታዊ ገቢን ወደ 14.2 ቢሊዮን ማሳደግ፣ መንገድ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች 100 በመቶ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲኖራቸው በማድረግ የመድን ፈንድ ገቢውን አሁን ካለበት 530.965 ሚሊዮን በ2022 ወደ 3.2 ቢሊዮን ማድረስ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት ይሰበሰብ ከነበረው ገቢ 2.39 ቢሊዮን ብር በ2022 ወደ 7.71 ብር ቢሊዮን ማሳደግ፣ በውጭ ሀገር የመርከብ ኩባንያዎች የሚቀጠሩ ኢትዮጵያውያን ባህረኞችን ብዛት ከ4,215 ወደ 40,000 ለማድረስ፣ በመንግስትና የግል አጋርነት የሚተገበሩ 23 ፕሮጀክቶችን በማስጀመር የዘርፉን የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ እንዲሁም በትራንስፖርት ዘርፍ ለ1,425,286 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትራንስፖርት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ የዘርፉን የአስር ዓመት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ሀገራዊ የትራንስፖርት ማስተር ፕላን ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ የክፍያ መንገዶች ግንባታ በመንግስት እና በግል ባለሃብቱ አጋርነት (PPP) መገንባት፣ መንግስትንና የግል ባለሃብቱን በማሳተፍ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የትራንስፖርት መሠረተ ልማትና የሎጂስቲክስ ማዕከላት ማስፋፋት፣ ሀገር በቀል አማካሪዎችና ተቋራጮች በባቡር ፕሮጀክት

አዋጭነት ጥናት፣ ዲዛይንና የሲቪል ወርክ ግንባታ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሚገነቡ ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገዶች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ አሠራር መዘርጋት እና የተናጠል በጀት እንዲመደብላቸው ማድረግ፣ አሁን ያለውን የሁለተኛ ትውልድ መንገድ ፈንድን ወደ ሦስተኛ ትውልድ መንገድ ፈንድ በማሳደግ ሁሉንም የጥገና፣ የመልሶ ግንባታ እና ደረጃ ማሻሻል ወጪዎችን መሸፈን የሚያስችል አቅም መፍጠር፣ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ፍትሐዊነትንና ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚተገበሩ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

○ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፣ የሞተር አልባ ትራንስፖርት ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ በከተማ ትራንስፖርት ሞዶች መካከል ቅንጅት እንዲኖር ማድረግ፣ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ትስስር መፍጠር፣ የትራንስፖርት ኦፕሬተሮች አደረጃጀት እና አሠራርን ማሻሻል፣ የሲቪል አቪዬሽን ሀገራዊ ፖሊሲ ማጽደቅና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የተቀናጀ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማረጋገጥ የሚተገበሩ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

○ ከዚህም በተጨማሪም የመንገድ ትራንስፖርት ደኅንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ የባቡር ዘርፍ ተቆጣጣሪ አካል ማቋቋም እና ወደ ሥራ ማስገባት፣ ዓለም አቀፍ የባህር ድርጅት የሴፍቲ ስታንዳርዶችን መተግበር፣ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት የሴፍቲ ስታንዳርዶች የሚተገበሩ ይሆናል። የሎጂስቲክስ ሥርዓትን እና አገልግሎትን ከማሻሻል አንጻር የብሔራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ፤ የባህር ወደብ ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ፤ የዲሜሬጅ ሕግን ተግባራዊ ማድረግ፤ የኮሪደር ልማት እና ማኔጅመንት አደረጃጀት መፍጠር እንዲሁም አሠራር ሥርዓት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## 4.2 የውኃ ሀብት ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን እና የተፋሰስ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማስፋፋት፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማትን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማስቻል፤ የታዳሽ ኃይል የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፤ የከተሞች ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ማሳደግና ድንበርና ድንበር ተሻጋሪ የውኃ ሀብት ጉዳዮች ፍትሐዊ አጠቃቀምን ማረጋገጥ ላይ በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን የአቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት ማከናወን፤ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ወጥነትና ዘላቂነት ያለውን ድጋፍ ማድረግ በቀጣይ በልማት ዕቅዱ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን እና የተፋሰስ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው

ተለይተዋል፥

○ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦቱን በማስፋፋት የአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ፤ ንፁህ፣ አስተማማኝና በቂ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት በ2022 በጀት ዓመት ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ፤ የከተሞችና ገጠር ሳኒቴሽን አገልግሎት አቅርቦትን ማሳደግ፤ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፤ በ2022 በጀት ዓመት የውኃ ጥራት ደረጃ ማስጠበቂያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ የመጠጥ ውኃ ጥራትን ማረጋገጥ፤ የዋሽና የተፋሰስ ዘመናዊ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፤ በዘርፉ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ አለመኖሩን ማረጋገጥና የውኃ ሀብት አስተዳደርን ማስፋፋትና ማጠናከር ዋና ዋና አላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን እና የተፋሰስ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ በ2022 በጀት ዓመት የገጠር መጠጥ ውኃ አቅርቦት ደረጃን በማሻሻል ከ25 ሊትር በሰው በቀን ከ1ኪ.ሜ ባልበለጠ ርቀት በማዳረስ ሽፋኑን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 54.88 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስና ከዚህም መካከል 50 በመቶ የቧንቧ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤ በ2022 በጀት ዓመት የከተማ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን አገልግሎትን ከ100 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 1፣ ከ80 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 2፣ ከ60 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 3፣ ከ50 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 4 እና ከ40 ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 5 ከተሞች በማቅረብ ሽፋኑን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 58.9 በመቶ ወደ 100 ማድረስና ሁሉም የቧንቧ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በ2022 በጀት ዓመት ድርቅ በተደጋጋሚ በሚያጠቃቸው 100 ወረዳዎች የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም የባለ ብዙ መንደሮች የመጠጥ ውኃ ለማቅረብ ታቅዷል።

○ በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ በ100 ከተሞች መሠረታዊ የተቀናጀ የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ሁሉም የገጠር መንደሮች የመፀዳጃ ቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። በተመሳሳይ ለሁሉም የትምህርትና የጤና ተቋማት የንፁህ የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊውን የቴክኒክና የአቅም ግንባት ድጋፍ በማድረግ የብልሽት ምጣኔን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19 በመቶ ወደ 7 በመቶ ዝቅ ማድረግና የሚባክነውን ውኃ መጠን ከ39 በመቶ ወደ 20 በመቶ ዝቅ ማድረግ፤ በፍሎራይድ የተበከለ ውኃ ተጠቃሚ የሆነውን ነዋሪዎች ቁጥር ከ3.5 ሚሊዮን ወደ 0 ሚሊዮን ዝቅ ማድረግ፤ በ2022 በጀት ዓመት በዘመናዊ የአይ ሲቲ ቴክኖሎጂ የታገዘ የዋሽ ብሔራዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

○ የውኃ ሀብት አለኝታ ዳሰሳና ቁጥጥር በማድረግ በየተፋሰሱ የሚገኘውን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት ፍሰት መረጃዎችን በማደራጀት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ፤ የተፋሰሶቹን ደህንነት በመጠበቅ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሽፋንን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.25 ሚሊዮን ሄክታር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10 ሚሊዮን ሄክታር ሽፋን ማድረስ፤ የመሬትና የውኃ ነክ ሥነ ምህዳር ውህደትና የሥነ ህይወት ስብጥር ለመጠበቅና ለማሻሻል የሚደረጉ ጥረቶችን ማጠናከር፤ የኢኮሀይድሮሎጂ ሰርቶ ማሳያዎችን ቁጥር ከ10 ወደ 55 ከፍ ማድረግ፤ በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ ላይ የሀገራችንን ጥቅም ሙሉ በሙሉ ማስጠበቅ፤ መረጃ ላይ መሠረት ያደረገ የውኃ ሀብት አስተዳደርና ልማት እንዲኖር የተሟላ የተፋሰስ መረጃ ቋት ማደራጀት፤ የገጸ ምድር ውኃ ሀብት የፍሰት መረጃ ከ78 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ እንዲሁም የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት መረጃ ሽፋንን ከ17.95 በመቶ ወደ 35 በመቶ

ከፍ ማድረግ የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን እና የተፋሰስ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ የውኃ ጥራት ማረጋገጫ ፕሮቶኮሎችና ደንቦችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፤ የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ግንባታ ማካሄድ፤ የውኃ ጥራት መመርመሪያ ቁሳቁሶችና ኬሚካሎችን ማቅረብ፤ የውኃ መገኛ አካባቢዎችን ከንርፍ መከላከልና ከንክኪ ነፃ ማድረግ፤ የዋሽ ኮሚቴዎችን ማደራጀት፣ የከተሞች ውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ቦርድ ማደራጀት፣ ለፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ምህንድስና ጥናትና ዲዛይን መሥራትና የገጠርና የከተማ ማህበረሰብ ስለሳኒቴሽን ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመስኖ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሳደግ የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፦ የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት በመስኖ ልማት ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ ዋነኛ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚተገበር ይሆናል።

○ የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማረጋገጥ፦ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና ዝርጋታ በራሱ የሚኖረው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በአካባቢዎች ላይ ያለውን እምቅ የመልማት አቅም በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ለአካባቢውና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የሚኖረውን ፋይዳ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም የመሠረተ ልማት አቅርቦትና ዝርጋታው በቀጣይ የሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ እንዲሆን በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

○ የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማጎልበት፦ የመንግስት ወጪ ሊቀንሱና ሊቆጥቡ የሚችሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ በዘርፉ የሚሰራ ይሆናል። በተጨማሪም የመስኖ መሠረተ ልማት ዝርጋታ የሚፈልገው ፋይናንስ ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር በመንግስት ወጪ ብቻ ለማከናወን አዳጋች በመሆኑ በቀጣይ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን በመከተል ዘርፉ የሚፈልገውን ኢንቨስትመንት ለመሳብ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በዘርፉ የግሉ ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ለማጎልበት የተለያዩ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የመንግስትና የግል አጋርነት በዘርፉ በሰፊው ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

○ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጎልበት የሚያስችል ሥርዓትን መከተል፦ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር አስተሳስሮ ማካሄድ ዘርፉ ከመሠረተ ልማት ዝርጋታ ባሻገር በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የሚኖረውን አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም በቀጣይ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራርን እውን ለማድረግ በትኩረት ይሠራል።

○ ተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሃብት ልማት ማሳደግ፦ በመስኖ ልማት ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት በዘርፉ የሚፈለገውን ክህሎትና ዕውቀት ያሟላ የሰው ኃይልና ተቋማዊ አቅም መገንባት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህም የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የበለጠ በማጎልበት በዘርፉ የተቀመጡ የመስኖ ልማት ግቦችን ለማሳካት ያስችላል። በመሆኑም በቀጣይ ጠንካራ ተቋማዊ አቅምና የመስኖ ዘርፍ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማልማት ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ማስፋፋት፤ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፤ ለተማሩና መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች በዘመናዊ መስኖ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በተፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቅቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማስቻል፤ ተቋማዊ አቅምና የሰው ሃብት ልማትን ማሳደግ፤ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማደራጀት የጥገና ወጪን እንዲሸፍኑ ማስቻል፤ የስርዓተ ፆታና አካል ጉዳተኞች አካታችነትን ማረጋገጥና የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ በመስኖ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የመካከለኛ ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 600 ሺህ ሄክታር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2 ሚሊዮን ሄክታር፣ እንዲሁም የመካከለኛ ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ግንባታ በዚሁ ጊዜ ከ490 ሺህ ሄክታር ወደ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ፣ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ከ2 በመቶ ወደ 20 በመቶ ማሳደግ፣ በ20 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች የውኃ አጠቃቀም ውጤታማነትን ከ30 በመቶ ወደ 50 በመቶ እንዲሁም የሚለማ መሬት መጠን መጠቀምን ከ33 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ የዕቅዱ ዋና ግቦች ናቸው። ለተማሩና መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች በዘመናዊ መስኖ የሥራ ዕድል መፍጠር ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የመስኖ አውታርን በማስፋት ለዜጎች 820,000 የሥራ ዕድል መፍጠር፤ በመስኖ መሠረተ ልማት ጥገና፤ ግንባታና ተዛማጅ ሥራ ለወጣቶች 110,000 ሥራዎች እንዲሁም ለተማሩ ወጣቶች 120,000 የሥራ ዕድል መፍጠር የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ በመስኖ ልማት ዙሪያ የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በተፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቅቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፤ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በማደራጀት የጥገና ወጭን እንዲሸፍኑ እንዲሁም ለመስኖ ልማት አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በማጎልበት የበጀት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ፤ በመስኖ ልማት ዘርፍ የተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሃብት ልማት ለማሳደግ አስቻይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያዎችና ስታንዳርድ ማዘጋጀት፤ ተቋማዊ አሠራርን በማጠናከርና ፋሲሊቲዎችን ማሟላት፤ በመስኖ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችና የመስኖ ተጠቃሚዎችን አቅም መገንባት፤ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

# 4.3 የኢነርጂ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢነርጂ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ፍትሐዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፦ በልማት ዕቅዱ ዘመን የኤሌክትሪክ ሽፋን ባልተዳረሰባቸው የገጠርና ከተማ አካባቢዎች ለማዳረስ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። ለዚህም በዘርፉ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን በአግባቡ በመለየትና በመፍታት ያሉ እምቅ አቅሞች በሙሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። በተጨማሪም በየደረጃው ያሉ አደረጃጀቶችን የበለጠ በማጠናከርና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በሰፊው በማረጋገጥ ፍትሐዊና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ለማረጋገጥ በትኩረት ይሠራል።

○ የንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትንና አማራጭ የፋይናንስ ምንጭን ማሳደግ፦ ወጪ ሊቀንሱና ሊቆጥቡ የሚችሉ ንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል። በተጨማሪም የኢነርጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ትልቅ የፋይናንስ ፍላጎት የሚጠይቅ ከመሆኑ አንጻር ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋምና ጠንካራ የኢነርጂ ዘርፍ ኢንቨስትመንት እንዲፈጠር ማድረግ የግድ ነው። በመሆኑም በቀጣይ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን በመጠቀም ዘርፉ የሚፈልገውን ኢንቨስትመንት ለመሳብ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በኢነርጂ ዘርፍ የግሉ ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ የፖሊሲና የአሠራር ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የመንግስትና የግል አጋርነት በሰፊው ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

○ ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ፦ ባለፉት ዓመታት ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት አሰጣጥን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በርካታ ጉድለቶች ተስተውለዋል። ይህም በዘርፉ ያለው የደንበኞች የአገልግሎት እርካታ ምጣኔ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል። የኤሌክትሪክ አገልግሎት በተደጋጋሚ የመቆራረጥና ለረዥም ጊዜ መጥፋት የደንበኞች ዕርካታን የሚያወርዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሳያዎች ናቸው። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን አስተማማኝ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ዝርጋታን በማረጋገጥ ጥራት ያለውና ስታንዳርዱን የጠበቀ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አሰጣጥን ማጎልበት የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ተግባራዊ ይደረጋል።

○ ተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሃብት ልማት ማሳደግ፦ ውጤታማ የሆነ የኢነርጂ ዘርፍ ልማትን በልማት ዕቅዱ ዘመን ዕውን ለማድረግ ዘርፉ የሚፈለገውን ክህሎትና ዕውቀት ያሟላ የሰው ኃይልና ተቋማዊ አቅም መገንባት ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢነርጂ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ አቅምን ያገናዘበ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ ንፁህ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ለገጠሩ ሕብረተሰብ ማዳረስ፣ ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ማቅረብ፣ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማት መገንባት፣ ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋም እንዲኖር ማድረግ፣ ባለሃብቶች በዘርፉ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ ማበረታታት እንዲሁም ብቃትና ሥነ ምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል መፍጠር የዘርፉ ዋና ዋና አላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢነርጂ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 4478 ሜ/ዋ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 19,900 ሜ/ዋ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር ርዝመት በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 18,400 ኪ.ሜ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 29,900 ኪ.ሜ ማድረስ፣ በዚሁ ጊዜም ኤክስፖርት የሚደረገውን የኢነርጂ መጠን ከ2,803 ጊዋሰ (GWH) ወደ 7,184 ጊዋሰ (GWH) ለማሳደግ ታቅዷል። የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ከማደረስ አኳያም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞችን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 5.8 ሚሊዮን ደንበኞች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 24.3 ሚሊዮን ማሳደግ፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም የግሪድ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎችን ብዛት ከ33 በመቶ ወደ 96 በመቶ እንዲሁም ከግሪድ ውጭ ተጠቃሚ የሆኑ ድንበኞችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 11 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 4 በመቶ መቀነስ፣ የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይልን በውጤታማነት ለመጠቀም የኤሌክትሪክ ብክነትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 19.6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 12.5 በመቶ መቀነስ የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢነርጂ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ አስተማማኝና ዘመናዊ የኃይል መሠረተ ልማት መገንባት፣ አቅምን ያገናዘበ ፍትሐዊ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ ዓለም አቀፍ የጥራት መስፈርቶችን የሚያሟላ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረብ፣ በዘርፉ ዘለቄታዊ ኢንቨስትመንትና ገቢ ለማረጋገጥ ተቋማዊ ገቢን ማሳደግና የንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማስፋፋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

## 4.4 የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማትን ውጤታማ ለማድረግ በቁስ፣ በአሠራር ሥርዓቶችና በሰው ሃብት አቅም ግንባታ ረገድ ሰፋፊ ሥራዎች ይሰራሉ። ከዚህ አኳያ ለኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ ልማቶችን መገንባትና ማደራጀት፣ የሠው ኃብት አቅምን መገንባት፤ ወሳኝ የሆኑ ተቋማትን ማቋቋም መደገፍና ማብቃት፣ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት ትኩረት የሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች ይሆናሉ። ሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባትና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን በመከወን ረገድ ሀገራዊ የዳታ ማዕከል መገንባት፣ የተቋማትን የኢንተርኔት ትስስር ሽፋንና የመጠቀም ደረጃን በማሻሻል በቀጥታ (online) የሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ ሀገር አቀፍ የአድራሻ ሥርዓት መዘርጋት፣ ኮምፒውቴሽናል ቴክኖሎጂዎችንና ብሔራዊ የዳታ ቋቶችን ማልማት እንዲሁም የመንግስት አገልግሎቶችን ተገልጋዮች በኤሌክትሮኒክ አግባብ እንዲያገኙ ትኩረት ይሰጣል።

○ ሀገራዊ ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም ለመግንባት የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለዚህም የቴክኖሎጂ ማጎልበቻ፣ ማላመጃና

ማሸጋገሪያ ኢንተርፕራይዞችንና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ኢንድስትሪዎችን መገንባትና መደገፍ፤ ምርምሮችን ማካሄድና መደገፍ፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ማጎልበት፣ ማልማት፣ ማላመድና ማሸጋገር እንዲሁም ምርት፣ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል የሚያግዙ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችን መፍጠርና ማጎልበት ትኩረት ይሰጣቸዋል። ቴክኖሎጂዎችን ከመምረጥ፣ ከማላመድ፣ ከመጠቀምና ከማስወገድ አንጻር የሬጉላቶሪ ሥርዓት የመዘርጋትና የማጎልበት ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናል። በተጨማሪም ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በማሻሻል ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ ሥርዓቶችን መዘርጋትና ቴክኖሎጂን መሠረት በማድረግ የሥራ ዕድል መፍጠርና ሀብትን ማፍራት ትኩረት የሚሰጣቸው ሥራዎች ይሆናሉ።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ሀገራዊ የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ አቅምን መገንባት፤ የዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤ የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሻሻልና የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ የሬጉላቶሪና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ ለኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ ልማቶችንና ተቋማትን የመገንባትና የማደራጀት ግብን ለማሳካት የስቴስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊያዘምኑ የሚችሉ 9 የመሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ሥራዎችን ለማጠናከር የሚያስችሉ 20 አዳዲስ የኢንኩቤሽን ማዕከለትና 8 የቴክኖሎጂ ማዕከላት፣ የኒውክሌር ፍንዳታ እገዳ (CTBTO) ስምምነትን ለማስፈጸም የሚያስችል አንድ የራዲዮ ኒውክላይድ ጣቢያ፣ 50 ያለማቋረጥ ከሳተላይት መረጃ የሚቀበሉ ጣቢያዎች (CORS)፣ 450 መሠረታዊ የምድር መረጃ መቆጣጠሪያ ነጥቦች (Zero Order)፤ 1000 የምድር መቆጣጠሪያ ነጥቦች (1st order)፤1 የጂኦስፓሻል ላብራቶሪና 1 የጂኦስፓሻል ሰርቨር ሩም ይገነባሉ። በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂና ምርምር ዘርፍ ሊሰማራ የሚችለውን የሰው ሀብት አቅም በመገንባት አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ወደ 5.7 ሚሊዮን እንዲደርስ ይደረጋል።

○ የዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት ዝግጁነትን በማጎልበት ረገድ አሁን ያለውን 1 ብሔራዊ ዳታ ማዕከል የማሻሻልና ተጨማሪ 2 ዳታ ማዕከሎችን የመገንባት ሥራ ይሠራል። በዚህም ብሔራዊ የዳታ ማዕከሎች ብዛት ወደ 3 ያድጋል። ለዲጂታል መታወቂያ ቴክኒካል ድጋፍ በመስጠት ወደ ሥራ አስገብቶ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ነዋሪዎች ተጠቃሚነትን አሁን ካለበት 0 በመቶ ወደ 90 በመቶ የማሳደግ ሥራ ይሠራል። የአድራሻ ፕላትፎርሞችን ለከተሞች በማዘጋጀት የአድራሻ ሥርዓት የሚጠቀሙ ከተሞችን ብዛት ወደ 73 ለማድረስ ታቅዷል። በመንግስት ኔትውርክ ውስጥ የሚካተቱ የመንግስት ተቋማት ሽፋን ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ከነዚህም ውስጥ 85 በመቶው ቢያንስ 10 Mbps ኮኔክሽን እንዲኖራቸው ይደረጋል። 2 የሪሞት ሴንሲንግና 1 ኮምዩኒኬሽን ሳታላይቶች ይመጥቃሉ። አሁን ያሉት 176 የመንግስት የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ወደ 2,500 እንዲደርሱ ይደረጋል። ይህም የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን ሽፋን አሁን ካለበት 2 በመቶ ወደ 85 በመቶ ያሳድገዋል። የኤሌክትሮኒክ ግብይት አገልግሎትን የሚጠቀሙ ተቋማት ብዛት 3,500 የሚደርስ ይሆናል።

○ ከኢንተርፕራይዝ ግንባታ አኳያ 20 ኢንተርፕራይዞች የሳተላይት መረጃዎችን በማጎልበትና በማሰራጨት መስክ እንዲሁም የስፔስ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ በማላመድና በማሸጋገር መስኮች 36 ኢንተርፕራይዞች (8 በግብርና፣ 6 በጤና፣ 12 በኢንዱስትሪና 10 በአካባቢ) ከባዮ ቴክኖሎጂ የምርምር ውጤቶች

በመነሳት ምርትና አገልግሎቶችን ለማሕበረሰቡ በማቅረብ መስክ የሚቋቋሙ ይሆናል። እንዲሁም 50 የተለያዩ የቴክኖሎጂ ስታርትአፕና የፈጠራ ውጤቶች ያላቸውን ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች (10 በግብርና፣ 10 በማኑፋክቸሪንግ፣ 5 በጤና፣ 15 በአገልግሎት፣ 10 በአይሲቲ ዘርፍ) በማበረታታት ወደ ምርትና አገልግሎት አቅርቦት እንዲገቡ ይደረጋል። በአጠቃላይ በዘርፉ 106 ኢንተርፕራይዞች የሚፈጠሩ ሲሆን ይህም በልማት ዕቅዱ መነሻ ወቅት ያለውን ዝቅተኛ ቁጥር በእጅጉ ያሳድገዋል። ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ ለሆኑ ለ3,000 የተመረጡ የቴክ ስታርታፖችን (tech startup) ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ 2,100 የሚሆኑትን ውጤታማ በማድረግ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል። ይህም የቴክ ስታርታፖችን ብዛት በልማት ዕቅዱ መነሻ ወቅት ከነበረበት ዝቅተኛ ቁጥር ወደ 2,100 ያሳድገዋል።

○ የግሉ ዘርፍ የኢኖቬሽን፣ ቴክኖሎጂና ዲጂታላይዜሽን ኢንዱስትሪውን መምራት እንዲችል ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን፣ የግሉ ዘርፍ የሚፈጥረው የሥራ ዕድል ሸፉን በልማት ዕቅዱ መነሻ ላይ ከነበረበት 50 በመቶ ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል። የፖሊሲ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ የቴክኖሎጂ ሙያ ማኅበራትን ቁጥር ከ1 ወደ 20 ማሳደግና የብድር ሥርዓቱ ለግሉ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጥበትን አሠራሮች በመዘርጋት ከፋይናንስ ተቋማት የሚሰጥ ብድር ምጣኔ ከመንግስት በንፅፅር (መንግስት፡በግል) በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 2፡1 ወደ 1፡2 እንዲቀየር ይደረጋል።

○ የዘርፉን ሠራተኞች የፍልሰት ምጣኔ ለመቀነስና በሥራቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን የመዘርጋትና አደረጃጀቶችን የማሻሻል እንዲሁም መልካም የሥራ አካባቢ እንዲኖር የማድረግ ሥራ ይሠራል። በዚህ ማዕቀፍ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ የሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥርዓት ዝርጋታ፣ ወቅታዊ የሆኑ ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ዝርጋታ፣ ቅንጅታዊ አሠራርና ተቋማዊ የውስጥ አሠራርን የሚያሳልጡ ሥርዓቶች ዝርጋታ ተጠቃሽ ሲሆኑ ተቋማዊ አደረጃጀትና ውስጣዊ የአሠራር ሥርዓትን የማጎልበት ሥራ በትኩረት ይከናወናል።

○ የሬጉላቶሪ ሥራዎችን በአግባቡ ከመምራት አኳያ የጨረራ ደህንነትና ጥበቃ ፖሊሲ፣ የራዲዮአክቲቭ ዝቃጭ ማሰወገጃ ፖሊሲ፣ አዮን ፈጣሪ ያልሆኑ ጨረራ አመንጪዎችን የማስፈጸሚያ ደንብና የስፔስ ቴክኖሎጂ የአሠራር ሥርዓቶች ይዘጋጃሉ። የሬጉላቶሪ ሥራዎችን ከመሥራት አንጻር ቀደም ብለው የተዘጋጁ አሠራር ሥርዓቶች ላይ ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም ወቅታዊ እንዲሆኑ የማስተካከልና የመከለስ ሥራዎች ይከናወናሉ። በዘርፉ ከሚካሄዱ የቁጥጥር ሥራዎች አኳያ በጂኦስፓሻል ዘርፍ 4,375 የብቃት ማረጋገጫና የጥራት ቁጥጥርና በጨረራ መከላከል ባለስልጣንም በአጠቃላይ 18,241 የብቃት ማረጋገጫና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች በጨረራ ቁሶች ላይ ይሠራል። በአጠቃላይ በዘርፎቹ የሚካሄዱት የቁጥጥር ሥራዎች ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 4,234 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 34,586 እንዲያድግ ይደረጋል።

○ በዘርፉ 12 የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሬጉላቶሪ ሥርዓቶችን የመዘርጋት ሥራ የሚከናወን ሲሆን በነዚሁ ተቋማት የሚገኙ 15 የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሬጉላቶሪ ሥርዓቶች (የሳይበር ሴኩሪቲ፣ የስማርት ሲቲ፣ የኢመርጂንግና የወደፊት ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች) ወቅታዊ እንዲሆኑ የማስተካከል፣ የመከለስና የማጎልበት ሥራዎች ይከናወናሉ። የሞባይል ተጠቃሚዎችን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 37.2 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 100 በመቶ እንዲሁም ጥራት ያለው ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ተደራሽነትን በዚሁ ጊዜ ከ18.6 በመቶ ወደ 100 በመቶ የማሳደግና በቴሌኮም ዘርፍ ለተሰማሩ ተቋማት 2 አዳዲስ ላይሰንሶችን የመስጠት ሥራዎች ይከናወናሉ።

የቀጣይ አስር ዓመታት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የዘርፉ ነባር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለዕቅዱ ስኬት አስተዋፅዖ በሚያበረክቱበት መንገድ እንደአስፈላጊነቱ ተሻሽለው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል። ከዚህ በፊት የተዘጋጁ የፖሊሲ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችና ፍኖተ ካርታዎችም በዚሁ አግባብ ማሻሻያ እየተደረገባቸው ለዕቅዱ አፈጻጸም በቀጣይነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ምርትና ምርታማነት እያደገና ኢንዱስትሪዎች ወደ አዲስ አስተሳሰብ እየተቀየሩ ሲመጡ አዳዲስ የቢዝነስ ሞዴሎችን፣ የንግድ ትስስር ሰንሰለቶችንና የመገበያያ መንገዶችን በመፍጠር በቴክኖሎጂ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ የምርታማነት አቅጣጫን የተከተለ አሠራር ተግባራዊ ይደረጋል።

- ቴክኖሎጂዎች የታሰበላቸውን የምርትና አገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና በሚያመጡበት ልክ ለመተግበር ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን በግልጽ የሚያስቀምጥ የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል። በዘርፉ ያሉ አቅሞችን በተገቢው መልክ በመለየትና በመተንተን ዕቅዶችን ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ይዘጋጃሉ። በተጨማሪም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማትን ተቋማዊ አቅም በመፈተሽ የአደረጃጀት ለውጥና አዳዲስ ተቋማትን እስከመፍጠር የሚዘልቁ ሥራዎች ይሰራሉ። ከሰው ሃብት ልማት ጋር ተያይዞ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችና ቁልፍ ተዋናዮች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሥራ ላይ ሥልጠናና ትምህርት እንዲያገኙ በማድረግ አቅማቸው እንዲገነባ እንዲሁም የሀገራት ልምድን በመቀመር ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ተሞክሮዎችን በመቅሰም ለዘርፉ አጋዥ እንዲሆኑ የማድረግና ከዩኒቨርስቲዎች ብሎም ከኢንዱስትሪዎች ጋር ተቀራርበው እንዲሰሩ ይደረጋል።



# ምዕራፍ አምስት

## የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

# 5.1 የሥነ ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት

## 5.1.1 የሥነ ሕዝብ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሥነ ሕዝብና ልማት የትኩረት አቅጣጫ በዋናነት አሁን በትግበራ ላይ ባለው የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ የተቀመጡ ዓላማዎችንና በቀጣይ ፖሊሲውን ከመከለስ ጋር ተያይዞ የሚካተቱ አዳዲስ ዓላማዎችን ውጤታማ በሆነ አግባብ ተፈጻሚ ለማድረግ ማስቻል ነው። ከዚህ አኳያ በቀጣይ በአጠቃላይ ኢኮኖሚ በተለይም በሠው ሀብት ልማት ዙሪያ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ የሥነ ሕዝብ ሽግግርን ማፋጠንና የሥነ ሕዝብ ትሩፋትን አዎንታዊ በሆነ አግባብ መጠቀም፤ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲና ፕሮግራሞችን የሚያስፈጽሙና የሚተገብሩ የፌዴራል የዘርፍ አስፈጻሚ አካላት የሚመለከታቸውን የሥነ ሕዝብ ተግባራት የዘርፍ ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩ ማስቻል፤ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ እንዲሁም ውጤታማነት እንዲጎለብት ማድረግ፤ ወቅታዊ የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ከገጠር ወደ ከተማ እንዲሁም ከትናንሽ ወደ ትላልቅ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰት ውጤታማ እንዲሆን ማስቻልና የአካባቢ ደህንነት እንዲሻሻል የሚመለከታቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች በተቀናጀ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚያዊ፣ ከማህበራዊ እንዲሁም ከተፈጥሮአዊ የሥነ ምህዳር አቅሞች ጋር ማጣጣምና ሚዛናዊ ሁኔታ መፍጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን አጠናክሮ መቀጠል፤ አማካይ ሀገራዊ የውልደት ምጣኔ እንዲሁም የሞት ምጣኔ እንዲቀንሱ በማድረግ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን መቀነስ፤ የሠው ሀብት ልማት ጥራትና ተደራሽነትን በማሳደግ የሥነ ሕዝብ ትሩፋትን በዕቅድ ዘመኑ ዕውን ማድረግ፤ የወጣቶችና ሴቶችን የሥራ አጥነት ምጣኔን መቀነስ፤ በሁሉም የአደረጃጀት እርከን የሚዘጋጁ የልማት ዕቅዶች ተአማኒነት ባላው መረጃ ላይ ተመስርተው እንዲታቀዱና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን በጥቅል ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም በዘርፍ የልማት ዕቅዶች እንዲካተቱ የሥነ ሕዝብና ልማት መረጃዎችን ጥራት ማረጋገጥና ይበልጥ ተደራሽ ማድረግና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትንና የሲቪክ ማህበራትን ተሳትፎ ይበልጥ ማጠናከር የቀጣይ አስር ዓመታት የሥነ ሕዝብና ልማት ዘርፍ ዕቅድ ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- በልማት ዕቅድ ትግበራ ዘመን የሀገሪቱ አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት በ2012 ከነበረበት 99.8 ሚሊዮን በ2022 ወደ 121.3 ሚሊዮን እንደሚደርስ፣ በዕቅዱ ዘመን (2012-2022) የሕዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔ በአማካይ 2 በመቶ እንደሚሆን ሲታሰብ የከተማና የገጠር የሕዝብ ብዛት የዕድገት ምጣኔ በቅደም ተከተል 4.2 በመቶና 1.3 በመቶ፤ የከተሜነት ምጣኔ በ2012 ከነበረበት 21.4 በመቶ በ2022 ወደ 35 በመቶ ከፍ እንዲልና ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት የኢኮኖሚ ጥገኝነት ምጣኔ በ2012 ከነበረበት 68 በመቶ በ2022 ወደ 59 በመቶ ዝቅ እንዲል ግቦች ተቀምጠዋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ በትግበራ ላይ ያለውን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በመከለስ ወቅታዊ የሥነ ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ከግምት እንዲገቡ ማድረግ፤ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በበለጠ ብቃት ለመፈጸም ያለውን ተቋማዊ አደረጃጀት ማጎልበት፤ በሥነ ሕዝብ መረጃ አሰባሰብ፣ ዝግጅትና ትንተና መስክ ብቁ የሆነ የባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት፣ ፖሊሲ ተኮር የምርምር ፍላጎትን መለየት፣ ከምርምር ተቋማትና በግል ጥናት ከሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ጋር በመተባበር በሥነ ሕዝብና ልማት ዙሪያ የምርምር አጀንዳን ማዘጋጀት፣ በሥነ ሕዝብ ፕሮግራም አመራር የሥነ ሕዝብ ፈጻሚ አካላት ባለሙያዎችን ክህሎትና የቴክኒክ ብቃትን በማሳደግ የሥነ ሕዝብና ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ማጎልበት፣ ሁሉንም የሥነ ሕዝብ ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው።

## 5.1.2 የትምህርትና ሥልጠና ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የትምህርትና ሥልጠና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ፍትሐዊ ተደራሽነት ማረጋገጥ፦ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በገጠር፣ በከተማ፣ በጾታ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በስጦታና ተሰጥኦ በመሳሰሉት ምንም ልዩነት ሳይፈጠር ለሁሉም ዜጎች ፍትሐዊ የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ በቀጣይ አስር ዓመታት በትኩረት የሚሰራበት ጉዳይ ይሆናል።

○ ጥራትና ተገቢነትን ማረጋገጥ፦ በሁሉም የትምህርት ደረጃ ሁሉም ህጻናትና ወጣቶች ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ማስቻል ዋና የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህም ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ አፈጻጸም ካላቸው ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች ጋር የሚነፃፀሩ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ውጤቶችን እንዲያገኙ ዕድል መፍጠር፤ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የማስተማር ሥነ ዘዴው፣ የማስተማሪያና የመማሪያ ቁሳቁሶችና የግምገማ ስርዓቶቹ ከገበያው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆን ማድረግን ያካትታል።

○ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፦ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን በማሻሻል የተጠያቂነት፣ የግልጽነትና የባለቤትነት ስሜትን የሚፈጥር ሥርዓት ለመገንባት በትኩረት ይሠራል። በዚህም የትምህርት አመራርና አስተዳደሩን በማጠናከርና አቅሙን በማጎልበት ብቃትና ውጤታማነትን እንዲያሻሽልና ተጠያቂነትን፣ ግልጸኝነትንና ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ አሠራር በመዘርጋት መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

○ ብሔራዊ አንድነትና ብዝሀነት የሚያረጋግጥ የትምህርት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፦ የትምህርት ተቋማት ከተለያየ ሃይማኖት፣ ማንነት፣ ማህበራዊ መሠረት የመጡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ፣ እንዲግባቡ፣ መስተጋብር እንዲፈጥሩና ልዩነቶቻቸው በማክበር የጋራ የሆነ ልምድና ትልም በመያዝ ብሔራዊ አንድነትን እንዲያጠናክሩ በመቅረጽ ጠቃሚ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በቀጣይ ጉልህ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትምህርትና ሥልጠና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጨረሻ ድረስ ሁሉም ህጻናትና ወጣቶች ያላቸውን እምቅ አቅም መጠቀም የሚያስችላቸውን ጥራት ያለው ነጻ ትምህርት በፍትሐዊነት ማዳረስ፤ የትምህርት ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል፣ የትምህርትና ሥልጠና ጥራትንና የምዘና ሥርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ካሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሰጡ መመዘኛዎች ከፍተኛ የተማሪ ውጤት ካስመዘገቡ ሀገሮች ተርታ ማሰለፍ፤ ሥርዓተ ትምህርትን፣ የመማር ማስተማር ሂደትን፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የመገምገም ሥርዓቱን ከሥራ ዓለምና ማህበራዊ ተሳትፎ ጋር በማቀናጀት ተገቢነቱን ማረጋገጥ የዘርፉ ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትምህርትና ሥልጠና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 41.8 በመቶ በ2022 በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተሳትፎን ከ100.2 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ፤ 7ኛና 8ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ተደራሽነትን ከ97.4 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 100 በመቶ፤ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ25.3 በመቶ በሁለቱም ጾታዎች ወደ 75 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

○ የትምህርት ውስጣዊ ብቃትን (Internal Efficiency) ከማሳደግ አንጻር መጠነ ማቋረጥ ምጣኔን በ1ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 25 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1 በመቶ እንዲሁም ከ7ኛ-8ኛ ክፍል በተማሳይ ዓመት ከነበረበት 12 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል። በተጨማሪም 8ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔን በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 62.1 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

○ የሴቶችንና የወንዶችን የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነትን በቅድመ አንደኛ ትምህርት፣ ከ1-6ኛ ክፍል እና ከ7-8ኛ ክፍል በቅደም ተከተል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 1፡0.95 ፤ 1፡0.91 እና 1፡0.94 በ2022 በጀት ዓመት በሁሉም ደረጃዎች ወደ 1፡1 ለማድረስ እንዲሁም ከ9-12ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 0.87፡1 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1፡0.96 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። የሴት መምህራን ድርሻን በአንደኛ ደረጃ በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 40.6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከ19.3 በመቶ ወደ 30 በመቶ ለማድረስ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎን በከ1-8ኛ ክፍል በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.8 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

○ የአርብቶ አደር ተማሪዎችን ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት ከ13.4 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 92 በመቶ እንዲሁም የአርብቶ አደር ተማሪዎች ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ74.2 ወደ 96 በመቶ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ትምህርት ንጥር ተሳትፎን ከ16.8 በመቶ ወደ 75 በመቶ፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎን ከ14 በመቶ ወደ 60 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል። የትምህርት ውጤትን ለማሳደግም በ6ኛና በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናና በ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶና ከዚያ በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎችን በ2022 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል ወደ 100፣ 100ና 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

○ በትምህርት ምዘና መሠረት ደረጃ 4 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛትን በቅድመ መደበኛ፣ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በቅደም ተከተል ከ0 ወደ 30 በመቶ፣ ከ0.01 ወደ 30 በመቶ እና ከ0.1 ወደ 30 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በተመሳሳይ በትምህርት ምዘና ደረጃ 3

የደረሱ ትምህርት ቤቶችን በቅድመ መደበኛ ከ5 ወደ 70 በመቶ፣ በአንደኛ ደረጃ ከ11 ወደ 70 በመቶ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከ11 ወደ 70 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የትምህርትና ሥልጠና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ በትምህርት ዘርፉ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ዘርፉን አጋርነት ማጠናከር፤ የክልል የልማት ማህበራት የትምህርት ዘርፉን እንዲደግፉ ማበረታታት፤ የግል ዘርፉን በትምህርት ግብዓቶች ማምረት እንዲሁም በትምህርትና ስልጣናው ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታትና የግል ዘርፉን በማሳተፍ ልዩ ተሰጥኦና ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት ዕድል የሚያገኙበት ሥርዓት ይዘረጋል። የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን በሃብት ለመደገፍ የሚያስችል የትምህርት ልማት ባንክ ማቋቋም፤ የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፤ የተጠናከረ የፋይናንስ ኦዲቶችን ማካሄድና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣ የሃብት ስርጭት ካርታ በማዘጋጀት ፍትሐዊ የሃብት ስርጭትና አጠቃቀምን በማሻሻል የባለድርሻ አካላት ትስስር እንዲኖር ማድረግ ሥራ ላይ የሚውሉ ሥልቶች ናቸው።

○ የትምህርት ሥርዓቱን ፍትሐዊና ተደራሽ ለማድረግም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ፤ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞችን በመንደፍ የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነትን ተግባራዊ ማድረግ፤ የሴቶች ትምህርት ተደራሽነት፣ ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ የአዎንታዊ ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፤ በትምህርት ዘርፍ የሚተገበሩ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች ሥርዓተ ትምህርቱ የሥርዓተ ፆታና የልዩ ፍላጎት ጉዳዮችን አካታች ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአግባቡ ይተገበራሉ።

○ የትምህርት ቤቶችን ሚናና ኃላፊነት ግልጽ ማድረግና ግንኙነትን ማጠናከር፤ የትምህርት አመራርና የባለሙያውን አቅም ማጎልበት፤ የዝውውር፣ ቅጥርና የደረጃ ዕድገት እንዲሁም የማበረታቻ ሥርዓት በመዘርጋት መልካም አስተዳደርን ማስፈን፤ የትምህርት መርጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓትን ማዘመንና ሀገር አቀፍ የትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት ፖሊሲን ማዘጋጀት የመተግበሪያ መንገዶች ናቸው።

○ ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክር የግብረ ገብ ትምህርትን በአንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የማካተት፤ የተማሪዎችን የሥነ ምግባር ለውጥ አስመልክቶ ተከታታይ የዳሰሳ ጥናት በማከናወን የማሻሻያ እርምጃ የመውሰድ፤ በትምህርት ተቋማትና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት የማጠናከር፤ ተማሪዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የማጎልበት፤ መምህራን የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን የሚማሩበትን ዕድል የመፍጠር፤ በመልካም እሴቶች የታነጹ በሁለንተናዊ ስብዕናቸው ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት በሚያስችል መልኩ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሚዲያን መጠቀም የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን የመንደፍ ሥራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## 5.1.3 የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት፣ ተገቢነትና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፤ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና አመራርና አስተዳደርን ማጎልበትና ማጠናከር፤ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምርምርና ሀገር በቀል እውቀትን ማጎልበት፤ የግልና የማህበረሰብ፣ የሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነትን የሚመሩ የትምህርትና

ሥልጠና ተቋማትን የማስፋፋት ሥራዎች ትኩረት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም በተግባር የዳበረና የተጠናከረ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ትምህርትን ማረጋገጥ፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በሙያ መስክ መለየት፤ አለማቀፋዊነትና አጋርነትን ማጠናከር፤ ሁለንተናዊ ብቃት ያለው ሠልጣኝና ምሩቃንን ማፍራት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ የማህበረሰብ፣ የዘርፍ መስሪያ ቤቶችንና የኢንዱስትሪዎችን ትስስር ማጠናከር፤ የተማሪዎች አገልግሎትና ተሳትፎን ማጎልበት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሃብት ፈጠራን ማጎልበትና የትምህርት አቅርቦትና የአሰጣጥ አማራጮችን ማስፋት የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፦

○ በሀገሪቱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተለያዩ የትምህርት አሰጣጥ ስልቶችን በመጠቀም የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና በቅርበት ሊያገኙ የሚችሉበትንና በሚመርጧቸው የትምህርት መስኮች የመግባት ዕድል ማስፋት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በሥነ ልቦና፣ በሙያ፣ በአእምሮ፣ በመንፈስ፣ በአካልና በማሕበራዊ ዕድገቱ የዳበረ ሀገርንና ወገንን የሚወድና የሚያከብር ምሩቅ እንዲያወጡ ለማስቻል ይሠራል። የትምህርትና የሥልጠና ብቃት እንዲጠናከር፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና የኢኮኖሚውን የሙያና የሥራ ፍላጎት ያማከለና ያስተሳሰረ እንዲሆንና የሀገር በቀል እውቀቶችን ማልማት በቀጣይ የሚሰራባቸው ናቸው። ለተግባር አመቺና ተደራሽ እንዲሆኑ፤ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድውን የመማር ማስተማርና ሥልጠና በተሟላ የመረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማዘመን፤ የመምህራንና የአሰልጣኞች ልማት ማጠናከርና ማስፋፋት፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በጥንካሬያቸውና በአካባቢያቸው ባለ እምቅ ሀብት በመለየት እንደየትኩረት መስካቸው አቅማቸውን ማጎልበት፤ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና በኢንዱስትሪ መካከል የሥራ ትስስር መፍጠርና ማጠናከር፤ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማሳደግ፣ ማስፋፋትና ማጠናከር፤ የሳይንስና ምርምር ማህብረሰብና ባህል መፍጠርና ማጠናከር የዘርፉ ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፦

○ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች አመታዊ ጥቅል ተሳትፎው በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 13.8 በመቶ በ2022 ወደ 23 በመቶ ለማድረስ፤ የመንግስትና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅደም ተከተል አሁን ካሉበት 45ና 238 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 55ና 550 ለማድረስ፤ የመንግስት እና የግል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት በተመሳሳይ ጊዜ በቅደም ተከተል ከ672 ወደ 922 እና ከ950 ወደ 1700 ለማሳደግ ታቅዷል። በተመሳሳይ በዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተሳትፎ ከ0.29 ወደ 5 በመቶ፤ በዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከ35.9 ወደ 48 በመቶ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ የሴት መደበኛ ሰልጣኞች ተሳትፎ ከ49.8 ወደ 51 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በሁለተኛ እና በሦስተኛ ዲግሪ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ በተመሳሳይ ዓመታት በቅደም ተከተል ከ19ና 10 በመቶ ወደ 35 እና 23.4 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በዩኒቨርሲቲ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከ30.7 በመቶ ወደ 40 በመቶ፤ በቴክኒክና ሙያ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ተሳትፎ በመደበኛ ከ1365 ወደ 1443 ለማድረስ ግቦች ተይዘዋል።

○ በተጨማሪም የመምህር ተማሪ ጥምርታን በመጀመሪያ ዲግሪ አሁን ካለበት ከ1፡19 ወደ 1፡15፤ በድህረ ምረቃ ከ1፡20 ወደ 1፡5 ለማውረድ ግብ ተጥሏል። በኢንዱስትሪው ባለቤትነት የተዘጋጀ የሙያ ደረጃ ከ750 ወደ 850 ለማድረስ፤ በኢንዱስትሪ ፍላጎት መሠረት የተከለሰ የዩኒቨርሲቲዎች የሙያ

ፕሮግራሞች ብዘት ከ282 ወደ 512 ከፍ ለማድረግ እንዲሁም በግብዓቶች የተሟሉ ቤተ ሙከራዎች ያሏቸው የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከ40 ወደ 100 በመቶ፣ የዩኒቨርሲቲዎች ከ65.3 ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

○ በሌላም በኩል የመንግስት የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች መመረቅ ምጣኔ አጠቃላይ ከ84.2 በመቶ ወደ 92.5 በመቶ፣ በዩኒቨርሲቲ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የማጠናቀቅ ምጣኔ ከ89.14 በመቶ ወደ 95 በመቶ፤ በዩኒቨርሲቲ የሴቶች የማጠናቀቅ ምጣኔ ከ74.04 በመቶ ወደ 90 በመቶ፤ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ተማሪዎች ምረቃ ምጣኔ ከ94.5 በመቶ ወደ 97 በመቶ ለማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ የቴክኒክ ሙያ ሰልጣኞች አመታዊ መደበኛ መርሃ ግብር ቅበላ ዕድገት ከ45 ወደ 80 በመቶ፤ የቴክኒክና ሙያ አጠናቃቂዎች የመቀጠር ምጣኔ ከ78 ወደ 96 በመቶ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂዎች የመቀጠር ምጣኔ ከ59 ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች የመብቃት ድምር ምጣኔ ከ55 ወደ 85 በመቶ፤ በቴክኒክና ሙያ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰልጣኞች የትምህርትና ሥልጠና የመብቃት ምጣኔ ከ40 ወደ 70 በመቶ፤ በበቴክኒክና ሙያ የሴቶች ሰልጣኞች የመብቃት ምጣኔ ከ45 ወደ 75 በመቶ፤ በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ያሉ የሴት ተመራማሪዎች ድርሻ ከ16.4 ወደ 40 በመቶ ለማድረስና የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በተቋማቱ የተሸፈነ በጀት መጠን ዕድገት 40 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

የቀጣይ አስር ዓመታት የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ የተመራቂ ተማሪዎችን/ሰልጠኞችን የሙያ ብቃት ለማጠናከርና ለማጎልበት የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ሥርዓቱን ማጠናከር፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኮሚዩኒቲና የኃይማኖት ተቋማት የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚከፍቱበትን የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ማበረታታት፤ ተመራቂዎቹ በሙያቸው ብቁ ለመሆናቸው ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና መስኮች በየመሃሉ ምዘና ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ማበጀትና መተግበር፤ ለእያንዳንዱ ሙያ የሙያ ማረጋገጫ ምዘና የሚሰጥበት ሥርዓት መዘርጋትና የተጠናከረ የምዘና ሥርዓት ማዕከል በየተቋማቱ እንዲኖሩ ማድረግ ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ብሔራዊ አገልግሎት እንዲሰጡና የተለያዩ አካባቢዎችን ባህሎች፣ ወጎችና ቋንቋዎች እንዲማሩና መከባበር እንዲፈጠር የማድረግ ስልቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

○ የሥርዓተ ትምህርቱ ዝግጅትና ትግበራ ውጤታማ መሆኑን የሚከታተልና የሚገምግም ራሱን የቻለ አካል ማቋቋም፤ ተመርቀው የወጡ ምሩቃን ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ግምገማና ክለሳ ሲካሄድ በሂደቱ የሚሳተፉበትን ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤ የተማሪዎች መንፈሳዊ ዕድገት እንዲጎለብትና ሌሎችን መረዳትና የአብሮነት ስሜት፣ የማህበራዊ ትስስር አስፈላጊነትና እሴቶች ማሳደግ እንዲችሉ ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ ሀገር በቀል እውቀቶችን በሚገባ ከሳይንሳዊ ዘዴ ጋር ማጣጣምና በተገቢ መንገድ የማዋሃድ ዘዴዎች ይተለማሉ፡፡ መምህራን/አሰልጣኞች መማር ማስተማሩን በምርምር የተደገፈ እንዲያደርጉ አቅማቸውን ማጎልበት፤ መምህራንና አሰልጣኞች በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ገብተው የተግባር ልምድ የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች በመማር ማስተማሩና በምርምሩ የሚሳተፉበትን ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ በእውቀት የጎለበቱና ክህሎታቸው የዳበረ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና አመራሮችን ለማሰልጠን የሚረዱ ማዕከላትን ማቋቋም፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ባላቸው ጥንካሬና በአካባቢያቸው ባለው እምቅ ሀብት አንጻር በመስክ እንዲለዩና እንዲጠናከሩ የሚያስችሉ ስልቶች ይተገበራሉ፡፡

መምህራንና ተማሪዎች ከኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ጋር በጥምረት ምርምር ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማፍለቅ፣ የማሳደግና የማሸጋገር ባህል እንዲያሳድጉ ሥርዓት መፍጠርና መተግበር፤ የምርምርና የሳይንስ ማበልጸጊያ ማዕከላትን (incubation centers) በየተቋማቱ እንዲቋቋሙ በማድረግ የመሞከር ባህልን ማዳበር፤ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር የልቀት ማዕከላት እንዲቋቋሙ ማድረግ፣ መከታተልና መደገፍ፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበት አሠራር፣ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና መተገበርና አደረጃጀት ማጠናከር/መፍጠር፤ በሀገሪቱ በተመረጡ ቦታዎች የተወሰኑ ለምርምር አገልግሎት የሚሆኑ የምርት ናሙና የሚሞከርባቸውና ፕሮቶታይፕ የሚሠራባቸው ዓለም አቀፍ ጥራታቸውን የጠበቁ ቤተ ሙከራዎች መገንባት፤ መምህራንና የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ወደ ምርምርና ሳይንስ እንዲገቡ የሚያበረታቱ ስልቶችን መጠቀም፤ የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የገቢ አቅማቸውን ማጎልበትና የወጪ አጠቃቀማቸውን ማዘመን ተግባራዊ ይደረጋል።

## 5.1.4 የጤና ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የጤና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፦

○ ውጤታማ፣ ጥራት ያለውና ፍትሐዊ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦትና ሽፋንን ለማረጋገጥ የሚሰራ ሲሆን የጤና አገልግሎት ወጪም የፋይናንስ ስጋትን ለመቅረፍ የሚደረገውን ትግበራ ማፋጠን ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል እንዲሁም የጤናውን ሥርዓት በየግዜው ለሚቀያየረው የህብረተሰቡ ጤና ፍላጎት ምላሽ ሰጪ የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ። በተጨማሪም በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የተሃድሶና የህመም ማስታገስ የጤና አገልግሎቶች ዜጎችን ለፋይናንስ ችግር ሳያጋልጡ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋንን ማሻሻል ትኩረት ይሰጠዋል።

○ በተመሳሳይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በማህበረሰብ ግጭቶች፣ ባልተጠበቁ የበሽታ ወረርሽኞች እና በአዳዲስ የጤና ስጋቶች ምክንያት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን በፍጥነት በመለየት፣ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጭነትን በማጠናከር የዜጎችን የጤና ደህንነት መጠበቅ አፅኖት ይሰጣቸዋል። የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ አካታችነት እና ባለቤትነትን በማጠናከርና በማሻሻል በጋራ ጤና ነክ ችግሮችን እየለዩ መፍትሄ በመስጠት የተሻለ የጤና ስኬት እና ፋይዳ የማምጣት ሥራዎች ይሰራሉ፤ ቤተሰቦች በጤና ፕሮግራሞች ዙሪያ በተለይም በሃይጅንና አካባቢ ጤና ሥራዎች፣ የእናቶች እና ህጻናት ጤና አገልግሎቶች የአጠቃቀም ሽፋን እና የጤና መድን ሽፋን ላይ የሚያድርጉትን ተሳትፎ ለማሳደግ ትኩረት ይደረጋል። የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት በማሻሻል የህክምና ተቋማት የሚፈልጉትን ጥራት ያላቸውን መድሃኒቶችን፣ የላቦራቶሪና የምርመራ መሳሪያዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ ትኩረት ይሰጠዋል። የጤናው ዘርፍ የቁጥጥር ሥርዓትን በማሻሻል ለህብረተሰቡ የሚቀርበውን ጤና ነክ ምርት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሻሻል የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ።

○ የጤና ዘርፍ ሰው ሃብት ልማት እና አስተዳደርን በተመለከተ በመጭው አስር ዓመት የዘርፉ የሰው ኃይል ብዛት፣ ክህሎትና የሙያ ስብጥር እንዲሻሻል ይደረጋል። በተለይም በህክምና ባለሙያዎች ፍልሰት ሳቢያ የሚፈጠረውን የህክምና ባለሙያዎች እጥረት ለመቅረፍ በጥናት ላይ የተመሠረተ የህክምና ባለሙያዎች ሥልጠና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

○ የጤናው ዘርፍ የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ የማህበራዊ እና ማህብረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓትን በሀገር አቀፍ ደረጃ መተግበር፣ የህክምና ተቋማት የህክምና አገልግሎት ክፍያ ለጤና አገልግሎት

የሚወጣውን ወጪ እና የህብረተሰቡን የመክፈል አቅም ያማከለ ማድረግ፣ ለጤናው አማራጭ የገንዘብ ምንጮችን መጨመር እና ሌሎችንም የጤና ፋይናንስ ዘዴዎችን መተግበር ትኩረት ይሰጠዋል።

○ የሥራ አመራር እና መልካም አስተዳደርን በማሻሻል ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው የአመራር እና የአስተዳደር ሥርዓት በየደረጃው የመዘርጋት ሥራ ይሠራል።

○ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሻሻል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ይህም የግሉ ዘርፍ በጤናው ላይ ያለውን ተሳተፎ በተለይም ደግሞ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት በመስጠት እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ።

○ ከዚህ በተጨማሪም የባህላዊ ሕክምና አገልግሎትን በማጠናከር በሀገር አቀፍ ደረጃ የባህል ህክምና ከዘመናዊው ህክምና ጋር አሠራሩን ከዘመናዊው መድህኒት ጎን ለጎን እንዲሰራ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ላይ ያተኮረ የማይበገር የጤና ሥርዓት በመገንባት የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጾኦ ማበርከት፣ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ማረጋገጥ፤ ዜጎች በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ ሳይዳረጉ የጤና አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች የሚደርሱ የእናቶችና ህጻናት ሞትን መግታት፤ ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ሳቢያ የሚደርሱ ህመምና ሞትን መከላከልና መቀነስ፣ ዜጎችን ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች መጠበቅ፣ የወረዳ ትራንስፎርሜሽንን ማምጣት እና ተገልጋይ ተኮር እና ተዓማኒነት ያለው የጤና ሥርዓትን መፍጠር የዘርፉ የልማት ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የእናቶች ሞት ምጣኔን በ2009 በጀት ዓመት ከነበረበት 401/100,000 በ2022 ወደ 140/100,000፤ ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህጻናት ሞት ምጣኔን ከ59/1,000 ወደ 37/1,000 እና ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔን ከ47/1,000 ወደ 29/1,000 ለመቀነስ ታቅዷል። በተመሳሳይ ወቅት ከአምስት ዓመት እድሜ በታች ያሉ ህፃናትን የመቀንጨርና የመቀጨጭ ምጣኔ በቅደም ተከተል ከ37 በመቶ ወደ 13 በመቶና ከ7 በመቶ ወደ 3 በመቶ ለመቀነስ ግብ ተጥሏል። የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎትን በተመለከተ የቤተሰብ ዕቅድ ሥርጭት ምጣኔ ከ41 በመቶ በ2022 ወደ 54 በመቶ ማሳደግ፣ በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የሚወልዱ እናቶችን ከ50 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ ሁሉንም አይነት የክትባት አይነቶች የወሰዱ ከ 1 ዓመት በታች ያሉ ህፃናትን ከ 44 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

○ በቲቢና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ የሚደርሰውን የሞት ምጣኔ በቅደም ተከተል አሁን ካለበት 22/100,000 በ2022 ወደ 4/100,000 እና ከ1.2/10,000 ወደ 0.45/10,000 ለመቀነስ ታቅዷል። በተመሳሳይ በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስና በወባ በሽታ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን ምጣኔም በቅደም ተከተል አሁን ካለበት ከ1.6/10,000 ወደ 0.6/10,000 እና ከ28/1,000 ወደ ዜሮ ለማውረድ ግብ ተጥሏል። በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የሚከሰት የደም ማነስ በሽታ ምጣኔን ከ24 በመቶ ወደ 12 በመቶ ለመቀነስ ግብ ተቀምጧል። የዘርፉን የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር በማሻሻል የጤና ባለሙያ (ሐኪም፣ ነርስ፣ አዋላጅ ነርስ፣ ጤና መኮንን) ለ1000

ተገልጋዮች ጥምርታን በ2012 ከደረሰበት 1 በ2022 ወደ 4.5 እና ሐኪም ለ10,000 ተገልጋዮች ጥመርታን ከ0.86 ወደ 2.7 ለማሳደግ ታቅዷል።

○ መንግስት ለጤና ዘርፍ የሚመድበው በጀት ከጠቅላላ የመንግስት በጀት አንጻር ያለው ድርሻ አሁን ካለበት 8.1 በመቶ ወደ 15 በመቶ እና በማህበረሰብ ጤና መድህን ሥርዓት የታቀፉ ቤተሰቦች ሽፋንን ከ49 በመቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ ለማድረግ እንዲሁም ሶሻል የጤና ኢንሹራንስን መጀመርና 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ለ100,000 ሕዝብ ጥምርታን ከ0.3 ወደ 0.85 ለማሳደግ እና አጠቃላይ አማካይ የመኖር ዕድሜ ጣሪያን በ2011 ከደረሰበት 65.5 ዓመት በ2022 ወደ 70 ዓመት ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ የጤና አገልግሎት አቅርቦትና አደረጃጀት፦ የኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ በሦስት ደረጃዎች እንዲዋቀር ተደርጓል። የመጀመሪያው እርከን መሰረታዊ ጤና እንክብካቤ (Primary Health Care level) የሚባለው የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ የጤና ጣቢያ እና የጤና ኬላን ይይዛል። ሁለተኛው እርከን አጠቃላይ ሆስፒታልን ሲይዝ ሦስተኛው እርከን ደግሞ ሪፈራል (ስፔሻላይዝድ) ሆስፒታሎችን ይይዛል። ይህ አዎቃቀር በየደረጃው የበሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የተሃድሶና የህመም ማስታገስ የጤና አገልግሎቶችን ለማዳረስ ይረዳል። እንዳስፈላጊነቱም የጤናው አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተቋማት አወቃቀር እና በየደረጃው የሚሰጡትን አገልግሎቶች የማሻሻል (re-design) ሥራዎች ይሰራሉ።

○ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር፦ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዘንድ መቀናጀት ያለባቸውን አገልግሎቶች በማቀናጀት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ይህም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለመጨመር ይረዳል። በተጨማሪም ጥራት፣ ፍትሐዊነት፣ ሥነ ያታና የመሳሰሉት በሁሉም የአገልግሎት አይነቶች ተቀናጅተው እንዲሰጡ ይደረጋል።

○ የጤናውን ሥርዓት ዕቅድ እና አፈጻጸም ከባለድርሻ አካላት በጋራ መሥራት፦ የዕቅዱ ትግበራ እንዲቀናጅ፤ እንዲመራ እና ወደ ተለያዩ አካላት ተግባቦት ለመፍጠር የተለያዩ ፎረሞችን የማጠናከር ሥራ ይሠራል። በዚህም መሠረት የጤና ሚኒስቴር እና የልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ምክክር ፎረም (Joint Consultative Forum -JCF) እና የጋራ ማዕከላዊ አስተባባሪ ኮሚቴ (Joint Core Coordinating Committee) ፎረሞች ከልማት አጋሮቻችን ጋር በጋራ ሥራዎችን ለማቀድ፣ ለመከታተል እና ችግሮችን በጋራ ለመፍታት በየጊዜው ይከናወናሉ። የጤና ሚ/ር እና የክልል ጤና ቢሮዎች የጋራ ኮሚቴ (MOH-RHBs Joint Steering Committee) ስብሰባ በየሁለት ወሩ የሚደረግ ሲሆን ይህም የልማት እቅዱን በየጊዜው ለመገምገምና ለችግሮች በጊዜ መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪም በየደረጃው የተለያዩ ፎረሞች/ኮሚቴዎች ተቋቁመው እቅዱን የመከታተል ሥራ ይሠራል።

○ ከሌሎች ሴክተሮችና የዘርፈ ብዙ አካላት ጋር በትብብር መሥራት፦ የጤና አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ በማድረስ ጤናን ለማሻሻል የሚቻለው በጤናው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሴክተሮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ እና ለትርፍ የተቋቋሙ አካላትንም በማሳተፍ ነው። በመሆኑም የዘርፈ ብዙ አካላት ህብረትን የማጠናከር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት የትብብር አሠራር ይዘረጋል።

○ የመንግስት እና የግል አጋርነትን በጤናው ዘርፍ ማስፋት፦ የግሉ ዘርፍ በመዳኃኒትና በህክምና መገልገያ ቁሳቁስ ማምረት፣ የመረጃ አያያዝ፣ የሰው ኃይል ልማትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ እና በሌሎች ክፍተት በሚታይባቸው የጤና ዘርፍ አገልግሎትና መሠረተ ልማቶች ዙሪያ እንዲሰማራ አስፈላጊ የሆኑ የማበረታቻና የማትጊያ አሠራሮች ይዘረጋሉ። መንግስትና የግሉ ዘርፍ የአጋርነት አሠራርን በመዘርጋት በተመረጡ የጤና ሥራዎች ጋር የጤና ሥራዎችን በሽርክና ይሰራሉ።

## 5.2 የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፡

○ የዘርፉ የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ በዋናነት መብት (Right)፣ ውክልና (Representation) እንዲሁም ሀብት (Resource) ላይ ያተኮረ ይሆናል።

○ መብት (Right)፦ ይህ የትኩረት አቅጣጫ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ተፈጥሮአዊ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩላቸው የማድረግ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዙሪያ የፈረመቻቸውን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችና ቃልኪዳኖችን ተግባራዊነት የማረጋገጥ፤ በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ከባህልና ወግ ተቃራኒ የሆኑ መጤ ባህሎችን፣ ሱሰኝነትን፣ ብዝበዛና አድሎዎችን፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን የማስቀረት፣ የሴቶችና ወጣቶችን በነፃ ፍላጎት የመደራጀት መብት የማረጋገጥ እንዲሁም ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች የተሰጡ ሁለንተናዊ መብቶችን በህበረተሰቡ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና እንዲከበሩ የሚያስችሉ ሥራዎችን ያቀፈ ነው።

○ ውክልና (Representation)፦ ይህ አቅጣጫ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች በየደረጃው በሚካሄዱ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶችን ጉዳይ ማካተትና ተቋማዊነትን የማረጋገጥ፤ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች በመረጧቸው አደረጃጀቶች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማሳደግ፤ ሴቶች ህፃናትና ወጣቶች በቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማጎልበት እንዲሁም በሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት በየደረጃው የሚኖራቸውን ውክልና ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

○ ሀብት (Resource)፦ በዚህ የትኩረት አቅጣጫ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ላይ መሠረት ያደረገ የሰብዓዊ ልማት ግንባታ የማሳደግ፤ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ከሀገሪቱ አጠቃላይ ልማት የሚኖራቸውን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና የንብረት ባለቤትነት የማረጋገጥ፤ ለሴክተሩ የአስር ዓመት ዕቅድ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊና የፋይናንስ ሃብቶችን የማሳደግና አጋርነትን የማጠናከር ሥራ ማዕከል ያደረገ ነው።

○ በዚህም መሠረት የሴቶችንና ህፃናትን ጥበቃ ሥርዓት በማጠናር ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን ማስጠበቅና መብታቸውን ማስከበር፤ ሴቶችንና ወጣቶችን በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ፍትሐዊ ተሳትፎና ውክልና

እንዲኖራቸው ማድረግ እንዲሁም ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች ላይ ያላቸውን ሚና እንዲያጎለብቱ በማድረግ ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የዘርፉ የቀጣይ አስርት ዓመታት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ የሴቶችን፣ ህፃናትንና ወጣቶችን መብት፣ ውክልናና ተጠቃሚነት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ መስኮች ማረጋገጥ የዘርፉ አጠቃላይ ዓላማ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ፦ ሴቶችና ህፃናትን ከሚደርሱባቸው ጥቃቶችና ከሚፈፀሙባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርቶች በመከልከል ለአካላዊ ጥቃት የተጋለጡ የሴቶች ምጣኔን በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 23 በመቶ፣ ለሥነ ልቦናዊ ጥቃት (emotional) የተጋለጡ ሴቶች ምጣኔን ከነበረበት 24 በመቶ፣ ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ ሴቶች ምጣኔን ከነበረበት 10 በመቶ ወደ 5 በመቶ የመቀነስ እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛት ምጣኔን ከነበረበት 65 በመቶና ያለዕድሜ ጋብቻ ምጣኔን ከነበረበት 6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ ግብ ተጥሏል።

○ የህፃናት መብትና ሁለንተናዊ ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር በዕቅዱ የትግበራ ዘመን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 15 ሚሊዮን ህፃናት በተለያዩ የሀገር ውስጥ አማራጭ ፕሮግራሞች ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል። የህፃናትን መብቶች ለማስጠበቅ የህፃናት ልደት ምዝገባ ተደራሽነትን በ2022 በጀት ዓመት 100 በመቶ ለማድረስ እንዲሁም በሕግ አባትነትን የማወቅ መብትን አስመልክቶ ያሉ ችግሮችን የመለየትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚፈታበትን አሠራር ተግባራዊ በማድረግ ህፃናትን በሕግ አባትነታቸውን የማወቅ መብታቸውን የማስጠበቅ ሥራዎች ይከናወናሉ። ሴቶችና ወጣቶች በፍላጎታቸውና በመረጧቸው መስኮች የመደራጀትና ነፃ ሆነው የመንቀሳቀስ መብታቸውን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

○ የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ፦ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የሴቶች አመራር ማዕከል በማድረግ ከሀገር አልፎ ለአህጉር ብሎም ለዓለም ተምሳሌት የሆኑ የሴት አመራሮችን ለመፍጠር የአፍሪካ ሴት አመራሮች ማዕከል በመገንባት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ለአመራር ብቁ የሆኑ 10,000 ሴቶችን ለማፍራት ታቅዷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሴቶች በተለያዩ እርከኖች ውክልና እንዲኖራቸው በማድረግ የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን ለማረጋገጥ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ድርሻ በሕግ አውጪ 50 በመቶና በሕግ ተርጓሚ 50 በመቶ ለማድረስ እንዲሁም በሕግ አስፈፃሚ አሁን ያለውን የ50 በመቶ ድርሻ ለማስቀጠል ግብ ተጥሏል። በተመሳሳይ በዕቅድ ዘመኑ ለህፃናት ተሳትፎ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸውን ህብረተሰብ 80 በመቶ ለማድረስ፣ የህፃናት ፓርላማ አደረጃጀቶችን በ2012 በጀት ዓመት ካለበት 8,428 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 20,015 ለማሳደግ እንዲሁም በህፃናት ፓርላማዎች ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ የህፃናትን ድርሻ 75 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

○ በተመሳሳይ በበጎ ፈቃድ የአገልግሎት መስኮች ላይ የተሰማሩ ወጣቶችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 21 ሚሊዮን በ2022 ወደ 30 ሚሊዮን ለማድረስ፤ በወጣት ማዕከላት ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ23 ሚሊዮን ወደ 28 ሚሊዮን እንዲሁም በሕግ አውጪ ተሳታፊ

የሆኑ ወጣቶችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 11 በመቶ ወደ 30 በመቶ፣ በሕግ ተርጓሚ 10.2 በመቶ ወደ 35 በመቶ እንዲሁም በሕግ አስፈፃሚ ከ12.2 በመቶ ወደ 30 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

○ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፦ ሴቶች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የሴቶችን የሥራ ክፍያ ልዩነት አሁን ካለበት 44 በመቶ በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት እንዲሁም የሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብትን ለማስጠበቅ የመሬት ባለቤትነት መብት ያላገኙ 59.7 በመቶ ሴቶችን የመሬት ባለቤት ለማድረግ ታቅዷል። በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ምጣኔ በ2012 ካለበት 41 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ፤ በህብረት ሥራ ማህበራት በአባልነት የታቀፉ ሴቶችን በ2012 ከነበረበት 3,385,412 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 11,338,412፤ ብድር አግኝተው በገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሳተፉ ሴቶችን በ2012 ከነበረበት 33 በመቶ ወደ 55 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ የብድር አገልግሎት ያገኙ ወጣቶችን በ2012 ከነበረበት 25 በመቶ ወደ 50 በመቶ፤ የቁጠባ ምጣኔያቸው ያደገ ወጣቶችን አሁን ካለበት 7 በመቶ ወደ 15 በመቶ ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል። ከህፃናት ተጠቃሚነት አንጻር በሰብዕና ማዕከላት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን 50 በመቶ፤ በህፃናት ማቆያ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን 70 በመቶ፤ ለትምህርታቸው፣ ለራሳቸውና ለብዛህነት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ህፃናትን 95 በመቶ፤ ከቤተሰብና ከማህበረሰባቸው ጤናማ ግንኙነት ያላቸው ህፃናትን 90 በመቶ ለማድረስ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፦

○ በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱና እንዲቀንሱ ለማድረግ ብሔራዊ የጥቃት አድራሾች መረጃ ሥርዓትን መዘርጋት፤ሥርዓተ ፆታ ላይ መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የመንግስት ዜሮ የመታገስ አቋም ተግባራዊ ለማድረግ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶችና ህፃናትን በልዩ ሁኔታ የሚመረምሩና ጥቃትን ለመከላከል የሰለጠኑ የፖሊስ አባላት ያሉት ግብረኃይል ማቋቋም፤ ፍኖተ ካርታውን መተግበርና የግንዛቤና ንቅናቄ ፕሮግራሞችን ማካሄድ ከዋና ዋናዎቹ መተግበሪያ ስልቶች መካከል ናቸው። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት የተጠናከረ ድጋፍ ለማድረግ የህፃናት ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ የማቋቋምና የኬዝ ማኔጅመንት ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል። የወጣቶችን የእርስ በርስ ትብብር ለማሳደግ፣ የወጣቶች ጉዳይ በየደረጃው በሁሉም ዘርፎች እንዲካተት የሚደረግ ሲሆን የወጣቶች ድምፅ ተሰሚ እንዲሆን የወጣቶች ካውንስል ይቋቋማል።

○ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ተሳትፎና ውክልናን ለማረጋገጥ የአፍሪካ ሴቶች አመራር ማዕከል፤ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶችን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ውይይቶችን የሚያካሂዱባቸውና ልምድ የሚለዋወጡባቸውን ምቹ ማዕከላት፣ የአፍሪካ ወጣቶች ማዕከል፣ የወጣቶች የግንኙነትና የመረጃ ማዕከል፣ ወጣቶች ከአህጉራዊ አቻዎቻቸው ጋር ትስስር የሚፈጥሩበትን የዩዝ ኮኔክት ፕሮግራምን የመመስረትና ነፃና ጠንካራ የሴትና የወጣት አደረጃጀቶች የመፍጠር ሥራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

የሴቶችና ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል የልማት ፈንድ በማቋቋም ሥራ ፈጣሪ ሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚ የማድረግ፤ ሴቶች የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበትን የገበያ ማዕከል የማቋቋም፤ ወጣቶች ከሱስ የሚያገግሙበትን የወጣቶች የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን የማቋቋም፤ የህፃናትን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ህፃናት ማግኘት የሚገባቸውን ሁለንተናዊ ጥቅሞችን ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ

እንዲሁም ምቹ የህፃናት መጫወቻና መዝናኛ ሥፍራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሀገራዊ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። በተጨማሪም በሴክተሩ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤ የቅንጅትና ትብብር ሥርዓትን ማሳደግ፤ አደረጃጀትን መፍጠር፤ የተለያዩ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች አደረጃጀቶችን እንዲቋቋሙ የመደገፍና የማጠናከር፣ የአሠራር ማዕቀፎች ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ የተጠያቂነትና ውጤታማ የተግባቦት ሥርዓትን መዘርጋት በዘርፉ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚደረጉ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

# 5.3 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥

○ ሠላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነትን ማስፈንና የሕግ ተፈፃሚነትን ማረጋገጥ፣ ዘመናዊ፣ ተደራሽና ፍትሐዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎትን ማስፋፋት፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ደሃና ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች በኢኮኖሚና በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተካታች፣ ተደራሽ፣ ተሳታፊና ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን መዘርጋትና አገልግሎቶችን ማስፋፋት በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራባቸዋል። ከዚህ አኳያ የኢንዱስትሪ ሰላም በዘላቂነት እንዲሰፍን ፈጣን ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ፍትሐዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት እንዲጎለብት ይደረጋል። ይሄውም አሠሪዎችና ሠራተኞች በሕግ የተሰጣቸው መብት ተጠብቆ በማህበራዊ ምክክርና በሥራ ቦታ ትብብር (social dialogue and workplace cooperation) የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ እንዲሁም ከሥራ ግንኙነት የሚመነጩ አለመግባባቶችና ክርክሮች በአማራጭና በመደበኛ የሥራ ክርክር መፍቻ መንገዶች እንዲፈቱ ይደረጋል። የማማከርንና የሕግ ተፈፃሚነትን ባመጣጠነ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት በማጠናከር የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ፤ የሥራ አካባቢዎችና የአሠራር ዘዴዎች ከአደጋዎችና ከጤና ጠንቆች ተጠብቀው ምርታማነታቸው እንዲያድግ፣ የጥሬ ዕቃና የተረፈ ምርት አያያዝና አጠቃቀምን ከብክነትና ከብክለት የፀዳ በማድረግ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል። ለጉልበት ብዝበዛ በተዳረጉ ሕጻናት ላይ ያተኮሩ ልዩ ልዩ የመከላከያና የሕግ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

○ የሀገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ከማጣጣም አኳያ ዜጎች ባላቸው አቅምና ችሎታ መሠረት በነፃ በመረጧቸው የሥራ መስኮች በሥራ መሰማራት የሚችሉበት ዘመናዊ፣ ተደራሽና ፍትሐዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል። በሀገሪቱ ምቹና ምርታማ የሥራ ዕድሎችን ከመፍጠርና ከማስፋፋት አኳያ አግባብነት ካላቸው የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር በመሥራት ሥራ አጥነት እንዲቀንስ ይደረጋል። በሕጋዊ መንገድ በውጭ ሀገር ለሥራ መሠማራት የሚፈልጉ ዜጎች በሀገራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና የሁለትዮሽ ስምምነት ማዕቀፎች መሠረት መብታቸው፤ ደህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ የዓለም ሥራ ገበያን በቃኝ አግባብ ባላቸው አቅምና ችሎታ ልክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችና ድጋፎች ተጠናክረው እንዲሰጡ ይደረጋል። በሌላ በኩል ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በዘላቂነት ለመከላከል (prevention) የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም

የህብረተሰቡን ግንዛቤ የሚያሳድጉ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲከናወኑ ይደረጋል። በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጎጂ የሆኑ ዜጎችንና ተመላሾችን መልሶ ለማቋቋም (reintegration) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

○ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት ተመጋጋቢነቱ፣ ተደጋጋፊነቱ፣ ሽፋኑና ደረጃው በየጊዜው እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል። በማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተለዩ የልማታዊ ሴፍቲኔት፣ የማህበራዊ መድንና የሥራ ዕድል ማስፋፋት እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎችም የሕግ ጥበቃና ድጋፍ ይደረጋል። የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት አካታችነትና ተደራሽነትን ማሻሻል ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ከዚህ አኳያ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋዊያንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተካታችነትና ተደራሽነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሀገር በቀል የአሠራር ስልቶች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን የጎዳና ተዳዳሪነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት ተፈጻሚ ይደረጋሉ። የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተሃድሶ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፤ የችግሩ ሰለባ የሆኑትንም የማቋቋም ሽፋኑ እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል። በግሉ ክፍል ኢኮኖሚ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን ለማሳደግ የግል ድርጅቶችና ሠራተኞችን የመደበኛ የምዝገባ ሽፋን በማሳደግ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋኑ በሀገር ደረጃ እንዲስፋፋ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

○ ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን በዘላቂነት ማሻሻል፤ በመከላከል መርህ የተቃኘ የሕግ ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ፤ ፍትሐዊና ዘመናዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎቶችን ማስፋፋት፤ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን መዘርጋትና አገልግሎቶችን ማስፋፋት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተካታችነት፣ ተደራሽነት፣ ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

○ የአሠሪዎች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ2.5 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 20 በመቶ ለማሳደግ፣ የሠራተኞች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን ከ2 በመቶ ወደ15 በመቶ ለማሳደግ፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎትን በማስፋፋት በድርጅቶች የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ሽፋኑን ከ372,245 ድርጅቶች ወደ 838,551 ድርጅቶች ለማሳደግ፣ በሥራ ላይ የሚደርሱ የሞት አደጋዎችን ክስተት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 52/100,000 ሠራተኞች ወደ 35/100,000 ሠራተኞች እንዲሁም በሥራ ላይ ሞት ያላደረሱ አደጋዎችን አሁን ካሉበት 25,000/100,000 ሠራተኞች ወደ 10,000/100,000 ሠራተኞች ለመቀነስ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን አሁን ካለበት 23 በመቶ ወደ ዜሮ ለማውረድ ታቅዷል። የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓትን (LMIS) በማዘመን እንዲሁም የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማመቻቻ ማዕከላትን (Employment Service Facilitation Centers) በሁሉም ክልሎችና ፌዴራል ከተማ አስተዳደሮች በማቋቋም በሀገር ውስጥ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ የሥራ ስምሪት ድጋፍ አግኝተው በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎችን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት ከደረሰበት 1.96 ሚሊዮን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 20 ሚሊዮን ለማድረስና ሥራ አጥነትን

ለመቀነስ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል። በተጨማሪም በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል መረጃ አሰባሰብ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከለበት ከ50 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 100 በመቶ በማድረስ የመረጃ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

○ በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙ አረጋዊያን መካከል 563,640፣ ከአካል ጉዳተኞች መካከል 323,000 እና ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ ከሆኑ የህረተሰብ ክፍሎች (Urban Destitute) መካከል 189,000 የትምህርት፣ የሥልጠና እና የሥራ ስምሪት አድል እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል። የአካል ድጋፍና ሌሎች አገልግሎቶች የሚደረግላቸው አካል ጉዳተኞች ቁጥርን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 412,867 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 659,558 ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንና የጡረታ ፈንድን ከማሳደግ አንጻር የግል ድርጅት ሠራተኞችን ምዝገባ አሁን ካለበት1,669,521 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3,050,847 እንዲሁም የግል ድርጅቶችን ምዝገባን ከ203,458 ወደ 311,887 ለማሳደግ፣ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ገቢ 43.9 ቢሊዮን ብር በዕቅዱ መጨረሻ ዘመን ወደ 231 ቢሊዮን ብር ለማድረስ፣ የጡረታ ፈንዱን በኢንቨስትመንት ላይ በመዋል አሁን ካለው ትርፍ 1.4 ቢሊዮን ብር በ2022 ወደ 39 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

○ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አዋጆች፣ ፖሊሲዎችና የተለያዩ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ። ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ሳይንሳዊ መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ መንገድ ተሰብስበው፣ ተደራጅተውና ተተንትነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም ከሚመለከተው አካላት ጋር በመተባበር የኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ ሁኔታ ጥናት በማካሄድ ዘርፉ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ የሚሸጋገርባቸው ስልቶች ተቀይሰው ሥራ ላይ ይውላሉ።

○ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ተግባራዊነት ለማሳለጥ የተቋቋሙ መድረኮች፣ የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ በማቋቋም አቅማቸውን በመገንባት ከህብረተሰቡ ሀብት በማሰባሰብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል። በሥራ ቦታ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚያስችል የሁለትዮሽና የሦስትዮሽ ሥርዓቶች እንዲዘረጉ ይደረጋል። በተጨማሪም ሠራተኛው በተገቢው ሁኔታ የመደራጀት መብቱን እንዲጠቀም ውጤታማ የሆኑ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተከታታይነት ባለው መንገድ በአሠራር ሥርዓት ተደግፈው እንዲከናወኑ ይደረጋል።

○ የተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት ዘርፈ ብዙና ሴክተር ዘለል እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ የግሉ ዘርፍ፣ ዓለም አቀፍና ሀገራዊ የልማት አጋሮችና ማህበራዊ ተጓዳኞች (social partners) ለዘርፉ ልማት የሚጠበቅባቸውን የጋራና የተናጠል ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉበት የትብብርና የቅንጅት አሠራሮች በየደረጃው እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል። በተለይም የማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ የሚመጥን ውጤታማ የክትትልና ግምገማ እንዲሁም የተጠያቂነት ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በተጨማሪም የዘርፉ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማስተባበር በወረዳና በቀበሌ ደረጃ መዋቅር እንዲፈጠር በሰው ኃይል እንዲጠናከር ይደረጋል።

# ምዕራፍ ስድስት

## የሕዝብ አገልግሎት፣ የፍትሕና
## የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕቅድ

# 6.1 የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፦

- ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የህዝብ አገልግሎት ሥርዓት መገንባት፣ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ሥራ አመራር ሥርዓት ማሻሻል፣ የህዝብ ሠራተኞችን እሴት መገንባትና ሥነምግባርን ማሻሻል፣ ውጤታማ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ በሲቪል ሰርቪስ ዘርፉ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት በሀገራዊው የልማት ጉዞ ጉልህ ሚና መጫወት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፦

- ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የህዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት ማጎልበትና በህዝ አገልግሎት አሠጣጥ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ የዕቅዱ ዋና ዓላማዎች ሲሆኑ የዜጎችን እርካታ ማሳደግ፣ የለውጥ አመራር ውጤታማነትን ማሳደግ፣ የሰው ሀብት አቅምን ማሳደግ፣ የመንግስት ተቋማትን አደረጃጀት ውጤታማነት ማሳደግ፣ የሲቪል ሰርቪሱን የሰው ሀብት አቅም ማሳደግ፣ በሰው ሀብት ሕጎች አተገባበር ውጤታማነትን ማጎልበት፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ማጠናከርና በአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል ተቋማትን ማበራከት የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፦

- የመንግስት ተቋማትን አደረጃጀት ውጤታማነት በማሳደግ ነጻ፣ ገለልተኛና ብቁ ሆነው የተፈጠሩ የተቋማት አደረጃጀቶችን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 100 በመቶ ለማድረስ፣ በ2012 በጀት ዓመት በዘርፉ ያለውን 20 በመቶ የውጤታማ አምራች የሰው ኃይል ምጣኔ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ፣ የሰው ሀብት የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ሥርዓቱን አሟልተው የተገበሩ የፌዴራል ተቋማትን በ2012 በጀት ዓመት 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

- የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓትን ሙሉ በሙሉ የተገበሩ ተቋማት በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 100 በመቶ ለማድረስ፣ ሞዴል የሆኑ የፌዴራል መንግስት ተቋማትን ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 75 ለማድረስ እንዲሁም በመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የዜጎችን እርካታ በ2012 ከለበት 59 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

- ደረጃቸውን የጠበቁ ምቹና ማራኪ የሥራ ቦታ የፈጠሩ የፌዴራል ተቋማትን ወደ 100 በመቶና በመንግስት ተቋማት የሴት/ወንድ አመራር፣ ባለሙያዎች ጥምርታን ወደ 36 በመቶ ከፍ ለማደረግ፤ ሁሉም የመንግስት ተቋማት የህጻናት ማቆያ እንደሚያዘጋጁና ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቸ ሥራ ቦታ እንዲኖራቸውና 50 በመቶ የሚሆኑት አዳዲስ ተመራቂ ወጣቶችን ማስገባትና በፍጥነት ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- በፌዴራል፣ በኮሚሽኑ፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደር የሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች መካከል የጠበቀ የመደጋገፍ፣ የመመካከር፣ መረጃዎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን በጋራ የመንደፍ አካሄድን አጠናክሮ መቀጠል፤ ከፌዴራል ዘርፍ አስፈፃሚ ተቋማት ጋር በሕግ የተደገፈ ግንኙነትን ማጠናከርና እንደአስፈላጊነቱ ከሲቪል ማህበራት፣ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላትም ጋር በቅርበት መመካከር ሥራ ላይ የሚውሉ ሥልቶች ናቸው። የተቋማትና ዜጎች እርካታ ጥናት፤ የመንግስት ተቋማት ማወዳደሪያ ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ የካይዘን ትግበራ፤ የነፃ፣ ገለልተኛና ብቁ ተቋማት መዋቅርና አሠራር ጥናትና ትግበራ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ ሥርዓት የሰው ሀብት ብቃት ማረጋገጫ የአፈጻጸም ሥራ አመራር ማዕቀፍ ዝርጋታና በዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የመደገፍ ፕሮጀክቶች ትግበራና የአመራርና ባለሙያዎች ልማትና በተለይ ሴቶችን የማብቃት ፕሮግራሞች ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው።

# 6.2 የፍትሕ ዘርፍ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የፍትሕ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን፡-በኢትዮጵያ መሰረታዊ ለውጥ ከሚያስፈልግባቸው ጉዳዮች አንዱ የአስተዳደራዊ ፍትሕ ነው። ዘመናዊ አስተዳደር እና የመንግስት መዋቅር በሀገራችን መገንባት ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን፣ ይህ መዋቅር የሚሰጠው አገልግሎት እና የሚሸከመው ሃላፊነት ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጥቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በዜጎች የቀን ተቀን ህይወት የአስተዳደር አካላት ሚና እና ተጽዕኖ እየጨመረ መሆኑ እሙን ነው። የመንግስት ተቋማት የአስተዳደር እና የቁጥጥር ሥራ ሲሰሩ እና አገልግሎት ሲሰጡ ይህን የሚያደርጉበት ሂደት በሕግ እና በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የመንግስት የአስተዳደር ተቋማት ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን ባረጋገጠ መንገድ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ የሚታመን ቢሆንም፣ ይህን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት እና አሠራር ሳይዘረጋ እስካሁን ቆይቷል። የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ በቅርቡ የፀደቀ ሲሆን አዋጁን ተግባራዊ በማድረግ የአስተዳደራዊ ፍትሕን ለማረጋገጥ በቀጣይ ዓመታት ሰፊ ሥራ ሊሰራ ይገባል። በመሆኑም የአስተዳደር አካላት አስተዳደራዊ መመሪያዎችን የማውጣት (administrative rule making) ስልጣናቸውን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ግልጽ፣ ተገማች እና አሳታፊ የሆነ ሥርዓት እንዲከተሉ ማስገደድ ነው። ይህን ግዴታ የሚደነግግ አዋጅ የፀደቀ ሲሆን አዋጁ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆን ስለአዋጁ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የአዋጁን አፈፃጸም የሚያሳልጡ አሠራሮችን በመዘርጋት እና አፈፃፀሙን በመከታተል ረገድ ሰፊ እንቅስቃሴ ከመንግስት ተቋማት ይጠበቃል። በተጨማሪም የመንግስት ተቋማት አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሲያሳልፉ ውሳኔዎቻቸው በሂደትም ሆነ በይዘት የሕጋዊነት እና የምክንያታዊነትን መርህ የተከተሉ እንዲሆኑ፣ ውሳኔዎቹ አግባባነት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት መብት እና ጥቅም ከግንዛቤ ያስገቡ በተቻለ መጠን ግልጽ እና አሳታፊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ መሆን ይኖርበታል። ይህን ለማረጋገጥ የወጣውን አዋጅ ትግበራ አስመልክቶ ፍርድቤቶች ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው። ፍርድ ቤቶች አዋጁ ላይ ተመስርቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና ውሳኔ በመስጠት የአስተዳደር ተቋማት አሠራር ሕጋዊ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ

የሕግ ሥርዓት ሰፊ ክፍተት የነበረበት እና አስተዳደራዊ ፍትሕን እንደ አንድ የፍትሕ ዘርፍ እውቅና የማይሰጥ የነበረ ሲሆን፣ በቀጣይ ዓመታት ይህን አስመልክቶ ትልቅ ለውጥ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል።

- የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፡- በቀጣይ አስር ዓመታት የስነ ስርዓት ፍታዊነትና ሚዛናዊነት ለማጎልበት ወጪን፣ ጊዜን፣ ክርክርን፣ ውስብስብ ሂደትን የሚቀንሱ አሰራሮችን ማጎልበትና ማስፋፋት፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ጥራት፣ ተገማችነትና ወጥነት ማጎልበት፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በህግ በመመሥረት የማስረጃ ምዘና ስርዓትን በአግባቡ መከተል የሚያስችል እርምጃዎችን መውሰድ፣ ቀልጣፋ እና ፍትሀዊ ውሳኔዎች እንዲሰጡ የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው የምርምር፣ የስልጠና እና የአቅም ማጎልበቻ እርምጃዎችን መውሰድ፣ የተለዩ የዳኝነትና ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስርዓቶችን እና አቅሞችን በተለያዩ የህግ ዘርፎች ማስፋፋት እንዲሁም ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ፍትህ መስጠት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

- የዳኝነት ተደራሽነትን ማስፋፋት፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አካላዊ ተደራሽነትን ማስፋፋት፣ የፍርድ ቤት ክፍያዎችና ሌሎች የክርክር ወጪዎች አግባብነታቸውን ማረጋገጥ፣ የፍርድ ቤት አገልግሎቶች ለሴቶች፤ ህጻናት፤ አካል ገዳተኞችና ልዩ ትኩረት ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተደራሽነታቸውን ማረጋገጥ፣ ባለጉዳዬች የተሻለ የጥብቅና ወይም የህግ ውክልና አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማጎልበት፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ተደራሽ ማድረግና በሰበር ችሎት የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

- የፍርድ ቤት ነጻነትና ተጠያቂነትን ማጎልበት፡- ፍርድ ቤትና ዳኞች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ሂደት ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች አካላትና ግለሰቦች ከሚደርስባቸው ማንኛውም ጫናና ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል የዳኝነት ስርዓቱ ህግን መሰረት ያደረገና ከብልሹ አሰራር የጸዳ አሰራር እንዲዳብር ከማስቻል አንጻር ነጻነትን ብቻ ሳይሆን ተጠያቂነትንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ በቀጣይ አስር ዓመታት ስለ ፍርድ ቤት ገለልተኝነትና ነጻነት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ግንዛቤን ማጎልበት፣ ፍርድ ቤት ከሌሎች የመንግስት አካላት (ህግ አውጪና አስፈጻሚ) ጋር ያለውን ግንኙነት እና የነጻነት ወሰኑን በሚመለከት የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ማጎልበት፣ የዳኞችን ጥቅሞችና መብቶችን ማስፋትና ማጎልበት፣ በፍርድ ቤት አባላት የሚፈጸሙ የስነምግባር ጥሰቶችን በአግባቡ ተከታትሎ ውሳኔ መስጠት፣ የፍርድ ቤቶችን በጀት ነጻነት ማረጋገጥ እንዲሁም ስለ ፍርድ ቤት ገለልተኝነትና ነጻነት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ግንዛቤን ማጎልበት ያስፈልጋል።

- የወንጀል ሕግን አፈጻጸም ውጤታማነት ማረጋገጥ፡- አላስፈላጊ የሆኑ የቅብብሎሽና የምልልስ አሠራሮችን መቀነስ፣ እሴት የማይጨምሩ ሥራዎችን ማስወገድ፣ ለፈጻሚዎች ተጨማሪ ኃላፊነቶችን ከተጠያቂነት ጋር መስጠት፣ ጥራት ባለው ፣ በአነስተኛ ወጪና በቅርበት እንዲሰጥ ማድረግ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው። በተጨማሪም የስትራቴጂክ አመራርና ማስፈፀም አቅም ማሳደግ፣ ተቋሙን በሰው ኃይል በማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት፣ ውስጣዊ አሠራርና አደረጃጀቶችን ማሻሻል፣ የሕግ የበላይነትን የሚያከብርና የሚያስከብር፣ ፍትሐዊ፣ ተደራሽና ጠንካራ፣ የፍትሕ አገልግሎትን ማስፈን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የፍትሕ ዘርፍ ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የዕቅዱ ዓላማ ፍርድ ቤት እና ዳኞች ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች አካላትና ግለሰቦች ከሚደርስባቸው ማናቸውም ጫና እና ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ

ክፍሎች የፍርድ ቤት አገልግሎቶችን በእኩልነት እንዲያገኙ ማስቻል፣ ሕገ መንግስቱንና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤ የወንጀል ሕግን ማስከበርና የፌዴራል መንግስቱንና የሕዝብን የፍትሐብሔር ጥቅም ማሳካት ነው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የፍትሕ ዘርፍ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፡

- የወንጀል ጉዳዮችን የማጥራት ምጣኔ ከ80 ወደ 100 በመቶ፤ የእርቅ ምጣኔን አሁን ካለበት 81.2 ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ፤ የመንጠባጠብ ምጣኔን ከ1.9 ወደ 0.5 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል። በተመሳሳይ የቅጣት አፈጻጸምን አሁን ካለበት 91.8 ወደ 98 በመቶ ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን በወንጀል የተገኘ ሃብትን ከሀገር ውጪ 59 በመቶ ለማስመለስ ግብ ተጥሏል። ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ምላሽ ያገኙ የውል ምርመራ ዝግጅቶችን ወደ 98 በመቶ፤ የሕግ ማርቀቅ፣ ምክርና እርማትን ወደ 100 በመቶ፣ በሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር አፈጻጸምን ወደ 90 በመቶ፣ ለሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን ወደ 100 በመቶ እንዲሁም የይቅርታ ውሳኔዎችን ማፀደቅ ወደ 98 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም የፍትሐብሔር ፍርድ አፈጻጸም ምጣኔን ከ50 ወደ 100 በመቶ፤ በፍትሐብሔር ጉዳዮች አለመግባባትን በድርድር የመፍታት አቅምን ከ70 ወደ 92 በመቶ፣ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ክርክር መርታትን ከ94 ወደ 99.5 በመቶ ማድረስና በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የተደረጉ ሰዎችን ለፍርድ ማቅረብን ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

- የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳት እና ሥነ ምግባር ክትትል አፈጻጸምን 100 በመቶ ማድረስ፣ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ጠቋሚዎችና ምስክሮች አገልግሎት መስጠትን ከ61.1 ወደ 79 በመቶ ማሳደግ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን አፈጻጸም ክትትል 100 በመቶ ማድረስ፣ የዜጎች ንቃተ ሕግ ትምህርትን ተደራሽነት ወደ 85 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም በዘርፉ የሕግ ድጋፍ ያገኙ ሴቶችና ህፃናትን ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ ግቦች ተጥለዋል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የፍትሕ ዘርፍ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፡

- ለተገልጋዮች መረጃ የሚደርስባቸውን አሰራሮች ማዘመን፣ ቀጣይነት ያለው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት፣ ግልጽ የሆነ የዳኞች ምልመላና ሹመት ሥርዓት መዘርጋት፣ የዳኝነት አገልግሎት የእርካታ ዳሰሳ ማድረግ፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ ፍርድ ቤት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው የህግ ባለሙያዎች እና የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች ተመራጭ መስሪያ ቤት የሚሆንበትን ልዩ ልዩ እርምጃዎችን መውሰድ፣ የፍርድ ቤት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በየጊዜው ያለውን ለውጥ ያገናዘበ እና ከወቅቱ ጋር የሚሄድ እንዲሆን የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣ የዳኞች እና የአስተዳደር ሰራተኞች አቅም የሚያጎለብቱ ልዩ ልዩ የሰልጠና እና የትምህርት መርሀግብሮችን ማመቻቸት እና አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎችን ማውጣት የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

- በዕቅድ ዘመኑ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና መርሃግብሮችን መንደፍና መተግበር፤ ወንጀልና የወንጀል ሥጋት አካባቢዎችን፣ የወንጀል አይነትና ወንጀል ፈፃሚዎችን መለየት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ በወንጀል መከላከል ስትራቴጂ ህብረተሰቡን በተደራጀ መልኩ ማሳተፍ፤ የሕገ ወጥ የሰዎችን ዝውውር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተጋላጭነት ሁኔታ ከቦታ፣ ከተጎጂዎችና ከአዘዋዋሪዎች አንጻር የተጋላጭነት ካርታ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ማድረግ የሥልቶቹ አካል ናቸው። ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማጠናከር፤ የወንጀል ምርመራ ዘርፉን ብቃት በሰው ኃይል እውቀት፣ በቴክኖሎጂና ልዩ ክህሎት በሚፈልጉ ዘዴዎች

ለማጠናከር፤ የወንጀል የጥቆማ፣ ክስና አቤቱታ አቀባበልና ምዝገባ ሥርዓቱን ቀላልና ዘመናዊ ለማድረግና የሳይንሳዊ፣ የፎረንሲክና ሕክምና ምርመራ አቅምን (forensic and medical investi-gation) ለማጠናከር ዕቅድ ተይዟል። በወንጀል ጉዳዮች የባህላዊና ሀይማኖታዊ ተቋማትን ለማሳተፍ ተቋማቱንና የሚያዩዋቸውን ጉዳዮች የመለየትና ከፍትሕ አካላት ጋር ስለሚኖራቸው መስተጋብር የሕግ ማዕቀፍ ማውጣትና መተግበር፤ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ የሚያስችል አሠራርና አደረጃጀት መፍጠርና መተግበር፤ ከክስ ውጭ በድርድር ሀብት ማስመለስ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በመቅረፅና በመተግበር ሥራዎች ይሠራሉ።

- የፍትሐብሔር ጉዳዮች የውል ዝግጅት ምርመራ፣ ድርድርና ክርክር ጉዳዮች አያያዝ የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣትና መተግበር፤ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ወይም የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች አፈፃፀማቸውን መከታተል፣ ሪፖርትና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤ የተያዙ፣ የተከሰሱ፣ በሕግ ቁጥጥር ሥር የሚገኙና የታራሚዎች ሰብአዊ መብት አከባበርና አያያዝ ፍኖተ ካርታ መቅረፅና መተግበር፤ ቋሚ የንቃተ ሕግ ትምህርት የሚሰጥበት ሥርዓት መቅረፅና መተግበር፤ የፌዴራል ሕጎች ተፈፃሚነት ክትትልና የተጠያቂነት ሥርዓት መቅረፅና መተግበር፤ አስፈፃሚ የመንግስት አካላትና የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሕግ የማመንጨት፣ የማጥናትና የማርቀቅ ብቃት ማሳደጊያ የቅንጅታዊ አሠራር መቅረፅና መተግበር፤ አዲስ የሚረቀቁና የሚሻሻሉ ሕጎች እንዲሁም አፈጻጸማቸው ለንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋትና ሕጋዊ ውድድር የሚያበረታቱና ሕገወጥነትን የሚከላከሉ መሆናቸው ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መቅረጽና መተግበር፤ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ስትራቴጂ ማፅደቅና የሕግ ድጋፍ መስጫ ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር እንዲሁም በፍትሕ አገልግሎት የግል ዘርፉን ማሳተፍ ሌሎች የማስተግበሪያ ስልቶች ናቸው።

## 6.3 የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ

የቀጣይ አስር ዓመታት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን ማሳደግ፤ የመንግሰት አስፈጻሚ አካላት በግልጸኝነትና በተጠያቂነት መርህ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፤ ሕግ አውጪው እና ሕግ አስፈጻሚው በሕገ መንግስትና ሕጎች መሠረት በግልጽ የስልጣን ክፍፍል መሥራት የሚያስችላቸው ቁመና መፍጠር፤ ዜጎች በየትኛውም በሀገሪቱ ክፍሎች የመንቀሳቀስ እና የመሥራት መብታቸው ጥበቃ እንዲደረግለት ማድረግ፤ ሲቪክ ማህበራት በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፎች ላይ ተሳታፊነታቸውን ማጠናከር፤ የዜጎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብታቸውን ማረጋገጥ፤ ነጻ እና ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋማትን ማጠናከር፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችንም በሕገ መንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የድርሻቸውን እንዲወጡ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

- መገናኛ ብዙሀን በሕገ መንግስቱ ለተረጋገጡ መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች እንዲሁም ለሠላም፣ ለእኩልነት፣ ለፍትሕ እና ለዴሞክራሲ እንዲቆሙ በአጠቃላይ ለልማት እና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የድርሻቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ ከመንግስት እና ከፖለቲካ ፓርቲ ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሁም ተፎካካሪ ሆነው ሊሰሩ የሚችሉበትን ምህዳር መፍጠር፤ በመገናኛ ብዙሀን ዘርፍ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ

ማጎልብት፤ የህዝብ ተሳትፎን የስልጣን ባለቤትነት የማረጋገጥ እና የአሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሠፈነበት የመንግስት አሠራርና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፤ የተደነገጉ የሰዎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍና እና ግልጽነት ያለው የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ፤ ለዜጎች ሁሉን አቀፍ (Holistic) እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን (Domestic Campaign)፣ ለሙስና ወንጀል የሚያጋልጡ አሠራሮችንና የሕግ ክፍተቶችን በመለየት የመንግስትም ይሁን የግል ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ፣ የሙስና ወንጀል ፈጽመው በተገኙ አካላት ላይ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ እና ለህብረተሰቡ በሚዲያ የማጋለጥ ሥራ መሥራት፣ የክልል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች የመፈጸም አቅም መገንባትና ተልዕኮ ተኮር የህብረተሰብ ተሳትፎን በማሳደግ የፀረ ሙስና ትግሉ ተባባሪና አጋር አካላትን ማብዛት ሌሎች የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፦

- የዴሞክራሲ ተቋማትን እና የዜጎችን አመለካከት መቅረጽ ላይ ወሣኝ ሚና ያላቸውን ተቋማት አቅም መገንባት፣ ሠፊ የህዝብ ተሳትፎ ማድረግ፣ የትውልድ ሥነምግባር እና የሞራል ግንባታ እሴቶችን በብቃት መገንባት፣ የሙስና ወንጀልን መከላከል፣ ለፀረ ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህዝቡ የፀረ ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፣ በህዝብ ተመራጮች፣ በመንግስት ተሿሚዎች ላይ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ሥርዓት መፍጠር፣ በሰላም፣ በልማት እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ወቅታዊ እና ተዓማኒ ዜናና ዜና ነክ ሥራዎችን ማሠራጨት፣ የመገናኛ ብዙኃን የምርትና አገልግሎት ጥራትን የሚያስጠብቁ ወሣኝ የሥራ መሣሪያዎችንና ግብዓቶችን እንዲያሟሉ ማድረግ፣ የገበያ ድርሻን ማሣደግና አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም መገንባት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የዴሞክረሲ ሰርዓት ግንባታ ዘርፍ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፦

- በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን በማሳደግ የተጠያቂነትና የግልፀኝነት ሥርዓት ማረጋገጥ፣

- የሀገራችን መገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ተዓማኒነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነትን ከ20 በመቶ ወደ 85 በመቶ ለማሳደግ፥ የባለድርሻ አካላት አጋርነትና ዕርካታን ከ60 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል። የሚዲያውን ዕድገትና ተደራሽነት ለማስፋት የሚያስችል በቂ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ፣ የመገናኛ ብዙኃን የምርትና አገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍናን ከ30 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሣደግ፥ የመገናኛ ብዙኃን ይዘት ልማትን፣ ምርት ማሣደግ እና የአገልግሎትና ምርት ውጤቶች ተደራሽነትን በየዓመቱ በ30 በመቶ ለማሣደግ፥ የአመራር፣ የሰው ኃብት፣ ተቋማዊ እና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅምን ለማሳደግ ታቅዷል።

- በተጨማሪም የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ ውስጥ የትውልድን የሥነምግባርና የሞራል እሴቶችን መገንባት፤ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን መከላከል እንዲሁም ህብረተሰብና የባለድርሻ አካላት በፀረ ሙስና ትግል በንቃት ለማሳተፍ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የዴሞክራሲ ግንባታ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የመልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ ተቋማት የሚባሉት የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ፣ የኢትዮጵያ የሕዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ነጻነትና ገለልተኛነታቸውን ጠብቀው ሚናቸውን እንዲወጡ ይደረጋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ የተማከለ የመረጃ ማዕከል (Centralized Data Center) በመገንባት መረጃን ተደራሽ ማድረግ፥ በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች እና ውሳኔዎች ለዜጎች ለሕገ መንግስቱ የተደነገጉ መብቶቻቸውን ባከበረ መንገድ መወጣታቸውን ማረጋገጥ፥ ስለ መልካም አስተዳደር እና ስለ አስተዳደራዊ ፍትሕ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት የዲሞክረሲ ሥርዓት ለመገንባት የሚውሉ የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው። በተጨማሪም በቀጣይ አስር ዓመታት በዴሞክራሲ ግንባታ የታቀዱ ግቦችን እውን ለማድረግ የዜጎች የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከልን ተቋማት የሥራቸው አካል (mainstream) እንዲያደርጉት ማድረግ እንዲሁም የፀረ ሙስና ፖሊስ፣ የትውልድ የሥነምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው የሚተገበሩ ይሆናል።

# ምዕራፍ ሰባት

## የሰላም ግንባታና ቀጠናዊ
## የጋራ ልማት ዕቅድ

# 7.1 የሰላም ግንባታ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የሰላም ዘርፍ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- አዎንታዊ ሰላምና የዳበረ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ ማህበራዊ ሀብቶችን፣ እሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን ማሳደግ፣ ሕግ የማስከበር ሥራን ማጠናከር፣ በክልሎች ማካከል ግንኙነቶችንና ትብብሮችን ማጠናከር እንዲሁም ሕዝብ ተኮርና የዕውቀት ሥራ አመራር ሥርዓትን ማጎልበት እና ተቋማዊ አቅምን በዘላቂነት መገንባት በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት የሚሰጣቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሰላም ዘርፍ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሀገራችንና የህዝቦቿን ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ፣ አብሮነትና የሕግ የበላይነትን ማስፈን የዕቅዱ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

በቀጣይ አስር ዓመታት የሰላም ዘርፍ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የዜጋው የውስጠ ሰላም የጥልቀት ዕድገት አሁን ካላበት 25 በመቶ በ2022 ወደ 85 በመቶ ለማድረስ፤ የዴሞክራሲ ተቋማት በሰላም ባህል ግንባታ ንቁ ተሳትፎ ዕድገት አሁን ካለበት 5 ወደ 85 በመቶ ለማድረስ፤ በማህበረሰብ ምክክር ማህበረሰባዊ ምክንያታዊነት፣ መግባባት፣ ችግር ፈቺነትና እርካታን አሁን ካለበት 40 ወደ 90 በመቶ ለማሳደግና በሊህቃን ተኮር ምክክርም የሊህቃናት ምክንያታዊነት፣ ጥምረት፣ የሕዝብ አገልጋይነትና የዴሞክራሲ ተገዥነትን አሁን ካለበት 10 ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

- የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ በማህበረሰቡ፣ በፖሊስና በጸጥታ ተቋማት መካከል መተማመንን አሁን ካለበት 40 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤ የሕግ ማስከበርና የደህንነት ተቋማትን የአገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ የሕግ አስከባሪና የደህንነት ተቋማት አቅምን አሁን ካለበት 10 ወደ 95 በመቶ የማሳደግ ግቦች ተይዘዋል። በክልሎች እና በፌዴራል ደረጃ የመተማመንና የመግባባት ደረጃና ክልል ለክልል ግንኙነትና መተማመንን አሁን ካለበት 25 ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ፤ አደረጃጀቶችን በትስስርና በትብብር በማጠናከር ሰላማዊነትና አብሮነትን አሁን ካለበት 40 ወደ 80 በመቶ ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል።

- በቀጠናው ባሉ ሀገራት መካከል ግንኙነትና ትብብርን በማጠናከር ድንበር ዘለል የተደራጁ ወንጀሎችና ሽብርተኝነትን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 40 በመቶ በ2022 በጅት ዓመት ወደ 2.5 በመቶ ለመቀነስ፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ከ40 በመቶ ወደ 2.5 በመቶ ለመቀነስ እንዲሁም የወሳኝ ሁነቶች ምዝገባ ሽፋንን ለመሳደግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የሰላም ዘርፍ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የኢትዮጵያ ሰላም ፖሊሲና የማስፈጸሚያ ፍኖተ ካርታን ማዕከል ያደረገ፣ ሰላምን በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣

በማህበረሰብና በተቋም ደረጃ በማስረጽ፣ የዜጎችና ወጣቶችን በጎ ፈቃደኝነትንና የመስጠት ዜግነታዊ ኃላፊነትን የህይወት ዘመን ባህል እንዲሆን በማድረግ፣ ማህበራዊ ሃብቶች፣ እሴቶችና ብሔራዊ ጥቅሞች በተልዕኮ ሥምሪት ውስጥ ተካተው በመተግበር ሁለንተናዊና ዘላቂ ሰላምን የመገንባት ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል።

- በሀገራችን የመጀመሪያው የሆነውን የፖሊስ ዶክትሪንን የማስፈጸሚያ ስታንዳርዶችንና ማንዋሎችን ተግባራዊ ማድረግ፤ የጦር መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓትን በመተግበር ሕገ ወጥነትን በመከላከልና የህዝቡን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ እንዲሁም የወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራ አመራር ሥርዓትን በመተግበር የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችንና ሽብርተኝነትን የመከላከል ሥራ ይሠራል። በተመሳሳይ ማንነትን በባዮ ሜትሪክ የሚለይ የብሔራዊ የመታወቂያ ሥርዓት በመተግበር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። የሳይበር ጥቃቶችን አስቀድሞ መከላከልና የኮሙኒኬሽንና የሳይበር ደህንነት መከላከያ መረቡን በወቅታዊነት የማበልጸግ ሥራ ይሠራል።

- የፌዴራልና ክልል ግንኙነት ፖሊሲን ማዕከል በማድረግ በክልሎች መካከል ያለው መስተጋብርና መደጋገፍ፣ በትብብርና አብሮ በማደግ እንዲሆንና አካባቢያዊነት እንዳይበረታ በማድረግ በፌዴራልና በክልል እንዲሁም በክልሎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በመተማመንና በአብሮነት እንዲያድግ ይደረጋል።

# 7.2 የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት

የቀጣይ አስር ዓመታት የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- በአካባቢያችን ዘላቂ ሰላምን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስርንና የጋራ ብልጽግናን ለማምጣት የሚያስችል መሪ ስትራቴጂ (grand strategy) በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፣ በአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች መካከል ሁሉን አቀፍ ትብብርና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የሕዝብ ለሕዝብ ፎረም መመስረት፣ የድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ሃብቶችን ጨምሮ ከውጭ ግንኙነታችን ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ጉዳዮችን በሚመለከት በዕውቀትና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የአፍሪካ ህብረት ውጤታማ የአህጉራዊ ውህደት እንዲያሳካ እንደ አባልና አስተናጋጅ ሀገር መደገፍ፣ ድርጅቱ የሀገራችን ባለብዙ ወገን ድጋፍ መነሻ ሆኖ እንዲቀጥል የተለያዩ ማዕቀፎችን መተግበር፣ ስትራቴጂካዊ አጋርን ለመለየትና የውክልና አድማስን ለማስፋት የሚያስችሉ መስፈርቶችና መርሆዎችን መከተልና የሀገራችንን ስትራቴጂካዊ ጥቅሞች በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የልዩ መልዕክተኛ አሰያየምና አጠቃቀም የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የሀገራችንን ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚያስከብር ዲፕሎማሲን በማጠናከር የዜጎች ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በመተግበር እንዲሁም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለንን የመሠረተ ልማትና የኢኮኖሚ ትስስር በማጠናከርና የገጽታ ግንባታን በማሳደግ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም

ማስጠበቅ የውጭ ጉዳይ ልማት አበይት ዓላማዎች ናቸው። ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም፣ የባህል ትስስሮችና ጉድኝቶችን በመፍጠር፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድንን በመመስረትና በማጠናከር የሀገራችንን ገፅታ መገንባትና ተጠቃሚነታችንን ማረጋገጥ፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የውጪ ምርቶቻችን በዓለም አቀፍ ገበያ ያላቸውን ተደራሽነት በማስፋት፣ የቱሪዝም ፍሰትን በማሳደግና የልማት አጋሮቻችን በማበራከት እንዲሁም ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታችንን ማሳደግ፣ የሀገራችንን ልማት መደገፍ፣ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን ተግባራዊ በማድረግ የዜጎችን ክብርና ጥቅም ማስጠበቅ፣ የዳያስፖራውን የልማት ተሳትፎ ማሳደግ፣ ግልጽና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ተገልጋይን ማርካት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም፣ ማህበራዊ መስተጋብርና የኢኮኖሚ ትስስርን ማጎልበት፦ ኢጋድን እንደገና ሪፎርም በማድረግ አካባቢያዊ የውህደት ድርጅት ሆኖ እንዲወጣ ቅድሚያውን በመውሰድ ከአባል ሀገራት ጋር ተባብሮ በመሥራት፤ ለቀጠናዊ ሰላምና ትስስር እንዲሁም በቀይ ባህርና ኤደን ባህረ ሰላጤ የአካባቢው ሀገራትና ሌሎች በአካባቢው ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ሀገሮች ጋር የአባል ሀገራቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ይሠራል። በተጨማሪም በቀጠናው ዘላቂ ሰላም፣ የተሻለ ማህበራዊ መስተጋብር፣ የኢኮኖሚ ትስስርና የጋራ ብልጽግናን በማጠናከር የሀገራችንን ጥቅም ማስጠበቅ፣ የድንበር ጉዳዮችን በሰላማዊ መንገድ እልባት መስጠትና የድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችን ፍትሐዊ አጠቃቀምን የማረጋገጥ ዕቅድ ተቀምጧል። ለዚህም ከጅቡቲ ጋር ያለንን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስትራቴጂያዊ ትስስር ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣ ከሱዳንና ኬንያ ጋር ያለንን ሁለንተናዊ ትስስር አጠናክሮ በማስቀጠል የጋራ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞቻችንን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣ በሶማሊያና በደቡብ ሱዳን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ ትብብርን ማሳደግ፣ ከኤርትራ ጋር የተጀመረውን ግንኙነት በማጠናከር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ ትብብር ተግባራዊ ማድረግ፣ አማራጮችን በማስፋት ቀልጣፋ፣ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የወደብ አገልግሎት ማግኘት በዕቅዱ ውስጥ የተካተቱ ሥራዎች ናቸው።

- በድንበር ጉዳዮችና በድንበር ተሻጋሪ ሀብቶች ትብብሮችንና ድጋፎችን ማሳደግ፦ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የተካለሉትን ድንበሮች በማስተዳደር፣ ሊካለሉ የሚችሉ ድንበሮችን በማከለል ለዘላቂ ሰላምና ትብብር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችን ፍትሐዊ አጠቃቀም ማሳደግ፣ ስለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ለዓለም አቀፉ ማህብረሰብ ትክክለኛ ግንዛቤ በማስጨበጥ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፎችን ለማስፋትና ለማጠናከር ሥራዎች ይሰራሉ።

- በሁለትዮሽ ግንኙነቶች ጥቅሞቻችንን ማሳደግ፦ ከነባር ስትራቴጂያዊ አጋሮቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር እንዲሁም አዳዲስ ስትራቴጂያዊ አጋሮችን በማፍራት ለሰላማችንና ለልማታችን ፋይዳ ያለውን ድጋፍ ማስገኘት፣ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር ያሉንን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር፣ አዳዲስ ግንኙነቶችን በመመስረትና የውክልና አድማሳችንን በማስፋት ለሰላማችንና ለልማታችን ድጋፍ ማስገኘት ቁልፍ ተግባራት ይሆናሉ።

- በባለብዙ ወገን መድረኮች ተደማጭነታችንና ጥቅሞቻችንን ማሳደግ፦ ሀገራችን በተለያዩ የባለብዙ ወገን መድረኮችና ፎረሞች ውክልናችንን በማሳደግና ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የሀገራችንን ጥቅም ማስጠበቅ፣ በሰላም ማስከበርና ማስጠበቅ ተልዕኮ ያለንን አስተዋጽዖ ማሳደግ፣ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም

ማረጋገጥ፣ ሀገራችን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን የምታደርገው ድርድር እንዲሳካ በመደገፍ ሀገራዊ ጥቅማችንን ማስጠበቅ፣ በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ማዕቀፎች ሸብርተኝነትንና ጽንፈኝነትን ለመዋጋት፣ ትብብርን ለማጠናከርና ድጋፍ ለማስገኘት ታቅዷል።

- በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ የሀገራችንን መልካም ገፅታ ግንባታን ማሳደግ፦ 300 ዋና ዋና በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋማት እንዲሁም 100 በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች የሚጽፉ ታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመተባበር የገፅታ ግንባታ ሥራ መሥራት፣ 50 የተመረጡ ዋና ዋና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሚድያዎች በሀገራችን ጉብኝት እንዲያደርጉ በማድረግ የሀገራችንን በጎ ገጽታ እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፣ የኢትዮጵያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድንን በማጠናከር ከ20 ሀገራት ጋር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለማጠናከርና ለማሳደግ ታቅዷል።

- የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሮችንና ጉድኝቶችን ማሳደግ፦ ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ጋር በጋራ በመሥራት የተመሠረቱ 225 ነባር ጉድኝቶችን ወደ 624 በማሳደግ የሀገራችን ከተሞችና ተቋማት ከሌሎች ሀገራት ከተሞችና የምርምር ተቋማት ጋር ትስስርና ጉድኝነትን እንዲፈጥሩ የመደገፍ፣ የባህል ማዕከላትን በማስፋፋትና በማጎልበትና የባህል ማስተዋወቅን በማካሄድ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የማጠናከር ሥራዎች ታቅደዋል።

- የዜጎችን መብትና ጥቅም ማሳደግ፦ ለሥራ መዳረሻነት ከተለዩ ሀገራት ውስጥ ከ90 በመቶ ከሚሆኑት ጋር የሁለትዮሽ የውጭ የሥራ ስምሪት ስምምነቶችን አዘጋጅቶ በመፈራረም 6,000,000 ዜጎችን የውጭ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የውጭ ጉዳይና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የተቋሙን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን ማሻሻል፣ መስሪያ ቤቱ ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችለው አደረጃጀትና አሠራር መዘርጋት፣ ውጤታማ የግብዓት አቅርቦትና የሃብት አስተዳደር ማረጋገጥ፣ ብቃት ያለውና ሙያዊ ሥነ ምግባር የተላበሰ የሰው ሃብት መገንባት፣ የተቋሙን የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት የሚረዱና ሀገራዊ ሪፎርምን መሠረት አድርገው የሚወጡ አዳዲስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን የአደረጃጀትና የአሠራር ማሻሻያዎችን መተግበር የሥልቶቹ አካል ናቸው። የተቋሙ የንብረት ማፍራት፣ የሪከርድ አስተዳደርና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ፖሊሲ እንዲወጣ ማድረግ፣ በመዲናችን ከሚገኙ ሚሲዮኖች ጋር ያሉንን ግንኙነት የሚመራ መመሪያ ማውጣትና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ተገልጋዮችን ማዕከል ያደረገ፣ ተደራሽነቱ የሰፋ፣ ጥራቱን የጠበቀና በተክኖሎጂ የተደገፈ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ የዘርፋን የልማት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከናወኑ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

# ምዕራፍ ስምንት

## የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የሀገራችንን የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳትና ሌሎች የብዝሃ ሕይወት ሀብትን በማልማት፣ በማንበር፣ በመጠበቅና ዘላቂ አጠቃቀምን በማስፈን እንዲሁም ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብርን በማሳደግ ዘላቂ ሀገራዊ ልማትና ዕድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፥

- የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፤ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የመጤ ወራሪ ዝርያዎችን የመለየትና እያደረሱ ያሉትን ጉዳት በጥናትና ምርምር በመታገዝ በቅደም ተከተል መቅረፍ፣ የተለያዩ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን በመሰብሰብ የጀኔቲክ ሀብትን ማንበር፤ ጠንካራ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ድርድርና ዲፕሎማሲ በማካሄድ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ የሚሆን የቴክኖሎጂ፤ የፋይናንስና የአቅም ግንባታ ድጋፍን ማሳደግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት በሀገሪቱ የልማት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተትና እንዲተገበር በማድረግ ከዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መጠን መቀነስና የደን፣ የብዝሀ ህይወትና የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃን ማጠናከር የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፥

- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት አሁን ካለበት 92.7 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ (MtCO2eq.) በ2022 በጀት ዓመት 162.3 ሚሊዮን ቶን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ መቀነስ፣ የአካባቢ ሕግ ተከባሪነትን ለማጎልበት በ2012 ተዘጋጅተው ከተተገበሩ 56 የሕግ ማዕቀፎች በ2022 ወደ 64 ማድረስ፣ በዱር እንስሳት መጠለያ የሚፈጸሙ ሕገወጥ ድርጊቶችን የመከላከል ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 62 በመቶ በ2022 ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፤ ሀገራዊ የደን ሽፋንን አሁን ከደረሰበት 15.5 በመቶ በ2022 ወደ 30 በመቶ የማሳደግና የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን በ2012 ከነበረበት 8.6 በመቶ የቆዳ ሽፋን በ2022 ወደ 14 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በተመሳሳይ የዱር እንስሳትና የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን የማበልጸግ ሥራን አሁን ካለበት 311,470 በ2022 ወደ 743,447 ማሳደግ፣ የማንበር ሥራን አሁን ካለበት ከ179,285 ዝርያዎችን በ2022 ወደ 764,361 ዝርያዎች ማሳደግ፤ በብዝሀ ሕይወት ዘለቄታዊ አጠቃቀም የተሠጠ የአርክቦት ፈቃድ ቁጥር በ2012 ከነበረበት 1,010 በ2022 ወደ 2,024 ለማድረስ ታቅዷል።

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥

- የዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶችና ድርድሮች የሀገራችንን ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ የሚያደርግ አሠራር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፤ የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ፤ የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፤ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፤ የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተቋማዊ አደረጃጀት እስከ ቀበሌ መዘርጋት፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ማሻሻል፣ ሀገር አቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች መረጃ መሰብሰብያ የዳታ ቋት በማሻሻል ወደ ሥራ ማስገባት፤ ሀገራዊ የሥርዓተ ምህዳር መረጃ ቋትን መዘርጋት፤ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ቋት መመሥረትና የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# ክፍል አራት

## የልማት ዕቅዱ የማስፈጸሚያ ስልቶች
## እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት



# ምዕራፍ አንድ

## የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች

ዘላቂ ልማትና ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚቻለው ውስን ሀብቶችና አቅሞችን በአግባቡ አስተባብሮና አሰናስኖ በመጠቀም አዳጊ፣ ተለዋዋጭና እየሰፉ የሚሄዱ በርካታ ፍላጎቶችን በቅድመ ተከተል በማሟላት ብቻ ነው። ስለዚህ የልማት ዕቅዱ ሲካሄድ በአጠቃላይ ያሉትን የሀብት አይነቶችና አቅሞች አሟጥጦ መጠቀምና በሂደት የአቅሞቹን አድማስ እያሰፋ መሄድ ጠቃሚ ይሆናል። እነዚህም እንደሚከተለው ተዳስሰዋል።

የተፈጥሮ ሀብት፦ በገጸ ምድርና በከርሰ ምድር የሚገኙ እንደ መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድን፣ መልካም የአየር ንብረት፣ የብዝሃ ሕይወት እንዲሁም የንፋስና የፀሃይ ኃይል የመሳሰሉ መሠረታዊ የተፈጥሮ ጸጋዎችን ያካትታል። ኢትዮጵያ ባላት የሥነ ምድር አወቃቀር፣ የተለያየ ሥነ ምህዳርና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምክንያት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ያሏት ሲሆን እነዚህም እንደሚከተለው ተዳስሰዋል።

- **መሬት፦** ኢትዮጵያ ሰፊ የመሬት ሀብት ያላት ሲሆን ካላት አቅም ውስጥ እስካሁን ጥቅም ላይ የዋለው ትንሽ ነው። በተለይም መታረስ ከሚችለው መሬት ውስጥ የተጠቀመችው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። በዚህም በሚቀጥሉት ዓመታት ለግብርና ምርት እንዲሁም ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ የልማት ፍላጎቶች መዋል የሚችል ሰፊ የመሬት ሀብት ታሳቢ ተደርጓል።

- **ማዕድን፦** የተለያዩ የከበሩ፣ ብረትና ብረት ነክ፣ የኢንዱስትሪ፣ የግብርናና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ የጌጣጌጥና የኢነርጂ ማዕድናት እንዳሏት ባለፉት ዓመታት በዘርፉ የተካሄዱ የሥነ ምድር ጥናቶች ያሳያሉ። በቀጣዮቹ አስር ዓመታትም የወርቅ፣ የከሰል ድንጋይ፣ የብረት፣ የፖታሽ፣ የታንታለም፣ የእምነ በረድ፣ የነዳጅና ሌሎች ማዕድናት የማውጣትና የማልማት ሥራዎች ይከናወናሉ።

- **ውኃ፦** በውኃ ረገድ ያሉን ከሀይቆች፣ ከኩሬዎችና ከረምት ከበጋ ከሚፈሱ ወንዞች የምናገኘው የውኃ ሀብት ኢትዮጵያን የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ማማ ያሰኙ ሲሆን በዚህ ረገድ ያለው አቅም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመት ይህንን አቅም ጥቅም ላይ ለመዋል ታሳቢ ተደርጓል።

- **የተፈጥሮ መስህብ፦** የተፈጥሮ መስህብ ሀብቶች ማለትም ማራኪ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣ ፏፏቴዎች፣ የተፈጥሮ ፓርኮች፣ እሳተ ገሞራዎች፣ የዱር እንስሳት፣ ደኖችና በውስጣቸው የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አእዋፋት ለቱሪዝም፣ ለትምህርትና ለምርምር ሥራዎች አቅሞች ናቸው።

ቁሳዊ ሀብት፦ ቁሳዊ ሀብቶች በሰው ልጆች የተገነቡና ለተለያየ ጠቀሜታ ሊውሉ የሚችሉ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረቶችን ያጠቃልላል። የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የሚመጣው ከተሜነት ከፍተኛ የቁሳዊ ሀብት ልማት ዝግጅትን የሚጠይቅ ሲሆን እስካሁን በኃይል፣ በመጠጥ ውኃ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በመስኖ፣ በማምረቻ ፋብሪካዎች (የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ) የተፈጠሩት አቅሞች ለቀጣይ ልማት መነሻ ይሆናሉ። ቀጣይ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሰው ሠራሽ የቁሳዊ ሃብቶች አቅምን አሟጥጦ ከመጠቀም በተጨማሪ በተለይም የኃይል አቅርቦት፣ የአይሲቲ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመስኖ፣ የመጠጥ ውኃ፣ የመንገድ፣ የባቡርና የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶችን በማጎልበት ረገድ ተጨማሪ አቅሞች የሚፈጠሩ ይሆናል።

- **የኤሌክትሪክ ኃይል፦** ሀገራችን ከተለያዩ ምንጮች (በዋንኛነት ውኃ፣ ንፋስ፣ ፀሐይ፣ እንፋሎት) ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ እምቅ ሀብት ያላት ሲሆን፣ እስካሁን በሥራ ላይ የዋለው ግን አነስተኛው ክፍል ነው። የውኃና ታዳሽ ኢነርጂ ሃብትን በፍትሐዊነትና በዘላቂነት በማልማትና በማስተዳደር የዜጎችን የኃይል ፍላጎትና ሁለንተናዊ ሕይወት ማሻሻል፣ የኢነርጂ አቅርቦትና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ለፈጣን ልማትና ዕድገት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

- **መስኖ፡-** በአሁኑ ወቅት በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬት ከ5.8 እስከ 7.5 ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ የለማው 20 በመቶ ብቻ ነው። እየታረሰ ካለው 15 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ በመስኖ የለማው 8 በመቶ ብቻ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ አንጻር በቀጣዩ አስር ዓመታት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። በዚህም መሠረት የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን ከ6 መቶ ሺ ሄክታር ወደ 2 ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ ፤ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታን ከ490,000 ሄክታር ወደ 1,200,000 ሄክታር ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለይቶ መገንባትና ከዚህ በፊት የተጠኑና ወደ ሥራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ገምግሞ ወደ ግንባታ ማስገባትና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ።

- **ትራንስፖርትና መገናኛ፡-** በሀገር ደረጃ የተዘረጉ መንገዶች፣ ተገንብተው አገልግሎት መስጠት የጀመሩና በመጠናቀቀ ላይ ያሉ የባቡር መስመሮች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አውታሮች፣ ደረጃቸውን የጠበቁና የበረራ መቆጣጠሪያ የተተከለላቸው ኤርፖርቶች፣ መርከቦችና ደረቅ ወደቦች በዕቅዱ ዘመን ለሚጠበቀው አጠቃላይ ዕድገት ብሎም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። የእነዚህ መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ሎጂስቲክስን በማቀላጠፍ የሌሎች ዘርፎችን አፈጻጸም ያቀላጥፋል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ኢንዱስትሪ በቱሪዝም ልማት፣ በውጭ ንግድና በቀጠናዊ የልማት ትስስር ለተያዙ ግቦች መሳካት እንደ ትልቅ መሠረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል።

- **የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ፡-** ባለፉት ዘመናት የተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ የተከናወኑ ሰው ሠራሽ ቁሳዊ ሀብቶች በቀጣይ ለታቀደው ኢንዱስትሪያላይዜሽን የማስፈጸሚያ እንደ ግብዓት ያገለግላሉ።

ሰብዓዊ ሀብት፦ የአንድ ሀገር አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት፣ በተለይም ከፍተኛ የወጣቶች ድርሻ፣ የትምህርት፣ የዕውቀትና የክህሎት ዝግጅት ደረጃ እንዲሁም ጤንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ለዘላቂ ልማትና ብልጽግና መሳካት ቁልፍ ምንጮች ናቸው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በ2012 ከተገመተው 99.75 ሚሊዮን በ2022 ወደ 122.3 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በሀገሪቷ እየተስተዋለ ያለው የሥነ ሕዝብ ሽግግር (demographic transition) በቀጣዮቹ የልማት ዓመታት እንደሚቀጥል ይገመታል። ይህ ወጣት የሠራተኛ ኃይል የዕድገት ምንጭነት አቅሙ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም ከእንደዚህ ዓይነቱ የሥነ ሕዝብ ሽግግር በተለመደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማይገኝ የኢኮኖሚ ዕድገትን ወይም የሥነ ሕዝብ ለውጥ ትሩፋትን (demographic dividend) ዕውን ማድረግ ይቻላል።

በአጠቃላይ የሰብዓዊ ሀብት መሻሻል በራሱ ለምርት ግብዓትነት ከመዋሉም በላይ የቴክኖሎጂ አቅሞችን አሟጥጦ ለመጠቀም ይረዳል። ሆኖም ይህ እንዲሳካ የሕዝብ ብዛት የዕድገት ምንጭ እንዲሁም ምርታማ እንዲሆን በትምህርት፣ በሥልጠናና በምርምር ዙርያ ከፍተኛ ሥራዎች መሥራትን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ እስካሁን በትምህርት ዘርፍ የተገነቡ አቅሞች ሀገሪቷ የተሻለ የሰብዓዊ ሀብቶች አቅም እየገነባች ስለመሆኑ አመላካች ነው። በአሁኑ ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በትምህርት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት ከግልና ከመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ጨርሰው ለሥራ ዝግጁ ይሆናሉ። የተያዘውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እየተመረቁ ለሥራ ዝግጁ ከሚሆኑ ዜጎች ቁጥር አንጻር ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሰብዓዊ ሀብት አቅም ያላት ሀገር መሆኗ የማያከራክር ሲሆን ይህም ለታቀዱት የልማት ግቦች ከፍተኛ አቅም ይፈጥራል።

**የፋይናንስ ሀብት፦** አንድ ሀገር በጥሪት መልክ ያፈራቻቸውና በቀጣይም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨውም ሆነ ከሌሎች ምንጮች ልታሰባስባቸው የምትችላቸው ሀገራዊ የፋይናንስ ሀብት መጠን ለልማት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ወሳኝ ናቸው። በዚህ ረገድ ኢትየጵያ ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበች ሲሆን ከዚህም የሚሰበሰበው ገቢ እንዲሁም ቁጠባ ለተለያዩ የልማት ፋይናንስ ፍላጎቶች ማሟያነት ሲውል ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በተከናወኑ ሀብትን የማፍራትና የዜጎችን ገቢ የማሳደግ ሥራዎች እንደ ሀገር ያፈራናቸው የፋይናንስ ሀብቶች ለሀገራዊ ልማቱ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ነበራቸው። በሚቀጥሉትም ዘመናት የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማስቀጠልና ከዚህም ሊሰበሰብ የሚችለውን የገቢ መሠረትንና መጠንን እንዲሁም ቁጠባን በማሳደግና እነዚህንም ሀብቶች በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ዘላቂ ልማትንና ሀገራዊ ብልጽግናን ማሳካት ይቻላል። በዚህ ረገድ በተለይ ሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የሚኖሩትን ዜጎች በማስተባበርና በማቀናጀት የተነደፉትን የልማት ግቦች በማሳካት ሂደት ህዝባዊ የጋራ አሻራ እንዲያኖሩ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል።

**ማህበራዊ ሀብት፦** ህዝቦች ለዘመናት አብሮ በመኖር ሂደት የገነቧቸው ባህሎች፣ ልማዶችና ሌሎች የጋራ እሴቶች የሀገሪቷን የልማትና የብልጽግና ጉዞ ለማሳካትና የዜጎቿን መሻቶች ለማሟላት ከሚያስፈልጉ ውድ ፀጋዎች ውስጥ ይካተታሉ። ከላይ የተገለጹ ሀብቶች አቅም አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ እነዚያን ሀብቶች በሚፈለገው መልኩ አቀናጅቶ ሥራ ላይ ለማዋል መልካም ማህበራዊ መስተጋብርና ዘላቂ ሰላም የሚያመጡ እሴቶች ያስፈልጋሉ። በዚህ ረገድ ለዘመናት የኖረው የመከባበር፣ የመደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመሥራት ባህሎችና እሴቶች እንዲሁም በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ የተሰናሰሉ አዎንታዊ ሥርዓታት በቀጣይ የታቀዱ የልማት ግቦችን በማሳካት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

**ሌሎች ሀብቶችና መልካም አጋጣሚዎች፦** ሀገራችን ባላት ቀጠናዊና አህጉራዊ መልካም ትስስሮች ለምታቅዳቸው የልማት ግቦች መሳካት የሚያግዝ ተጨማሪ አቅሞች አሏት። በዓለም አቀፍ መድረክ የፖለቲካ ካፒታል ተጨማሪ የልማት አቅም ሲሆን ኢትዮጵያ በታሪክ በገነባችው ተሰሚነትና በቅርቡም በመደመር እሳቤ ባካሄደችው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሪፎርሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ተቀባይነትና ተዓማኒነት አግኝታለች። የፈረመቻቸው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶቿም የዚህ ተጨማሪ አቅም አካል ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ነጻነቷን አስከብራ ለማቆየት ባደረገቻቸው የፀረ ቅኝ ግዛት ትግሎችና ድሎች ጨምሮ ባገኘቻቸው አንጸባራቂ ድሎች እንዲሁም አህጉራዊና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምስረታዎች በነበራት ሚናዎችና አሁንም ባላት ንቁ ተሳትፎዎች ከፍ ያለ የፖለቲካ አቅም ፈጥራለች። በተመሳሳይ በተባበሩት መንግስታትና ሌሎች በዓለም አቀፍ ተቋማት ጥላ ስር የሰላም አስከባሪነት ተሳትፎ፣ በጂኦስትራቴጂክ አቀማመጥና በዓለም አቀፍ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ (geo-political) ማዕከልነት ያላት ተፈላጊነት ተጨማሪ የፖለቲካ አቅም ይፈጥርላታል። ይህም የፖለቲካ ካፒታል ለልማት ወሳኝ የሆኑትን የፋይናንስ አቅሞችና የፖለቲካ ድጋፎች ከአጋር ሀገሮችና ተቋማት ለማግኘት ተጨማሪ አቅም ይፈጥርላታል። ይህ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም ከመሆኑም በላይ የውጭ ምንዛሪ ዕጥረትን ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚቀንስ በመሆኑ ትልቅ የልማት አቅም ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና
## የማስፈጸሚያ ስልቶች

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ሊደረስባቸው የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚሆኑ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ስልቶች በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ተመላክተዋል። በዚህ መሠረት የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች በጥቅሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ጥራት ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥና ወደ አስተማማኝ የዕድገትና ብልጽግና ጎዳና ለመሸጋገር ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚመዘገብ አነስተኛ የካፒታል ክምችት ከአነስተኛ ቁጠባና ኢንቨስትመንት የሚመነጭ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ትርጉም ያለው የልማት ፋይናንስ በማመንጨት ከብክነት በፀዳ መልኩና በቅልጥፍና ለታለመለት ዓላማ ላይ በማዋል ጥራት ያለው ዕድገትን ማስመዝገብና የካፒታል ክምችትን ማሳደግ ይቻላል።

በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችንና ዋና ዋና ግቦችን ዕውን ለማድረግ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍን (financial resource envelope) ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የልማት ፋይናንስ ምንጭን ከሀገር ውስጥ ገቢና ቁጠባ እንዲሁም ከውጭ ምንጮች በአግባቡ በመለየት፣ የኢኮኖሚውን ገቢ የማመንጨት አቅም ከግምት በማስገባት፣ የልማት ዕቅዱ ባስቀመጣቸው የትኩረት መስኮችና አቅጣጫዎች ቅደም ተከተል መሠረት ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ባገናዘበ መልኩ አቅርቦትንና ፍላጎትን በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠንና ዝርዝር የልማት ፋይናንስ ምንጭ የሚያሳይ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

በዕቅዱ የትግበራ ዘመን የመንግሥት የኢንቨስትመንት ወጪ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ዋና ዋናዎቹን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዘርፎች ላይ በማተኮር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም ጥራት ያለውን የመንግሥት ኢንቨስትመንት በማከናወን በዕቅዱ የተመለከቱትን ግቦች ከማሳካት አንጻር ያላቸው ፋይዳ በተለይም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገብ፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከማስፈን፤ ድህነትን ከመቀነስ፤ የግል ዘርፉን ድርሻ ከማሳደግ፤ የሀገሪቱን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ከማዋል፣ ዘርፎች መካከል ትስስርና ተመጋጋቢነት በማጎልበት የሥራ ዕድል ከመፍጠርና የወጪ ንግድን ከማሳደግ አንጻር የኢንቨስትመንቱን ቅደም ተከተል የሚመሩ መሠረታዊ መነሻዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

በዚህም በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር 1210/2012 በጀት ዓመት መሠረት በዕቅዱ ዘመን በመንግሥት የሚከናወኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርተው በጥልቀት እንዲዘጋጁ ይደረጋል። ፕሮጀክቶቹም በገለልተኛ ወገን ተገምግመው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ። በተጨማሪም በዕቅዱ ዘመን የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነትና ቅልጥፍናን ለማሳደግ ከላይ በተጠቀሱ መስፈርቶች መሠረት በየዘርፉ የተለዩትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል። በተመሳሳይ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ተግባራዊ የሚደረጉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለተቀመጠው የልማት ግብ የሚኖራቸውን ፋይዳ እንዲሁም የሚጠበቁ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል። ጥራት ያለው የሰው ኃይል የኢኮኖሚን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ በዕቅዱ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል። የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነትና በጥራት ማቅረብ ካልተቻለ የዕቅዱን ትላልቅ ግቦች ለማሳካት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም ከኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አቅርቦትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን ከኢኮኖሚው ባህሪ ጋር

ተለዋዋጭ በመሆኑ ይህንን ቀድሞ በማቀድ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም የትምህርት ዘርፉ የሚያቀርበው የሰው ኃይል ከኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከሰተውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን (skill mismatch) ከማስወገድ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ዘላቂ ምርታማነትን በማሳደግ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ያለው አዎንታዊ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፍላጎት በክህሎት አይነት፣ መጠንና የጥራት ደረጃ በየዘርፉ በዝርዝር የሚለይ የልማት ዕቅዱ የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

ዘላቂ የሆነ የስርዓታት ግንባታ ማዕቀፍ፡- ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎችን ወጥና ተናባቢ ማድረግ፣ ዘላቂ የሆነ የተቋማት አደረጃጀት መፍጠር እና አቅም መገንባትና ተቋማዊ ድንበሮችን በመሻገር (across organi-zational boundaries) በጋራ ተግባራዊ በሚደረጉ አዳዲስ ሥልቶች አማካኝነት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል።

# ምዕራፍ ሦስት

## ክልላዊ እና አካባቢያዊ
## የተመጣጠነ ልማት እና ተወዳዳሪነት

ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግሥት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የተደረጉ የልማት ዕቅዶች ሀገራዊ የልማት ዕቅዱን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ቢሆንም ከሀገራዊ የልማት ዕቅዱ ጋር የሚያስተሳሥራቸው የአሠራር ሥርዓት አልነበረም። በተጨማሪም በክልሎችና ከክልሎች በታች ባሉ የመንግሥት አስተዳደር አካላት ደረጃ ጠንካራ የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ የትግበራና የአፈጻጸም ክትትል አቅም እንዲሁም በቂ ፋይናንስ አለመኖር በዕቅዶቹ ተግባራዊነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሠረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሠት በታቀደ መልክ የተከናወነ ባለመሆኑ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይልና ሌሎች እምቅ አቅሞችን ስልታዊ በሆነ አግባብ ለመጠቀም አላስቻለም።

በተጨማሪም በየደረጃው ያሉ በልማት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ሚና በግልጽ መግባባት የተደረሰበት ተቋማዊና ሕጋዊ አደረጃጀትና የተሰጡ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ ስልጣንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሠራር አልነበረም። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ ባሉ የመንግሥት አስተዳደሮች ከላይ ወደታችና የጎንዮሽ ግንኙነት በሚጠበቀው ደረጃ ካለመገኘቱም በላይ የትብብር ማዕቀፉ ደካማ ነበር። በፌዴራል፣ በክልልና ወረዳ አስተዳደሮች ታቅደው ተግባራዊ የተደረጉ ኢንቨስትመንቶች ለሀገራዊ ልማት የሚኖራቸው አስተዋጽዖና የሚፈስባቸው የሀገሪቱ ውስን ሀብት ውጤታማነት በአግባቡ ተጠንተው አልነበረም። በተጨማሪም የክልሎች የልማት ዕቅድ የአጎራባች አካባቢዎችና የልማት ዘርፎችን በማቀናጀትና በማስተሳሰር አለመከናወኑ የቅንጅት ችግር አስከትሏል።

ባለፉት ዓመታት በፌዴራል መንግሥትና በተለያዩ የመንግሥት አካላት የተከናወኑ መሠረተ ልማቶች ፍትሐዊነትን እንዲያስፋፉ ከማድረግ አንጻር ሰፊ የሆነ ሥራ የተሰራ ቢሆንም በክልሎችና በክልሎች ውስጥ ደግሞ ከማዕከል ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች የመንገድ፣ የመብራትና ሌሎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ፍትሐዊ ስርጭት ላይ ክፍተቶች ተስተውሏል። በመንገድ መሠረተ ልማት ዘርፍ ወረዳዎችን ከፌዴራል መንገድ ጋር ከማገናኘት አንጻር በሀገሪቱ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የግብርናና ሌሎች ተፈጥሮዊ እምቅ አቅሞች ያሉ ቢሆንም የመንገድ መሠረተ ልማት በአንጻራዊነት በእነዚህ አካባቢዎች ባለመስፋፋቱ ያላቸውን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ እንዳይውል በማድረግ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር ማነቆ ሆኗል።

ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ በከተማና በገጠር መካከል ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድል ልዩነት በመፈጠሩ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት እንዲጨምር፣ በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች መካከል ያለው የመሠረተ ልማት አቅርቦት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ልዩነት ደግሞ አብዛኛውን ሕዝብ የተሻለ አገልግሎት ለማግኘት ከተሞችን እንዲመርጡ አድርጓል። የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች እንዲሁም ክልሎች ለወረዳዎች የበጀት ድጎማ በማድረግ ተመጣጣኝ የሆነ የፊስካል አቅም በመፍጠር የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በአገልግሎት ላይ ያለው የጥራት ደረጃና የተደራሽነት ችግር በክልሎች መካከል እንዲሁም በክልሎች ውስጥ በገጠርና በከተማ ወረዳዎችና አካባቢዎች እንዲሁም ለማዕከል ቅርብና ሩቅ በሆኑ አካባቢዎች መካከል አለመመጣጠንን ፈጥሯል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተማ ልማትን ለማዘመንና የከተማ አሰፋፈርን ለመምራት የሚያስችሉ መጠነ ሰፊ የሆኑ የጥናት ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ከተሞች ካላቸው ውስጣዊ ጥንካሬ አንጻር ያላቸውን አቅም ለመጠቀም የሚያስችል የከተማ አመራር አለመኖር፣ ከተሞችና በከተሞች ዙሪያ ያሉ አካባቢዎችን አቀናጅቶ ከማቀድና ከመምራት አንጻር የተሞከሩ ሥራዎች ውጤታማ አለመሆናቸው፣ በከተሞች መሠረተ ልማት ለማስፋፋት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከተሞች በሚያስፈልጋቸው መጠን ፋይናንስ በማሰባሰብ የመሠረተ ልማትና የልማት ሥራዎችን በማከናወን ከተሞችን በሚጠበቀው ደረጃ ለኑሮ ምቹ ማድረግ አልተቻለም። ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት

ከተሞችን እንደዋነኛ መዳረሻ እያደረገ ቢሆንም በከተሞች ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ እምብዛም በመሆኑ የሥራ አጥነት ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በተጨማሪም ሀገሪቱ የምትከተለው የከተማ አሰፋፈር አማራጭ በሁሉም አካላት መግባባት ተደርሶበት እየተተገበረ ባለመሆኑ በከተሞች ውስጥ የሕግ ወጥ ግንባታዎች፣ የከተሞች ኢ-መደበኛ መለጠጦች (urban sprawl) እና የከተማ ውስጥና በከተማ ዙሪያ የመሠረተ ልማትና የመንግሥት አገልግሎቶች እጥረቶች እንዲከሰቱ እያደረጉ ይገኛል።

በከተሞች ውስጥ የመሬት አጠቃቀም በዕቅድ ባለመመራቱ ከተሞች ወደ ግብርናና ገጠር አካባቢዎች ባልታቀደ መልክ በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ። በከተሞች ላይ የተሠራው ሥራ እምብዛም ከመሆኑ አኳያ አዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ በዕቅድ ላይ ያልተመሠረተና የከተማዋን የወደፊት ዕድገትና በሀገሪቱ የከተሞች የተመጣጠነ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መከማቸትና ያልታቀደ የሰው አሰፋፈር እያታየ ይገኛል። በተመሳሳይ በክልል ዋና ዋና የከተማ ማዕከሎችና በአዲስ አበባ የሚታዩ ተግዳራቶች በተመሳሳይ ሁኔታ መታየት የጀመሩ ሲሆን እነዚህን ተግዳሮቶች በተቀናጀ መልክ የማስተዳደርና የመፍታት እንቅስቃሴ በተደራጀ ሁኔታ የተመራ ባለመሆኑ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ ነው።

በአርብቶ አደሩና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ሥነ ምኅዳሩን መሠረት ያደረገ የልማት ሥራ ያለማከናወን፣ የህብረተሰቡን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም ችግር፣ የመጠጥ ውኃና የእንስሳት መኖ እጥረት፣ የተፈጥሮ ሀብትና ግጦሽ መሬት መመናመን፣ የመሠረተ ልማት ሽፋን አነስተኛ መሆን፣ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቃም ላይ ግጭቶች መኖር፣ የእንስሳት ገበያ ትስስር ዝቅተኛ መሆን፣ የአየር ንብረት ለውጥና ድርቅ፣ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚከናወኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎችን በጥናትና በቅንጅት አለማከናወንና የአርብቶ አደር አካባቢ ልማትን የሚመራ የማስፈጸሚያ ፖሊሲ ያለመኖር ተጠቃሽ ማነቆዎች ናቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ የክልላዊና የአካባቢያዊ የልማት ሥራዎች የተከነወኑት በየደረጃው ባለው ሕጋዊ የመንግሥት አደረጃጀት በኩል (administrative regional planning approach) ሲሆን በተቀናጀ መንገድ ቦታን (space) መሠረት በማድረግ በተደራጀ ሁኔታ በአካባቢያዊ የልማት ዕቅድ ማዕቀፍ (spatial planning framework) የተከናወኑ አልነበሩም። በመሆኑም በቀጣይ የአስር ዓመት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ያሉትን እምቅ የተፈጥሮ አቅሞች መሠረት ያደረገ የኢንቨስትመንት ፍሰትና የመሠረተ ልማት ስርጭት እንዲኖር የማድረግ፤ ክልሎችና የአካባቢ መስተዳድሮች ተጨባጭ ሁኔታቸውን መሠረት አድርገው ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ከማድረግ ባሻገር እነዚህ የልማት ዕቅዶች ሀገራዊ የልማት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የክልላዊ፣ አካባቢያዊና የተመጣጠነ ልማት ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ የልማት ዕቅድ እንዲኖር ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም የተፈጥሮ ሀብት እምቅ አቅምን ለመጠቀምና ፍትሐዊና ውጤታማ የመሠረተ ልማት አገልግሎት ሥርጭትንና ተጠቃሚነትን እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የአካባቢ ጥበቃን ለማከናወን የሕዝብ አሰፋፈርን በታቀደ ሁኔታ የመምራት፤ የተለያዩ አካባቢዎችን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ለማዋል በቅድሚያ መሠረተ ልማቶችን የማልማትና የልማት ቀጠናዎችን ለማልማት የፋይናንስ አቅርቦትና የማትጊያ አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም በሀገራዊ የልማት ግቦች ላይ በየደረጃው ስምምነት ላይ በመድረስ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዘርፎችና አካባቢዎችን ማዕከል ያደረገ የኢንቨስትመንት ክንውን እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሕግ ከተቀመጠው የአስተዳደረዊ እርከን በተጨማሪ በተለያዩ ደረጃ ያሉ የልማት ሃይሎች በትብብር የልማት ሥራዎችን መከናወን አለባቸው። በሀገሪቱ የትኛውም አካባቢ የሚኖር ዜጋ ተመጣጣኝ የሆነ የመንግሥት አገልግሎትና መሠረተ ልማት እንዲያገኝ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትና እምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ሊደረግላቸው

ይገባል። ከዚህ ባሻገር የተለያዩ ክልሎችና የሀገሪቱ አካባቢዎች ያላቸው እምቅ አቅምና አለኝታ የተለያየ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እነዚህ ቦታዎች ውጤታማ በሚሆኑበት ዘርፍ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ (specialization based on comparative and competitive advantage) በክልሎችና በአካባቢዎች መካከል መስተጋብር እንዲኖር በማድረግ የልማት ትስስርን ማጠናከር አስፈላጊ ይሆናል።

ትላልቅ ከተሞችን በዙሪያቸው ካሉ ከተሞች ጋር በማስተሳሰር ማልማት (poly centric development)፣ በተመሳሳይ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ከተሞችን (secondary cities) ሚና በማሳደግ የሚገባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፤ ትላልቅ ከተሞች ያላቸውን የተከማቸ የምርት፣ የሰው ሃብትና የመሠረተ ልማት አቅም (agglomeration economies) በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማና ኢንዱስትሪ መስፋፋቶች ወደሌሎች ውጤታማ ቦታዎች እንዲሰራጩ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰው ኃይልና ኢንቨስትመንት ስርጭትን ውጤተማነት ለማጎልበት የዜጎችን በነፃነት መዘዋወር (Free Mobility) የሚያሳልጡ የሕግ ማዕቀፎችን፣ አሠራሮችንና ማበረታቻዎችን መተግበር ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪን፣ የመሠረተ ልማትንና የግብርና ልማትን ከመሬት አጠቃቀም ጋር በማስተሳሰር የተፈጥሮን ሁኔታ በመጠበቅ ልማት የሚበረታታባቸው (ሰፊ የከተማ ማስፋፋትና ኢንዱስትሪላይዜሽን)፣ ልማት በታቀደ ሁኔታ የሚከናወንባቸው (ከተማና ኢንዱስትሪ በተመጠነ ሁኔታ የሚስፋፋባቸው)፣ ልማት በተወሰነ ሁኔታ ብቻ የሚከናወንባቸው (የምግብና የአግሮ ኢኮሎጂካል ዞኖች) እና የማይፈቀዱ የመሬት አጠቃቀምን (የቅርስና የተፈጥሮ መስህቦችን) ማዕከል ያደረገ ልማት በማከናወን ዝቅተኛ አቅም ካላቸው አካባቢዎች ወደ ከፍተኛ አቅም ወደ አላቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴንና አሰፋፈርን ማበረታታት፤ እነዚህን በሚያሳልጡ የፋይናንስና አስተዳደራዊ ማትጊያዎች ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

በተመሳሳይ የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሀብት በላቀ ደረጃ ማልማትና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ ጥራት ያለው የእንስሳት ጤና ሽፋንና አገልግሎትን ማሳደግና፣ የእንስሳት ዝርያዎችን መጠበቅና ማሻሻል፣ የአርብቶአደር አካባቢ ምርምርን ማሻሻል፣ የእንስሳት መኖና ግጦሽ ልማት ማስፋፋት፣ የገበያና ግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ፣ በእያንዳንዱ እንስሳት ዓይነት የኤክስቴንሽን ፓኬጆችን መቅረፅ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የአርብቶ አደር በቅርብ ርቀት ከሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች በአጠቃላይ ልማት፣ በአገልግሎት፣ በግብዓትና ምርት አቅርቦት እንዲተሳሰሩ እንዲሁም የተለየ የኢኮኖሚ መሠረት ካላቸው አጎራባች አካባቢዎች በገበያ ትስስርና በሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲተሳሰሩ መደረግ አለበት። ለአርብቶ አደርና ለጠረፍ አካባቢዎች መሰረታዊ የሆኑ የአገልግሎት አሰጣጥና መሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሻሻል ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖራትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስር በማጠናከር ለተያዘው የልማት ግብ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል።

# ምዕራፍ አራት

## የልማት ዕቅዱ ስጋቶችና ስጋቶቹን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች

# 4.1 የልማት ዕቅዱ ስጋቶች

ስጋቶች (threats, vulnerabilities and risks)፦ የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ ውጤታማነት ሊያደናቅፉ የሚችሉና በልማት ዕቅዱ የታቀዱ ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ክስተቶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ስጋቶች ከመከሰታቸው በፊት የመከላከያ ስትራቴጂ ለመንደፍና የሚያስከትሉትን አደጋ ለመቀነስ ከወዲሁ መለየት ይገባል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱን ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ስጋቶች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

1. የአስር ዓመቱን ልማት ዕቅድ ለማስፈፀም የሚጠይቀው ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ ፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በሚፈለገው መጠንና ጥራት ካልተገኘ በልማት ፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ ድልድል፣ በግብዓት አቅርቦትና በመሳሪያዎች ግዥ ላይ ሊፈጥር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆን፣
2. የዓለም አቀፍ የንግድ አሠራሮችና ሕጎች ውስብስብትና በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆን እንዲሁም የዓለም ኢኮኖሚ በየጊዜው መቀዛቀዝና የሸቀጦች ዓለም አቀፍ ዋጋ በየጊዜው መቀያየር በወጪ ንግድ ገቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆን፣
3. በሰው ሠራሽ እንዲሁም በተፈጥሮ ለሚከሰቱ አደጋዎች ማለትም ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጤና ወረርሽኞች ተጋላጭ መሆንና አደጋዎችን ለመቀልበስ የሚወሰዱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ለልማት ሊውል የሚችለውን ሀብት የሚሻሙ መሆናቸው፣
4. የኮቪድ-19 አሉታዊ ተጽዕኖ ለሚቀጥሉት ሦስትና አራት ዓመታት ሊቀጥል እንደሚችል ጥናቶች የሚያመለክቱ ሲሆን ይህም ኢንዱስትሪዎቻችን በዋናነት ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ወረርሽኙ በዘርፉ ምርትና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መመላከቱና የዓለም ሀገራት በተናጠልና በቡድን ኢኮኖሚያቸውን ለማነቃቃት በሚወስዱት አስተዳደራዊና የፖሊሲ እርምጃዎች የሀገራችንን ምርት ተወዳዳሪነት ሊቀንስ እንደሚችል ይህም በአስር ዓመቱ ልማት ዕቅድ የተጣሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ግቦች ስኬት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆንና
5. ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን እየተስተዋለ የመጣው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ይህን ተከትሎ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የኢኮኖሚና ማህበራዊ አለመረጋጋቶች መከሰታቸው፣ ይህንንም በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት ረዘም ያለ ጊዜ የሚፈልግ ሲሆን በልማት ዕቅዱ ስኬት ዙሪያ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ስጋቶች ናቸው።

# 4.2 የልማት ዕቅዱ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች

ስጋቶች ከመከሰታቸውና ወደ አደጋ ከመሸጋገራቸው በፊት ለመከላከል የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል። በተለይም ደግሞ የአደጋ ስጋትን በመለየት፣ በመተንበይ፣ በመተንተንና የቅድመ ጥንቃቄ ዕርምጃዎችን በመውሰድ ጉዳት እንዳያደርሱ ወይም የሚስያከትሉትን ጉዳት መቀነስ የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል።

የፋይናንስ እጥረትን በተመለከተ፤ የተጀመረውን የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ዘመናዊ የማድረግ ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል እንዲሁም የታክስ መሠረቱን በማስፋት፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባን በማሳደግ፤ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚኖረውን የትብብር ማዕቀፍ ወደ መሬት በማውረድና የውጭ ምንዛሪ ዕድልን በአግባቡና በቁጠባ በመጠቀም ችግሩን ለመከላከል ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በተጨማሪም አዳዲስና ዘመናዊ የፋይንናስ አሠራር ምንጮችን (innovative development financing) ወደ ተግባር በማስገባት ሊከሰት የሚችለውን የፋይናንስ እጥረት ለመቅረፍ በትኩረት ይሠራል።

የአደጋ ተጋላጭነትን በተለይም የድርቅና የጎርፍ ተጋላጭነትን ከመከላከል አንጻር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የህዝቡን ግንዛቤ ይበልጥ በማስፋትና በማዳበር በተለይም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ የሚተገበሩ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራምን በማስቀጠል የሀገሪቱን የደን ሽፋን ለማሳደግ በትኩረት ይሠራል። በተመሳሳይ በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የውኃ ሀብቶችን በማነጽ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በአጠቃላይ ለተፈጥሮ አደጋዎች የማይበገር ኢኮኖሚና ማህበረሰብ ለመገንባት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊከሰት የሚችል የዋጋ አለመረጋጋትን በሀገር ውስጥ በሚወሰዱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ ዕርምጃዎች ሙሉ በሙሉ መቀልበስ እንደማይቻል የታወቀ ቢሆንም ሊከሰት የሚችለውን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል በበቂ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል። በዚህ ረገድ ለወጪ ንግድ የምናቀርባቸውን ሸቀጦች በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ በሁሉም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ምርት፣ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ አሠራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ። በተለይም የወጪ ምርቶችን መዳረሻ ለማስፋት ቀጠናዊ የልማት ትስስርን የሚያበረታቱ ስምምነቶችን ተግባራዊ በማድረግና የዓለም ንግድ ድርጅት ድርድርን በማጠናቀቅ አዳዲስ የገበያ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል። በተጨማሪም የገቢ ንግድ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ሸቀጦች ለመተካት የተጀመረው አቅጣጫ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የኮቪድ - 19 ተጽዕኖን ለመቀልበስና ኢኮኖሚውን ወደ ነበረበት ፈጣን የዕድገት መስመር ለመመለስ ለምርታማና ሰፊ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ ለሚችሉ ዘርፎች ትኩረት መስጠት፣ የመንግሥት ኢንቨስትመንት የግሉን ዘርፍ በሚያበረታቱ የተመረጡ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣ ውጤትን መሠረት ያደረገ የማበረታቻና የድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣ ዘመናዊ የአመራረት ስልትን መከተልና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ እንዲሁም አለማቀፋዊና ቀጠናዊ የገበያ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ ለወጪ ንግድ ምርቶች ገበያ በማፈላለግ በኮቪድ - 19 ምክንያት ሊከሰት የሚችለው በዓለም አቀፍ የፍላጎት መቀዛቀዝ ኢኮኖሚውን እንዳይጎዳው ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

በአንድ ሀገር በተለያዩ ጊዜያት የፖለቲካ ችግሮች፣ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮች ቢሆንም ችግሮቹ ለልማት፣ ለሰላምና ለመሰረታዊ የዜጎች ደህንነት አስጊ ሆነው እንዳይቀጥሉ ዘላቂ መፍትሄ ሊቀመጥላቸው ይገባል። በልማት ዕቅዱ የተያዙትን ውጥኖች ከግብ ለማድረስ የፖለቲካ ችግሮችን እንዲሁም በሀገሪቱ ክፍሎች ለሚከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶች፣ በክልሎችና በቡድኖች መካከል ለግጭት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ያደሩና ሌሎች አዳዲስ አስጊ የግጭት ምክንያቶች እልባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት የተቋቋሙ የእርቀሰላም ኮሚሽንና የድንበርና ማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን እንዲሁም የቤተሰብ፣ የማሕበረሰብና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር የዕምነት ተቋሞቻችን ለልማት አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው በማድረግ ለውይይትና መግባባት የሚረዱ መድረኮችንና ጉባኤዎችን በማጠናከርና በአግባቡ በመጠቀም ችግሮች እንዳይስፋፉ የማድረግ ሥራ ይሠራል። በተለይም በክልሎች መካከል የሚነሱ የድንበር ይገባኛል ጉዳዮችና የማንነት ይከበርልኝ ጥያቄዎች ሀገራዊ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጣቸው ይሆናል። በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚከሰቱ አለመስማማቶችና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ሕጋዊነት ባለው መልኩ እንዲፈቱ በማድረግ ዜጎች የፈለጉትን የፖለቲካ አመለካከት የማራመድ መብታቸው እንዲጠበቅና ለሀገራቸው ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ይከናወናል። ይህንንም በአግባቡ ለመምራት የሕግ ማስከበር፣ የሰላም፣ የደህንነት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማት በተሻለ ደረጃ ከፖለቲካ ገለልተኛና ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል።



# ምዕራፍ አምስት

## የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ሀገራዊ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዋና ዓላማ በየጊዜው የሚታቀዱ የልማት ዕቅዶችን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በመከታተልና በመገምገም ውጤታማ ሆነው እንዲፈፀሙ ማድረግ ነው። የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መከታተልና መገምገም በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት ለመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል።

በዚህ ረገድ በሀገር ደረጃ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደታየው ባለፉት የዕቅድ ዘመናት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የክትትልና ግምገማ አሠራር በሀገሪቱ ለተመዘገበው ልማት የራሱ አስተዋጽዖ ቢኖረውም በርካታ ድክመቶችም ነበሩበት። ከድክመቶች መካከል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የክትትልና ግምገማ አቅም ውስን መሆን፣ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተዛባ አመለካከት መኖር፣ የክትትልና ግምገማ አሠራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ ከስኬት (outcome) ይልቅ ሂደትና ውጤት (process and output) ላይ ማተኮር እንዲሁም በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከላይ የተገለፁትን ተግዳሮቶች ለመፍታትና በሀገር ደረጃ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለመገንባት የሚረዳ ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ መመሪያ ጥር 1 ቀን 2010 በጀት ዓመት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በመመሪያው ውስጥ የሚከተሉት የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተለይተው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛል፣

- ባለቤትነት፣ አሳታፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
- የመረጃ ጥራትንና ተዓማኒነትን ማረጋገጥ
- ቅንጅት፣ ወጥነት፣ ተመጋጋቢነትና ግልጽነት ያለውና ውጤታማ የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣
- የክትትልና ግምገማ አቅምን መገንባት፣
- የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ይዘቶችና የማቅረቢያ ጊዜን ወጥ ማድረግ፣
- የዕቅድ አፈጻጸም ስታንዳርዶችንና የምዘና አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ
- ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

የልማት ዕቅዱ ክትትልና ግምገማም በዚህ መመሪያ የተለዩ ስትራቴጂዎችን ተፈፃሚ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል።

# 5.1 የክትትል ሥርዓት

ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩበት ግልጽና መለካት የሚችሉ ቁልፍ አመልካቾች (key performance indicators) ያስፈልጉታል። ይሄንንም ለማሳካት የፕላንና ልማት ኮሚሽን ከሁሉም አስፈፃሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የራሱን ዘርፍ ቁልፍ አመልካቾች እንዲለይ በማድረግ ሀገራዊ ቁልፍ የውጤት አመልካቾች አዘጋጅቷል። በመሆኑም የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩት በእነዚህ አመልካቾች መሠረት ይሆናል።

የልማት ዕቅዱ የክትትል ሥርዓት በዋናነት ሁለት የመረጃ ምንጮችን ይጠቀማል። እነዚህም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ (Central Statistical Agency) የሚመነጩ የናሙና ጥናትና የቆጠራ መረጃዎች

እንዲሁም በዘርፍ አስፈፃሚ ተቋማት የሚመነጩ የአስተዳደር መረጃዎች ናቸው። የናሙና ጥናትና የቆጠራ መረጃዎች የሚመራው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅትን ተከትሎ በሚያዘጋጀው ብሔራዊ የስታትስቲክስ ልማት ስትራቴጂ (National Strategy for the Development of Statistics) ነው። ይህም የልማት ዕቅዱን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስፈልጉ መረጃዎች በሚገባና በተናበበ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያግዛል። በተመሳሳይ የአስተዳደር መረጃዎች በአስፈፃሚ ተቋማት የሚመነጩ ሲሆን የእነዚህ መረጃዎች ጥራትና ተዓማኒነት እንዲረጋገጥ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የጥራት ማረጋገጫ (data and information verification) ስልቶች እንዲዘረጉና እንዲጠናከሩ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። በተጨማሪም የመረጃዎችን ወጥነትና ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ቼክ ሊስት በፕላንና ልማት ኮሚሽን የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ ይህንን መሠረት በማድረግ መደበኛ የአፈጻጸም ሪፖርቶች የሚዘጋጁ ይሆናል።

በዓመታዊ ዕቅድና በጀት የተደገፈ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦ የልማት ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ በሁሉም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በባለቤትነት ተይዞ መፈጸም ያለበት ትልቅ ኃላፊነት ነው። በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱን የክትትልና ግምገማ ሜትሪክስ መሠረት ያደረገ፣ ቁልፍ የውጤት መስኮችን፣ ኢላማዎችንና ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን በግልጽ ለይቶ ያስቀመጠና በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀት ይህንንም ተፈፃሚ ማድረግ ከእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካል የሚጠበቅ ይሆናል። የክትትልና ግምገማው ሥራ በተለያዩ አካላት በተለያየ ደረጃ የሚከናወን ቢሆንም የማክሮ ኢኮኖሚና የዘርፍ መረጃዎችን በመጠቀም አጠቃላይ ዓመታዊ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም በፕላንና ልማት ኮሚሽን እየተዘጋጀ ለመንግሥት የሚቀርብ ይሆናል።

በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦ የመስክ ጉብኝት ክትትልና ግምገማ ማለት የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃን ለማረጋገጥ በተመረጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ የሚዘጋጅ ጉብኝት ሆኖ ዓላማው በየጊዜው ከሚዘጋጁ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የአፈጻጸም ልዩነቶችን በማረጋገጥና የአፈጻጸም ክፍተቶች ካሉም የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ እንዲወሰዱ ማስቻል ነው። ይህም በዓመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሐ ግብር በሚገባ በመካተት በሃላፊዎችና በከፍተኛ አመራሮች ደረጃም በተመረጡና ፋይዳቸው ከፍተኛ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ የሚከናወን ይሆናል። የመስክ ጉብኝቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከማመንጨት በተጨማሪ በአንድ የመረጃ ምንጭ ወይም በሪፖርት ላይ ከመወሰን ይልቅ የመረጃ ምንጮችን ማስፋትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመስክ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳከር (tri-angulation) ጠቃሚ በመሆኑ ነው።

ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን በባለድርሻ አካላት ማስገምገም፦ የምክክር መድረኮችን በፌዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ደረጃዎች በማዘጋጀት በዓመታዊ የልማት ዕቅዱ ረቂቅ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ይካሄዳል። ይህም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈንና ለማጠናከር እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ከምክክር መድረኮች የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት የአፈጻጸም ሪፖርቱ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቅጂዎች ታትሞ ለባለድርሻ አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ ይደረጋል።

# 5.2 የግምገማ ሥርዓት

የዕቅድ ትግበራ ዘመን አጋማሽ ግምገማ (mid-term review)፦ ሌላው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በዕቅድ ዘመኑ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው። ዓላማውም በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ግቦችና የማስፈጸም ኢላማዎች ምን ያህል እየተሳኩ እንደሆነ በዝርዝር ለመፈተሽና ለማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች ካሉም በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድና በቀሪው የዕቅድ ዘመን የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንዲረዳ ነው። በመሆኑም የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ የሚከናወን ይሆናል።

የዕቅድ ትግበራ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ (final evaluation)፦ የዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ የሚከናወን ግምገማ ሲሆን፣ ዓላማውም የልማት ዕቅዱ ግቦችና ኢላማዎች በዕቅዱ በተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች መሠረት መፈፀማቸውንና የዕቅዱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ መልካም ተሞክሮዎችንና የአፈጻጸም ጉድለቶች ካሉ ከነምክንያቶቻቸው በመለየት በቂ ትንተናና ግምገማ ማካሄድና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው።

የግምገማ ጥናት (evaluative research) ማካሄድ፦ ሌላው የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ዘዴ በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የግምገማ ጥናት ማካሄድ ሲሆን፣ በተመረጡ የማክሮ ኢኮኖሚ ወይም በዘርፎች የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ስኬቶች እንዲሁም ተግዳሮቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የግምገማ ጥናቶች ዓላማም በየጊዜው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን በማካሄድ እየተመዘገበ ያለውን ለውጥ፤ ውጤትና የግብ ስኬት እንዲሁም እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥልቀት በመዳሰስ ለፖሊሲ ውሳኔዎችና ለዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ማመንጨት ነው።

# 5.3 የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች

የክትትልና ግምገማ አሠራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም ማጠናከር፦ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ አሠራርና አደረጃጀቶችን አስመልክቶ በተለያዩ የመንግሥት አስተዳደር ዕርከኖችና የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሰፊ ክፍተቶች ይታይባቸዋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን እነዚህን ክፍተቶች በማስወገድ የልማት ዕቅዱን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በጠንካራ አሠራርና አደረጃጀት እንዲሁም በአስፈላጊ የሰው ኃይል በመደገፍ የሚጠበቀውን ዓላማ ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

በልማት ሂደት ውስጥ አሠራርና አደረጃጀት ብቻቸውን የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ አይችሉም። አሠራርና አደረጃጀት ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ የሚችሉት በተሟላ የሰው ኃይል ሲደገፉ ብቻ ነው። በልማት ሂደት ውስጥ ወሳኙ አቅም የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል ነው። በመሆኑም ይህን የልማት ዕቅድ ውጤታማ ለማድረግና በሀገራችን የተጀመረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማህበራዊና የአካባቢ ልማት ለማስቀጠል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የዜጎችን የልማት እኩል ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ

ለማረጋገጥ የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በተለያዩ የመንግሥት የአስተዳደር እርከኖች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተመድበው የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቀጣይነት ባላቸው የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲታነፁ በማድረግ የሰው ኃይል አቅም በየደረጃው እንዲጎለብት ይደረጋል።

ለክትትልና ግምገማ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት መገንባት፦ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በሕግ ከተሰጧቸው ኃላፊነቶች ጋር በተገናኘ ለልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የሚያግዙ መረጃዎችን ያመነጫሉ። የእነዚህ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና ሥርጭት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓትን የተከተለና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ከተወሰኑ የመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት በስተቀር የአብዛኛዎቹ አሠራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ አይደሉም። በመሆኑም የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ አቅም በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና የተቀናጀ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል።

በተጨማሪም መረጃዎቹን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት (management information system) በመዘርጋትና ሶፍትዌሮችን በማልማት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። የዘርፍ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የመረጃ ቋቶች ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመረጃ ቋት ጋር የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት በመፍጠር የመረጃ ፍሰትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ሪፖርት አቀራረብ (performance tracking and reporting) በቴክኖሎጂና ሶፍትዌር እንዲደገፍ ይደረጋል።

የዕቅድ አፈጻጸም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማጎልበት፦ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዓላማ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላትን የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ማሻሻልና በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው። ይህም በዕቅድ አፈጻጸም የሚታዩ ድክመቶች መንስዔያቸው ምን እንደሆነ ከመለየት ጀምሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማመላከትንና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተልን ይጠይቃል።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ደካማነት ከተቋሞቹ የበላይ ኃላፊዎች የሥነ ምግባር ችግር፣ የባለቤትነትና የቁርጠኝነት ጉድለት፣ የሕዝብ ጥቅምን ያለማስቀደምና የአቅም ማነስ ችግር ጋር የተያያዘ ከሆነ በየደረጃው የተቀመጡ የልማት ግቦችና ኢላማዎችን ለማሳካት የሚደረገውን የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ድጋፍ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ተገልጋዩ ሕዝብም በመንግሥት ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ እንዲሄድ ያደርጋል። ይህም በሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማህበራዊ ቀውሶች ሁሉ በዋናነት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚመነጩ ናቸው። በመሆኑም የአስፈፃሚ ተቋማትንና ተቋማቱን የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎችን የሥራ አፈጻጸም በተሟላ ሁኔታ በየጊዜው በመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃ በመስጠት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን፣ ይህንንም ለዜጎች ለማሳወቅና ይፋ ለማድረግ ከሚዲያዎች ጋር የሚሰራ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን